# የሐረር ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አጭር ታሪክ

ከአህመድ ዘከሪያዕ

አሳታሚ
በሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ

2012ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ገፅ
ክፍል አንድ ........ 1
ምዕራፍ አንድ ........ 1
የሐረር ምስረታና የታሪክ ምንጮች ........ 1
1.1 መግቢያ ........ 1
1.2 እስልምናና እስላማዊ ግዛት ........ 4
1.3 ከመቃብር ድንጋዮች የሚነበቡ ማስረጃዎች ........
እስልምናና ታሪክ ........ 5
1.4 የሥነ ጽሑፍ ማስረጃዎች እንደ ታሪክ አመላካችነት ........ 7
1.5 የሐረሪ ሳንቲሞች የታሪክ ማስረጃዎችን ........
ገላጭ ናቸው ........ 10
1.6 ከቁስቁሶች የሚገኙ የታሪክ ማስረጃዎች ........ 11
ክፍል ሁለት ፖለቲካ ........ 12
ምዕራፍ ሁለት ........ 12
2.ፖለቲካ ........ 12
2.1 ኢፋት አዜዎቹ ሙስሊሞቹ መሪዎችና አመፅ ........ 12
2.2 ኢፋቶች አዳል ሆኑ ........ 17
2.3 የደጋውና ቆላ እልህ አስጨራሽ ጦርነቶች ........ 18
2.4 የኢማም ኢብራሂም ብቅ ማለት ........ 21
2.5 የፍልሚያው እስትራቴጂያዊው የቦታ ለውጥ ........ 23
2.6 ራስ ሩፋኤልና ራስ ሐመልማል የፖርቱጋልና ........
ቱርኮች ግፊት ........ 24
2.7 አሚር ኑር ስልጣን ያዘ ........ 26
2.8 የሀረሪ ሽሪፎች ........ 26
2.2.1 የሐረር በግብፅ መያዝ ........ 28
ወደ ከተማዋ መዝለቅ ........ 30
ግንባታ ........ 30
ዲሞግራፊያዊ ክስተቱና አስተዳደራዊ ለውጥ ........ 31
ከፍተኛ የቀረጥ ገቢና ትሩፋቱን ወደ ካይሮ ........ 33
ከፍተኛ ጫና ከውጭ ቀውስ ከውስጥ ........ 34
3. አግሪ አግሪና በርቲ በርቲ የሐረር ኢ ማሬት ........
ይካሄድ የነበረውየወታደራዊ ሥልጠና ........ 36
3.1 የስልጠናው ባህሪ ........ 39
3.2 የሸዋል ዒድና ተንከስ በርቲ በርቲ ........ 43
3.3 በበድሪ የኽቲመት ቀናት የሚከናወን በበርቲ በርቲ ........ 44

ሐረር በሚኒሊክ መያዝና የመጨረሻው አሚር አብዱላሂ ....46
ሐረር በኢጣሊያ ዘመነ መንግሥት ....51
ሐረር ከኢጣልያ በኋላና ብላታ አየለ ገብሬ ....52
ሐረር በደርግ ሥርዓት 1967-1983 ....58
ሐረር ከሽግግር መንግሥት /1983/ ወዲህ ....60
ክፍል ሦስት ኢኮኖሚ ....63
ምዕራፍ ሦስት ....63
3.ኢኮኖሚ ....63
3.1 ንግድ ሽቀጥና ቀረጥ ....63
3.1.1 ቡና፤ ትምባሆና ወርሲ ....65
3.1.2 ልብስ ....66
3.1.3 የቤት ቁሳቁስና የቤት እንስሳት ....67
3.2 የሀረር ነዋሪዎች ኑሮአቸው በእጅ ሥራ ....68
3.3.1 መሐከለኛው የከተማ ዙሪያ ....70
3.3.2 ወደ ሐረር የገቡ አትክልቶችና ማን እንዳስገባቸው ....72
3.3.3 ቡና ....73
3.3.4 ወርሲ፤ ትምባሆና ጫት ....74
3.3.5 የመስኖ እርሻና የውኃ አስተዳደር ....75
3.3.6 የውጭ ክልል ....76
3.4 የመሬትና የእርሻ ቦታ የባለቤትነት መብት ....77
3.4.1 ከሐረር ከተማ ውጭ ባለው ወረዳ መሬት ....78
3.4.2 የመሬት ይዞታ አይናና ሐርታ ....80
3.4.3 የማሽላ ምርት ....81
3.5.1 የእርሻና የመስራት እንቅስቃሴ ....83
3.5.2 የአጨዳና የውቂያ ሁኔታ ....84
3.5.3 ጐተራ ....85
ከዓረብኛ ጽሑፍ የተገኘው በአጭሩ ....86
አላባ መሰብሰቡና ግብሩ ....86
ምዕራፍ አራት ንግድ ....88
ክፍል አራት ....88
4.ንግድ ....88
4.1 በአጠቃላይ የሀረር ንግድ ....88
4.2 ወደ ውጭ የሚላኩ የንግድ እቃዎች ....89
4.3 ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ....90

4.4 በከፍተኛ ደረጃ የሚካሔድ የውጭ ንግድ ............... እንቅስቃሴ.....................................................91
4.5 በንግዱ የትራንስፖርት አገልግሎት.................................91
4.5 በንግድ እንቅስቃሴውና አሚሮች.......................................93
4.6 በንግዱ ከሕንድ ጋር ይደረግ የነበረ ግንኙነት.............95
ስለ ሐረሩ አሚር አብድሽኩር ቢን ዩሱፍ ........
(1783-1794) .....................................................................95
5.አሚር አብዱሽኩር በአጭሩ..................................................97
5.2 የአሚሩ አስተዋፅኦ...........................................................100
5.3 አሚር አብድልሽኩር የሒሳብ መዝገብ አያያዝ ..................
መገበያያዎች ገንዘብ..........................................................102
5.4 ልኬትና ገንዘቡ...............................................................103
5.5 ዳኝነት .............................................................................104
6. ገንዘብ በኢትዮጵያ..........................................................105
6.1 ገንዘብ በሐረር .................................................................107
6.1.1 ሽያጭና ዋጋ በገንዘብ.....................................................107
6.2 መሐለቅና ሌሎች ሽርፍራፊዎች በምንዛሬ......................108
6.1.3 የሀረር ገንዘብ በሩቅ አገር ከነ አሻራቸው.......................109
6.3 በሳንቲሞች የተቀረፁት ማስረጃዎች ...............................110
6.2.4 የገንዘብ ዋጋ መቀነስ ዲቫሉኤሽን ...............................111
6.3 ገንዘቡን መለዋወጥ .........................................................112
ክፍል አራት ማህበራዊ ኑሮ ..................................................114
ምዕራፍ ሰባት.........................................................................114
7.የሐረር ከተማና ማህበራዊ ገጽታ .........................................114
7.1 ከተማዋ በአጠቃሎና በወፍ በረር እይታ .........................114
ትምህርት በዓረብኛ ቋንቋና በሐረሪ ...................................116
8.2 የስነ-ጽሁፍ እድገት በሐረር ...............................................123
8.2.1 የስነፅሑፍ ምንጭና መሰረታዊ እሳቤዎች...............123
8.2.2 መርህ ምሶሶዎችና መመሪያዎች ................................124
8.3 የሀረሪ ትውፊት ፎክሎር ...................................................126
8.3.1 ተረትና ምሳሌዎች...........................................................127
8.3.2 የልጆች ጨዋታዎችና በዘፈንና ያለ ዘፈን ................
የሚገልጹ ግጥሞች ጨዋታ....................................................128
ግርዛት ...................................................................................129
ምዕራፍ ሰባት.........................................................................130

የሐረር ከተማ አወቃቀር ........................................................ 130
7.2 ከተማዋ የቆሻሻ ማስወገጃ፤ መስኪዶችና .................... 130
አድባራት.............................................................................. 130
ምዕራፍ ስምንት ..................................................................... 135
የሐረሪ ቤቶች አሠራር ............................................................ 135
ጋብቻ በሐረሪዎች .................................................................. 136
1.ቅድመ ጋብቻ........................................................................ 136
2. የፍጥምጥም ጫት................................................................. 137
3. “አንቀር ማህጠብና አልአላ” ................................................... 138
አፎቻ.................................................................................... 142
1.አፎቻ በአጠቃላይ................................................................. 142
2. “ቶያ አፎቻ” እና የኅብረተሰብ ስብስብ..................................... 143
3.ጋር አፎቻ............................................................................ 144
የመስጂድ ቶያ ጉርብትና ......................................................... 146
ቶያ በከተማ ነዋሪዎች ሕዝብ አንፃር ሲታይ................................ 148
በሐረር ውስጥ የሙያ የሃይማኖት የጉርብትና ሁኔታ ......... 148
አፎቻ እንደ ባህላዊና ልማዳዊ ተቋም.................................... 150
የአፎቻ ታሪክ ....................................................................... 151
የወንዶች አፎቻ ..................................................................... 152
የሴቶች አፎቻ....................................................................... 153
ቤተሰብ ጓደኝነትና ማህበረሰባዊ አደረጃጀት /አፎቻ/ .......................
በከተማይቱ ያላቸው ቦታና ስርጭት ........................................... 157
ጓደኝነት በሐረሪ.................................................................... 158
የሐረር ሴቶች........................................................................ 158
የሴቶች ደረጃን በተመለከተ .................................................... 158
ምዕራፍ ዘጠኝ....................................................................... 162
የስፌት ሥራ በሐረር.............................................................. 162
የስፌት ስራ የሚያጠቃልለው.................................................... 164
ክፍል አምስት ........................................................................ 167
ምዕራፍ አሥር ....................................................................... 167
ሐረር የእስልምና ማእከል......................................................... 167
10.1 ታሪካዊ መልካ ምድራዊ ዳራ.............................................. 167
10.2 እስልምና በሐረር አምባ .................................................... 168
10.3 የእስልምና ወደ ሐረር መግባት............................................ 172
10.4 የሐይማኖት አባቶችና መስኪጊዶቿ........................................ 174

ምዕራፍ አስራ አንድ ........................................................ 175
የሐረር ክብረ በዓላት ........................................................ 175
11.1 የነቢዩ መውሊድ ........................................................ 177
11.2 ረመዳን ፆም ፍፃሜና ሹዋሊድ ........................................................ 177
11.3 ዓሹራ ........................................................ 179
11.4 የበዓላቱ ፋይዳ ........................................................ 181
ምዕራፍ አስራ ሁለት ........................................................ 182
እስልምናን እንደ ግል እምነት የመቀበያ መንገዶች ........................................................ 182
12. ፆም በአጠቃሎ ........................................................ 182
12.1 መማፀን ........................................................ 183
ምዕራፍ አስራ ሦስት ........................................................ 185
የሀረር አድባራት ........................................................ 185
13.1 አድባራቱ እንደ ልማድና ባህል ........................................................ 185
13.2 አዎች፣አድባራት ቅዱሳት እነማን ናቸው? ........................................................ 187
13.3 አድባራቱ ሲጠኑ በተመራማሪዎች ሲዳሰ ........................................................ 188
13.4 የአዋች ፅንሰ ሀሳቦች ........................................................ 191
13.5 "አው አባዲር አውዚኛ" (አባድር አባታችን) ........................................................ 193
ታጅ ሞውረድ፤ ኢማመት መጣለል ........................................................ 194
ምዕራፍ አሥራ አራት ........................................................ 195
ዚያራ ለጉብኝት መሄድ ሥርዓቱ ማህበራዊ ፋይዳው ........................................................ 195
ዚያራ ለጉብኝት መሄድ ........................................................ 195
ክፍል ስድስት ........................................................ 199
ምዕራፍ አሥራ አምስት ........................................................ 199
አድባራት ከሐረርና ከአካባቢዋ ሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት ........................................................ 199
15.1 የአድባራቱ ገፅታ ........................................................ 199
15.2 አድባራቱ የሚገኙበትና ህዝቡ ........................................................ 200
ቅድመ እስልምና በፊት የነበሩ የእምነት ቦታዎች ........................................................ 204
ማጠቃለያ ........................................................ 209
ዋቢ ጽሑፎች ........................................................ 210

# መግቢያ

የሀረር ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ክፍሎችና በአስራ ስድስት አጭር ታሪክ በአምስት ምዕራፎችና ንዑስ አርዕስቶች የቀረበ መፅሐፍ የሀረርንና የከተማዋን ለመዘገብ እንጂ ሰፊ ጉዳይ በመሆኑ በአጭሩና አንኳር አንኳር የሆኑ ጭብጦች የተስተናገዱበት ቢሆንም አንዳንድ ምዕራፎች በጥልቀት የተስተናገዱበት ነው፡፡ መፅሀፍ ባለሙያ በመፃፍ የመስክ ምልከታ ታከለበት ነው፡፡

የመጀመሪያው ክፍል ታሪክን ለመፃፍ አስፈላጊ ምንጮችን የሚያስተናግደው በምንጮቹ ዙሪያ ሆኖ መረጃዎች ቅድመ ታሪክን በማመሳከሪያነት የታሪክ አለትን በህዝቡና በከተማዋ ምስረታ ዙሪያ ሳንቲሞችና ሌሎች መረጃዎች የመቃብር ላይ ፅሑፎችና ወ.ዘ.ተ አመላካች ክፍል ነው፡፡

በሁለተኛው ክፍል የፖለቲካ ሁኔታ ያወያየናል፡፡ እንደ ዘመናዊ የታሪክ ዘገባ የመካከለኛውን ዘመን የከተማ መንግሥነት ስልጣኔዎችን በተግዳሮቱ የደገኞች አፄዎች ትግልና የደቡብ ምሥራቁን የስልጣኔ ትንቅንቅ እናነባለን፡፡ ኢፋቶች፤ አዳሎች፤ ፈጠገር ወ.ዘ.ተ የሥልጣንና የመናገሻ ከተማ መለዋወጥ ይዘገባል፡፡

ከዚህ በተያያዘ ኢማም ኢብራሂም አልጋዚ ዘመቻዎች መነሻ እስከ ጎንደር ጣና ሰሜን ኢትዮጲያ የምንሰጠው ሆኖ ከአሚር ቀጥለው የአሚር ኑር ቢን ሙጃሒድ የከተማዋ አጥር ግንባታ እናስተውልበታለን፡፡ የሱልጣኔቱ ከተማ መንግስት መዳከም ተከትሎ የስልጣን ሹኩቻዎች የአያሉ አሚሮችና ከተዳከሙት እየተተረከ በታሪክ ጉዞ የከተማ ፀጋ ያሰባቸው የግብፆች መምጣት፤ የኢጣሊያኖች መከተል፤ የአፄ ሚኒሊክ ከአሚር አብዱላሂ ጋር የተደረገ ጦርነት ከዚያም የንጉሡ ሀረርን ሙሉ በሙሉ ከድጡ ወደ ማጡ ወታደራዊ መንግስት የኢኮኖሚ አሉታዊ ሚና እስከ ሽግግር ወቅት የኢህአድ መንግስት የምንገነዘብበት ክፍል ነው፡፡ አንዳንድ ርዕሶች በጣም ሰፊና በመጠኑ ጠጠር ይላል ብዮ ያሰብኩት በንዑስ ርዕሶች አስቀምጨዋለሁ፡፡ ትንፋሽ እየወሰዱ ማንበብ ያስችላል፡፡

ክፍል ሦስት የኢኮኖሚው ክፍል ደግሞ ንግድ ግብርና ኢምፖርት ኤክስፖርት ገንዘብ የሚያወያይ ሲሆን ግብርንና ወይም በተያያዘ የመሬት ስሪትና አላባዎችን እፅዋቱን ከየት እንደተገኘ የላቀ የገቢ ምንጭ የሆኑትን ቡናና ጫት በታሪክ ለየት ያለ ገፅታቸውን በተመጠነ በማያሰለች አቀራረብ እንገነዘባለን፡፡

ክፍል አራት የሀረሪ ባህልና ማህበራዊ ህይወት የህዝቡን ማህበራዊ ተቋማትን አፎቻን፤ ከታሪካዊ ሚናው አሰራሩን ከሴቶች አፎቻ፤ አያች አፎቻና ባህን ከማወያየቱ በተያያዘ አፎቻ የጋብቻ እሳቤና ክንውን ከጥንታዊነቱ ኩነት ጋርያወያየናል፡፡ በተመሳሳይ የሴቶችን ጉዳይ በማህበረሰቡ ያለውን ሚናና ነፃነትን በሁለንተናዊነት በማንሳት አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ የሆነውን የስፌት ሥራ ሁለመናው በተገቢው ይተርካል፡፡

የሀረሪው ትምህርት በታሪካዊ ስነ ፅሑፍ እድገት አረብኛ ቋንቋ የተንፀባረቀበት የሀይማኖት ፅሁፎች ከሼኽ አብዱልማሊክና ሌሎች ዚክሪና የሰለዋት መፅሐፎች ምንጫቸውን በዚህ ክፍል ያስረዳናል፡፡ ሥነፅሑፍ በቅኔዎች ዘመነኛ ያቀርባል፡፡

ክፍል አምስት እስልምና በቀጠናው የአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባህር የአረብያ ፔኑሱላ ነባራዊ ኩነቶች የእስልምና ሃይማኖት አባቶች ፅንሰ ሀሳብ ወደ ኢትዮጵያ ፤እስልምና ወደ ሀረር አገባብ በሀረር አምባ እስልምና መስፋፋት መስጊዶችና የነበራቸው ሚና ቅድመ እስልምና የነበረ የእምነት ተቋማት ወደ ዘመናዊ እስልምና ማስተማሪያነት መለወጥ እነዚህ አዋቆች (አባቶች) ብፁአን አመልካቾች በተለያዩ ምሁራን ምርምርና ድምዳሜዎች በዚህ ክፍል ሰፋ ብሎ ይነሳል፡፡ ረቀቅ ያለ አስተሳሰቦች ተደማምረው የሀረር እሳቤ መቀረፃቸውን ያስተውሉታል፡፡

በመጨረሻ መደምደሚያ የከተማዋ ንግድና እስልምና መቆራኘት ከኢትዮጵያ ታሪክነት ባሻገርም ለትልቁ ስእል ያነሳበታል ያቋጫል፡፡

አርታኢ አሊ ናጂ

# ክፍል አንድ

# ምዕራፍ አንድ

## የሐረር ምስረታና የታሪክ ምንጮች

### 1.1 መግቢያ

የሐረር ከተማን ታሪክ በአጭሩም ቢሆን በመመልከት ለመረዳትና እንደ መነሻ የሚሆን ሃሳብ ለማግኘት ይቻል ዘንድ በዘመኑ ታሪክ የሳይንስ ያህል እያደገ በመምጣቱ በርካታ ማስረጃዎችን ማገናዘብ ግድ ማለቱን ዘመናዊ የታሪክ አዋቂዎች አበክረው ይገልፃሉ፡፡ አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎቹና አዋቂዎች የሐረርን ታሪክ በሚገባ ለማወቅ ከአስር በላይ የመረጃ ምንጮች መጠቀም ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስያሜዋን፣ የታሪክ ምንጮችን ምስረታዋን ከመቃብር ድንጋይ በላይ የሚነበቡት ማስረጃዎች ፣ዕሑፍና ሥነ ፅሑፍ እንደ ታሪክ ማስረጃ የሀረርን የመገበያያ ሳንቲሞችና ሌሎች የታሪክ አመላካች ቁሳቁሶች እናያለን፡፡

“ሐረር” ለሚለው ስያሜ የተለያዩ የታሪክ ሰዎች የተለያየ አይነት ትርጉም ይሰጡታል፡፡ አንዳንዱ ሐርላ ከሚል ነገዶች እንደሆነ ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ‹‹በአካበቢው ይበቅል ከነበረ የዛፍ መጠሪያ የተገኘ ነው ይላሉ፡፡ ከ1109-1982 ዓ.ም አሚር ሐርሐር ከተማ የተባለ መሪ ሐረርን ይመራ ስለነበርና በሐረር ውስጥም 800 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ቤቶች በነበሩ ምናልባትም ከዚያ ለብዙ ዓመታት ከገዛ መሪዋ የመጣ ሊሆንም ይችላል፡፡ ጥንታዊቷ ሐረር ልክ እንደ ቻይና፣ ሕንድና ባግዳድ ካሉ አገሮች ጋር ከፍተኛ የሆነ የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በዚያን ጊዜ ከውጭ ሀገር የምታስገባቸው ከነበሩ ሸቀጦች መካከል አንዱ ሐር ወይም በዓረብኛ “ሐሪር”በመባል የሚታወቅ ነበር፡፡ ይህም ምናልባት የሐር አገር የሚል ስም ከተሰጣት በኋላ ቀስ በቀስ “ሐረር” ወደ ሚባለው ተቀይሮም ሊሆን ይችላል፡፡

በአካባቢው የሚገኝ ሸለቆም “ኤረር” ከሚለው ወደ ሐረር የከተማዋ ስም ተለውጧል ይባላል፡፡ ከሼኽ አባድር ወደ ቦታው መምጣት ጋር በማያያዝ በዘመኑ እውቅ የስነ-ጽሑፍ በተለይም የስነ-ግጥም ሊቅ ከነበረውና ስራዎቹ በእስልምና ተከታዮች ዘንድ የተወሱለት አልሐረሪም ለከተማዋ ስም መፈጠር አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል፡፡

ቀደም ሲል የተጠቀሰውን መላምት ትክክል ወይም ትክክል አለመሆን ለታሪክ፤ ለአርኪዮሎጂና አንትሮፖሎጂ ዘርፍ አጥኚዎችና ተመራማሪዎች በመተው ዛሬ ሐረር የሚለው ሲነሳ ከዘመነ ወላስማ እስከ አህመድ ግራኝ፣ ከኢማም አህመድ እስከ አፄኃይለ ሥላሴ፣ከአፄ ኃይለ ስላሴ እስከ ደርግና ዛሬ ድረስ ያለው ሁኔታ የሚታሰባቸው የታሪክ ምሁራን እንደሚኖሩም የታወቀ ነው፡፡

ሐረር ከፖለቲካዊ ጠቀሜታ አንፃር የምስራቅ ኢትዮጵያና የአካባቢውን ደህንነትና ሰላም በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ወታደራዊ ማዕከል በመሆኗ በእስትራቴጂካዊ ቦታነቷ ምንጭም ትታወቃለች፡፡ ሐረር ጥንትም ሆነ ዛሬ በዋናው የንግድ መስመር ላይ በመሆኗ የኢኮኖሚ ጉሮሮ ነበረች ለማለት ይቻላል፡፡

ሐረር የሚለው ቃል አመጣጥ የተለያዩ አፈታሪኮች እንዳሉ ሁሉ የተቆረቆረችበትን ዘመን የምድረ ከርስ (የአርኪዮሎጂ) ቁፋሮ ተካሂዶ ትክክለኛው እስኪታወቅ ድረስ የወላስማ መንግስት በአካባቢው እስከተመሠረተበት ከ800-1000 ባለው ዘመን እንደሆነ የሚያሳይ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ይኼው ግምት ሐረር የተመሠረተችው ከአክሱም ዘመነ መንግስት ቀጥሎ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሐረርና አካባቢዋ መጥተው ያጠኑ አውሮፖውያን እንደሚጠቁሙት ግን ከ9ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሐረር እስልምና እምነት ተከታዮችና የሸዋ ክርስቲያኖች ጋር የንግድልውውጥና የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር በመፈለግ የተለያዩ ጦርነቶች አካሂደዋል፡፡

## ቋንቋ

በመሠረቱ ከቅድመ እስልምና መስፋፋት በፊት ይነገር የነበረው ቋንቋ ራሱ የሴሜቲክ ቋንቋ መሆኑና አካባቢውም የሴሜቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች ደሴት መሆኑን መናገር ይቻላል፡፡ በተጨማሪ የቤቶቹ አሠራር ከአርጎባ ከሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ ከትግራይ፤ ጎንደርና ወሎ ባህላዊ የድንጋይ የቤት አሠራሮች ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሥነ-ቃል አረስ እንዳለም በሐረሪ ስነ-ፅሁፍና በሌሎች የሴማዊያን ኢትዮጵያን ስነ-ጽሁፍ ላይ ይታያል፡፡ ምንም እንኳን በስነ-ልሳን ሊቃውንት መረጋገጥ ያለበት ቢሆንም ከጥንቱ የትግርኛና የአማርኛ ቋንቋ የጠፉ ቃላት በሐረሪኛ፣ በአርጎብኛና በስልጥኛ ቋንቋዎች ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ አንዳንድ ቃላት ይጠቁማሉ፡፡ ስለ አፍሮ ኤስያቲክ የቋንቋ አመሠራረትና አሰረጫጨት ከኢትዮጵያ የሚነሳ ከሆነ የኩሽ፣ የሴምና ኦሞቲክ ቋንቋዎች ትስስር እንዳገኘ መታየት ያለበት የእውቀት ዘርፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መስክ ለሚደረገው ጥናት የሐረሪ ቋንቋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡

## 1.2 እስልምናና እስላማዊ ግዛት

ይሁንና የእስልምና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ከአክሱም መንግስት መዳከም በኋላ በዘይላ፣በርበራ፣ አዱሊስና ምጽዋ በኩል የገቡ ሙስሊሞች የባህር ዳርቻ ግዛቶች ኢትዮጵያዊያንን የእስልምና እምነት ተከታዮች ካደረጉ በኋላ ያለውን ከ8ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ያለውን 11 ክፍለ ዘመናት ያለውን ታሪክ ብቻ እንመልከት።

የተለያዩ የታሪክ ምሁራን እንዳሰፈሩት ከ800-1270 ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ እስላማዊ የሆኑ ግዛቶች ተመስርቷል። ከ1270-1524 ድረስ አንዱ በሌላው ላይ ሲዘምት ከቆየ በኋላ ከ1524-1543 ባለው ጊዜ አህመድ ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ) የተባለ የሐረሩ መሪ ድል አድርጎ እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ድረስ ግዛቱን በማስፋፋትና የሸሪዓን ሕግ በአገሪቱ ተግባራዊ በማድረግ ለ19 ዓመታት ያህል ስልጣኑን ይዞ አቆይቷል። ከ1543-1887 ባለው ጊዜ በሐረር አካበቢ የጎረቤት ህዝቦች ሀይል አይሎ የነበረ ቢሆንም እንኳን በግንብ የታጠረችው ሐረር የሴማዊያን ደሴት የእስልምና ትምህርት ማዕከል የንግድና የሥልጣኔ ማዕከልም ሆኖ ቆይታለች። ይህም የ1100 ዓመታት ታሪክ ኢትዮጵያ ሙስሊምና ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን እየተፈራረቁ ሲገዟት የነበረች እንጂ አንዳንድ ፀሐፊዎች እንደሚሉት የክርስቲያን ብቻ አድርገው እንደሚያቀርቧት እንዳልነበረች ያረጋግጣል።

በዚህም የምርምር ሂደት ታሪክን በታሪክ ማስረጃዎች ከማረጋገጥ በስተቀር ለጊዜው የተለየ መንገድ ባለመኖሩ ወደፊት የከርሰ ምድር ቁፋሮ ጥናት ተካሂዶ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች እስከሚገኙና እውነታው እስኪረጋገጥ ድረስ ከምድረ ገፅ በላይ ያሉትን መቃብሮች፣ የጽሑፍ መረጃዎች፣ በመጀመሪያ እስልምናን የማስፋፋትና የሐረር ታሪክ እናስቀድም።

## 1.3 ከመቃብር ድንጋዮች የሚነበቡ ማስረጃዎች እስልምናና ታሪክ

ስለ ሐረር ቅዱሳን መቃብሮች በበርካታ የታሪክ ምሁራን የተፃፉ ሲሆን በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት መካል ቼሩሊ፣ ብራውካመር፣ ትሪሚንግሃምና ዴቪስ ይገኙበታል፡፡ ከእነዚህ የታሪክ ምሁራን ኡልሪች ብራውካመር "እስላም የማድረግና ቅዱሳን መቃብሮች" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

‹‹የሐረር አምባ ለደጋው ኢትዮጵያዊና ለአፍሪካ ቀንድ ቆላው ሕዝቦች ለዚህ አካባቢ ሕዝቦች ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜ አነስቶ የሚፋለሙበት ቋሚ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክርስትያኖችና ሙስሊሞች በተፃራሪነት የቆየ የጦርነት ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ምእተ አመት እስከተጠናቀቀ ድረስ ቀጥሏል››፡፡

*የሴማዊያን ደሴት የምትባልበት ዝርያ ሁሉ የኩሽ ህዝቦች ኦሮሞዎች፣አፋሮችና ሱማሌዎች በመሆናቸው መሀል ሀረር ግን የተቆረቆረችው የሴሜቲክ ቋንቋ ቤተሰብ ደቡብ ምስራቅ ሴሜቲክ ተናጋሪ በመሆናቸው ነው፡፡*

በመሠረቱ የሐረር አምባ (ሀረር ፕላቶ) ከአዋሽ ደቡብ መስራቅ ዝቅተኛ ስፍራዎች ከሚነሱ የጨርጨር ተራሮች ጀምሮ እስከ ሐርጌሳ የሚዘልቅ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ አለው፡፡ ከዚህ ስፍራ የተያያዙት የአርሲ ተራራ ሰንሰለቶች አካባቢ የሚገኙ ቅዱስ አድባራትም የአካባቢውን ታሪካዊ ትስስር ይጠቁማሉ፡፡

በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት ለእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ዋነኛ ምንጭ ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው የሰሜን ሱማሌ የባህር ዳርቻ ዘይላ ተብሎ የሚጠራው ወደብ ነው፡፡ ወደዚህ አካባቢ የዓረብ ነጋዴዎች ከጥንት ጀምሮ ቀይ ባህርን እያቋረጡ ይመጡ ነበር፡፡ ስለሆነም የዓረብ ነጋዴዎች ሙስሊሞችም እንደመሆናቸው ከ1000 ዓመታት ክርስትና ጀምሮ በዚያው አካባቢ የእስልምና እምነት በመቅደም ስር ሰዶ ነበር፡፡ ከአዋሽ ወንዝ በስተምስራቅ በሚገኙ ሕዝቦች መካከል “ኢስማኤል ጀበርቲ” የሚባል የሃይማኖት አባት 10ኛው/11ኛው ክፍለ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት እንዳስፋፋ ይጠቀሳል፡፡በዚህ ዘመን የእስልምና እምነት ከባህር ዳርቻ አካባቢ ወደ ውስጥ ዘልቆ በመግባት እከ ሐረር አምባቸው እንደተስፋፋ ይገመታል፡፡

በሐረርና ድሬደዋ መንገድ መካከል ልዩ ስሙ ሐርላ ተብሎ በሚጠራው መንደር ውስጥ በሚገኘው የመቃብር ላይ ድንጋይ በ400 ዓመተ ሒጅራ የተፃፈው ፅሑፍም የሚያሳየው በአካባቢው የሙስሊም ሕብረተሰብ ቀደም ብሎ እንደሰፈረ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ (የሐረሪዎች አሚሮች የዘር ግንድ ከ10ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ11ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ይገዛ ከነበረው አሚር ሐቦብ ዘመነ መንግስት ከ233-333 ዓመተ ሒጅራ ይገዛ ከነበረው ከማኽዙም ስርወ መንግስት ጋር ይገናኛል፡፡ በመቃብሩ ድንጋይ ላይ የተፃፈው ጽሁፍ በአሚሩ የትውልድ ሐረግ በሚገልፀው ሌላው ማስረጃ ሰፊ የዘመን ልዩነት ስለሌለው በአካባቢው ቢያንስ በ4ኛው ዓመተ ሒጅራ ክፍለ ዘመን የእስልምና እምነት መሰራጨት ጀምሯል ማለት ይቻላል፡፡

ብዙ ጊዜ ሲነገር እንደሚሰማው በሐረር ትልቁ የመቃብር ስፍራ የሐረር አባት የሚባሉት የሼኽ አባዲር መቃብር ነው፡፡ ከሺኽ አባድር ታሪክ እንደምንረዳው ከሌሎች 44 ሼኮች ጋር ሆነው በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሐረር ሲደርሱ ሐርላዎች ጋቱሩሪዎችና አርጎባዎች

ያደረጉላቸው ከፍተኛ አቀባበል የሚያመለክተው ሼኽ አባድር በስፍራው ከመድረሳቸው በፊት የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍቶ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የኢስማኢል አልጀበርቲ የእስልምና ሃይማኖት የማስፋፋት ዘመቻ ከሁለት ክፍለ ዘመን በፊት እንደተጀመረ ከሚገልፀው ታሪክ ጋር ይገጣጠማል፡፡ በሌላ አገላለጽ ሼኽ አባድርና ከእሳቸው ጋር የመጣው ቡድን የመጀመሪያው የሃይማኖት ትምህርት መምህራን ሳይሆኑ ሃይማኖቱን በተጠናከረ ድርጅታዊ ተቋምነት መልኩ እንዲቀጥል ያደረጉ መሆናቸውን ይረዱታል፡፡

ስለሆነም ለከፍተኛ የእስልምና ሃይማኖት አባቶች ቅዱስ መቃብር እየተሠራ ሐረር ከ1550ዎች እስልምና በሐረር አምባዎች ላይ ለ500 ዓመታት ያህል እስልምና የበላይ ሆኖ የቆየ ነበር፡፡

## 1.4 የሥነ ጽሑፍ ማስረጃዎች እንደ ታሪክ አመላካችነት

የእስልምና እምነት ወደ ሐረርና አካባቢዋ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የዓረብኛ ጽሁፍም አብሮ እንደገባ አያጠያይቅም፡፡ በ400ኛው ዓመተ ሒጅራ ድሬደዋ አካባቢ ሐርላ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ በሚገኘው መቃብር ላይ ያለው መግለጫም ይህንኑ እውነታም የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ጽሁፉ በመቃብር ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ባለመሆኑም በወቅቱ መማሪያ፣ ሃሳብ መግለጫ፣ የንግድ ቋንቋና የግንኙነት መሳሪያ ሆኖ ያገለግል እንደነበረም ይጠቁማል፡፡

እርግጥ ነው በርካታ የእጅ ፅሁፍ መረጃዎች በዕድሜ ብዛትና በጥንቃቄ ጉድለት ለረዥም ዓመታት በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል በተካሄዱ ጦርነቶች ወቅት ጠፍተዋል፡፡ ከተረፉትም መካከል ጥቂቶቹ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ የውጭ ሐገር ዜጎች ተወስደዋል፡፡ ሐረሪዎች ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስተማር በየወቅቱ ዘመናት ያስቆጠሩ የታሪክ ጽሁፎችን ወስደዋል፡፡ በቅርቡ ወደ ድሬደዋና አዲስ አበባና ሌሎችም ስፍራዎች ሲጓዙም ይዘዋቸው ሄደዋል፡፡

እስካሁን የተገኙት ጽሁፎች በአብዛኛው በዓረብኛ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን በሐረሪ ቋንቋ የተፃፉም አሉ፡፡ ይህ የሚያመላክተው እስላማዊ ባህል በሐረርና አካባቢዋ ተስፋፍቶ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ በዓረብኛ ከተፃፉት ሰመጻሕፍት ውስጥ አንዱ ‹‹ኪታብ አልፈራኢድ›› የተባለውና በሐረሪ ቋንቋ የተፃፈም ነው፡፡ ይህ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ የእስልምና ሃይማኖት ዋነኛ ትምህርት ሞራል ምን እንደሆነ በቀላል ዘዴ የሚያስረ ነው፡፡

እነዚህ ፅሑፎች በእጅ የተፃፉ መቼ እንደሆነ በሊቃውንት መጠናት ያለባቸው መጻሕፍት በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ከፍሎ ለማየት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያዎቹ ምሁራን በዓረብኛ ቋንቋ የጻፏቸው የሃይማኖት፣ የሳይንስ፣ የሕክምና፣ የጂኦሜትሪ ወ.ዘ.ተ ሲሆኑ እነዚህ መጻህፍት ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ የተጻፉት በዓረቦች ነው፡፡ መጻሕፍቱ ሐረር ውስጥ የተገለበጡ እንኳን ቢሆኑ በየትኛውም መለኪያ በሀገሩ ሰዎች ሊፅፉ እንደማይችሉ የታሪክ ተመራማሪዎች ይገምታሉ፡፡ ሁለተኛው ዓይነቶች ጽሁፎች የዚክር ዓይነት ባህርይ ያላቸውና መሠረታዊ የእስልምና ሃይማኖት አቅጣጫን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በአብዛኛው የነዚህ ጽሁፍ ደራሲያን የሐረር ተወላጆች ናቸው፡፡ ከነዚህም ሌላ በሐረሪ ሊቃውንት ዘንድ የሱፊዎች ስነ-ጽሁፍ ደብዳቤዎች፤ ምሳሌዎችና ጥቅሶች በሰፊው ጥቅም ላይ ስለሚውሉ በዚህ ረገድ የተደረጉ መጠነኛ የጥናት ሙከራዎች ቢኖሩም ወደፊት በስፋትና በጥልቀት መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ዓረብኛ ቋንቋ የበለፀገ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የምሁራን ቋንቋ ሆኖ ይቀጥል እንጂ የግጥምና ስነ-ጽሑፍ ግን ለሐረሪ ሕብረተሰብ ያልተለመደ አይደለም፡፡ የእነ ኢብን ማሊክ “ዓልፌያ”፣ የነኢብን ሐጋር “ቱሀፍ”፤ የነቡስር “ቡርዳ” እና “ሀምዚያ” የነጋዙሊ “ዳላኢል አልኸይራት” ሥራዎች በሐረርና በአካባቢዋ መገኘታቸውም ይህንኑ እውነታ ያረጋግጣል፡፡

ሐረሪ ምሑራን በዓረብ ደራሲያን የተጻፉትን መጻሕፍት ማንበብ ብቻ ሳይሆን እራሳቸውም በዓረብኛ “የዚክር” መጻህፍትን ጽፈዋል፡፡ እነዚህ መጻህፍት የአካባቢውን ቅዱሳንን የሚያወድሱ ናቸው፡፡
እነዚህ ጽሁፎች በሐረሪዎች የተጻፉ መሆናቸውን መረዳት የሚቻለው ሰዋሰዋዊ አጠቃቀማቸው በማየት ነው፡፡

በዓረብኛ ከተጻፉት መረጃዎች ሌላ እንደ "ኩም ጊር" ማለትም ሚሊዮን ጊዜ አንብባቸው የሚል ትእዛዝ በሐረሪ ቋንቋ ተጽፎባቸዋል፡፡ "ተስቢህ" የተባለ መጽሐፍም የተጻፈው በዓረብኛ ቢሆንም "ሶላዋት" እንዴት እንደሚደረግና እንደሚፀለይ ግን በሐረሪ ቋንቋ አረብኛ ፊደላት ተጽፏል፡፡

ሌላው ለየት ያለ ምሳሌ አብዱልማሊክ የጻፈው ዚክር 600 ያህል መስመሮች የያዘ ሲሆን የተፃፈውም ነቢዩ መሐመድን (የአላህ ሰላም ይውረድባቸው) ለማወደስ ነው፡፡ ይህንን ግጥም የመድረስ ስሜት ከሚያነሳሱት ጽሁፎች ውስጥ በሐረር ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ውለው የነበሩና የታወቁት የቡሲሪ "ቡርዳ" የወረቅ "አል-ቀሲዳና አል-ዊትሪያ "ይገኙበታል፡፡ የአብዱልማሊክ መጽሐፍት "ቃሲዳ" ተብለው ከሚታወቁትና ከቆዩት የሐረር ግጥሞች መካከል አንዱ ነው፡፡ የቃሲዳ ስነ-ጽሁፍ ደግሞ ከ859-941 ከነበረው ከፐርሺያዊው አቡ አብዱላህሒ ኢብን መሐመድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸው ፐርሺያዊ ቃሲዳ የተባለው ግጥም ደራሲ 100,000 የግጥም ስንኞችን እንደገጠመና እስልምና ስነ-ጽሁፍ እድገት አስተዋፅኦ እንዳበረከተ የሐረሪ አብዱማሊክም የሱ ተከታይ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

እንግዲህ አንድ መታወቅ ያለበት አብይ ጉዳይ የእስልምና ሃይማኖት ወደ ሐረርና አካባቢዋ ከገባበት ጊዜ አንስቶ በዓረብኛ ቋንቋና ፊደላት በሚፃፉ በሐረሪ ቋንቋ እምነቱ ይሰበክ የነበረ መሆኑ ነው፡፡

አንድ ኦሪጅናልና ወጥ የሆነ ፅሑፍ ሀረር ከገባ መፅሐፍ ሀረሪዎች እውቀትን ፍለጋ ያደርጉ የነበረው ጥረትን ገላጭ አስክርነት ኮፒ ፀሐፊዎች በሥርዓትና በንፅህና የኮፒ ቅጂ ያዘጋጁ እንደነበርና አያይዘው ወደ ጥረዛ ያደርሳቸው ነበር፡፡

## 1.5 የሐረሪ ሳንቲሞች የታሪክ ማስረጃዎችን ገላጭ ናቸው

ምንም እንኳን በሐረር የመገበያያ ሳንቲም መሥራት መቼ እንደተጀመረ ለማወቅ ገና ብዙ የከርሰ ምድር ቁፋሮ ጥናት ማድረግና ያሉትንም በሚገባ መመርመር እንደሚያስፈልግ የታወቀ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ግን በተገኘው መረጃ መሠረት ከ12ኛው ዓመተ ሒጅራ እስከ 1886/87 የተሠሩ ሳንቲሞች ተገኝተዋል፡፡ 12ኛው ዓመተ ሒጅራ ማለትም 1200 ዓመት ጀምሮ የተጠናከር የገንዘብ መቅረፅና ምርት ልውውጥ እንደነበረ የሚያሳይ የጽሁፍ መረጃ ይገኛል፡፡

ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የገንዘብ ምርት በተጠናከረ መልኩ መቀጠሉን ለአብነት ያህል መዘርዘር ይቻላል፡፡ እንደማስረጃ አሚሩንና የታሪክ ዘመኑን ይገልፃሉ፡፡ ምሳሌ፡-

ሀ. አሚር አብዱሽኩር /1783-1794/
ለ.አሙር አህመድሽኩር /1794-1821/
ሐ.አሚር አብዱከሪም /1825-1834/
መ.አሚር አቡበከር /1825-1834/
ሠ.አሚር መሐመድ /1856-1875/
ረ. አሚር አብዱላሂ /1885-1887/ በሚገባ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

## 1.6 ከቁሰቁሶች የሚገኙ የታሪክ ማስረጃዎች

እስካሁን ከተጠቀሱት የተለያዩ የታሪክ ማስረጃዎች ሌላ በሐርላ መንደርና አካባቢው በደከርና አካበቢው የተሠሩ የድንጋይ ቤቶች፣ ጥንታዊ የከብት በረቶች ዋሻዎችና የመሳሰሉት መረጃዎች መጠናት ይኖርባቸዋል፡፡ ሐረር የምስራቁ ኢትዮጵያ ዋናው የንግድ በር ሆና ለዘመናት ያገለገለች እንደመሆኑ መጠን ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡትንና ከሐገር ወደ ውጭ የሚወጡትን በማስረጃዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ይልቁንም እንደ ቻይና ካሉ ሐገሮች ጋር ይደረግ የነበረው የንግድ ልውውጥ ምክንያቱ ሸክላዎችንና የሸክላ አይነቶች መቼ እንደተሠሩ ስለሚታወቅ በደከር፣ በሐርላ፣ በሐረርና በአካባቢዋ በሚገኙ ፍርስራሽ መንደሮች ይገኙ እንደሆነ መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ በሀርላ መንደር ከስድስተኛው ምዕተ ዓመት በፊት የተመረተ የቻይና ገንዘብ በአካባቢው መገኘቱ ለሚካሄድ የከርሰ ምድር ጥናት አበረታች አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡ ወደ ሐረር ዘልቆ በመምጣት የመጀመሪያው የውጭ ዜጋ አውሮፓዊ የሆነው ሪቻርድ በርተን ወደ ሐረር በመጣበት ጊዜ እንደ ዘገበው በርካታ ቁሳቁሶች ከተለያዩ አገሮች የመጡ ቁሳቁሶች በወቅቱ ይታዩ እንደነበር ጠቁሟል፡፡

እንደማጠቃለያ የሀረርን አጭር ታሪክ ለመገንዘብ መረጀዎች በመነሻው ነጥቦችን አነሳን እንጂ በዚሁ መፅሐፍ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የባህል ታሪክ ስናነሳ በርካታ ጠቀሜታ ማስረጃዎች የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በዚህም ምዕራፍ ስያሜ ቋንቋን፤ ፅሑፍና ሥነ ፅሑፍ፤በመቃብር ድንጋይ የተፃፉትን ከእውኑ ታሪክ ጋር በማገናዘብ የሀረሪ “መሐለቅ” ሳንቲሞች በራሳቸው ታሪክ በነበሩ አሚሮች የታሪክ ዘመናቸውን የሚያስረዱ መሆናቸው በኢኮኖሚው ክፍል የሳንቲሞቹን ተጨማሪ ማስረጃ የምንመለከተው ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት ፖለቲካ

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.ፖለቲካ

ፖለቲካ የመንግስትን ስልጣን መያዝና መቆየት፤ ለስልጣን መፎካከር የተፎካካሪዎችን ባህሪያት ጭምር አመላካች በመሆኑ ከሺ ዓመታት በላይ የቆየ ታሪክ ያላት ሀረር ረዥም የፖለቲካ ታሪክ እንደሚኖራት የሚታወቅ ነው። ሆኖም ግን ይህ አጭር የፖለቲካ ታሪክ በእጅጉ የታጨቀ ነው። ሥልጣን ሀረር እንደ ከተማ መንግስት (city state) የዘለቀው የሀረር በግብፆች መያዝ አፄ ሚኒሊክ በግብፆች ቀጥለው ከዚያም ኢጣሊያኖችና የአፄ ሀይለ ስላሴ ሃይሎች ይጠቀሳሉ። ከዚያ የደርግ ዘመነ መንግስትና ከሽግግሩ መንግስት በኃላ የነበረውን ክስተት እናያለን።

የሀረር ፖለቲካዊ አስተዳደር ከሁለት አንፃር የሚታይ ሲሆን አንደኛው ከኢፋትና ፈጣጋር ከተነሱት አዳሎች ድረስ ያለው ሁለተኛው ደግሞ ዘይላን በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ሲገዙ ከነበሩት ዓረቦች ጋር አገናዝቦ ማየት ነው። በመጀመሪያ ከኢፋት የመነጨውን ታሪክ እንመልከት።

## 2.1 ኢፋት አፄዎቹ ሙስሊሞቹ መሪዎችና አመፅ

ኢፋት የሚባለው ከሰሜን ምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ቦታዎች በስተምስራቅ የሚገኘው ዝቅተኛ በረሃማ ስፍራ ማለትም ወደ ሰሜን በአመዛኙ ከአዋሽ ተፋሰስ ጀምሮ እስከ አቤ ሐይቅ የሚደርስ ከወደ ምስራቅ ደግሞ በሸዋና ዘይላ መካከል የሚገኘው ስፍራ ነው።

የኢፋት አዳሎች የእስልምናን ሃይማኖት ከተቀበሉ ወዲህ የክርስቲያኑን መንግስት ከመዋጋት ተቆጥበው አያውቁም። በዚህም ምክንያት ክርስትያኑ ሃይል ሲያሸንፍ የሙስሊሙን ሐብትና ንብረት ሲያጠፋ፣ሙስሊሙ ሲያሸንፍ ደግሞ በተመሳሳይ ሲያደርግ ቆይቷል።

እ.ኤ.አ በ1298 ማርኮ ፖሎ የተባለው ቬኑሳዊ አሰሸ እንደገለፀው ከ1283-1293 ድረስ ንጉስ ነገስት ያግብአ ስዩም የተባለ የሐበሻ ንጉስ ነበር፡፡

ይህም ንጉሰ በአዳል ግዛት በኩል ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ወሰነ፡፡ ይሁንና ወደ ቅዱስ ስፍራው ለመድረስ አለመቻሉን ማርኮ ፖሎ እንደሚገልፀው አዳሎች በወቅቱ ሌላ ጠላት ቢኖራቸውም የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ክርስቲያኑ ነበር፡፡ እንዲያውም የአዳሎች ሰጭለለጽነ የክርስቲያኖችን አቡን ወደ ሙስሊምነትእምነት ለመለወጥ ፈልገው እንቢ ስላላቸው ትታውት ሸኝተውታል፡፡

ቬኑሳዊው አገር ጉብኚ ጨምሮ እንደገለፀው የሙስሊም የክርስቲያን ጦርነት ብልጭ ድርግም እያለ ቢቀጥልም ከ1298-99 ባለው ጊዜ ግን መሐመድ ደቡ አብደላህ የሚባል የሙስሊም ሼኽ ተነሳ፡፡ ይህ ኼኽ በርካታ ሠራዊቱን ሰብስቦ የክርስቲያኑ መንግስት የበላይ አለቃ ለመሆን እድል ሳይቀናው ቀርቶ ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር ተስማምቶ ነበር፡፡

ይሁኖ አምላክ የመጀመሪያው የሙስሊም መሪ የተመረጠው ምናልባት በአጼ ይሁኖ ዓምላክ 1270-1285 ሲሆን ይህ ንጉስ የኢፋቱን ዑመር ኢብን ዱንያ ሑዝን ሱልጣን ብሎ ሾመው፡፡ ይህም የሙስሊሞች መሪ በ1275 በሞት እስኪለይ ድረስ በአፄ ይሁኖ አምላክ ዘንድ በፀባዩ በጣም የተወደደ ነበር፡፡ ከእሱም በኂላ አምስቱ ልጆቹ ሴት ልጁ አተለይላ ጭምር በተከታታይ በአጭር ጊዜም ቢሆን ሥልጣኑን ይዘዋል፡፡ ለዑመር ኢብን ዱንያ ሑዝን ልጆች ከ30 ዓመታት ላላነሰ ጊዜ 1279-1299 የገዛው ባዚቱ የተባለው ነው፡፡ ከእሱ በኂላም ሰብረዲን ናሕው ኢብን ማንሱር ኢብን ዑመር ወላስማ ወይም ቀዳማዊ ሰብረሰአዲን ለረዥም ዓመታት የኢፋት መሪ ሆኖ እስኪሞት ድረስ መርቷል፡፡

ቀዳማዊው ሰብረዲን አርጅቶ ሲሞት ልጁ ሱልጣን ዓሊ ተተክቷል፡፡ ማቅሪዚ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ እንደገለፀው ከሆነ ሱልጣን ዓሊ ዝናው በአጠቃላይ በአዳሉ ግዛት የገነነ ሲሆን በክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ለማመፅም የመጀመሪያው መሪ ነበር፡፡ አዳሎች በሱልጣን ዓሊ አስተባባሪነት አንገብርም በማለታቸው ንጉሰ ነገስት ያግበአ ስዩም (1283-1292) የበላይነቱን ለማስከበር እስከ ዘይላ አካባቢ ድርስ ዘመቻ አካሂዶ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የሙስሊሙ መሪዎች በአፄ አምደጽዮን (1312-1342) ዘመነ መንግስት አምፀው እንደነበር ተዘግቧል፡፡ ይህ አመጽ በ13200 የተመራው በቀዳማዊ ሐቅ አዲን ሲሆን አመፁ እንዲነሳሳ ያስደረገውም የግብፅ ማምሉክ አን ናስር መሐመድ ኢብን ቃሉን ነበር፡፡ አፄ አምደጽዮን የግብፁ መሪ የአዳል ሙስሊሞችን ማነሳሳቱን ካልተወ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ሙስሊሞች ላይ እርምጃ እንደሚወስድና የአባይንም አቅጣጫ እንደሚያስለውጥ የሚያሳውቅለት መልዕክተኛ ልኮ ነበር፡፡ ነገር ግን ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ የግብፁን መሪ ድጋፍ ያገኘው ቀዳማዊ ኢብን መሐመድ ኢብን ዓም ትዕይንታይ የተባለ የንጉሠ ነገሥቱን ወታደር ያዘ፡፡ በዚህ ጊዜ አጼ አምደጽዮን ዘምቶ የኢፋትን አዳሎች ደመሰሰ፡፡ ወታደሮቹንም እስከ "ኩአልጎራ" በቅለዛርና ሌሎች ስፍራዎች ድረስ ልኮ አካባቢውን በቁጥጥሩ ስር አደረገ፡፡ እነዚህም ስፍራዎች "አምባሃ ከሰም" አካባቢ የሚገኙና በዚህ ውጊያም የሐቀዲን ልጅ የሆነው ዶዳር ተገደለ፡፡

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ማለትም በ1332 የሰአዲ ወንድም ሱልጣን ሰብር አዲን ወይም ዳግማዊ ሰብረዲን ተተካ፡፡ ዳግማዊ ሰብረአዲን የአጼ አምደጽዮን ዜና መዋዕል ፀሐፊ እንደገለፀው ኢትዮጵያን አጠቃሎ ለመያዝ ክርስቲያኖችን ለመግዛትና ቤተክርስቲያን የተባለ ሁሉ ለመደምሰስ ፍላጐት ነበረው፡፡ በዚህም መሠረት የቆየውን የኢትዮጵያ ባህላዊ አገዛዝ ለመቀጠል ፋጣጋርና "አለመመል አይመለል" የተባለውን የጉራጌ አካባቢ፣ ዳሞት አምሐራ አንጎት፣ እንደርታ፣ በጌምድርና ጎጃም በተባሉ ክፍለ ሀገራት ግዛቱን ከፋፍሎ ለማስተዳደር ምኞት ነበረው፡፡

ዳግማዊ ሰብረዲን እንዷ ዜና መዋእሉ 1. የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያናት በሙሉ ወደ መስጊድነት ለመቀየር 2. ንጉሠ ነገስቱን ሙስሊም ለማድረግና እሺ ካለ የአንድ ክፍለ ሀገር ገዢ ሊያደርገው እምቢ ካለው ደግሞ የአንድ ወርጂ ከብት ጠባቂ ሊያደርገው፤3.ንግሥት ጃን መንገሻን ወፍጮ የሚፈጨው ለማድረግ፤4. የአምደጽዮን መናገሻ ከተማ የነበረችው ተጉለትን መር አጺ ብሎ ለመሰየምና መኖሪያው እንድትሆን ለማድረግ 5.ጫቱንም ለመትከል ነበር ሲል የአጼ አምደጽዮን ዜና መዋዕል ጸሐፊ ከትቧል፡፡

በዚህ ዜና መዋዕል ዘገባ መሠረት የዳግማዊ ሰብረዲን አመጽ የጂሃድ ጦርነት መልክ ስለነበረው የዳውሮ ገዥ "ሐይደራና" የሐዲያው መሪ አመነው ተባብረውታል፡፡ ጦርነቱም በከፍተኛ ውጊያ ቀጥሎ ድሉ የአጼ አምደጽዮን ሆነና ሰብረዲን አመለጠ፡፡

ከሰብረዲን በኋላ ወንድሙ ጀማልአዲን በአጼ አምደጽዮን መልካም ፍቃድ የሙስሊም ግዛቶች ሁሉ ንጉሥ ተብሎ ተሾመ፡፡ ጀማል አዲንም በማመጹ በሌላ ወንድሙ ናስርአዲን ተተካ፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ሐርላን፣ ደልሆያን፣ ደግዌንና መየርጄህን አስገብሮ ከተሞቹን አጥፍቶ ተቃዋሚዎቹን ማርኮ ክርስቲያን ገዥዎችን በመሾሙ ተመለሰ፡፡

ምንም እንኳን የአጼ አምደጽዮን የዜና መዋዕልለ ጸሐፊ ከላይ የተጠቀሰውን ቢጽፍም ፈድል አላህ አልኡመር የተባለ ከዘይላው ገዥ አብድላህ ባገኘው መሠረት ለየት ያለ መረጃን አጠናቅሯል፡፡ በዚህ ፀሐፊ መግለጫ መሠረት ኢፋት የሚበለው በጣም ሰፊና ሐብታም የሆነ የኢትዮጵያና የሙስሊሞች ግዛት ነበር፡፡ የሚናገሩትም በሐበሽኛ ቋንቋ ነበር፡፡ ግዛታቸውም በአንድ አቅጣጫ እስከ 20 ቀን በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ለአሥራ አምስት ቀን ድረስ ያስኬድ ነበር፡፡ በዚህም የግዛት ክልል ሺሚ፣ ሸዋ፣አዳል፣ ጀማ፣ ለኡ የተባሉ ስፍራዎችም ተጨምረው እናገኛለን፡፡

አል ዑመር እንደሚለው በግዛቱ ውስጥ አንድ ትልቅ ወንዝ ሲኖር ይህም የአዋሽ ወንዝ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ አልኡመር ስለነዚህ ሕዝብ ባህል ዝርዝር አድርጎ ጽፏል፡፡ ወደ ፖለቲካዊ ሁኔታው ስንመለስ ግን ከአምደጽዮን በኋላ የነገሠው ሰይፈ አርእድ ሲሆን እሱም የአባቱን ግዛት ለማስከበር ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህ ሐርብ አራድ ኢብን ወይም አህመድ የተባለውን ሾመ፡፡ የሰብብረዲን ልጅ የሆነው ይኸው ሱልጣን ማዕረጉን ከያዘ በኋላ በማመፅ ለስምንት ዓመታት ያህል ታስሮ የነበረ ቢሆንም ተመልሶ የንጉሠ ነገሥቱን ምህረት በማግኘቱ እንደገና ወደ ሥልጣን ወጣ፡፡ እሱም ሱልጣን እንደሆነ ዳግማዊ ሱልጣን ሐቅዲን ተነሳ፡፡ ይህ ሰው ዋላህ የምትባል ሌላ ከተማ መሠረተ፡፡ ይሁንና እሱም በማመፁ ለ30 ዓመታት ያህል ታሠረ፡፡ አፄ ሰይፈ አርእድ በ1370 ከሞተ በኋላ ሐቅዲን ከእስር ተለቀቀና ንጉሠ ነገሥት ዳዊት ምናልባትም ከ1370-1380 በነበረው አውዳሚና አስፈሪ ጦርነት ማካሄድ ጀመረ፡፡ ይሁንና በ1376 በተደረገው ጦርነት ሐቅዲን ሞተ፡፡

የነገስታቱ ስምና ዘመን በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ መረጃዎች ስለሚኖሩ በዚህ ጽሑፍ ግን የበለጠ ትኩረት የተደረገው በሙስሊም መሪዎቹ ላይ መሆኑንና በዚህ ረገድም ሰፊ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ በዚሁ አጋጣሚ መጠቆም ያስፈልጋል፡፡

ሐቅዲንም በሱልጣን ሰዕድዲን አብደላህ መሐመድ ተተካ፡፡ ይህም የኢፋት የመጨረሻው ታላቅ መሪ የነበረ ሲሆን ማቅሪዚ የተባለ የታሪክ ዘጋቢ ስለዚሁ ሱልጣን ሲገልጽ ብርቱ ተዋጊ በማለት ነበር፡፡ በመሆኑም አማኖ፣ ሀዲያ፣ ዘይላና አጎራባች ዘላኖችን ሁሉ በጦር ወሮ ነበር፡፡ ይሁንና ምናልባት አፄ ዳዊት ከፍተኛ ሠራዊት በማሰባሰብ በኢፋት ላይ ዘመተ፡፡ ከዚያ ሳዐደዲን እስከ ዘይላ ድረስ አሳደደው፡፡ በኋለ በ1415 ዓ.ም ሞተ፡፡ ልጁም ወደ የመን ተሰደደና ናስር አሕመድ ኢብን አሽራፍ ኢስማኤል ጥገኝነትን ሰጠው፡፡

ሰብረዲን ከሞተ በኋላ የክርስቲያኑ መንግስት በኢፋት ላይ ሙሉ በሙሉ ወታደራዊ የበላይነትን አገኘ፡፡ ማቅሪዝ እንደሚለው መስጊዶች ፈርሰው በምትካቸው ቤተ ክርስቲያናት ተሠሩ፡፡

ከአንድ ክፍለ ዘመን በኋላ ወደ የመን ተሰዶ የነበረው የአዳል ጎሳ መሪ ልጅ የሆነው ሱልጣን ሰብረዲን ሳልሳዊ ከአስር ፈረሰኞቹ ጋር ተመለሰ፡፡ ከወንድሞቹ ጋር በመሆን ወደ አገሩ ሲመለስ የአባቶቹ ግዛት የነበረው በክርስቲያኑ ንጉሰ ነገስት እጅ ስለነበረ ወደዚያው በመሄድ ፈንታ አቅጣጫውን በመቀልበስ ወደ ምሥራቁ በመዞር የዛሬይቱ ሐረር ከምትገኝበት አካባቢ ደከር ወደ ምትባል ስፍራ ሄደ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እሱና ተከታዮቹ በጋራ ኢፋት የሚለውን ስማቸውን በመተው አዳል ብለው መጥራትም ጀመሩ፡፡ ይህ የአዳል ግዛት በክርስቲያኑ ንጉሠ ነገሥት ግዛት በስተሥራቅ የሚገኝ ገና ግዛት ሆነ፡፡

## 2.2 ኢፋቶች አዳል ሆኑ

የመጀመሪያው የአዳል ሱልጣንም የሳዕደዲን የመጀመሪያ ልጅ ሳልሳዊ ሰብረዲን ሆነ፡፡ ሱልጣን ሰብረዲን ከወንድሞቹ ጋር "ሳያራ" ወደ ሚባል ስፍራ ሲሄዱ በቀድሞ አባቶቹና አያቶቹ ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ አቀባበል ተደረገለት፡፡ ከዚያም ከክርስቲያኑ ንጉሠ ነገስት ጋር ጦርነት መግጠም ጀመሩ፡፡ የሱልጣን ሰብረዲን ሳልሳዊ ጦር ምንም እንኳን ከክርስቲያኑ ንጉሥ ነገሥት ጦር ጋር ሲወዳደር በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ዚክር አምሐራ ሰርጃን በተባለው ስፍራ የተሳካ ድል አግኝቷል፡፡ ስለሆነም ሠራዊቱ የንጉሠ ነገስቱን ጦር በመበተን በርካታ ቤቶችንና ቤተክረስቲያኖችን አቃጠለ፡፡ ከፍተኛ የሆነ ሀብትና ንብረት እንዲሁም ብዙ ወርቅን ማረከ፡፡

ሰብረዲን በዚህ ጦርነት ድል ቢቀናውም የንጉሠ ነገሥቱ አዛዥ ሃያ ሺህ ጦር አሰባስቦ መጣና ብቻውን አስለቀቀው፡፡ መቅሪዚ እንደሚነግረን ቲባ፣ ባርቱ፣ጃብ በተባሉ ቦታዎችና በሌሎችም ስፍራዎች ጦርነቶች ተደርገዋል፡፡ በተለይም ጃብ በተባለው ስፍራ የተደረገው ፍልሚያ የጦሩ ብዛት ልክ ከሰማይ የሚዘንብ ይመስል ነበር፡፡ ይሁንና ሰብረዲን በፈጣን ፈረሶቹ አመለጠና ከ1422-12 ባለው ጊዜ የተፈጥሮ ሞት ሞተ፡፡

ከሱልጣን ሰብረዲን በኋላ ወንድሙ ሱልጣን መንሱር ተተካ፡፡ ሱልጣን መንሱርም መሐመድ የተባለ ጀግና የጦር ወንድሙ የቀኝ ክንዱ በመሆን ይረዳው ነበር፡፡ ይሁንና ከንጉሠ ነገሥቱ ዳዊት ጋር ያዳያ በተባለው ስፍራ ጦርነት አድርጎ ድል አደረገ፡፡

በኋላ ሰላሳ ሺህ የሚሆነውን የክርስቲያኑ ንጉሠ ነገሥት ጦር ሞሃ በተባለው አውደ ውጊያ ለሁለት ወራት መፈናፈኛ አሳጥቶ በመክበብ በረሃብና ውሃ ጥም ቀጣቸው፡፡ ከዚያም አንድም የእስልምናን እምነት እንዲቀበሉ ካለበለዚያ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ምርጫ ሰጣቸው፡፡ እነርሱም ውስጥ አስር ሺህ ያህሉ እምነቱን ሲቀበሉ የተቀሩት ግን ወደ ቤታቸው ተመለሱ፡፡

በ1424 ላይ አጼ ይስሃቅ እጅግ ከፍተኛ ኃይል አሰባስቦ መጣ። ኃይሉን መቅሪዚ እንደሚለው እንደአምበጣ የበዛ ነበር። ከዚያ ጦርነት ተደረገና የአዳል መንግስት እንደቀዳማዊ የኢፋት መንግስታት ሁሉ በክርስቲያኑ መንግስት እጅ ወደቀ። ሱልጣን መንሱርና ወንድሙ መሐመድም ተማረኩ።

## 2.3 የደጋውና ቆላ እልህ አስጨራሽ ጦርነቶች

ከሱልጣን መንሱር መሞት በኋላ በ1424 አካባቢ ታናሽ ወንድሙ ሱልጣን ጀማል አዲን መሐመድ የአመራሩን ኃላፊነት ወሰደ። ዳግማዊ ጀማል አዲን ሐርብ ጃውሽ የተባለ ኃይለኛ የጦር መሪ ይረዳው ነበር። ዳግማዊ ጀማል አዲን ብልህና ብቃት ያለው መሪ ስለነበር ከአጼ ይስሃቅ የጦር መሪ ጋር የሰላም ድርድር ለማድረግ በማሰብ መልእክተኞቹን ላከ፡ ፡ ነገር ግን አዛዡ ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ ጦርነቱ ተጀመረ። ምንም እንኳን የአጼ ይስሃቅ ጦር 7 ሺህ ቀስተኛና ጦር ሰባቂ ቢያሰልፍም የሐርብ ጃውሽ ጦር አነስተኛ ቢሆንም አሸነፈ። በኋላም ሁኔታው አማራጭ ስላልነበረው በጀማልአዲን ሕግ ለመገዛትና ግብር ለመክፈል አዛዡ ፍቃደኛ መሆናቸውን ገለፁ።

በሱልጣን ጀማልአዲንና በአጼ ይስሃቅ መካከል በተደጋጋሚ ጦርነት የተደረገ ሲሆን በኋላም የሱልጧን ጀማል አዲን ኃይል በማሸነፉ ንጉሱን እስከ ጥቁር አባይ ድረስ እንዲሸሽ አድርጓቸዋል። ጀማል አዲን በጣም ጀግናና ብልህ መሪ የነበረ ሲሆን በሰባት ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ወቅት በርካታ የጦር ምርኮኞችንም ወደ ሕንድ ሆርሙዝ፣ ሂጃዥ፣ ግብጽ፣ ሶሪያ፣ ግሪክ፣ ኢራቅ፣ የፋርስ ባሪያ አድርጉ ሸጧቸዋል። መቅሪዚ እንደሚለው ጀማል አዲን የሚወስደው እርምጃ ሁሉ የእስልምና ሕግን መሠረት ያደረገ ነበር።

ከጀማል አዲን መሞት በኋላ ወንድሙ ሱልጣን ባድላይ ኢብን ሳዕደዲን ተተካ። ይህ ሱልጣን ሺሃብ አዲን አህመድ ባድላይ እየተባለ ይጠራ የነበረ ሲሆን ዋና ከተማውን ደከር ላይ አደረገ። ደከርን መሥርቶ በርካታ ቤተክርስቲያናትን ግዛት ያዘ ። ሀብትና ንብረት እንዲሁም እጅግ ብዙ ባሮችን ማረከ።

በዘመኑ የነበረው የክርስቲያኑ ንጉሠ ነገስት አጼ ዘርአያቆብም በ1445 በሱልጣን ባድላይ ኢብን ሳአደዲን የሚሰነዘረው ጥቃት እየከፋ ሲሄድ ጦሩን ይዞ ዘመተ፡፡ አጼ ዘርአያቆብ የሱልጣኑን ጦር ሲመለከት እጅግ ከፍተኛ ሆኖ አገኘው፡፡ ይልቁንም ጦር የማያስነካ የመተት አሸንክታብ (ጥፋት የሚባለው ቀርጣስ) አለው ተብሎ ስለሚታመን ሰግቶ ነበር፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ ወታደር ወደ ሱልጣኑ ጦሩን ሲወረውር ሱልጣኑ የተወረወረውን ጦር ለቀም አድርጐ በመስበር ወደ አጼ ዘርአያቆብ ገሠገሠ፡፡

ይሁንና ንጉሱን አንገቱ ላይ ወግቶ ገደለው፡፡ ሱልጣኑ ከሞተ በኂላ ሠራዊቱ የንጉሠ ነገስቱ ጦር በርካታ “ዓይን ፈረስ” በተባለው ስፍራ ፈጀው፡፡ ከዚያ በኂላ ስፍራው “አይፋር” እየተባለ ይጠራ ጀመር፡፡ አክታግሬ ቢርዲ የተባለ የዓረብ ጸሐፊ በ1452 ባቀረበው ዘገባ መሠረት ሱልጣን ባድላይ ከሞተ በኂላ ልጁ መሐመድ (1445-1471) ተተክቶ ለሃያ ስድስት ዓመታት ያህል መርቷል፡፡ ሱልጣን መሐመድ አካባቢውን ይመራ የነበረው የአጼ በእደማሪያም ዘመነ መንግስት ስለነበረ የንጉሠ ነገሥቱ ወታደሮች እንዳይዘምቱበት ግብር እንደሚልክላቸው እየገለጸ ከልዩ ልዩ ገጸ በረከቶች እያደረገ የሰላም ውይይት እንዲካሄድ የዳውሮ ሙስሊም በሆነውና ገባብ ሐኺድ በተባለ መልዕክተኛው ይልክ ነበር፡፡ አፄ በእደማሪያ ሱልጣኑ ቃሉን ጠብቆ እንዲገብር ተስማምቶ ነበር፡፡ ዳሩ ግን የዘይላው ገዥ ላዳኤ ዑስማን ስምምነቱን መጣሱ ንጉሡ በመስማቱ ለጦርነት ተዘጋጀ፡፡ በዚህም ጊዜ የባሌ ገዥ የነበረው ገብረ እያሱ ከዳውሮና ከሌላም ስፍራ ተጨማሪ ሠራዊት ተጨምሮለት የጦር መሪ ሆኖ ዘመተ፡፡

በዚህ ጦርነት ገብረ እያሱ ድል አደረገ፡፡ ከገብረ እያሱ በኂላ የተላከው መሃረ ክርስቶች የተባለ የጦር መሪ ግን ተሸነፈ፡፡ የመሃረ ክርስቶስ ጦር እንደተሸነፈም የአዳሉ መንግስት እንደገና ኃይሉን አሰባስቦ ወደ ገብረ እያሱ ጦር ፊቱን አዞረ፡፡ በዚህ ጊዜም ድሉ የሱ ሆነ፡፡ ጦሩ ድል በመመታቱ እጅግ ያዘነው በዕደማሪያም ሞተ፡፡

ከአጼ በዕደማርያም መሞት በኂላ ልጁ አጼ እስክንድር (1478-1449) ነገሠ፡፡ በሱ ዘመን የአዳል መሪ የነበረው አሚር ሽምሰዲን ኢብን መሐመድ (1472-1487) ኢብን ነበር፡፡ የአጼ እስክንድር ጦርም በ1478 ደከር ላይ የነበረው የአሚር ሽምሰዲንን ጦር አሟጥቶ ጨረሰው፡፡

ይሁንና ድል አድርጌ ተመለስኩ ሲል መንገድ ላይ ይጠብቀው የነበረው የአዳል ሠራዊት የንጉሠ ነገስቱን ጦር በፋንታው ሙጥጥ አድርጎ ጨረሰውና ንጉሱ ብቻውን አመለጠ።

የሚቀጥለው የአዳሎች መሪ የነበረው መሐመድ ኢብን አዝሃር ሲሆን ይህ መሪ ከክርስቲያኑ ንጉሥ ነገሥት ጋር ተስማምቶ ለመኖር ይፈልግ ነበር። ዳሩ ግን ማሕፉዝ የተባለው የዘይላው የጦር መሪ ከክርስቲያኑ መሪዎች ጋር ጦርነት ለመግጠም ዝግጅት ማድረግ የጀመረው ከአጼ እስክንድር ናኦድ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ነበር። ይህም ዝግጅት እስከ አጼ ናኦድ ዘመነ መንግስት (1491-1508) ድረስ ቀጠለ። ከዚያም ኃይሉን አጠናክሮ አምሐራ፣ ሸዋ እንዲሁም ፋጣጋር ይባል የነበረው ግዛት ማለትም ከሚታወቀው የክርስቲያኑ ግዛት 85 ኪሎ ሜትር ያህል ዘልቆ በመግባት ማጥቃት ጀመረ። ከ19ሺህ ያላነሱ ሰዎችን በመማረክም ለዓረቢያ ሙስሊም ገዥዎች እንደ ባሪያ አድርጐ ላከ።

በ1517 አጼ ልብነ ድንግል ሌት ተቀን ገስግሶ አዳል ገበያ አጠገብ ደረሰ። ጦሩን ከማህፉዝ ጦር ፊት ለፊት አሰፈረ። በዚህ ጊዜ ከፍተኛ ወኔ የነበረው ማህፉዝ የአጼ ልብነ ድንግል ጦር እንደማያሸንፍና ጦርነቱ ቢጀመር ለአዳል ሕዝብ መጥፎ እንደማይሆን በመገመት አሚሩ ከአራት ፈረሰኞች ጋር እንዲያመልጥ መከረው። ከዚያ ጦርነቱን በመግጠም ከዚያ ከዚህ ብሎ ሕዝቡ ከሚያልቅ አንድ የንጉሠ ነገስቱ ሰው እንዲፋለመውና እንዲለይለት ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ገብረ እንድርያስ የተባለ መነኩሴ ፈቃደኝነቱን ገለፀ።

ወዲያው የሁለቱ ጀግኞች የጎራዴ ፍልሚያ ተጀመረ። እጅግ ከፍተኛ ፍልሚያ ከተደረገ በኋላ መነኩሴው የጀግናው ማህፉዝን አንገት ቀላው። ይህም የአዳል ሠራዊትን ሽንፈት አስከተለና አጼ ልብነ ድንግል በርካታ የጦር መሳሪያዎችና ሀብት ለመማረክ በቃ። ይህ ሽንፈት በአዳሎች ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ኪሳራ በማስከተሉ የአጼ ልብነ ድንገል አጋር የነበሩትና የፖርቱጋል የባህር ኃይል ጦረኞች ዘይላን በ1517 አቃጠሏት። ሱልጣን አህመድ በዓመቱ ኃይሉን አሰባስቦ በአጼ ልብነ ድንገል ላይ ቢነሳም እሱም ተገደለ። በሱልጣን መሐመድ አዝሃራዲን (1488-1518) ዘመን በአዳሎች መካከል መከፋፈል ተፈጠረ።

## 2.4 የኢማም ኢብራሂም ብቅ ማለት

በዶክተር ላጵሶ ጌ ዴሌቦ “ የኢትዮጵያ ረዥም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ” መፅሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው አዳል የመስተዳድርና የጦር መሪ ማህፉዝና ሱልጣን መሐመድ መሞት በኋላ አቡበከር መሐመድ /1518-1527/ ድረስ በአዳል መሪዎች በጦር ሹማምንቱ መካከል ታላቅ የሥልጣን ይገባናል ጦርነት ተፈጠረ፡፡ በዚህ የሽግግር ወቅት በ1520ዎቹ የሚቹ ሱልጣን ልጅና ወራሽ ሱልጣን አቡበከር መሐመድ /1518-1527/ የአዳልን የፖለቲካ ማዕከል ከደከር ወደ ሐረር መዲና አዛወረ፡፡ በዚህ ወቅትም ሱልጣን መሐመድ አዝሃረዲን ተገደለና መሐመድ ማሕፉዝ በ1519 ገደማ ለአንድ ዓመት ያህል የአዳል መሪ ሆኖ ገዛ፡፡ እሱም በሁባት ገዥ ኢብራሂም መሐመድ ተገደለ፡፡ ኢብራሂም መሐመድ ከሦስት ወራት በኋላ በመንሱር ማህፉዝ ተሸንፎ ዘይላ ላይ እሱም ተገደለ፡፡ አሚር መንሱር የኢማም አህመድ ኢብራሂም ሞግዚትና አስተማሪ በነበረው ገራድ አቦኝ ተገደለ፡፡ ገራድ አቦኝ አገሩን ለሦስት ዓመታት ያህል በሰላምና በፍትህ ካስተዳደረ በኋላ በ1520 መጀመሪያው አጋማሽ ላይ በሱልጣን አቡበከር መሐመድ ዘይላ ላይ ተገደለ፡፡ አህመድ ኢብራሂም በሱልጣን አቡበከር መሐመድ ላይ አምፆ ሁበት ገባ፡፡ ሱልጣን አህመድ ኢብራሂምን ለመግደል ከ1525-1527 ጥረት ቢያደረግም ሳይሳካለት ቀረና እራሱ ሱልጣን አቡበከር በ1527 በአማፂው እጅ ተገደለ፡፡ ኢማም አህመድ አቡበከርን ከገደለ በኋላ የሚቹን ወንድም ዑመር ሲንን (1527-1553) በሥልጣን ላይ አስቀመጠ፡፡

ኢማም አህመድ በ1529 ደዋሮን አስገበረ፡፡ ከዚያም የአካባቢውን የወላስማ ባላባቶች አሚሮች፣ ቃዲዎችና ገራዶች ለሁሉ በማስተባበር ከጎኑ አሰለፈ፡፡ ከዚያም ፊቱን ወደ ኢፋትና ፋጣጋር አዞረ፡፡ በ1532 የሸዋን ግዛት ያዘ፡፡ በሚቀጥለው የክረምት ወራት ፊቱን ወደ ባሌ ምድር አዞረ፡፡ በዚህ ጊዜ አጼ ዳዊትን ከትግራይ ጀምሮ እስከ ስናር ድረስ ማሳደዱን ቀጠለ፡፡ በእንባ ንጉስ ላይ የነበሩትን ንጉሳዊያን ቤተሰቦችን ፈጃቸው፡፡ የንጉሦችም ንጉስ ይባል የነበረውን ንጉስ አጼ ዳዊትንም በ1540 ላይ ገደለው፡፡ ከጦርነቱ ያመለጠውን ሕዝብ በወቅቱ በአካባቢው የነበረው ረሃብ እንዳልነበር አደረገው፡፡

ከ1332 እስከ 1524 ድረስ ክርስቲያኑ ነገሥታት ከሸዋ ማዕከላቸው ከሸዋ በደቡብ ኢትዮጵያ ነባር አዋማዊና እስላም ሕዝቦችና መንግስታት ላይ ዘወትር የንግድ፣ የግዛትና የሃይማኖት ጦርነቶች በማካሄድ ላይ ስለነበሩ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተከዜና ዓባይ እስትራቴጂያዊ ክልል የሰሜኑ ፈላሻ ሕዝብና አገር በተመሳሳይ የትጥቅ ፖሊሲና ተግባር ለመያዝና ለመግዛት ጊዜና አቅም አልነበራቸውም።

ከ1524 እስከ 1535 ድረስ ኢማም አሕመድ ግራኝ የአጼ ልብነ ድንግልን መንግስትና ጦር ደምስሶ መላ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉርን በቀይ ባሕር እስላማዊ የዳህላክና የምፅዋ ደሴቶችን ጭምር በሥሩ አደረገ። ከ1535 እስከ 1543 ድረስ ለዘጠኝ ዓመታት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሰሜን ፈላሻ ምድር የደምቢያን መሬትና ለም ሀብታም አገር የሱልጣኔት /መንግስቱ/ መሠረትና ማዕከል አድርጎ ቆረቆረ። በዚህ ወቅትና ሁኔታ ሰሜን/ፈላሻ ሕዝብና መንግስት በአጼ ልብነ ድንገል መንግስትና ጦር ላይ ከኢማም አሕመድ ግራኝ ግምባር ጋር በህብረት ተሰለፈ። ይሁን እንጂ በ1543 የንጉሡ ክርስቲያን መንግስትና ጦር ለመርዳት ከሕንድ የመጣው የፖርቱጋል የነፍጠኞች ግብረ ኃይል የኢማም አህመድን ክፍለ አህጉራዊ ሱልጣኔት ደመሰሰ።

በየካቲት 1543 በደምቢያ ክፍለ ሀገር በጣና ሐይቅ አጠገብ በወይና ደጋ ጦር ሜዳ በጥምር የፖርቱጋል ነፍጠኞች ግብረ ኃይልና የአጼ ገላውዲዎስ ሠራዊት ህብረት የኢማም አሕመድ ግራኝ ጦርና ሱልጣኔት ተደመሰሱ። ከዚያ በኋላ ከ1543 እስከ 1597 ድረስ ለስድስት አሥርታት ሦስቱ የአጼው ነገስታት ገላውዴዮስ፤ ማናስና ሠርፀ ድንግል በክፍለ አህጉሩ /1524-1543/1524 የኢማም አሕመድ ግራኝ አመጽና በታላቁ የ/1520-1660/ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ጥምር ግሪት የፈረሰውን የሰለሞናዊው መንግሥትና ጦር በክፍለ አህጉሩ እስላማዊ አዋማዊና ኦሪታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ መልሰው ለመቋቋም ያካሄዱት የትጥቅና የሃይማኖት ጥረቶች ሁሉ ሳይሳኩ ቀሩ። ነገር ግን በተለይ ሁለቱ አጼ ነገስታት ገላውዴዎስና ሠርጸድነግል በፊት በሰለሞናውያኑ መንግስት ሕዝቦችና መንግስታት ላይ መልሰው ለመቋቋም ያካሄዱት የትጥቅና የሃይማኖት ጦርነቶች ሁሉ ሳይሳኩ ቀሩ።

ነገር ግን በተለይ ሁለቱ አጼ ነገሥታት ገላውዴዎስና ሠርጸ ድንግል በፊት ለሰለሞናውያኑ መንግሥት ለሦስት ምዕተ ዓመታት ሁለት ታላላቅ የጂኦ ፖለቲካ ጠላቶች የነበሩትን የአዳል ሱልጣኔትና የሰሜን/ፈላሻ መንግሥት ለመጨረሻ ጊዜ በጦር ኃይል አጠፋው፡፡

ከዚያ አኳያ ከኢማም አሕመድ ግራኝ ሞት በኋላ ከየካቲት እስከ መስከረም 1543 ድረስ አጼ ገላውዴዎስ ጊዜያዊ የጦር ሠፈሩን በደምቢያ አድርጎ በደንቢያ ጎጃም፣ በጌምድር፣ ላስታ፣ የሰሜን/ፈላሻ የትግሬ ሕዝቦችና አገሮችን ከሥሩ በሹም ሽር አደራጃቸው፡፡

## 2.5 የፍልሚያው እስትራቴጂያዊው የቦታ ለውጥ

በዚህ ወቅት በሌላ ግምባር እንዲሁም የሚቹ ኢማም አሕመድ ግራኝ የወንድም ልጅና አልጋ ወራሹ ወዚር ዓባስ አቡን ከበጌምድር የቀድሞ ግዛቱ ከኢማሙ ዝነኛዋ ሚስት ከባቲ ድል ወንበራ ማሕፉዝ ጋር በሽሽት አምልጦ በደቡብ ምስራቅ ሦስቱን የፈጠጋር የደዋሮና የባሌ አጎራባች እስላማዊ አገሮችን በአንድነት ከሥሩ አደረጋቸው፡፡

በደቡብ ምሥራቅ በወዚር አባስ አቡን ወደ ሚመራው አዲሱ የአዳል መንግስት ግምባር ከመመለሱ በፊት አጼ ገላውዴዎስ በፖርቱጋል ነፍጠኞች እርዳታ በደቡብ ምሥራቅና በመሀል ምዕራብ ኢትዮጵያ የሸዋ፣ የዳሞት፣ ጋፋት፣ እናርያ፣ ቦሻ፣ጉራጌ፣ የዋጅና የሀዲያ ሕዝቦችንና አገሮችን ከሥሩ ለማምጣት ያልተሳኩ ወታደራዊ ዘመቻዎችን በማካሄድ በአገሮቹ ላይ የሕይወትና የንብረት ትልቅ ጥፋት አደረሰ፡፡

በተጨማሪም በ1543 መጨረሻ በዝዋይ አካባቢ የዋጅን አገር የመንግስቱ አዲስ ማዕከል አድርጎ ያዘ ፡፡ ከ1543 እስከ 1559 ድረስ የንጉሡ የዋጅ ጦር ሠፈር በአዳልና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች ግምባር የአገሪቱ ዋናው የፖለቲካና የጦርነት ዞን ሆነ፡፡

በጥቅምት 1544 አጼ ገላውዴዎስ ወዚር አባስ አቡንን በዋጅ በተካሄደ ጦርነት ገደለ፡፡ ከዚያ ከወዚር አባስ አቡን ሞት በኋላ ከዋጅ ማዕከሉ አጼ ገላውዴዎስ በተከታታይ በሀዲያ የጉራጌ ገዳሞት በጋፋትና በእናርያ ላይ በሁለተኛ ጊዜ ብዙ የቅጣት የዘረፋ የፀጥታና የግብር ዘመቻዎችን አካሄደ፡፡

በተጨማሪም በቢፎሌ ሉባ ዘመን /1546-1554/ ከአዋጅ ሠፈሩ ተነስቶ ከኦሮሞዎች በባሌ አካባቢ በአገሩ ታሪክ የመጀመሪያውን ጦርነት አካሄደ፡፡

ከ1540ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ እስከ 1550ዎቹ ድረስ አጼ ገላውድዮስ ከዋጅ የጦር ሠፈሩ ከአዳሎች፣ ኦሮሞዎች፣ ሀዲያዎች፣ፖርቱጋሎችና ቱርኮች ጋር በትጥቅ፣ በፖለቲካና በሃይማኖት ሲዋጋ የህይወት ዘመኑ በጦር ሜዳ ሞት ተፈፀመ፡፡

## 2.6 ራስ ሩፋኤልና ራስ ሐመልማል የፖርቱጋልና ቱርኮች ግፊት

ከ1547 እስከ 1550 ድረስ ገላውዴዎስና ሁለቱ ታላላቅ የጦር አበጋዞች የነበሩት ራስ ሩፋኤልና ራስ ሐመልማል ከሐረር እስከ ዘይላ "ከቢር ሰልደዲን እስከ በር አጀም ድረስ" ማለትም ከአዋሽ እስከ ኤደን ባሕረ ሰላጤና እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍ ድረስ በታላቁ የአዳል አገርና መንግስት ላይ ብዙ ተከታታይ የቅጣት ዘመቻዎችን በማካሄድ በሕይወትና በንብረት ትልቅ የሆነ ጥቃትና ጥፋት አደረሱ፡፡ መንደሮች፣ ከተሞች መስኪዶች በማፈራረስ አቃጥሏል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግስታት ላይ አጼ ገላውድዮስና የጦር አበጋዞቹ እንደዚህ የበቀልና የጥፋት ዘመቻዎች ሲያካሄዱ፣ በሌላ በኩል ከ1555 እስከ 57 ቱርኮች በሰሜኑ ጠረፍ የዳህላክና የምጽዋ ደሴቶችን በጦር ያዙ፡፡ በሚቀጥሉት ዓታትና አሥርታት ቱርኮች ከምጽዋና ከሰዋኪን ተነስተው በአርኪኮ፣ ሐማሴን፣ ሰራዬ፣ በደባርዋ፣ አከለጉዛይ፣ በቡር፣ ትግሬና መዘጋ ከተሞች፤ ቀበሌዎችና አውራጃዎች ላይ ረጅም የወረራ ጦርነትን ከፈቱ፡፡

ቱርኮች በሰሜን ኢትዮጵያ ላይ የወረራ ጦርነት በከፈቱበት ዘመን አጼ ገላውዴዎስ በደቡብ ምስራቅ፣ በአዋሽ-ዝዋይ ክልል፣ በፈጠጋርና በደዋሮ አካባቢ ከኦሮሞ የምችሌ ሉባ /1554-1526/ ጋር በጦርነት ላይ ነበር፡፡ በመሆኑም በ1558 በሰሜን ባሕረ ነጋሽ ይስሕቅን ከደባርዋ ከተማ በቱርኮች ላይ አዘመተ፡፡

በ1558 አጼውና ባሕረ ነጋሹ በየግምባራቸው በጠላቶቻቸው ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ በመጋቢት 1559 በዋጅ ለቸደሰሉ አሚር ኑር፣ የሐረር ግምብ መሥራች፣ ጋር ሲዋጋ አጼ ገላውዴዎስ እራሱ ተገደለ።

በአፄ ገላውዴዎስ ሞት ወንድሙ አጼ ሚናስ /1559-1563/ ነገሠ። የአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት አጭርና የውጥረት ወቅትም ነበር። መንግሥቱ በደቡብ በአዳ፣በሀዲያና ኦሮሞ የፍለሳና የሰፈራ እንቅስቃሴዎች፣ በሰሜን ደግሞ ፈላሻና በባሕረ ነጋሽ ይስሐቅ አመጽ እንዲሁም ፖርቱጋሎችና በቱርኮች ግፊት እንደተወጠረ አጼ ሚናስ ራሱ በየካቲት 1563 በዋግ የዘረፋና የቅጣት ዘመቻ በማካሄድ ሱልጣን መሐመድ አራተኛን ከቀድሞ የኢማም አሕመድ ግራኝ የጦር አለቆችና ከሦስቱ የሐረሩ አሚር ኑር ልጆች ጋር በመግደል የአዳልን መንግስት ወደ ዘመነ ፍፃሜው አደረሰው።

በመጋቢት 1577 የዋቤ ሸለቆ ጦርነት የአዳልን መንግስት ከደመሰሰ በኋላ ለአጼ ሠርፀ ድንግል በደቡብ ኢትዮጵያ በአራት የጎሳ አካባቢዎች በግምባሮች ተከፋፍለው በፍለሳ ስምሪት ከእንስሳት መንጋዎች ጋር የሚንቀሳቀሱ የከረዩ፣ወሎ፣ ቱለማና የሜጫ ኦሮሞ ማህበረሰቦች፣ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የአገው የሰሜን ፈላሻና ጉሙዝ ሕዝቦች እንዲሁም በሰሜኑ ጠረፍ አካባቢ ከምፅዋ የቱርክ ወራሪዎች ከአካባቢው አማጽያን ጋር በትጥቅ መፋለማቸው በውስጥና የውጭ ዋና ዋና ጠላቶች ሆኑ።

በዚህ ሁኔታና ወቅት ከመጋቢት 1577 ከዋቢ ሸበሌው ጦርነት በኋላ አጼ ሠርፀ ድንግል በደቡብ ኢትዮጵያ የኦሮሞዎችን ግምባር ክፍት ትቶ ከሠራዊቱ ጋር በሰሜን ምዕራብ በሰሜን/ፈላሻ ምድር በፊት የኢማም አሕመድ ግራኝ ዋና ማዕከል የነበረውን የደንቢያ ለምና ሰፊ የእርሻ አገር የጦሩና የመንግስቱ ቋሚ ማዕከል አድርጐ በፋይል ያዘ።
ማለትም በአካባቢው የጎንደር ዘመነ መንግስት /1577-1855/ ግንባታ ተግባር ጉባኤ በተባለ መንደር በንጉሡ የጦር ሠፈር ተጀመረ።

## 2.7 አሚር ኑር ስልጣን ያዘ

አህመድ ግራኝ ካረፈ በኋላ ዙፋኑን የአዳሉ አሚር ኑር ስልጣኑ ያዘ። አሚር ኑር ደግሞ የራሱ የአህመድ ግራኝ ዘመድ ነው። አሚር ኑር የአህመድ ግራኝ ባለቤት የሆነችው ድል ወምበራን እንድታገባው ሲጠይቃት የንጉስ ግላውዲዮስ ጭንቅላት ቆርጦ በማምጣት እግሯ ስር እንዲያስቀምጥላት ጠየቀችው። እሱም በወቅቱ መናገሻ ከተማው ተቃጥላ የነበረችውን ደብረ ወርቅን መልሶ በመገንባት የነበረው አፄ ግላውዲዮስ ጦር እንዲገጥመው መልዕክት ላከበት። ግላውዲዮስም አልገጥምም ቢለው የሚከተለውን ሁኔታ በመገምገም እስላሞች እንደገና ይነሳሉ የሚለውን ትንቢት እንዳይፈጸምና የጠላቱን እንቅስቃሴ ለመግታት ሲል የቀረበለትን ፍልሚያ ተቀበለ። ማርች 22 ቀን 1559 የግላውዲዮስ ሠራዊት የአሚር ኑርን ሠራዊት ለመግጠም በሚሰናዳበት ጊዜ አንድ የደብረ ሊባኖስ ቄስ ንጉሡ ሕይወቱን በከንቱ እንዳያጣ ገብርኤል በህልሜ ተገልጾ ነግሮኛል የሚል ትንቢት ተናገረ። በትንቢትና ንግርት የሚያምኑ ሐበሾችም ይህንን ሲሰሙ መሸሻቸውን ንጉሱ ከጥቂት ፖርቱጋሎች ጋር ቀረ። ጦርነቱ በተጀመረ አጭር ጊዜ ውስጥም አፄ ግላውዲዮስና ጥቂት ተከታዮቹ ተገደሉ። አሚር ኑር ለድልወንበራ በገባው ቃል መሠረት የአጼውን ጭንቅላት በገፀ በረከትነት አቀረበላትና ሊያገባት ቻለ።

## 2.8 የሀረሪ ሸሪፎች

አሚር ኑር በሕዝቦቹ ዘንድ እንደታላቅ ቅዱስ ተቆጠረ። በወሳኙ ጦርነት ክርስቲያኑን ንጉስ እንዳሸነፈው የአሁኑ የሀረር ጀጎል ግንብ አሠራ። ከዚያ በኋላ የሐረር ጦር መሪ ከአል-ዂዝሪ ጋር በተከታታይ ውይይት ማድረግ ጀመሩ። በአንድ ወቅት ጌይ “ሕምብርተ” ወይም “የሐረር እምብርት” በተባለው ድንጋይ ላይ ተቀምጠው አንድ ቀን የመካ ሸሪፍ መጥቶ ቋሚ ከተማ እንዲመሠርት ሊረዳው እንደሚችል /አል-ዂዝሪ/ ለመነው። ይህንኑ በመንፈስ የሰማው የነብዩ መሐመድ የዘር ሐረግ የሚቆጥረው ሸሪፍ ዮኒስ ወዲያው ልጁን ፈኽርአልዲንን ላከለት። እሱና ተከታዮቹም ሐረር መቀመጥ ስለ ጀመሩ የቅዱስነት ትሩፋት ተገኘ። በዚህ ምክንያት ከተማዋ በሌላ ሳትነካ ለመቆየት ቻለች የሚል አፈታሪክ ይነገራል።

ከዚያ በኋላ የተነሱት የሐረር ሸሪፎች በሙሉ አልፎ አልፎ ከሚያጋጥመው ችግር በስተቀር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያለማቋረጥ ገዝተዋል፡፡ ሪቻርድ በርተን እንደሚለው ከሆነ እነዚህ ሐረርን የገዙ ሸሪፎች "ሰይድ" የሚባሉትን የባላባት ልጆችን እያገቡ የኖሩ ጀበርቲዎችም የአቡ ጧሊብ ልጅ እና የዓሊ ወንድም የሆነው የኻሊፋ አቡበከር ልጆች ናቸው፡፡

ከአሚር ኑር በኋላ የሐረር ድምቀት እየከሰመ መጣ፡፡ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ ቀውስ ክፉኛ ከተማዋን አዳከማት፡፡ በመሆኑም የአዳል አስተዳደር ማዕከል ወደ አዋሳ ተዛወረ፡፡ ሐረር በጭለማው ዘመን ተሸፍና እስከ 1647 ዜና ሳይሰማ አለፈ፡፡ በ1647 የአሚር ዳውድ ኢብን ዓሊ ስርወ መንግስት ተመሠረተ፡፡ ይህ ስርወ መንግስት እስከ መጨረሻው አሚር አብዱላሂ ድረስ የዘለቀ ሲሆን የሐረርን ዝና እንደገና በታሪክ ስፍራውን እንዲያገኝ ያደረገ ነው፡፡

እንደ አሚር ኢብን አቡበከር (1755-82) ማለትም የአሚር አህመድ ኢብን መሐመድ /1794-1821/ ያሉ ጀግኖች ደግሞ ጥቃት ለመሰንዘር የፈለጉትን በመጡበት እግራቸው እንዲመለሱ ያደርጉ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ሽንፈት ምክንያት የንግድ መስመሮች በኦሮሞዎች ይዘጉ ነበር፡፡ ሆኖም ሐረሪዎች በነበራቸው የጋብቻ ዝምድና በአካባቢው ገበሬዎች ነጋዴዎችና ከብት አርቢዎች ለጊዜው የሚያስፈልጋቸውን ማግኘታቸው አልቀረም፡፡ የኋላ ኋላ ግን ኦሮሞዎችና ሐረሪዎች መግባባትና መረዳዳት ጀመሩ፡፡

## 2.2.1 የሐረር በግብፅ መያዝ

ሐረር አንድ ጊዜ ግዛቷ ሲሰፋ በሌላ ጊዜ ደግሞ እየጠበበ ለአምስት ምዕተ ዓመታት ያህል ጊዜ የእስልምና ማዕከል ሆና የቆየች ከተማ እንደነበረ አልፎ አልፎ ተጠቅሷል፡፡ አህመድ ኢብራሂም አልጋዚ ስልጣን ይዞ በነበረበት ዘመን የኢትዮጵያ መዲና ሆና ቆይታለች፡፡ ይሁንና በየትኛውም አህጉርና አገር ሊያጋጥም እንደሚችለው ሁሉ መንግስቷ ተዳከመ እስከ ሰሜን ኢትዮጵያ ተዘርገቶ የነበረው በትረ መንግስት በሐረር ግንብ ውስጥ ብቻ ተገደበ፡፡ ይልቁንም የመጨረሻው የሐረር አሚር መሐመድ አብዱሽኩር ስልጣን በያዘበት ዘመን 1856-1875 በውጭና በውስጥ ተቀናቃኝ ኃይሎች ምክንያት ተዳከመ፡፡ በዚህ መሰረት የሐረር መሳፍንትና መኳንንት አሚር አብድሽኩር የአካባቢው ኦሮሞዎች አሻንጉሊት የሆነ መንግስት ነው ተብሎ ከመወገዙም በላይ ገንዘቧንም ከጥቅም ውጭ አድርገው በወቅቱ የምስራቅ አፍሪካና የኤደን ባህረ ሰላጤ አካባቢ ግዛቷን ታስፋፋ በነበረችው ግብጽ መግባት የጀመረ ዘመን ሆነ፡፡

በዚህ ዘመን በግብፅ መንግስት ውስጥ አድራጊ ፈጣሪ የነበረውና ከዲቭ ኢስማኤል ርዕሰ ጃንዋሪ 10/1974 መጽሐፍ ጽፎ ለአንባቢ ያበቃው ሰዋሰዋዊ ቨርነር ሙዚንገር  መረዋን ሐረር እንዲይዝ ይጎተጉተው ጀመረ፡፡ ይኸው ሳዋሰዋዊ አማካሪ የምስራቅ አፍሪካ የንግድ ማዕከል የሆነችውን ሐረር፤ በርበራና ዘይላ ከተባሉ ወደቦች ጋር የሚያገኘው ቀረጥ የመላውን ግብፅ ሠራዊት ወጪ ይሸፍናል በሚል ሀሳብ ይህን እንደ ቀኝ ግዛት ማድረግ አማራጭ እንደሌለው ሽንጡን ገትሮ ለማሳመን ጥረት አደረገ፡፡

በምስራቅ አፍሪካ ሰፊ ቅኝ ግዛት መስርቶ አገሩን ሊያበለጽግ ከፍተኛ ምኞት የነበረው ከዲብ ኢስማኤል ሐረርን ለመቆጣጠር ቁርጥ ያለ ሐሳብ አደረገው፡፡ በውሳኔው በመጽናቱም በረዑፍ ባሻ 1200 በወቅቱ ዘመናዊ ጦር መሳሪያ የተደራጀ ወታደሮችን አሰልፎ ዘይላና በርበራን ጁላይ 1875 ላይ ያዘ፡፡ ጉዞውን ሴፕቴምበር 1819ቀን 1875 ከዘይላ በመነሳት ጦሩ አሰማርቶ ያልምንም መከታ በግንብ የታጠረችውን ሐረር ኦክቶበር 11 ቀን 1875 ለመቆጣጠር በቃ፡፡ አሚር አብዱሽኩርም አቀባበል አደረገለት፡፡

የአሚር አብድሸኩርን አቀባበል በመከተልም የሀገር ሽማግሌዎችም እንኳን ደህና መጣችሁ አሏቸው፡፡ ከእነዚህ ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ሐጂ ዩሱፍ የአሚር ልጅና ቃዲው መልካም ምኞታቸውን ገለፁ፡፡ እንደዚህ በመሆኑ በመጀመሪያ ላይ አሚሩ ያለአንዳች ማንገራገር የግብጽን ወራሪ ኃይል በመቀበሉ ይህ ክስተት ያልተቀበሉት ክፍሎች ጦርነት ማካሄድ ውጤቱ ሰዎችን ማስጨረስ እንደሆነ አምነው ተቀበሉት፡፡ ይህም ሆኖ የኖሌ ኦሮሞዎች የራዑፍ ባሻን ጦር በግምባር በሐረር መካከል በምትገኘውና ኢጉ ተብላ በምትጠራው ስፍራ ገጥመውት ነበር፡፡

የግብፅን ጦር የገጠመው ኃይል ከፍተኛ ስለሆነ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮም ነበር፡፡ ለሰባት ሰዓታት በተካሄደው ውጊያም ከሁለቱም ወገኖች በርካታ ሰዎች አልቀዋል፡፡ ሆኖም የግብጽ ጦር ዘመናዊ ዕውቀትና የጦር መሳሪያ የታጠቀ ስለነበር የሚበገር አልሆነም በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሚገጥማቸውን ተፋላሚ ኃይሎች ለመደምሰስ የሚችል ነበር፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በሰላም ተቀብለው አሚር መሐመድ አብዱሽኩር በማታው ፀሎት ምዕመናኑን እያሰራ ሲያሰግድ ባሺ ባዙቅ የተባለ ህገወጥ የግብጽ ወታደር ተገደለ፡፡ የአሚርሩ ዘመዶች ወደ አካባቢው ኦሮሞና ሱማሌዎች በመሄድ ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡ የእነዚህ ቤተሰብ አባላት ከከተማዋ ለቀው መውጣት ግን የጥንቱ ኢምሬት ዘመን ፍፃሜ አስመስሎት ነበር፡፡

ምንም እንኳን ሐረር ያለ አንዳች ችግር በግብፅ ቅኝ ግዛት ቁጥጥር ስር ብትወድቅም በአካባቢው የነበሩትን ኦሮሞዎችን ጨፈጨፉ፡፡ ከሐረር መሳፍንትና መኳንንት ጋር የነበሩ ኦሮሞዎች መቀጣጫ እንዲሆኑ እየገደለ በሐረር አምስቱ በሮች ላይ ከመረው፡፡ ሠራዊቱ ሲመናመንም ሱማሌዎችን አየመለመለ መራራ ጦርነት አካሄደ፡፡ ነገር ግን ጠላቶቹ እንዲህ በቀላሉ የሚበገሩ አልሆኑምና ግዛታቸውንም በ40 ኪሎ ሜትር አሰፉ ሁለተኛው የሐረር ገዥ ከዲቪ ፖሻ ሲሾም 35 ሺህ ያህል የአካባቢው ሕዝብ ጦሩን ሰብቆ ሐረረን ከበባት የቅኝ ገዥው

*የግብፅ ወደ ሀረር መግባት ታሪክ በመጠኑ ረዥም ያበሰለ ሆነ ምንም ጭብጡ ሳይነካ በንዑስ ክፍሎች ስያሜ ለንባብ እንዲመች ተደርጓል፡፡ (አርታኢው)*

ሠራዊት መግቢያ መውጫ አጥቶ በረሀብ እጁን እንዲሰጥም ሞከረ ነገር ግን የግብጽ ተጨማሪ ኃይል ከወደብ ሲመጣ ያሰበው ዓላማ ከሸፈ፡፡ እንደገና ኃይሉን መጨመርና ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑም በ1884 3411 የግብፅ ወታደሮች ገብተው በሐረርና በአካቢው ቁልፍ ቦታዎች እንዲመሸጉ ተደረገ፤160 ባለስልጣኖችንና 5 ሺ ያህል ሴትና ሕፃናትም ሰፈሩ፡፡

## ወደ ከተማዋ መዝለቅ

የከተማውን ህዝብ አንድ አምስተኛ ያህል የቅኝ ገዢ ኃይሎች ሲገቡ ሁኔታዎች መለዋወጥ ጀመሩ፡፡ ይልቁንም ሠራዊቱ ሐረርን ሲቆጣጠር ምሽግ መሥራት ስላስፈለገው ከከተማው ነዋሪ ጋር ተቀላቀለ ብዙዎቹ የግብፅ ወታደሮች የሐረርን ልጃገረዶች ማግባት ጀመሩ፡፡ ጥቂቶቹ የግብፅ ባለስልጣኖችም ለዘልአለሙ የሚኖሩ ስለመሰላቸው የመሬት ባለቤት ሆኑ፡፡

ታዋቂው የታሪክ ጸሐፊያቸው መሐመድ ሙኽታር እንደጠቀሰው የሐረሪ ጨዋዎች ለውጭ ሀገር ሰዎች መልካም እንደሆነ የመሰከረላቸው ሀቅ ነው፡፡ የግብፅ ቅኝ ገዢዎች ለአስር ዓመታት ያህል በቆዩበት ጊዜ ሁሉ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ነበር፡፡ ስለሆነም ከነሱ በፊት ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ዙሪያ ጥምጥሙ የጀገል ግንብ አጥር ተጠናክሮ መሠራት ያለበት መሆኑን አመኑበት በርግጥም ከሐኪም ጋራ ላይ ባመጡት የኮረት ድንጋዮች የተሰራው ግን በጥሩ ሁኔታ አልነበረም፡፡

## ግንባታ

ከቀይ አፈር በተቦካ የጭቃ ግንብ የተሰራ በመሆኑም ይህን ያህል ጠንካራ ከመሆኑ አልፎ አልፎ ፈርሶ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቁመቱ እስከ አራትና አምስት ሜትር ያህል ከፍ ያለና ጠላትን ከርቀት ለመቆጣጠር የሚረዱ 24 ግንብ ቢኖሩትም የግንቡ አጥሩ በአብዛኛው ከአንድ ሜትር ተኩል አይበልጥም ነበር፡፡ ይህንን አስጊ ሁኔታ ለማስቀረት ሲባል የአጥሩን ቁመት ማስረዘም አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡

ከከተማው በስተሰሜን ምስራቅ በሚገኘው 100 ሜትር ያህል ርቀት ባለው ኮረብታ ላይ ክሩፕ እየተባለ ይጠራ የነበረው የወቅቱ ከፍተኛ የጦር መሳሪያ ተተከለ አምስቱ በሮች ሌት ተቀን በግብጽ ወታደሮች አማካኝነት በጥብቅ ይጠበቁ ጀመር ዘወትር ዓርብም የግብጽ ሰንደቅ አላማ በክብር መውለብለቡ እየተለመደ ሆነ።

የታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚሉት ከሆነ የግብፅ ቅኝ ገዥዎች ከተማዋን ከያዟት በኋላ ጎጆ ቤቶች እየፈረሱ ከድንጋይ የሚሰሩ ቤቶች እየተበራከቱ ሄዱ። ከስሩ በርካታ እስረኞች የታጎሩበት ቤተመንግስት ፈርሶ በምትኩ ሁለት ፎቅ ያለው ሕንፃ ተሠራ እስረኞችም ወደሌላ ወህኒ ቤት ተዘዋወሩ ሐረሪዎች "ዲዋን" (ፍርድ ቤት) ብለው የጠሩት ይኸው ቤተመንግስት በአጥር የተከበበና የዋናው በር መግቢያ በአትክልትና በአበቦች የተዋበ ነበር።

ራኡፍ ባሻ ከዚህ በተጨማሪም አንድ ዋነኛ መስጊድ ከአሚሩ ቤተመንግስት አጠገብ አሰርቶ ነበር። ይህም ሰፊ የመስገጃ ክፍልና ሚናሬት ያለው መስጊድ ጀማ ራዑፍ ባሻ እየተባለ ሲጠራ ቆጥቷል። ግብጻውያን በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ አካበቢ በሚገኘው በር አከባቢ ሆስፒታል ሠርተዋል። ሐረርን ሬድዋን ባሻ የተባለው ግብጻዊ ሲገዛትም በከተማው ውስጥ የቧንቧ ውሃ የመዘርጋት ዓላማ ነበረው ሆኖም አላማውን ከግብ ሳያደርስ የቅኝ አገዛዝ ዘመኑ አስቀድሞ አከተመ በግብርናው መስክም ቢሆን መሻሻል ታይቷል። እንደ ወይን፣ ስኳር፣ አገዳ፣ ድንች፣ዳቦ ስኳር ድንች የመሳሰሉት አትክልቶች እንደ ሎሚ ያሉ ፍራፍሬዎችም ለምተው ነበር ይባላል መንገዶችም ተጠርገዋል።

## ዲሞግራፊያዊ ክስተቱና አስተዳደራዊ ለውጥ

የጤና ሁኔታ በመሻሻሉ አንዳንድ የልማት ሥራዎች በመሠራታቸው ምክንያት በ1875 30 ሺ ያህል የነበረው ሕዝብ በአስር ዓመታት ውስጥ ቁጥሩ ወደ 35 ሺ ከፍ አለ። በከተማ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥርና የፖለቲካ የበላይነት የነበራቸው ሐረሪዎች በአካባቢው ኦሮሞዎች፤ ሱማሌዎችና አፋሮች ተጥለቀለቁ። ስለሆነም ከ24ሺ እስከ 25 ሺ ሐረሪዎች 3ሺ የግብጻ ወታደሮች 5ሺ የግብፅ ሴቶችና ሕፃናት 3ሺ ያህል ከሸዋ የመጡ አሚሮች እንደነበሩ ተመዘገበ።

ከዚህም በተጨማሪ ግብጻውያን ቅኝ ገዢዎችን ተከትለው ከየመን የመጡ 100 ዓረቦች ፤50 ያህል ቱርኮችና ግሪካውያን ነጋዴዎች ሦስቱ ኢጣልያውያን ነበሩ፡፡ በተለይም አውሮፓውያኑ በአብዛኛው ነጋዴዎች የተቀሩት ዳቦ ጋጋሪና ፈረሰኛ ነበሩ፡፡

የግብፆች የቅኝ አገዛዝ ዘመን በጥቅሉ ሲታይ ጥንታዊና ባህላዊ መልክ የነበረው የሀረር አስተዳደር በዘመናዊ መልኩ ተቀይሯል፡፡ ለአስተዳደር ሲባልም ከተማዋ በ147 ወረዳዎች ተከፋፍሏል የሰዎች የቤት፤ የንብረትና የአትክልት ቆጠራም እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡ የአካባቢው ኦሮሞዎች የቡና ተክላቸውን ጠንክረው እንዲያለሙ የተሻለ የከብት እርባታ ዘዴ እንዲስፋፋ ጥረት አድርገዋል፡፡

ንግድ በአሚሮች ዘመን ከሐረር ወደብ ቦታዎች መጓዝ እጅግ አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም ግብፃውያኑ ቅኝ ገዥዎች ግን በየአማካይ ቦታዎች የደህንነት ቀጠናዎችን በማቋቋምና ያልተቋረጠ ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም የታወቁ የቅፍለት መናሐሪያዎችን በማጠናከርና የውሃ ጉድጓዶችን በማስቆፈር የነበረውን ችግር አስቀርተው ነበር፡ ፡ በዚህ ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ የቅፍለቱ መጠን ከሰባ ወደ አራት መቶ ከፍ አለ፡፡ የቡና፤ የቆዳ፤ የዝሆን ጥርስ፤ የሙጫ ንግድ እየተስፋፋ በአሚሩ ዘመን አብቦ የነበረው የባሪያ ንግድ በግብፆች ዘመን በይፋ ባይቀርም በሕግ ታገደ ወደ ውጭ ሀገር ገበያ የሚላከው የምርት መጠን ሲጨምር ከውጭ የሚመጣውም ዕቃ ዘይላ የተባለች ወደብ ላይ ቅባት፤ ልብስና ሌሎች በፋብሪካ የተመረቱ ውጤቶች በብዛት ይገቡ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በሀገር ቤት ይመረቱ የነበሩ ልብሶች ከሕንድና አሜሪካ በርካሽ ዋጋ ይሸጡ የነበሩትን ልብሶች በገበያ ለመወዳደር አልቻሉም፡፡ ይህም የእጅ ጥበብ ባለሙያዎችን ሚና በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀዘቅዝ አደረገው፡፡

# ከፍተኛ የቀረጥ ገቢና ትሩፋቱን ወደ ካይሮ

ምንም እንኳን ቤቶች ቢሰሩ፤ መንገዶች ቢገነቡ የምርቱ መጠን የግብርናውም ሆነ ንግዱም ሲጨምርም ከፍተኛ ገቢ አገኛለሁ ብሎ የመጣው ቅኝ ገዥ ውሎ አድሮ ለሠራዊቱ ስንቅና ትጥቅ እንዲሁም ለሐገሬው በጀት መደጎሚያ የሚውል የሚገባኝን ያህል ግብር ስፈሩልኝ ማለቱ አልቀረም፡፡ በዚሁ ምክንያት ከፍተኛ ቀረጥ በመጨመር በአካባቢው ሕዝብ ላይ ተጣለ ለምሳሌ ከሐረር የሚወጣውም ሆነ የሚገባ እያንዳንዱ ግመል አስር ፒያስተር፤ በበቅሎ ላይ ደግሞ አምስት "ፒያስተር" እንዲከተል ተደነገገ፡፡ የቡናው ቀረጥ 25 በመቶ፤ እያንዳንዱ የበሬ ቆዳ 25 ፒያስተር፤ እያንዳንዱ የፍየል ቆዳ ግማሽ ፒያስተር ቀረጥ ተጣ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የነበረው ቀረጥ ዋጋ ቀነሰ የአካባቢው ኦሮሞዎች የሐረሪዎች መገበያያ የነበረው መሐለቅና አሽራፍ ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ተደረገ፡፡

---

*ቅፍለት የሲራራ ንግድ የሩቅ መንገድና በርካታ ግመሎች አማካኝነት የሚጓጓዝ ነው፡፡*

በመጀመሪያ ላይ የግብፅን በጀት እንዳቃወሰች ተደርጋ ስትቆጠር የነበረችው ሐረር በዓመት እስከ 25 ሺ የግብፅ ጁኔ እስከ 60 ሺ አርደብ መለኪያ እህልም ወደ ካይሮ መንግስት ገቢ የምታስገባ ሆነች። በአንድ በኩል ህዝቡ ሲበዘበዝ በሌላው በኩል ደግሞ አሊ ባሻ የተባለው ሦስተኛው ግብፃዊ ገዥ ጠንቋዮችን የሐገር ባሕል መድሐኒት አዋቂዎችን፤ የጥንቆላና የኮከብ ቆጠራ መፃሕፍትን አስወግዶ የናርኮቲክ ቅመም ያለው "ጫት" መቃም እንዲቀር በንግዱ ላይም ከፍተኛ ቀረጥ ጣለ። ሬድዋን ባሻ የተባለው አራተኛ የግብፃዊ ገዢ ደግሞ በጠላና በአልኮል መጠጥ ላይ ቁጥጥር ሲያደርግ በጫት ላይ ደግሞ ከፍተኛ እርምጃ ወሰደ።

ምንም እንኳን የግብፃዊያን የቅኝ አገዛዝ ቀንበር በሐረሪዎች ላይ ቢጫንም በአንዳንድ መልኩ ግን የልማትና ዕድገት መታየቱም አልቀረም። ስለሆነም ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ሁሉ ባህላዊው የአሚሩ አስተዳደር ቀርቶ አንፃራዊው የውጭ ሀገር ተወላጆች ከየሀገሮቻቸው ጋር በደብዳቤ መገናኘት ጀመሩ። የሃይማኖት ነፃነትም ቢሆን ከአሚሩ ጥብቅ አመራር ወቅት ጋር አንፃር ሲታይ የተሻለ ነበር። ለምሳሌ የሮም ካቶሊክ ሚሽን ከተማዋ ውስጥ እንዲገቡ የተደረገው በዚሁ ዘመን ነበር።
ናዳር ባሻ የተባለው ግብፃዊ ደግሞ እስከነጭራሹ በግምብ በታጠረችው ሐረር ውስጥ ካቶሊኮች ቤተክርስትያን እንዲሰሩ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ደውላቸውም እንዲደረግ ተፈቀደላቸው።

## ከፍተኛ ጫና ከውጭ ቀውስ ከውስጥ

ግብፆች ለአስር ዓመታት ከሐረር እስከ ዘይላ ያለውን የንግድ መስመር ሲቆጣጠሩ ቢቆዩም የእንግሊዝ ግብፅን መያዝ የሱዳን ማህዲስቶች በሷ ላይ በመነሳታቸውና የእንግሎዝ መንግስትም የከዲቭ ኢስማኤል ቅኝ ግዛት ማዳከምና ማጥፋት ስለመጀመሩ በሐረር ላይ የነበረው አቅማቸው ተዳከመ በተለይም በ1884 ላይ ስንቅና ትጥቅ መምጣቱ ሲቀር ወታደሩ ምግብ ለማግኘት ሲል ኦሮሞዎችን እየሸጡ ወደ ሐገራቸው ሲገቡ ቆሻሻና ቅራቅንቦ በየመንገዱ በመጣላቸው ንጹህ የነበሩት ጎዳናዎች ቆሸሹ ይህንን ሁኔታ የተገነዘቡትና ለአስር ዓመታት ጥቃት ሲፈፀምባቸው የነበሩት ሐረሪዎች ኦሮሞዎችና ሱማሌዎች እንደ ድሮው አንበዘበዝም፤ ትዕዛዛችሁንም አናከብርም አሉ ወደ ድንበር በሚወስደው መንገድ ላይም በደፈጣ ጥቃት አደጋ መጣል ጀመሩ።

እንግሊዝ የግብፆችን መውጣት ተከትላ የሚቆጣጠሩ ሁለት መኮንኖችን ወደ ሀረር ላከች፡፡ የዲቭ ሠራዊት አባላት ሚስቶቻቸውን እየተወ በየቀኑ ከሐረር ወጡ በራዑፍ ባሻ ቤተመንግስት ውስጥ የእንግሊዝ ቆንስላ ተቋቋመ፡፡ የግብፅ ቅኝ አገዛዝ ማክተሙን የተመለከቱ አውሮፓውያን በመጀመሪያ ላይ የእንግሊዝ መንግስት የቅኝ አገዛዝ ቀንበሩ ዘርግቶ የሚቆይ መስሏቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ለመቀጠል አለመፈለጉን በማስታወቂያ የአሚር አብዱሽኩር ልጅ የሆነው አብዱላሂ ስልጣኑን እንዲይዝ ስላደረገው ወታደሩንም ማሰልጠን ስለጀመረ እቃቸውን እያቃጠሉ ማስወጣት ጀመሩ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የግብጽ ቀኝ ገዥ መንግስት መንኮታኮት የተመለከተችው ኢጣልያ ዘይላን በመያዝ ሐረርንም ለመቆጣጠር ፈለገች፡፡ በዚህ መሰረት የኢጣልያው ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማንቺኒ ጃንዋሪ 2 ቀን 1885 ወደ ብሪታንያ በመሄድ ሠራዊቷን ወደ ሐረር ለመላክ ዝግጁ መሆኗን አረጋገጠች፡፡ እንግሊዝ የዚያን ጊዜ ኢጣልያ ሠራዊቷን ወደ ሐረር ብትልክ ተቃውሞ እንደሌላት ብትገልፅም ፈረንሳይ ግን በጭራሽ እንደማይሆን በመግለፅ ተቃውሞዋን ይፋ አደረገች፡፡ ስለሆነም የኢጣልያ መንግስት ምኞት ሳይሳካ ቀረና እንግሊዝ ለአሚር አብዱላሂ ሁለት መድፍ 300 ጠመንጃዎች በሜይ 20 ቀን በመስጠቷ እሷ በጁን ወር ሙሉ በሙሉ ዜጐቿን አስወጣች፡፡

አብዛኞቹ በግብጽ ቅኝ ገዢዎች ደግነት የተሳቡት የውጭ ሀገር ዜጐች ከሐረር የወጡትም በዚሁ ጊዜ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ሶርያውያን ግሪኮች በባህር ዳርቻው ቀሩ ይህም ሆኖ በግብፅ መንግስት ተመልምለው ከሱዳን በተለይም ከዳርፉር የመጡት ወታደሮች ለአዲሱ አሚር አብዱላሂ መንግስት አድረው ማገልገል ቀጠሉ፡፡ ምንም እንኳን የብሪታንያ መንግስት ሐረርን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ባይፈልግም አንዳንድ እንግሊዞች ወደ ከተማዋ መጥተው ካስተዋሉ በኋላ መቆጨታቸው አልቀረም፡፡ ያም ሆነ ይህ አሚር አብዱላሂ ስልጣን ከያዘ በኋላ ግብፆች በጣሉት ታክስ መቀጠል አልፈለገም፡፡ እንዲያውም ተወዳጅነትን ለማትረፍ ሲል ወደ ከተማዋ ለሽያጭ በሚገባው ዕቃ በድምሩ አምስት በመቶ ግብር እንዲከፈል አደረገ፡፡ የግብጾችን ምሽጐች በማፍረስ መስጊድ አደረጋቸው፡፡ የዘይላን መንግስት ይቆጣጠሩ ከነበሩት ኢሳ ሱማሌዎች ጋር ወዳጅነትን መሠረተ፡፡

የእስልምና ሃይማኖትንም በአዲስ ወኔና ሀይል ማስፋፋት ቀጠለ፡፡ የሸሪዓ ህግም ተዘረጋ፤ አልኮልና መጠጥ እንዳይጠጣ፤ በግብጾች ታግዶ የነበረውን የባርያ ንግድ መልሶ እንዲቀጥል ፈቀደ፡፡

አሚር አብዱላሂ በእንግሊዞች አማካኝነት ስልጣን ላይ የወጣ መሪ ቢሆንም አውሮፓውያንን አምርሮ ይጠላ ነበር፡፡ ይህንንም አመለካከቱንም በሱ ስልጣን ዙሪያ የተሰበሰቡት ሁሉም ይጋሩታል፡፡ ሕዝቡ ግን መውጣትና መግባት የማንችል እስረኞች ሆንን በማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያማርር ነበር፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ንጉስ አፄ ምኒልክ ደግሞ ግዛቱን ወደ ደቡብና ምስራቅ እያስፋፋ የሐረርን ሰሜናዊ ግዛቶች ይቆጣጠር ጀመር ይህም በሁለቱ መካከል የሚደረገውን ጦርነት አይቀሬ አደረገው፡፡

## 3. አግሪ አግሪና በርቲ በርቲ የሐረር ኢ ማሬት ይካሄድ የነበረውየወታደራዊ ሥልጠና

አግሪ አግሪ ማለት እንደዚህ ትንታኔ መሠረት በጦር፤ በዓርማና በጋሻ በመታገዝ ውጊያ ማካሄድ ማለት ነው፡፡ ከጥናቱ ውጭ ግን አግሪ የሚሰራው ከጉማሬ ወይም ከጕሽ ቆዳ ነው፡፡ አዛውንቶች እንደሚያስረዱት ከሆነ እስከ 1905 እያንዳንዱ ቤት የራሱ አግሪ ነበረው፡፡ ይህ የሆነው በዚያን ወቅት ሐረሪዎች ልጅ እያሱን በመደገፋቸው አግሪአቸውን እንደወረሱባቸው የቀሩት ደግሞ በ1945 ሐረሪዎች በሙሉ በአጼ ኃይለሥላሴ ላይ ተንኮል ሸርበዋል በተባለበት ወቅት በፖሊስ ታስረው አግሪዎቻቸው ተወስደዋል፡፡

በርቲ ማለት በሐረሪ ቋንቋ ከእንጨት የሚሰራ ኢላማ ማሳያ መዋጊያ ፍልሚያ ማካሄጃ ማለት ነው፡፡ ኢላማ ማሳያ የውጊያ መሳሪያ በ1.15 ሜትር ርዝመት የሚቀረጠው ከእንጨት ሆኖ እንጨቱ እንደተቆረጠ በፀሐይ እንዲደርቅና ጭስ እንዲጠጣ ማድቤት ውስጥ ይቀመጣል፡፡

ሐረር ራሷን የቻለች አገር በመሆኗ በአሚሮች ሥር በነበረችበት ዘመናት ሁሉ የሐረር ከተማ መንግስት የራሱ የሆነ ቋሚና ሥራው ወታደርነት ብቻ የሆነ ኃይል አልነበረባትም፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እንኳን የአንድ አሚር ጠቅላላ ጦር 200 ያክል ሆኖ ቁጥር 50 ባለጠመንጃ ሲሆኑ ከተቀሩት ግማሹ የጦር ተጠቃሚዎች እና እንደዚሁም ባላካራና ባለጕራዴዎች ነበሩ፡፡ ይኸው ኃይል ብቻ የሀገርን ስርዓት ያስከብራል ማለት ያስቸግራል፡፡ በአካባቢው አፈ ታሪክ /ኦራል ትራዲሽን/ እንደሚታወቀው ከሆነ አብዛኛው የሐረሪ ጦር ኃይል ዋነኛ ሥራው የአሚሮችን ሕይወት መጠበቅ ከዚያም አልፎ የነዋሪውን ህዝብ ጸጥታ ማስከበር፤ ንግድ በሚገባ መካሄድና ከዚህ ይበልጥ ሁኔታ የንግድ መስመሮች ላይ የፀጥታ፤ ደህንነት ማስፈንና መጠበቅ ሕዝባዊ ንግድ በሚገባ መካሄዱን መከታታል ነው፡፡

---

*አግሪ ጋሻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አላማ የቀስት ከደጋን የሚጣመረው መሳሪያ ሆኖ የሀ ረሪው ግን እንደ ጦር ሆኖ ከጋሻ የሚጣመር ነው፡፡*

የከተማ መንግስቷ ሀረርን የሚጠብቋትና የሚከላከሉላት ወታደሮችን የምታሰለጥንበት ባህላዊ የስልጠና ዘዴዎች ገና ከቁርዓን ጌይ ‹‹በቀራ ቀራ›› ቀጥላም “በርቲ በርቲና” “አግሪ አግሪ” የተባሉትን ኩነቶች የሚያልፍ ስልጠናዎች በባህል ተሰንዶ ይገኛል፡፡

ከልጅነት ጀምሮ የፉክክሩ ስሜት በራስ የመተማመን ሥነ-ልቦና የአሸንፋለሁ እሴት በማስረፅ ይከናወናሉ፡፡ ስልጠናው አሳታፊና ትምህርት የሚቀርብበት ነው፡፡ ከየዞኖቹ የሚመጡት ወጣቶች ይወዳደሩበታል፡፡ መደበኛ የሆነ የእርከን ደረጃም አለው፡፡ ድፍረትን፤ መግፋትና ታክቲካዊ ማፈግፈግን ይኖሩበታል፡፡ በህዝብ ፊት በመቅረብም ወጣቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ቦታ ይገነዘቡበታል፡፡ ከእድሜ እኩያ የተቀባይነት፤ ሌሎችን አሸንፎ ማእረግ ማግኘት፤ መሳሪያ አያያዝና አጠቃቀም ትምህርቱ በደረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ በአላቱ በድሪ፤ ኸቲመት ወ.ዘ.ተ የሚቀርብው እሴት አፈጣጠር አቀራረፅ በእውኑ ለሚጋጡ ተጨባጭ እውነታና ነባራዊ ክስተት እንግዳ አይሆንበትም፡፡ በዚህ ክፍል አግሪ አግሪ በርቲ በርቲ ቡድኖችን መዝሙሩና ስልጠናዎችን እንወያይበታለን፡፡

እንደ ሐረሪዎች አፈ ታሪክ ጥንካሬና ብርታት ብቃት የተገኘው በአግሪ አግሪ እና በርቲ በርቲ አማካኝነት የማናቃቂያና የማሰልጠኛ ዘዴ ነው፡፡ ስልጠናው ወንድ ወጣቶችን በዘዴ አደራጅቶ ያቀፈ ነበር፡፡ እነዚህ ወንዶች የሚመረጡት ከየዞኖችና ሌሎችም በተጨማሪ የሚውጣጡት ተጐራባች ከሆነው የአካባቢው የገበሬ ልጆች ነበር፡፡ እነርሱም ሐረርን በሐረሪነቷ ራሷን የቻለች ሀገር ሆና እንድትቆይ ረድተዋታል፡፡

## 3.1 የስልጠናው ባህሪ

አግሪ አግሪ ይብዛ ይነስም በቁርአን ጌይ /ቁርአን ትምህርት ቤት/ የሚማሩ ተማሪዎች መሠረታዊ የሆነውን ወታደራዊ ትምህርት የሚቀስሙበት የትምህርት ዓይነት ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር ወጣቱ በግዴታ ማሟላት የነበረበት የጦር ትምህርት ነበር በሌላ አንፃር ደግሞ በርቲ በርቲ ማለት ከላይ የተጠቀሱት ወጣቶች የበለጠ የሥልጠና ተግባር እንዲካሄድ ይበልጥ የጦር ትምህርት በአእምሮአቸው ውስጥ እንዲሰርጽና ፈጣን የጦር ሰዎች የሚሆኑበትን ዘዴ የሚቀስሙበት ከጥንታዊ የጦር ትምህርት ዘረፍ የሚመደብ ነው፡፡ በተለያየ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ወጣቶች ያጠቃልላሉ እነዚህን ወጣቶች የከተማው ህብረተሰብ በ5 ደረጃ ይከፍላቸዋል ይህ ክፍፍል የሚደረግበት በ5ቱ የከተማይቱ የመኖሪያ ዞኖች በመመርኮዝ ነበር፡፡

የዚህ ዓይነቱ የውጊያ ስልት ወጣቶቹ ተማሩ የሚባሉት በተወሰነ ክብ ብረት ወይም ከቀጭን ሐረግ በተሰራ ክብ ነገር ውስጥ ጦር ወርውሮ የማሳለፍ ቴክኒክ ነው፡፡ በዚህ የቴክኒክ ሙያ የተካኑት ወጣቶች በችሎታቸው ለጠላቶች በቀላሉ አይበገሩም፡፡

ከሰሜን ምስራቅ በሮች ማለትም "ከአሱምበሪ" እስከ "አርጐበር" ድረስ ባለው ከግንቡ ውጫዊ ሰሜን ምስራቅ በኩል "አውወሪቃ" የሚባል አጎራባች ቦታ አለ፡፡ በአንድ ቅዱስ ስም የተሰየመው ይህ ቦታ እስካሁን ድረስ በነዋሪዎቹ ሕዝብ ከአግሪ አግሪ ወይም "ስንዋዬ ሺዋዬ" ጋር ተያይዞ ይታወቃል፡፡

"አግሪ አግሪ" ልጆችን መሠረታዊ የሆነ የወታደራዊ ስልቶችን ጋር ለማስተዋወቅ ተብሎ የታሰበ የመጀመሪያ ደረጃ የወታደራዊ ስልጠና ባህልም ነበር የስልጠና ተቋሙ የተዋቀረው "አሱምበሪና" እና "አርጎበሪ" በመባል የሚታወቁ ተፎካካሪ ቡድኖች መካከል የሚደረግ የውጊያ ፍልሚያ ነበር፡፡ በትክክለኛው ገጽታው ስንመለከተው የመጀመሪያው አሱምበሪ የተመሰረተው በአሱምበሪና አስማዲንበር ዞኖች ውስጥ ከሚገኙት የቁርአን ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባሉ የወንድ ተማሪዎች በሙሉ ሲሆን "አርጎበሪ" የተዋቀረው ደግሞ ከቀሩት የከተማዋ ዞኖች ነበር፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር በሚመረጠውና "ፋሪስ" በሚባለው ጊዜያዊ የቡድኑ መሪ የበላይነት ይተዳደር ነበር፡፡

ለፍልሚያው ይሰጥ የነበረው ጊዜ በዓለ ተልሒጅ 12ኛው ወር የመጀመሪያዎቹ 8 ቀናት ከሰዓት በኋላ ሲሆን ከወሩ የመጀመሪያ ቀን አንስቶ የሚያበቃውም የኢድ አልአድሃ ዋዜማ ነበር፡፡ የየእለቱ የልምምድ እንቅስቃሴ ወቅት በእያንዳንዱ በቁርአን ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች የከሰዓት በኋላ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ጦራቸውንና ጦሩ የሚወረወርበት ክብ የኢላማ ገመድና አርማ በመያዝ ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ቀናት በሁሉም የቁርአን ትምህርት ቤት የሚውሉ ተማሪዎች በቡድን በመሆን ከሌላ አካባቢዎች ዞኖች የሚመጡትን ጓደኞቻቸውን ወደ ሚገናኙበት አንድ የተመረጠ ቦታ ይጓዙና በኃላም ወደ "አው ወሪቃ" ይሄዳሉ፡፡

ወደ አው ወሪቃ ጉዞ በሚያደርጉበት ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን የበላይነት ሊያስገኝለት የሚችል ብቃት እንዳለው ለማሳየት ጥረት ይደረጋል፡፡ ከየአካባቢው ከነበሩትና ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተው ካለፉት አባቶች ያገኙት ባህላዊና ታሪካዊ ውርስ ጀግንነትና ቆራጥነትን በመግለፅ ፉከራና ቀረርቶ በከፍተኛ ድመፅ ያሰሙ ነበር፡፡ በዘፈኑ መሃልም የሁሉም የቁርዓን ትምህርት ቤትና ቁርአን ጌይ መምህራንን የሚያሞግሱ የግጥም ስንኞች ይገኙበታል፡፡ እየዘፈኑ በሚጓዙበት ጊዜ ጋሻቸውን ያጋጨሄ ነበር፡፡

በተፋላሚዎቻቸው ክልል አቋርጠው ሲያልፉ አሸናፊነታቸውን ያረጋግጡ ነበር፡፡ ተሸናፊዎቹም መሳሪያዎቻቸውን ለከቢር ያስረክቡ ነበር፡፡ ከዚያም በአባቶች አስታራቂነት የተወሰዱት መሳሪያዎች በሚቀጥለው ቀን ለእውነተኛው ባለቤታቸው ይመለሳሉ፡፡

በመጨረሻ ይህ የአግሪ አግሪ ሥርዓት አካል ሆነውን ቀን ከቢር ይመራና በእያንዳንዱ ክብረ በዓል ላይ የተወሰኑት የቅዱስ ቁርዓን ምዕራፎች ይነበብ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉም ተፋላሚዎች ወደ የቤታቸው የሚመለሱት በሐረሪው ቋንቋ የሚከተለውን በመዝፈን ነው፡፡

አባ አሐዱው ማን ገደሌው? አባ ኮኦቱው ማን ገደሌው፤
አባ ኮኦቱው ማን ገደሌው? አባ ሺኢሽቲ ማን ገደሌው፤

ወደ አማርኛ ሲለወጥ ትርጉሙ
ብቸኛውን ሰው ማን ገደለው? በሁለት ሰው ተገደለ
ባለ ሁለቱን ሰው ማን ገደለው? በሦስት ሰዎች ተገደለ።

ከዚህ የቅብብሎሽ ዘፈን አረፍተ ነገር መገመት የምንችለው ነገር ቢኖር እነዚህን ልጆች ለማስተላለፍ የሚፈልጉት ብዙሃኑን ኃይል በጥቂቱ ኃይል ላይ ያለውን የበላይነትና ሚና ነበር። በእያንዳንዱ ቀን ከስልጠና እንቅስቃሴ በፊት ስለአጠቃላይ ጋሻና ጦር በሚያልፍባቸው ገመዶች የሚደረግ የአላማ ቴክኒኮችና ሌሎች ታክቲክ የተሞላበትን ስልቶች በተመለከተ አጭር ገለፃ ይሰጥ ነበር።

በጥቅሉ ሲታይ አግሪ አግሪ የሐረሪ ልጆች ጦርና አላማቸውን ይዘው የውጊያ ልምድ የሚያካብቱበትና በጦር ስልት ኩነት ራሳቸውን ለመከላከል የሚረዳቸው የጦር ስልት ነበር። ከጊዜ በኋላ በዚሁ ስልት ጦርና አላማ እንዲሁም ጋሻ እንዴት እንደሚያዝ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በቀውጢው የጦርነት ወቅት ራሳቸውን ተከላክለው በጦርነት የድል ፍሬን ይቀምሱበታል ተብሎ ይታመን ነበር።

ከዚህ ሌላ ታክቲካዊው የማፈግፈግ ዘዴ ለመማርና ለአጥቂነት ለመዘጋጀት ለተፋላሚው ጎራ በመግባት ጭንቀትና ረብሻ ለመፍጠር በቀላል ወሳኝ ድል የሚቀዳጁበትን መንገድ የሚያስችል የወታደራዊ ስልጠና ዘዴ ነበር።

“ከበርቲ በርቲና” “ከአግሪ አግሪ” ሌላ “ቁጢ ተከል ቀራ” ማሽላ አገዳ እና ዱላ በተለያዩ የዓመቱ ወቅቶች ተደራጅተው በመዋቀርሰ የሚያገለገሉ የውጊያ ፍልሚያዎች ከቤት ውጭ ከሚደረጉት ስፖርቶች ጋር የሚመሳሰሉ ሲሆን የሚከናወኑትም በአነስተኛ የእድሜ ደረጃ ውስጥ በሚገኙ ወጣቶች መካከል ነበር። የተጠቀሱት ፍልሚያዎች በዝቅተኛ እድሜ ውስጥ የነበሩት ወጣቶች ጦርና አላማ ተሸክመው በአግሪ አግሪ በርቲ በርቲ ያለምንም ችግር እንዲሳተፉ አስፈላጊውን ልምድ ለማካበት የታቀዱ ነበር። በዚህ መሰረት ወጣቶች የሃይማኖት ትምህርት እንዲጠናቀቁ የህብረተሰቡን የተዋጊ ኃይል ከሚያሰባስቡትና በተዋረድ ከተዋቀሩት ከአምስቱ የሐረሪ ሙጋዶች የአንዱ አባል ይሆኑ ነበር።

በእርግጥ በአምስቱ የከተማዋ በሮች አሱምበሪ፤ አርጎበሪ፤ ሱቅጣጥበሪ፤ በድሮበሪና አስማዲንበሪ ቁጥራቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ሙጋዶች ነበሩ፡፡ በተለምዶ በአንድ ዞን የሚገኙ ልጆች በአንድ የቁርአን ትምህርት ቤት እንደሚማሩ ሁሉ ወደፊት አባል የሚሆኑትም በሚኖርበት በር ባለው ሙጋድ ነበር ፡፡ በእነዚህ ሙጋድ መዋቅር ዶርሲስ፤ ሳዲያን፤ ቫኖን፤ ዴቢስና አደል በመባል የሚታወቁ አራት የበላይነት የስልጣን ተዋረዶች ነበሩ፡፡ አዳልና ዶርሲስ የተዋቀሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከከፍተኛና ከጀማሪ የስልጣን ደረጃዎች ነበር፡፡ በተለያዩ ዞኖች የሚገኙት ሙጋዶችና እንደዚሁም በሙጋዶች ውስጥ የሚገኙ የስልጣን ደረጃዎች አንዱ ከሌላ ተለይተው የሚታወቁበት የሚገኙበት ዞኖች ስም ከሙጋድና የስልጣን ደረጃው ርእስ ጋር አያይዘው በማቅረብ ነበረ፡፡

በተወሰኑ በሪዎች የሚገኙ ወንድ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ የቁርአን ትምህርታቸውን ጥናታቸውን የሚያጠናቅቁት በመሀከለኛው የጉርምስና እድሜያቸው ሲሆን በዞን አባልነት ራሳቸውን ያደራጁት ባሉበት ዞን የጀማሪ "ዶርሲነት" ማዕረግ ያገኛሉ፡፡ አዳሎች በፍቃደኝነት ራሳቸውን ከማዕረጉ ሲያገልሉም ወዲያውኑ በአራት የስልጣን ደረጃዎች ባሉ የመጀመሪያዎቹ ባለማእረግ አባላት ይተካሉ፡፡ በዚህ ጊዜ "የደርሲ" የስልጣን ደረጃ ክፍት ስለሚሆን በአዲስ ወጣት አባላት ይሟላል፡፡

ከዚህ ገለጻ የምናገኘው ማጠቃለያ ሙጋዶች ከቁርዓን ትምህርት ቤት እድሜ በላይ በመካከለኛው የእድሜ ክልል በታች ያሉትን የህብረተሰብ አባላት በበርቲ በርቲ አሰልጥነው በማደራጀት የሚያስታጥቁ አባላት ነበሩ፡፡ ይህ በተለምዶ የሚደራጅ በአንድ ሙጋድ ውሰጥ ባሉት የተለያዩ ግለሰቦች እና በሌሎች ሙጋዶች መካከል ሲሆን በየዓመቱ ደግሞ በአምስት በሮችች ውስጥ ባሉት ሙጋዶች በጡንሱስ በቅድመ ሰርግ ባሉት ምሽቶች እና እንዲሁም የ6ቱ የሙስሊም ፆም ፍቺ ሸዋል ዒድ፤ በድሪና በኸቲመት በዓላት ወቅቶች ነበር፡፡

## 3.2 የሸዋል ዒድና ተንከስ በርቲ በርቲ

ወጣቶች ወደ ሙጋድ መዋቅር ውስጥ የመመልመሉ ባህላዊ ልማድ ውጤታማና የተሳካ ከሆነ በርቲ በርቲ አብዛኛውን ጊዜ የሚዘጋጀው በተለያዩ ሙጋዶች በእኩል የማዕረግ ደረጃ ባሉ ግለሰቦች በተዋቀሩት ቡድኖች መካከል በሸዋል ኢድና ጡንሱስ በዓላት ወቅት ነበር። ይህ ሆኖ በአንድ ሙጋድ የተወሰነ ማእረግ ያላቸው አባላት በሌሎች ሙጋዶች ባሉ የማዕረግ እኩዮቻቸው ላይ የበላይነት ለማግኘት ይሞክሩ እንጂ በአንድ ሙጋድ ውስጥ የተለያዩ ማዕረግ ባላቸው አባላት መካከል የሚከሰት ግጭት የተለመደ አልነበረም።

በእነዚህ ባህላዊ የፍልሚያ ውድድሮች ተሸናፊው ቡድን ወዲያውኑ ከጨዋታ ውጪ ይሆንና በተቃራኒ ቡድን ለሚገኙ ሙጋድ የስልጣን ተዋረድ ተጨማሪ ማዕረግ ለሚያገኙ አሸናፊዎች ማዕረጋቸውን አሳልፈው ይሰጡ ነበር። ለምሳሌ የአሱንበሪ ዶርሲሶች ተፎካካሪዎቻቸውን በአርጎበሪ ሙጋድ የመጡትን ዶርሲሶች መድረክ ከፍልሚያ ካስወጡ የዶርኪስነት ማዕረግን ከአሱምበሪ ብቻ ሳይሆን ከአርጎበሪ ይሰጣቸዋል። አንድ ጊዜ ከጨዋታ ከተባረሩ ተሸናፊዎቹ ማዕረጋቸውን ባጡበት መንገድ ለሽንፈት ያበቋቸውን ተፎካካሪዎች መልሰው ካሸነፉ በስተቀር በምንም ዓይነት ሁኔታ ያጡትን ማዕረግ እንደገና ለማግኘት አይችሉም። ከዚህ መገንዘብ የምንችለው በተለያዩ ሙጋዶች ያሉ የተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ባለማዕረጎች የማዕረግ ውድድር ያደረጉ እንደነበር ነው። ስለዚህ የእያንዳንድ ሙጋድ ባለማዕረጎች የራሳቸውን ማዕረግ ማስከበርና ሌላም ከፍተኛ ማዕረግ ለማግኘትና በስልጣን ተዋረዱ ያላቸውን ቦታ ለማስጠበቅ ከፍተኛ ትግል ያደርጉ ነበር። የህብረተሰቡ ባሕልም በዚህ መንገድ ባደጉ ወጣቶች የማህበረሰቡን የወታደራዊ ስልት ያጠነክረዋል ብለው ያምኑ ነበር።

## 3.3 በበድሪ የኸቲመት ቀናት የሚከናወን በበርቲ በርቲ

በጣም ልዩ የሆኑት የውድድር እንቅስቃሴዎች በቅዱሱ የረመዳን ወር 17ኛ ና 27ኛ ቀናት ውስጥ የሚከናወኑት የበርቲ በርቲ ጨዋታዎች ነበሩ። በእነዚህ ቀናት በአካባቢው ህዝብ እስካሁን ድረስ በድሪና ኸቲመት በመባል ይታወቃሉ። ሁለቱም ቀናት በአጠቃላይ የህብረተሰቡን የፍልሚያ ኃይል የሚያሳትፍ በከፍተኛ ደረጃ ውድድር የሚዘጋጁባቸው መንፈሳዊ የህዝብ በዓላት ነበሩ። እነዚህ የፍልሚያ እንቅስቃሴዎች በአንድ ጊዜ ሃይማኖታዊና ወታደራዊ ዓላማዎች ነበራቸው።

የበድሪ ክብረ በዓል አንድ ጊዜ ይዘጋጅ የነበረው ነብዩ መሐመድና ተከታዮቻቸው ከሒጅራ ሁለት ዓመት በኋላ በረመዳን 17ኛ ቀን ከመካ ጠላቶቹ ጋር በድሪ የሚል ስያሜ ባገኘው ጦርነት ላይ ለተቀናጁት ወሳኝ ድል መታሰቢያነት የተሰጠና ምናልባትም እለቱ በድሪ ሊባል የቻለበት ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል። ትርጉሙ በሐረሪ ቋንቋም በተመሳሳይነት ያገለግላል።

በተመሳሳይ ወር 27ኛው ቀን የሚዘጋጀው ፍልሚያ ውድድር ሃይማኖታዊ ምክንያት ነበረው። በሁሉም ሙስሊም ይህ ምሽት "ለይለቱል ቀድር" በመባል ይታወቃል። የኃይል ክብር ምሽት ማለት ነው። ቀኑ ከቅዱስ ቁርዓን ለመጀመሪያ ጊዜ መውረድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተከበረ ቀን ነው። ምናልባትም ሐረሪዎች የእለቱን ክብረ በዓል ያዘጋጁ የነበሩት ከዚህ ጋር በተያያዘ ምክንያት ይሆናል።

ምንም እንኳን የኸቲመት እለት የሚደረገው የፍልሚያ ውድድር ትክክለኛው ቦታና የተፎካካሪዎች አሰላለፍ ባይታወቅም ሁሉንም ወጣቶች ማሳተፍ እንዲቻል ተደርጐ ይዘጋጁ እንደነበር ይታመናል።

በሌላ በኩል በበድሪ እለት የሚዘጋጀው የፍልሚያ ውድድር በተለያዩ የእድሜ ክልል በሚገኙ ወጣቶች መካከል የሚደረግ ሲሆን የፍልሚያ ውድድር ይካሄድ የነበረው አሁን አው ባሶር ከበድሮ በሪ ውጭ ከበሩ በስተደቡብ የሚገኝ ቦታ ላይ ነበር። በበድሪ እለት የሚደረገው ውድድር በበድሮበሪና አስማዲ በሪ ወይም በተለምዶ አጠራር ቡዳበር ዝቅተኛ የሆነ ዞን ውስጥ የሚገኙትን የሙጋዶች አባላት ሁሉ ያሳትፍ ነበር።

በበድሪ እለት የሚከናወነው ፍልሚያ የራሳቸውን ቡድን ለማበረታታት ወደ ውድድሩ የሚመጡት እድሜያቸው የገፋ ሰዎች ጨምሮ ለማንኛውም ፍላጐት ላለው ሰው ሁሉ መድረኩ ክፍት ነበር።

ሁለቱንም ፆታዎች የሚያካትት ቁጥሩ እጅግ ከፍያለ የውድድሩ ተመልካቾች በተጨማሪ መሪዎችን ጨምሮ የተለያየ የፖለቲካና የሃይማኖት የበላይ አካላትን ያቀፈ ነበር። በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው እንዲህ ያሉ ውድድሮች የወጣቱን ወታደራዊ ችሎታና የተዋጊነት ብቃት ለመገምገም ስለሚያስችሉ በአሚሮች ዘንድ ይወደዱ ነበር። በሌላ በኩል ግን የፍልሚያ ተሳታፊዎች መድረኮች ያላቸውን ጠንካራ ጐንና የየግል ችሎታና ቆራጥነት ለመንግስት ከፍተኛ አካላትና ለሕብረተሰቡ ለማሳየት እድል የሚሰጡ ተደርገው ይወሰዱ ነበር።

ነገር ግን በተለያየ የበዓል ቀናት የሚከናወኑ የፍልሚያ ውድድሮች አብዛኛውን ጊዜ በትከሻና በወገብ ላይ የአካል ጉዳት በራስ ላይ ብዙውን ጊዜ ጉዳት አያስከትሉም ነበር። ይሁንና በአግሪ አግሪና በበድሪ እንቅስቃሴዎች ወቅት ድርጊቱ ሕይወትን እስከማጣት የሚያደርስ ቢሆንም በማንኛውም መንገድ ሕግ ጣልቃ አይገባበትም ነበር። ነገር ግን አፄ ምኒሊክ የሐረርን ሃይማኖታዊ ገጽታ ለተወሰነ ጊዜ ቢቀጥልም የሐረር ወታደራዊ ገደል ግን ጠፍቶ ነበር። የሐይማኖት ገጽታው ቢሆን እየተዳከመ ሄደና ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የውጊያ ልምምድ ወረደ። ይህም በሰርግ ወቅት በምሽት ሰዓት ብቻ ይጠቀሙበት እንደነበር እንረዳለን።

በአጠቃላይ ሐረሪዎች እንደሚሉት ከሆነ ሐረር በዙሪያዋ ከነበረው ህዝብ ተከታታይ ወረራዎች አንድነቷን ጠብቃ ልትቆይ የቻለችው በነበራት 200 ባለ ጠመንጃዎች እና ጥቂት ጦር ባነገቡ ሰዎች ብቻ ነበር ማለቱ የማይታመን ነው። የሐረር ከተማ መንግስት ህልውና ለመጠበቅ የቻለው ጥንታዊ የሆነ የጦረኝነት ውርስ ወታደራዊ አመራርና ችሎታ በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ባደረገው በሳልና ያልተቋረጠ ወታደራዊ ትግል ነበር ለማለት ይቻላል።

እዚህ ላይ መታለፍ የሌለበት አንድ ጉዳይ በእያንዳንድ የሐረሪ ቤት ውስጥ የፊት ለፊት ግድግዳ ላይ በተለይ ለጦርና ጋሻ ማስቀመጫ እንዲሆን ተብሎ የተሰራ “ወረም ሞራጃ” የተባለ መደርደሪያ የወታደሩ ስልጠና ጥንካሬ እያንዳንዱ ግለሰብ ከጦር መሳሪያዎች ጋር ያለውን ግንኙነትና ፍቅር አመላካች ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለፈረስ የሚሰጠውን ክብር ስንመለከት ሐረር በከተማ መንግስትነት ባሳለፈችው ዘመናት በሙሉ በሳልና በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ ወታደራዊ የሆነ ህብረተሰብ ይኖርባት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

## ሐረር በሚኒሊክ መያዝና የመጨረሻው አሚር አብዱላሂ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ሁሉ ሐረር በምስራቅ ኢትዮጵያ ለብዙ ዓመታት የእስልምናን እምነት ተከትላ አንድ ጊዜ ግዛቷን ስታስፋፋ በሌላ ጊዜ ደግሞ ስትነጠቅ ቆይታለች፡፡ በመጨረሻ ግን የኢማም አሕመድ ኢብራሂም አልጋዚ መሸነፍ የኦሮሞ ሕዝብ መስፋፋትና የግብፆች ቅኝ አገዛዝ አደከማት፡፡እ.ኤ.አ በ1887 በተደረገው የጨለንቆ ጦርነት በአፄ ሚኒሊክ ጦር በመሸነፍ የተቀረው ኢትዮጵያ አካል ለመሆን በቃች፡፡ ለመሆኑ ለጨለንቆ ጦርነት የተደረገው ዝግጅት የጨለንቆ ጦርነትና ውጤቱ ምን ይመስላል፡፡

ያኔ የሸዋ ንጉስ የነበረው ምኒሊክ ሐረርን ለመያዝ የፈለገው በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሁሉ በታሪካዊ ምክንያትነቱ ነው፡፡ ይኸው ታሪካዊ ምክንያት “የኢትዮጵያ ግዛት የአፍሪካ ቀንድን በተለይም ኤርትራ፣ የዛሬው የአፋር ግዛትን ጅቡቲን፣ ዘይላንና በርበራ ያጠቃልላል” በሚል እሳቤ ይነሳል፡፡ ንጉስ ምኒልክ እ.ኤ.አ ሜይ 25 ቀን 1884 በወቅቱ ወዳጁ ለነበረው ለኢጣሊያ ንጉስ በጻፈው ደብዳቤ “ጃንሆይ ቱርኮች በግብጾች አማካኝነት አጠገቤ ተቀምጠዋል፡፡ ይህም ለኔ አስተዳደር በጣም ጉጂ ከመሆኑ በላይ በየቀኑ ችግር እየፈጠረብኝ ይገኛል፡፡ ይልቁንም ሐረርን ከወሰዱብኝ በኋላ በግዛቴ አካል የሆኑ ኦሮሞዎችና በረሃማውን ግዛቴ ለመያዝ እየጣሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ከግብጾች ጋር ጦርነት ብንገጥም የአውሮፓ መንግስታት እንደጠላታቸው እንዳይመለከቱኝ አንተ ምስክሬ ትሆናለህ” ማለቱን ያረጋግጣል፡፡

ይህ ደብዳቤ በአንድ በኩል የሚያመለክተው ሚኒልክ ሐረር ኢቱ ኦሮሞዎች ያሉበት ግዛትና በረሃማው ክፍል ሁሉ ከግዛቱ ጋር አንድ ማድረጉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቱርክን በመተካት ከምጽዋ እስከ ዘይላ ያለውን የያዘችው ግብፅ በ1875 በወቅቱ ደካማ የነበረውንና እንደ ነፃ መንግስት ይቆጠር የነበረውን የሐረር ኢምሬት በጥቅምት ወር መግቢያ ላይ ይዛ እንደነበር ያሳያል፡፡ ምኒልክ ከዚህ በተጨማሪ ክርስትናን እንደ መሳሪያ በመጠቀም "የመስቀል ምልክት ያለበትን ዘውድ በጨረቃ ሊቀይሩብኝ" ነውና "ክርስቲያን" ነን የምትሉ አውሮፓውያን አገሮች ሁሉ ከጐኔ ቁሙ" የሚል ጥሪ ያስተላልፍ እንደነበር ይታወሳል፡፡

ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ እንደ ጥንት አባቶች የሐረር አሚሮችም ሆኑ የአካባቢው ኦሮሞዎች፣ እንደቀድሞው እየገበራችሁ ከኖራችሁ አልቃወማችሁም፡፡ በባህላችሁ፣ በእምነታችሁ አልገባም" በማለት ፋንታ ሠራዊቱን በማሰለፍ ግዛቱን ራሱ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር የፈለገበት መሠረታዊ ምክንያት እንደ ሉዓላዊነት መሳሪያ የሚያስገባትን ወደብ ከግብጽ በማስመለስ፣ የንግድ መስመሩን በመቆጣጣር የገቢ ምንጩን ለማዳበር፣ መንግስቱን ለማስተዳደር የሚጠቅመውን ቁሳቁስ ከውጭ ገበያ እየተገዛ እንዲገባ ለማድረግ ቁርጠኛ ዓላማ ስለነበረው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን ፅኑ ዓላማ ግብ ለማድረስ ቆርጦ የተነሳው ንጉሥ ምኒልክ የጦር ኃይሉን በማሰባስብ ፊቱን በ1883 ወደ መስራቅ አዞረ፡፡ ከሸዋ በስተምሥራቅ ያለውን ግዛት እየተቆጣጠረ ወደፊት ገፋ፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለት ዓነይት ታሪካዊ ክስተቶች እንደነበሩ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ አንደኛው ግብጽ ከሐረር በስተምዕራብ ያሉት ግዛቶች በመቆጣጠር ወደፊት ለመግፋት ብትሞክርም ያልተሳካላት በመሆኑ፣ ይልቁንም የካይሮ መንግስት ሐረር ለነበረው ቅኝ ገዥ እርዳታ ለማድረግ አለመፈለጉ፣ በዚህም ምክንያት መሪዎቻቸው ከኦክቶበር 1884 እስከ ሜይ 1885 ድረስ ሐረርን ለቀው ባህር ዳርቻ መድረሳቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ፈረንሳይ ጁላይ 1884 ላይ ከኦቦክ ጀምሮ የታጁራ የባህር ወሽመጥን ጨምራ ስለነበር ወደ ሐረርም ትስፋፋለች የሚል ዓለም አቀፍ ጥርጣሬ መኖሩ ነው፡፡ ይህ ማለት የኢጣሊያ፤ የእንግሊዝ፣ ጀርመንና የሌሎችን ቅኝ ገዢዎች ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ምኒልክ በመጠኑም ቢሆን ይህንን መረጃ እንዳገኘ መገመት አያዳግትም፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ኢጣልያም ፌብርዋሪ 5 ቀን 1885 ላይ የምጽዋ ወደብን ያዘች፡፡

ሚኒልክም በኤፕሪል መጀመሪያ 1885 ላይ ሰላዮቹን ወደ ሐረር በመላክ ግብያች ለቀው መውጣታቸውንና ሐረርን ይገዛት የነበረው አሚር አነስተኛ ክቡር ዘቦች ብቻ እንዳሉት መረጃ አገኘ።

ንጉስ ምኒልክ መረጃውን እንዳገኘ 1886 ክረምት ማብቂያ ላይ ሠራዊቱ ለጦርነት እንዲከት አወጀ። ከዚያም ሠራዊቱ ከተተና ኖቬንበር 12 ቀን 1886 እንጦጦን ለቆ ወጣ። ሴፕቴምበር መጀመሪያ ላይ ከ30 እስከ 35 ሺ የሚገመተው የምኒልክ ጦር አርሲ ከነበረው ከራስ ደርጌ ጦር ጋር በመቀላቀል የአርሲን ሰሜናዊ ግንባር በመተው በአዋሽ ሸለቆ በተለይም በሰሜን ምሥራቅ አርሲ አቅጣጫ በኩል ወደ ሐረር ተጓዘ። የሸዋ ዘማቾች ኢቱ ኦሮሞዎችን አሸንፈው የመያዛቸው ወሬ በሜይ 1886 በሐረር ውስጥ ተሰማ። በእርግጥም በጁን 1886 በደጃዝማች ወልደገብርኤል የሚመራው የምኒልክ ጦር ኢቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ገለምሶ የተባለችው ከተማን የቆረቆረ ከመሆኑም በላይ የኢቱ ኦሮሞዎችን እስከ ቡርቃ ወንዝ ድረስ አባሯቸው ነበር።

የሚኒልክ ጦር ከሸዋ ተነስቶ ወደ ምሥራቁ ሲገሰግስ የሐረሩ አሚር ጦር ከቡርቃ በስተ ምሥራቅ እስከሚገኙት የአቦራ ኦሮሞዎች ድረስ ወደ ፊት ገፍቶ ነበር። የሐረሩ አሚር ጦር ከምኒልክ ሠራዊት ጋር የሚመጣጠን ባይሆንም ከተማዋን ግብያች ጥለውለት በሄዱት መድፍ አስጠብቆ ወደፊት ሲገሰግስ የደጃዝማች ወልደገብርኤል ጦር በረሃብና በሽታ መመናመኑ ተሰማ። በዚህ ጊዜ የአሚሩ ኃይል የምኒልክን ጦር ለማስፈራት ብሎ በተኮሰው መድፍ ምክንያት የደጃዝማች ወልደገብርኤል ጦር የተከበበ መስሎት ወደ አሰቦትና ወደ አዋሽ ሸሽቶ ነበር። የዳግማዊ ምኒልክ የምስጥር መረጃ አቀባይ የነበረው አለቃ እድሜም የደጃዝማች ወልደገብርኤል ኃይል ፈርቶ "በቀለም በተዋበ እሳት" አቃጥለው ሊፈጁን ነው ሲሉ ነበር። በዚያ ሌሊት ምሽጋቸውን ለቀው አምልጠዋል። ሠራዊቱን ለማረጋጋት የተደረገው ሙከራ ከሸፏል" ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ በመሆኑ የደጃዝማች ወልደገብርኤል ጦር እየሸሸ አዲስ ከታጨደ የአገዳ ማሳ ውስጥ እየገባ እግሩ ሲቆራረጥ ሐረሪዎች እየተከታተሉ ያሳድዱት ነበር። በዚህ ጊዜ የሐረር ከተማ በመጠኑም ቢሆን እፎይታ ከማግኘት በላይ ለሚኒልክ ዘመቻ የበለጠ ለመዘጋጀት ፋታ አግኝታ ነበር።

የደጃዝማች ወልደገብርኤል ጦር ችግር ቢደርስበትም የምኒልክ ጦር ኃይሉን አሰባስቦ ወደፊት በመግፋት ቡርቃ ወንዝ አጠገብ ለመመሽግ በቃ፡፡ ያኔ አሚሩ ጦሩ ከሐረርና 65 ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘውና ወራቢሊ ተብላ በምትጠራው ስፍራ እንደሚገኝ ሲረዳ ወደዚያው ገሠገሠ፡፡ከዚያም ከጃንዋሪ 2 ቀን ጀምሪ በማንኛውም ጊዜ ጦርነት ሊከፈት እንደሚችል በመግለጽ ጦሩ ዝግጁ እንዲሆን ታዘዘ፡፡ አሚር አብዱላሂ ጨለንቆ ላይ መሽጐ እስከ ጀምዋሪ 5 ቀን ሲጠባበቅ ከቆየ በኋላ ጃንዋሪ 6 ቀን የገና በዓል ስለነበርና አጋጣሚው የምኒልክ ጦር ከብት በማረድ በዓል እንደሚያከብር በመገመት ድንገተኛ ተኩስ በመክፈት ውጤት የሚያስመዘግቡ ኃይሎች ወደ አካባቢው ሄደው ምርኮ እንዲያመጡ ታዘው ነበር፡፡

እንደዚህ ያለው ፍጥጫ እስከ ጃንዋሪ 5 ቢኖርም በሸዋ መረጃ ዜና ዘጋቢዎች መሠረት አሚር አብዱላሂ ወረራ ሳይካሄድበትና ለመንበረ መንግስቱ በኃይል ሳይነሳ እንዲገብር ሐሳብ ቀርቦለት ነበር፡፡ አሚር አብዱላሂም የሚኒልክን ሐሳብ ለሐረር ሕዝብ አቀረበ፡፡ ሕዝቡም “በአላህ ለማያምን መንግስት አንገብርም” በማለት ቁርጠኛ አቋሙን አሳወቀ፡፡

አንዳንድ የሐረሪ አዛውንቶች እንደሚሉት ደግሞ አሚሩ ታማኝ አማካሪዎቹን ሰብስቦ ስለጦርነቱ ሲጠይቃቸው “ግብጾች የተውትን የጦር መሳሪያ እንድናስረክብና እንድንገብር ተጠይቀናል፡፡ ስለዚህ ምን ይሻላል ሲኋቸው የምኒልክ ጦር ኃይለኛ ስለሆነ ለጊዜው የተስማማን በመምሰል የተበላሹ የጦር መሳሪያዎችን እንላክለት የሚል ሐሳብ አቅርበውለት ነበር፡፡ እሱ ግን “እኔ ምኒልክ ምን ያህል ኃይል እንዳለው አልጠየቅሁም፡፡ ጥያቄዬ ለካፊር የጦር መሳሪያ መስጠት መጽሐፉ ይፈቅድልኛል ወይስ አይፈቅድልኝም የሚል ነው፡፡ በማለት ሐሳባቸውን በመቃወም ብዙዎቹ አማካሪዎቹን እስር ቤት አስገባና ጂሃድ አወጀ፡፡ ከዚያም ጦርነቱ አይቀሬ ሆነና ጨለንቆ የነበረው የምኒልክ ሠራዊት የገናን በዓል ለማክበር ከጠዋት ጀምሮ ሽርጉድ ሲሉ የአሚሩ ጦር ፊት ለፊት ካለው ተራራ ላይ ታየ፡፡ ወዲያው ወደ ሚኒልክ ሠራዊት በፍጥነት ወረደ፡፡ አሚር አብዱላሂም ድንገተኛ ውጊያ በመክፈት በመጀመሪያ ላይ የሚኒልክን ሠራዊት ያደናገጠው ቢመስልም ሙስሊሞች ይህንን በዓል መርጠው ጥቃት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ ቀድሞ ታውቆ ስለነበር ራሳቸውን ለጦርነት ዝግጁ ለማድረግ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ ጦርነቱ እንደተጀመረም በንጉስ ምኒሊክ ጦር አሸናፊነት በአጭር ጊዜ ውስጥ አበቃ፡፡

ከአሚር አብዱላሂ ጋር የተሰለፉ በርካታ የሐረር የሱማሌና የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላትም የሞቱት ሲሞቱ የተቀሩት ሸሹ፡፡ አሚር አብዱላሂም ወደ ሐረር ሸሹ፡፡ ምኒልክ ጃንዋሪ 8 ቀን በከፍተኛ ኃይል እየታጀበ ሐረር ሲደርስም አሚሩ እጁን ካልሰጠ በስተቀር ከተማዋን እንደሚወራት አስታወቀ፡፡ በዚህ ምክንያት አሚር አብዱላሂ እጁን ሰጠ፡፡ ምኒልክ እንደሎሌው ተቀበለው፡፡ ዳሩ ግን በዚያው ዕለት አሚር አብዱላሂ ወደ ጂጂጋ መሸሹ ተሰማ፡፡

ከዚያ የአሚር አብዱላሂ ዘመዶች ከዓሊ አቡበከር ጋር ሆነው ጃንዋሪ 9 ቀን የሽምግልና ተግባር ሊያከናውኑ ወደ ምኒልክ ሄዱ፡፡ እዚያ እንደደረሱ ንጉሥ ምኒልክ የአሚር አብዱላሂ ንብረት እንዲያስረክብ ፣ ሐረርን ግን እንደማወራት ቀደም ሲል ቃል እንደገባው ሁሉ የአካባቢው ሙስሊሞች በሸሪዓ ህግ እንዲመሩ ተማፀኑ፡፡ በዚህ ዕለት የምኒልክ በጅሮድ የአሚሩን ንብረት ተረከቡ፡፡ በየበሮቹ የምኒልክ የጦር አበጋዞች ቆሙ፡፡ ከተማዋ እንዳትዘረፍም ጥንቃቄ ተደረገ፡፡ በሦስተኛው ቀን ምኒልክ ሐረር ግዛቱ መሆኗን አወጀ፡፡ ጃንዋሪ 27 ቀን ባላምበራስ በኋላ ደጃዝማች የነበሩት ራስ መኮንን የሐረር ገዢ ሆኖ ተሾመ፡፡ በዚህ ዕለት ወይም በማግስቱ ደግሞ አሚር አቡበከር የከተማውን የሙስሊም ሕብረተሰብ እንዲያስተዳድር ተደረገ፡፡

ምኒልክ ሐረርን ከያዘ በኋላ አሚር አብዱላሂን አሳዶ ለመያዝና ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በከተማው አስተዳደር ላይ ችግር ይፈጥሩ የነበሩ ኦሮሞዎችን ሰጥ ለጥ አድርጐ ለመግዛት ከጃንዋሪ 29 ቀን ጀምሮ አሰሳ ተደረገ፡፡ በአሰሳው ከብትና ንብረት እየተወሰደ ለሠራዊቱ ተከፋፈለ፡፡ ከዚያ እያንዳንዱ በሬ አስር ብር ቀረጥ የማስከፈሉ ኃላፊነት ለአቡበከር ተተወ፡፡ ሐረሪዎች ከኢትዮጵያ ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ የንግድ መስመሩ ከሁሉም አቅጣጫ ቢከፈትላቸውም መጉዳታቸውን ያወቁት ግን በዓመቱ ዋናው መስጊድ ፈርሶ በምትኩ መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን መገንባት ሲጀመር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ክርስቲያን የማድረጉ ሂደት ቀስ በቀስ ቀጠለ፡፡ ይህንን ይቃወሙ የነበሩ ሐረሪዎች ከሀገር የመሰደድ ዘመናቸውን ጀመሩ፡፡ ንጉሥ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ካለፈ በኋላ ስልጣን ላይ የወጡት እያሱ፣ የዘውዲቱና ኃይለ ሥላሴ መንግስታት የከፋ የአገዛዝ ቀንበራቸውን ከመጫን በስተቀር የተሻለ ሁኔታ አልፈጠሩም፡፡

## ሐረር በኢጣሊያ ዘመነ መንግሥት

የኢጣሊያ ፋሽስት መንገስት ግፉን በመላው ኢትዮጵያውያን እኩል የፈፀመና የቅኝ አገዛዝ ቀንበሩን የጣለ ቢሆንም፣ እርስ በርስ ለመከፋፈል በወሰደው እርምጃ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግስት በሙስሊሙች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያደረሰ እንደነበረ ለማሳየት ያደረገው ጥረት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። በዚህ ምክንያት ምንም እንኳን የዓለምን ታሪክ በተለይም የኢጣሊያን ፋሽስታዊ አገዛዝ ምንነት የተረዱት ሙስሊሞች በፖለቲካው ረገድ ጥልቅ ግንዛቤ ያልነበራቸው ሐረሪዎች ግን የጊዜው ፕሮፓጋንዳ አሸንፏቸው የኢጣሊያን መንግስት ለመተባበር በስሜት ተነሳስተው ነበር። ሰባቺ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ በዘገበው መሠረት፣

*‹‹ሙስሊሞች ሙሉ የሐይማኖት ነጻነት ተሰጥቷቸዋል። ቃዲ የአማራውን ዳኛ ተክቷል። በሐረር ዓረብኛ ቋንቋ ሕጋዊ ቋንቋ ሆኗል። የሙስሊም ትምህርት ቤቶችም ይማሩበታል። ሁሉም የኢጣሊያ ግዛቶች የዓረብኛ ቋንቋ የሚታተሙ ጋዜጦችና የዓረብኛ ቋንቋ ፕሮግራሞችን የሚያስተላልፉ የሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ። ኦፊሴላዊ የሆኑ በዓላት ሙስሊም ባለሥልጣኖች ተመርጠው እንዲገኙ ይደረጋል። ተብሎ መታወጁን ጽፏል››።*

እነዚህ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ የተደረጉ ቸርነት መሰል ልገሳዎች፣ የቁሳቁስ ስጦታዎች የገንዘብ ሽልማቶች፣ በተለይም የእስልምናና ለሙስሊሞች ባህል ያሳዩት አክብሮት "የክርስቲያን መንግስት አድልዎና ጭቆና በተሞላበት ሁኔታ ይገዛናል ብለው ያምኑ በነበሩ ሙስሊሞች ልቦና ዘልቆ ለመግባት ረድቶት ነበር።

በእርግጥ አዋጁ በጽሑፍ ብቻ ሰፍሮ ስላልቀረ አዋጁ በዓረብኛም ታወጀ፡፡ በዋነኛው የቁርዓን ትምህርት ቤት 60 ያህል ብቻ የነበሩት የተማሪዎች ቁጥር 450 ደረሰ፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የነበሩት የቅኝ ገዥዎቹ ባለሥልጣኖች የተቀበሉ ሐረሪዎችም ከኢጣሊያ መንግስት ከፍተኛ ደሞዝ ይከፈላቸው ጀመር፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ጐን ለጐን የሀገራቸው ዓይነት ሕንፃዎችን ከግንቡ ውጭ በማነጽ ከተማዋን ዘመናዊ አደረጓት፡፡ የተሻሻሉ ጎዳናዎችንና መንገዶችን ሠሩ፡፡ ማዘጋጃ ቤቱን ገነቡ፡ ፡ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ቴሌኮሙኒኬሽንና የውሃ ቧንቧ ዘረጉ፡፡ ፖስታ ቤት አቋቋሙ፡፡ለቱሪስቶች የሚሆኑ ሆቴሎችን ከፈቱ፡፡ ለወታደራዊ ኃይል አገልግሎት የሚውሉ ቪላዎችንና ሕንፃዎችን ገነቡ፡፡ የአስተዳደሩ ስርዓትም የእስልምና እምነት በሚያዘው መሠረት እንደገና አንሠራራ፡፡

## ሐረር ከኢጣልያ በኋላና ብላታ አየለ ገብሬ

የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ዘመን አክትሞ የአፄ ኃይለስላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ እንደተተካ ሐረሪዎች እንደ ከሐዲና እንደጠላት ጋሻ ጃግሬ ተፈርጀው ነበር፡፡ ስለዚህ

አፄ ኃይለስላሴ ሐረሪዎችን ሰጥ ለጥ አድርገው ለመግዛት ብቃት አላቸው ብለው ያመኑባቸውን ብላታ አየለ ገብሬ የሐረርጌ ክፍለ ሐገር ምክትል ጠቅላይ አገር ገዥ አድርገው ሾሙ፡፡ ብላታ አየለ ገብሬ የፈላጭ ቆራጭነቱ ስልጣን እንደተሰጣቸው በኢጣልያ ዘመን ያልከፈሉትን ግብር ሁሉ እንዲከፍሉ አስገደዷቸው፡፡ በመንግስት ሥራ የመቀጠር እድል ነፈጓቸው፡፡ ወደ ወታደራዊ ክፍል እንዳይገቡ ተከለከሉ፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባ እንዳያደርጉ ታገዱ፡፡ ኦፊሴላዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ ቋንቋቸውንም ሆነ ዓረብኛ እንዳይጠቀሙ፣ እስልምና ነክ የሆነ ትምህርት እንዳይማሩ ተከለከሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሐረሪዎች “ጀሚዓያ ሑርያ አል ሐረሪያ” የተባለ የፖለቲካ ድርጅት አቋቋሙ፡፡ የሐረር ጥንታዊ ታሪክ ጠንቅቀው የሚያውቁት እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች መሠረታዊ ዓላማቸው አፄ ሚኒልክ በ1887 ሐረርን በያዘበት ጊዜ ያረጋገጡላቸው መብቶች ተፈፃሚነት እንዲያገኙ መሆኑን ይፋ አደረጉ፡፡

በዚህ መሠረት “ጃሚዓያ” ንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡ የተሰማውን ቅሬታ አዳምጦ ይረዳቸው ዘንድ የተወሰኑ ተወካዮችን ወደ አዲስ አበባ ላከ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የተለያዩ አስተያየቶች ይደመጣሉ፡፡ አብዛኞቹ አስረጂዎች “አጼ ኃይለስላሴ በሐረሪዎች ላይ ያደረሰው በደል ትክክል አለመሆኑን በመግለጽ ችግሩ እንዲስተካከል ወደ ብላታ አየለ ደብዳቤ ጽፎ ነበር፡፡ ብላታ አየለ ግን ደብዳቤውን እንዳላየ አለፈው ይላል፡፡ አንዳንዶች ግን “ኃይለ ስላሴ ለተወካዮቹ የሞቀ አቀባበል ካደረገና ከሸነገላቸው በኋላ መለሳቸው ይላል፡፡ ያም ሆነ ይህ ለንጉሠ ነገስቱ የቀረበው አቤቱታ ያስገኘው ለውጥ አልነበረም፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በመቀጠል ጣሂር የሚመራው”የሱማሌ ወጣቶች ክለብ” (SYC) በሐረር ውስጥ ቢሮውን ከፈተ፡፡ ይህ ድርጅት የተለያዩ ስሞች ቢሰጡትም በመጨረሻ ግን “ኩሉብ” የሚል መጠሪያ ተሰጠው፡፡ ይህ የፖለቲካ ድርጅት ሐረሪዎችን ስለ ሌሎች ሕዝቦችና ስለነፃነት ያስተምሯቸዋል፣ ሌሎችንም ጉዳዮች ያንቀሳቅሳል የሚል አመለካከት ነበራቸው፡፡ በኦጋዴን የነበረው የኤስ ዋይ ሲ መፈክር ደግሞ “ሶማሊያ ሐኖላቶ፣ ኢትዮጵያ ሐዲምቶ” ማለትም “ረጅም ዕድሜ ለሶማሊያ ሞት ለኢትዮጵያ” የሚል ነበር፡፡ “ሐኖላቶ” የሚለው ስም “ኩሉብ” ከሚለው ስም ጋር እየተለዋወጠ ሲሠራበት ቆይቷል፡፡ በሐረር ውስጥ የኢስ ዋይ ሲ ዓላማና ግብ ከጃሚዓያ ዓላማና ግብ ጋር ስለማይጋጭ ብዙ ሐረሪዎች የሁለቱም ቡድኖች የእስልምና እምነትን የተቀበሉ በመሆናቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ጭቆና የደረሰባቸው በመሆናቸው ተባብረው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት ከዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ፣ ከታላቋ ብሪታኒያ፣ ከፈረንሳይና ከሶቪየት ሕብረት የተውጣጡ አራት አባላት ያሉት የአራቱ ኃያላን ኮሚሽን “የኢጣልያ ግዛት የነበረው የሱማሌ ክፍል ሁኔታ ለመመርመር ሞቃዲሾ ሲገባ 13 አባላት ያሉት የሐረሪዎች ልዑካን ቡድን ወደ ሞቃዲሾ በመላክ የኢትዮጵያ መንግስት በሐረሪዎች ላይ የሚፈፅመው ግፍና ጭቆና አመለከተ፡፡ ከዚያ በመቀጠል ወደ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ወደ ግብጽና ወደ ሌሎች ሙስሊም አገሮች በመሄድ በሐረሪዎች ላይ የጭቆና ቀንበር ምን እንደሚመስል እየተዘዋወረ አስረዳ፡፡

በዚህ ወቅት የካይሮ መንግስት ችግራቸውን በከፊል ያደመጠ ቢሆንም ሐረሪዎች የጦር መሳሪያ አለመታጠቃቸውና በሕቡዕ የሚንቀሳቀስ ጉሬላ ተዋጊ እንደሌላቸው ሲረዳ ፍልስጤሞችን ነፃ ለማውጣት በሚደረገው ጦርነት ተሳታፊ ስላልሆነ ምንም ሊያደርግላቸው እንደማይችል አስታወቃቸው፡፡ ንጉሥ ፋሩቅም በጉዳዩ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ጋር እንደሚነጋገርበት ቃል ገባላቸው፡፡ ንጉሥ ፋሩቅም የገባውን ቃል ኪዳን ከመፈፀሙ በፊት ግን የኢትዮጵያ መንግስት የልዑካን ቡድኑን ተልእኮ በሚመለከት የተላለፈውን ዜና በሞቃድሾ ሬድዮ ጣቢያ አዳመጠ፡፡ በዚህ ምክንያት በሐረሪዎች ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈፀምባቸው ጀመር፡፡

ጃንዋሪ 20 ቀን 1948 ላይ የመንግስት የጦር ኃይሎች የኤስ ዋይ ኤል (SYL) እና የጃምዓያን ጽሕፈት ቤቶችን በቁጥጥር ስር በማድረግ ሁሉንም ሰነዶች ጀምአያ የአባልነት መዝገቦችንና በጽሕፈት ቤቶቹ የነበሩ ሰዎች በሙሉ ታሰሩ፡፡ ይህም ሲሆን የሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት ሰላማዊ በሆነ መንገድ የተፈጠረውን ችግር ለማሳወቅ ወደ መንግስት ፅ/ቤቶች ሄዱ፡፡ አስረጂዎች እንደሚሉት ከሆነ ከሁለቱ ድርጅቶች በአንዱ ያልተመዘገቡ ሐረሪዎች ቢኖሩ እጅግ ጥቂቶች ነበሩና በሰላማዊ ሰልፍ ወደ መንግስት ቢሮዎች የሄዱት ሰዎች ቁጥር በርካታ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ እነዚህ አስረጂዎች ጨምረው እንደገለጹት ሕዝቡ ወደ ጠቅላይ አገር ገዥው ቢሮ ሲሄድ ብላታ አየለ በረንዳው ላይ ባለው መደገፊያ /ባልኮኒ/ ብቅ አለና ይህንን ሁሉ ሕዝብ በአንድ ጊዜ ሊያነጋግር እንደማይችልና አምስት ሽማግሌዎችን ከመካከላቸው መርጠው እንዲሰጠው፤ ይህም ከሆነ ስለአጠቃላይ ጉዳይ ከተመረጡት ሰዎች ጋር እንደሚነጋገር አስታውቃለው አለ፡፡

የተመረጡት ሰዎች ወደ ቢሮው እንደገቡ ምክትል ጠቅላይ አገር ገዥ ብላታ አየለ አንድ በርካታ ብሶት የተፃፈበት ደብዳቤ አወጣና የልዑካን ቡድን ወደ ግብፅ ልከው እንደሆን የሐረርጌ ጠቅላይ አገር ገዥ የሆኑት ልዑል መኰንን ኃይለ ስላሴ ባለበት ጠየቋቸው፡፡ እነርሱም ብላታ አየለ የያዘው ደብዳቤ ጽ/ቤቱ ሲዘጋ በመንግሥት ኃይሎች እንደተወሰደ በማወቅ ለአራቱ ኃያላን መንግስታት ኮሚሽን አባላትና ለዓረብ አገራት የተላከው ደብዳቤ ግልባጭ መሆኑን አረጋገጠላቸው፡፡ ከዚያም ብላታ አየለ ከጽ/ቤቱ ወጥቶ ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ በመሄድ በሚቀጥለው ቀን መልሱን እስኪሰጣቸው ድረስ ሁሉም ወደ የቤቱ እንዲመለስ አስታወቃቸው፡፡

ሕዝቡን ከበተኑ በኋላ አምስቱ ሽማግሌዎች አንዳንድ ነገሮች እስኪያረጋግጡ ድረስ ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲጠብቁ ነገሯቸው፡፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላም አምስቱን ሽማግሌዎች እስር ቤት ከተታቸው፡፡

በሚቀጥለው ቀን ማለትም የጠቅላይ ግዛቱ አስተዳዳር ተሰብስቦ ከተበተነ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ብላታ አየለ ለየት ያለ አቋም ይዞ የተነሳ በመምሰል ሦስቱን ሽማግሌዎች ጠራና ሕዝቡ ከመካከሉ በጣም የሚያከብራቸውን ሰዎች እንዲመርጥና እነዚህ የተከበሩ ሽማግሌዎች የሕዝቡ ፍላጐት ምን እንደሆነ በጽሁፍ ይዘው እንዲመጡ አዘዛቸው፡፡ ሽማግሌዎቹም ጠቅላይ አገር ገዥው ያለውን እንዲፈጽሙና የታሠሩት ሰዎች ግን ምህረት አድርገው ከእስር ቤት እንዲፈታቸው ጠየቁ፡፡ ከዚያም ሌላ 13 ሰዎችን ወደ ሞቃዲሾ መላካቸውን፣ የላኩትም ሐረር ከንጉሠ ነገስቱ አገዛዝ እንድትላቀቅና ሐረሪዎ ግዛታቸውን ራሳቸው እንዲያስተዳድሩ በደብዳቤ ሲያቀርቡ አንዳችም ፍርሃት አለማሳደራቸውን ያስተዋለው ብላታ አየለ በሁኔታው በመደነቅ ሽማግሌዎቹ ባቀረቡት ጽሁፍ ላይ እንዲፈርሙበት ጠየቃቸው፡፡ በሕዝቡ የተመረጡት የሀገር ሽማግሌዎችም በደብዳቤው ላይ ግጥም አድርገው ፈረሙበት፡፡ ይህን ጽሁፍ ማረጋገጫ ያገኘው ብላታ አየለ "ከሞቃዲሾ ሶማሌዎች" ተባብራችኋል በመንግስት ላይም አሲራችኋል በማለት የሀገር ሽማግሌዎቹ እንዲታሰሩ አዘዘ፡፡

በማግስቱ ጠዋት የሽማግሌዎቹ መታሰር ዜና ተሰራጨ፡፡ ወዲያውም ሕዝቡ "ጃሚዕ" ተብሎ በሚጠራው መስጊድ ተሰበሰበና 50 ሐረሪዎችን መረጠ፡፡ እነዚህም ሐረሪዎች የላኳቸው ሰዎች ለምን እንደታሰሩ ለመጠየቅ ወደ ጠቅላይ አገረ ገዢ ቢሮ ሄዱ፡፡ እነሱም እንደቀደሙት በማን አለብኝነት ታሠሩ፡፡ ከዚያ የመንግስት ወታደሮች ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ ብዙ ሐረሪዎችን በቁጥጥር ስር አደረጉ፡፡ የሐረሪዎች የግል ንብረቶችንም ወሰዱ፡፡ ቤታቸውንና መሬታቸውን ሳይቀር ነጠቋቸው፡፡ የሼክ ሁሴን መቃብር ጠባቂዎችም ያ ሁሉ ሰው ሲታሰር እነሱ በመቅረታቸው የመቃብሩን አድባር እንደ አንድ ታአምር ሠሪ ቆጠሩት፡፡

ያ ሁሉ ሰው በታሰረ ማግስት የጠቅላይ ግዛቱ አስተዳደር ምን መደረግ እንዳለበት ለመወያየት ስብሰባ አካሄደ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ልዑል መኮንን ባደረገው የመክፈቻ ንግግር ደግሞ "የሐረሪ ሙስሊሞች" "የአደሬ እስላሞች" በማለት ንቅናቄው ብሔረሰባዊና ሃይማኖታዊ ይዘት እንዳለው ገለፀ፡፡ ከዚህም ሌላ "ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንደአንድ ቤተሰብ ተባብረው መገኘት ሲገባቸው ሐረሪዎች ግን በራስ ወዳድነት የአራቱ ኃያላን ኮሚሽን የኢትዮጵያን የውስጥ ጉዳይ እንዲመረምር ጠይቀዋልና ሲል ኮነናቸው፡፡ ብላታ አየለ በጀጉል ውስጥ ስለሚካሄደው የውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ መረጃ የሚሰጠው ስላልነበረ ስለኩሉብ ንቅናቄ የሚያውቀው አንዳች ነገር እንደሌለ አከለበት፡፡ ከዚህ ሌላ ሐረር የተመሠረተው እስላማዊ ድርጅት፣ ኩሉብና ሞቃድሾ ያሉ ሶማሌዎች ተባብረው ኤርትራና ሱማሊያ ከእናታቸው ኢትዮጵያ ጋር አንድ እንዳይሆኑ በማሴር ላይ መሆናቸውን የሚያመላክት መሆኑ አሳወቀ፡፡

ከዚያም ምን መደረግ እንዳለበት መመካከር ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳን ፍተሻውን ለማካሄድ ተጨማሪ ወታደራዊ ኃይል ከውጭ ማስመጣት እንዳለበትና እንደሌለበት ቢያከራክርም እያንዳንዱ ቤት ውስጥ የመሳሪያ ፍተሻ እንዲካሄድ ተወሰነ፡፡ የታሰሩት ሰዎች ፍርድ ቤት የሚቀርቡት ሐረር ከተማ ውስጥ ወይስ ሌላ ቦታ እንደሆነም ተወያዩበት፡፡ ውይይቱ ካበቃ በኋላ ብላታ አየለ ባደረገው የመዝጊያ ንግግር የተፈጠረውን ችግር ለማስወገድ ተጨማሪ ወታደራዊ ኃይል ማስመጣት እንደሚያስፈልግ ዳኞቹም አንዳንድ የማጣራት ሥራዎች ከተካሄዱ በኋላ በጥንቃቄ እንደሚመረጡና ዳኝነቱ ሐረር ውስጥ እንደሚካሄድ የሚታሰሩበትን ቦታ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች ጋር በመነጋጋር ወደፊት እንደሚወሰን የተደበቀ ጦር መሳሪያ መፈተሹ ግን አስፈላጊ እንዳልሆነና ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ከንጉሠ ነገስቱ ጋር የሚነጋገረው ራሱ ብላታ አየለ እንደሚሆን ይፋ አደረገ፡፡

መንግስት በርካታ ሰዎችን እስር ቤት ከመክተቱ በላይ የሐረሩን መድረሳ የሙስሊሞች ት/ቤት ጨምሮ ሌሎች የህዝብ ንብረቶችን በኃይል ወሰደ፡፡ በርካታ አስረጅዎች በምሬት እንደሚገልፁት በሙስሊሞች መዋጮ ሲንቀሳቀስና ሲስተዳደር የነበረው መድረሳ እስላማዊ ወዳልሆነ ትምህርት ቤት እንደተቀየረና እስካሁንም ወደቀድሞ ሁኔታው አልተመለሰም፡፡ እሥር ቤቶች ከመጠን በላይ በመምላታቸው ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ቢለቀቁም እነዚያ የተለቀቁ ሰዎች ግን የቁም እስረኞች ስለነበሩ ዘወተር ጠዋት ፖሊስ ጣቢያ እየሄዱ አገር ለቀው አለመሄዳቸውን የማረጋገጥ ግዴታ ነበረባቸው፡፡

ከዚያም ቀጥሎ ሐረሪዎች ያለልዩ ፈቃድ ሐረር ውስጥ እንዳይኖሩ ተከለከሉ፡፡ በጥቂት ወራት ውስጥ ከእስረኞች መካከል በትምህርት የተሻሉትን በፖለቲካው መስክ ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸውን እና በአካባቢው ሕብረተሰብ እውቅና የነበራቸውን 81 ሰዎች አስቀርተው የተቀሩትን ለቀቋቸው፡፡ እነዚህ 81 ሰዎች ጅማ፣ ጎሬና ጎጃም ወደ ሚገኙ እስር ቤቶች ከተቷቸው፡፡

ይሁንና ኖቬንበር 1948 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለብላታ አየለ በጻፈው ደብዳቤ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ሙስሊሞችን እንደምትጨቁን ተደርጐ በዓረብ አገሮች እየተወገዘ ስለሆነ ወደ ካይሮ የሄዱትን የልዑካን ቡድን አባላት ዘመዶቻቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመልሷቸው ማንኛውም ጥረት እንዲደረግ አሳሰበ፡፡ በዚህ ጊዜ ጥቂት ሰዎች ሐረሪዎች የመንግስት ባለስልጣኖችን ሲያነጋግሩም ወደ ግብፅ የሄዱት ሰዎች ከተመለሱ የታሰሩት 81 ሰዎች ሊፈቱ እንደሚችሉ  ገልፀውላቸዋል፡፡

ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ትንሽ ቁጥር ያላቸው ሐረሪዎችና የመንግስት ባለስልጣኖችን ወደ ግብፅ በመሄድ ስደተኞቹን አሳምነው ለመመለስ ጥረት ቢያደርጉም ግን ስደተኞች እስር ወይም ሌላ ሊከተል የሚችል አደጋ በመፍራት ለመምጣት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖች የግብጽ ባለሥልጣኖች እንደገለልተኛ ምስክር አድርገው ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው አረጋገጡላቸው፡፡ ይህንን ስምምነት ሁለቱም ወገኖች በፊርማቸው አረጋገጡ፡፡ በዚህ መሠረት ከ13ቱ ሰዎች አብዛኞቹ ተመለሱ፡፡ እነሱ በመመለሳቸው 81 እስረኞች ተለቀቁ፡፡ እንደተለቀቁም በወቅቱ በግብርናና የንግድ ሚኒስቴር የነበረው አቶ መኮንን ሐብተወልድ እስረኞቹን፣ ከካይሮ የተመለሱትን አዳራሽ ሰብስቦ “እናንተ ሐረሪዎች ከሆድ በሽታ ጋር የሚመሳሰል ችግር ፈጥራችኋል፡፡ የሆድ በሽታ ደግሞ የማይድን እንደመሆኑ መጠን እናንተም የኢትዮጵያ ዘላቂ በሽታዎች ናችሁ፡፡ ነገር ግን አጼ ኃይለ ስላሴ  ነፃ ናችሁ ስላለ ወደ ቤታችሁ ሂዱ” በማለት በግሳጼ ሸኟቸው፡፡

የእነዚህ ሰዎች መመለስም የኩሉብ እንቅስቃሴ በ1948 ላይ እንዲቆም አደረገው፡፡ ዋልድሮን በ1960 ያነጋገራቸው አስረጂዎች እንደገለፁት “የኩሉብ ሕልም ከከተማዋ ክብር ጋር አብሮ ጠፋ” ይላል፡፡ በእርግጥ ኩሉብ እስካሁንም ድረስ በእያንዳንዱ ልቦና የማይረሳ ታሪክ ሆኖ ኖሯል፡፡

ዳሩ ግን ሐረሪዎች ከአጼ ምኒልክ በተስማሙት መሠረት መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው በመጠየቃቸው ብላታ አየለ ለምን ይህንን መጥፎ እርምጃ ወሰደ? ለዚህ ጥያቄ ግንባር ቀደም መልስ ሊሆን የሚችል “ ኢትዮጵያ ለሐረሪዎች እንደዚህ ያለውን ሀብት ከሰጠች ኤርትራንና ኦጋዴን አጣለሁ ብላ ስለሰጋች ነው” የሚል ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አጼ ኃይለስላሴ በወቅቱ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ የበላይነት አልያዘም ነበር። ስላልያዘ ሐረሪዎች በጀመሩት ዓይነት ጠቅላይ ግዛቶች ከኢትዮጵያ እያፈተለኩ እንዳይወጡና በዓለም ሕዝብ ዓይን የፀና መንግስት እንዳለ ለማሳየት ስለፈለገ እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ መውሰድ ነበረበት። በእርግጥ ማህበራዊ መረጋጋት ይታይባት በነበረችው ኢትዮጵያ በምስራቅ ግዛቷ የተከሰተ ችግር በፍጥነት መቅጨት የማይታለፍ የወቅቱ ጥያቄ ሆነ።

## ሐረር በደርግ ሥርዓት 1967-1983

ሐረሪዎች ምንም እንኳን ከማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ያልተቋረጠ ጦርነት በማካሄድ አንድ ጊዜ ሲሸነፉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያሸንፉ፣ አንድ ጊዜ ግዛታቸው ሲጠብ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሲሰፋ፣ አንድ ጊዜ ለማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግስት ሲገብሩ ሌላ ጊዜ ደግሞ አሻፈረኝ ሲሉ ቢቆዩም ቢያንስ በአጼ ምኒልክ የተገባላቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ሙሉ በሙሉ የተነጠቁት ደግሞ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት እንደሆነና ከዚያ ዘመን ጀምሮ ሐረሪዎች ወደ መላው አለም መሰደድ መጀመራቸውን ለመጠቆም ተሞክሯል።

ነገር ግን በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ሥልጣን አልተደመደመም። ደርግ ከ1967-1983 በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜየ ከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን ለሕዝብ ባደረገው አዋጅ በሐረርና በአካባቢዋ የተሠሩ የሐረሪዎች ቤቶችና የቦታ ይዞታዎችን በመውሰድ ከምኒልክ ጀምሮ ሲሸራረፍ የነበረው መብታቸውን የበለጠ ጉዳው።

መሬት ላራሹ የተሰኘው አዋጅም ቢሆን አንድም እርሻን አለበለዚያም ሌላ ሙያን የሚያስመርጥ፣ ይልቁንም ጭሰኛውን የመሬት ባለቤት የሚያደርግ ነበር፡፡ ወቅቱ የአብዮት ወቅት ስለነበረ ሐረሪዎች በገጠር ያለውን መሬታቸውን ወይም ሌላ ሙያቸውን በመምረጥ እንዲወስኑ አደረጋቸው፡፡ ከዚህም በላይ የቀይ ሽብር ዘመቻው በሱማሊያ መንግስት የግዛት መስፋፋትን ተመርኩዞ ስለተካሄደ በርካታ ሐረሪ ወጣቶች የጸረ-አብዮተኛነት፣ ጸረ-አንድነትና በሱማሊያ መንግስት ጋሻ ጃግሬነት ያለአንዳች በቂ መረጃ ተረሸኑ፡፡ በሕይወት የተረፉትም ከአገር እየጠፉ ሸሹ፡፡

ምንም እንኳን ሐረር ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንገስት ጀምሮ የማዕከላዊ መንግስት ወታደራዊ ማዕከል ሆና ብትቆይም በወታደራዊው አምባገነን መንግስት ደግሞ እስከ 2 መቶ ሺ የሚደርስ ሆነ፡፡

ከሱማሊያ መንግስት ጋር በተደረጋው የጦርነትና በአካባቢው በነበረው አምጽ ምክንያት በርካታ ሰዎች በስደት ወደ ሐረር መጉረፍ ጀመሩ፡፡ ከዚህ ላይ የከተማ ቤቶችንና ትርፍ ቦታን ለመንግስት ያደረገው አዋጅ በይበልጥ ሐረሪ ያልሆኑ ሰዎችን ተጠቃሚ ማድረጉ ሲጨመርበት ለብዙ ዘመናት ጠብቆ የኖረው ባህላዊ የሐረሪዎች አኗኗር በአጭር ጊዜ ውስጥ መልኩን አጣ፡፡

ምንም እንኳን የሐረሪዎች ታሪክ ለመቶ ዓመታት ያህል እያደር እየደበዘዘ ቢሄድም እራስን በራስ የማስተዳደርና በሸሪዓ ሕግ የመመራት ፍላጎታቸው ግን አልሞተም፡፡ በዚህ መሠረት በሀገር ውስጥ የነበሩም ሆኑ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሐረሪዎች ሁሉ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡ ሌላውን ሁሉ ትተን የጨለንቆውን ታሪክ እንዴት እንደሚያስታውሱት እንመልከት፡፡

በርካታ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ዛሬም በሕይወት ያሉ የሐገር ሽማግሌዎች እንደሚገልፁት በጨለንቆ ጦርነት 3ሺ ያህል ሐረሪዎች የተካፈሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 700 መቶ ያህሉ የሐረሪን ነፃነት ለመከላከል የተሳተፉ አዳዲስ ሙሽሮች ነበሩ፡፡

እነዚህ በአፍላ የጫጉላ ጊዜያቸው ላይ እያለ የተገደሉ ወጣት ሐረሪዎችን ለማስታወስ ይቻል ዘንድ ለእያንዳንዱ ሙሽራ የሠርጉ ቀን ቀላል ጋቢ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ፎጣው "ሳቲ በቅላ" ሰባት መቶ ማለት ነው፡፡ ሙሽራው ይህን ከወንድ አማቱ በስጦታ መልክ ሲቀበልም በጨለንቆ ጦርነት የወደቁ ሙሽሮች ከተማቸውን ከወራሪ ለመከላከል ሲሉ ሕይወታቸው እንዳለፈ አምኖ ነው፡፡ በፎጣው ላይ የሚደረገው ቀይ ጥለትም በጦርነቱ ወቅት የፈሰሰው የሐረሪዎች ደም ማሳያ ነው፡፡ ፎጣው ከሠርግ በኋላም በሌሎች በዓላት ትከሻ ላይ ጣል ተደርጐ ይለበሳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሐረሪዎች የጨለንቆውን ጦርነትና በዚያን ዕለት የፈሰሰውን ደም በየዕለቱ ለማስታወስ የመኖሪያ ቤት ወለላቸውን ቀይ አፈር ይነሰኑሱታል፡፡ ሁለቱም ቀይ ምልክቶች በእያንዳንዱ ሐረሪ ቤትና በእያንዳንዱ ሐረሪ ሠርግ መስተዋላቸውና የሚተሳሰሩበት ሰነድ የጋራ የሆነ ልምድና ታሪክ እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ሲሆን ይህም እንደ አፎቻ እድር፣ የጐሳ ጓደኝነት፣ ከመሳሰሉት ልምዶች ጋር ሲጨመር አንድነታቸውን አጠናክሮ አቆይቶታል፡፡

## ሐረር ከሽግግር መንግሥት /1983/ ወዲህ

የደርግ መንግስት ከ1967-1983 አምባገነናዊ ስርዓትን አስፍኖ የቆየ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢሕአዴግ/ ግንቦት 20 ቀን 1983 ያንን ስርዓት ገርስሶ የራሱን መንግስት አቋቋመ፡፡
ኢሕአዴግ ጊዜያዊ መንግሥቱን ከግንቦት 20 ቀን 1983 ጀምሮ ዓ.ም ማቋቋሙን ካወጀ በኋላ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰባስበው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስትን እንዲመሠረት ጥሪት አደረገ፡፡ በዚህ መሰረት ሃያ አራት የሚሆኑ የብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶች አዎንታዊ ምልላሽ በመስጠታቸው ከሰኔ 24 ቀን 1983 እስከ ሰኔ 28 ቀን 1983 ባለው ጊዜ ተሰብስበው የሽግግር መንግስቱን ቻርተር አወጡ፡፡ የሽግግር መንግስቱንም ምክር ቤት አቋቋሙ፡፡

እነዚህም የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ቻርተር ያፀደቁ ድርጅቶችም በአዋጅ ቁጥር 7/1984 በቁጥር 3.64 ሐረር ራሷን የቻለ ክልል ሆና እንድትቋቋም ወስነዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የተወካዮች ምክር ቤት ከጥቅምት 4 ቀን እስከ 6 ቀን 1984 ባካሄደው 18ኛው መደበኛ ስብሰባ ሐረርና አካባቢዋን አስመልክቶ ባካሄደው ውይይት የሐረር ከተማ በአደሬ /ሐረሪ/ ብሔረሰብ የተቆረቆረችና ወደ አንድ ሺ ዓመት ዕድሜ ያላት መሆኑ ተጠቁሞ በውስጧ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ጭምር ስለሆነች ጉዳዩን የኦሮሞ፣ የሱማሌ፣ የሁንደኔ ወረዳ የአገር ሽማግሌዎች እንዲመለከቱት ለምክር ቤቱ ሐሳብ ቀረበ፡፡ በዚህ መሠረት መስከረም 26 ቀን 1985 የኦሕዴድና የሐረሪ ሊግ ተወካዮች እንዲሁም በሁንደኔ ወረዳ ከሚገኙ 17 ቀበሌ ገበሬ ማህበራት የተውጣጡ አባላት በሚገኙበት ከፍተኛ ስብሰባ አደረጉ፡፡ በዚህ ስብሰባ ከፖለቲካ ድርጅቶች አባላት በተጨማሪ ከየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ አምስት በድምሩ 85 የኦሮሞና የሐረሪ ብሔረሰብ ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ታዛቢዎች በተገኙበት በስፋት ከተወያዩ በኋላ፣

**ሀ.** የሐረር ከተማ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ከተማና ገጠርን ያካተተች ግዛት መሆኗን በመገንዘብ፣

**ለ.** በገጠሩ ክፍል የሚገኙ ገበሬዎች የሐረርና የኦሮሞ ብሔረሰብ ጭምር መሆናቸውን በማጤን፣

**ሐ.** በከተማና በገጠሩ ሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት በኢኮኖሚ በባህል በታሪክ፤ በጋብቻም ጭምር የተጠናከረ መሆኑን በመገንዘብ፣

**መ.** ክልሉ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወት ረገድ ቢያንስ ራሱን የመቻል አቅም እንዲኖረው የሚያስፈልግ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ በማጤንና በማመን፣

**ሠ.** በሁንደኔ ወረዳ የሚገኙትን የሁለቱን ብሔረሰቦች ፍቃደኝነት ጠይቆ ካረጋገጠ በኋላ የሁንደኔ ወረዳ ክልል 13 እንዲሆን የውሳኔ ሐሳብ አቅርቧል፡፡ ይህም የውሳኔ ሃሳብ የካቲት 24 ቀን 1984 ዓ.ም በተካሄደው የምክር ቤቱ 36ኛ መደበኛ ስብሰባ ወቅት ውይይት ተደርጐበታል፡፡ ጥቅምት 26 ቀን የሐረሪ ብሔራዊ ክልል ስፋት 340 ኪሎ ሜትር ካሬ በሆነው ሁንዴኔ ወረዳ እንዲሆን ወስኗል፡፡

ሐረሪ ክልል እስከ ሽግግሩ መንግስት ማክተሚያ ድረስ ክልል 13 እየተባለች ስትጠራ የቆየች ቢሆንም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት እውን ባደረገው ሕገ-መንግስት ደግሞ ሐረሪ ክልል ተብላ ተሰይማለች፡፡

እዚህ ላይ መታወስ የሚገባው አንድ አብይ ጉዳይ ቢኖር ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ደርግ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግስታት የሐረሪን ሕዝብ እራሱን በራስ የማስተዳደር መብት አፍነው የኖሩ ሲሆን ኢሕአዴግ የረጅም ጊዜ ታሪካቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን ያጎናፀፋቸው መሆኑ ነው፡፡

ሆኖም በአብዛኛው ሐረሪ ብሔራዊ ሊግና፣ የሐረር ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ ብቸኛ ተወዳዳሪዎች ሆነው በመቅረብ የሐረሪዎችን ብሔራዊ ምክር ቤት አቋቁመዋል፡፡ ከሐረር ግንብ ውጭ ባለው በአጠቃላይ የሁንደኔ ወረዳ ደግሞ ሐረሪ ብሔራዊ ሊግ፣ የሐረር ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲና የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ተወዳድረው የሐረር ብሔራዊ ሊግና የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በማሸነፍ የክልሉን ሥልጣን እኩል መቀመጫ በመያዝ የሐረርን ክልል አስተዳደር ምክር ቤትን ሥልጣን ይዘዋል፡፡ ክልሉ የሐረሪ ብሔራዊ ክልል በመሆኑ ፕሬዝዳንትነቱን የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡
ይህ በመደረጉ ለመቶ ዓመታት እንዲዳፈን ሲደረግ የነበረው ብሔራዊ ስሜትና የማንነት ጥያቄ መልስ አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡

# ክፍል ሦስት ኢኮኖሚ

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.ኢኮኖሚ

### 3.1 ንግድ ሸቀጥና ቀረጥ

ሪቻርድ በርተን በፃፈው መሠረት ሐረር የንግድ ማዕከል እንደመሆኗ መጠን በዘይላ እንደሚኖሩት ነጋዴዎች የኦሮሞ ነጋዴዎችን ስልት በተሞላበት መንገድ እየበዘበዙ የሚኖሩ ቢሆንም አሚሩ ሚዛን እየላኩ እንዲገዙና እንዲሸጡ ይህንን ካላደረጉ ግን እንደሚቀጡ ሕግ ደንግጓል፡፡ ነጋዴዎች እህል ይዘው ወደ ከተማ በሚገቡበት ጊዜም እያንዳንዱ ስልቻ አንዳንድ ቁና ቀረጥ መጠየቅ የተለመደ ሲሆን ነጋዴዎች ከፋፍለው በመጫን አህዮቻቸውን ሳይጉዱ መንዳት ሲገባቸው ቀረጡን ለማስቀረት ሲሉ በትልቅ ስልቻ በመጫን አህዮቻቸውን እየደጋገፉ ያስገቡ ነበር፡፡ በግብርና የተሰማሩት ክፍሎችም ታክስ የሚከፍሉት የሚያገኙት ምርት አስር በመቶ ያህሉን ሲሆን ይህ ክፍያ የሚከናወነው በዓይነት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የመንግስት ድርሻ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በሐረር ውስጥ ከፍተኛ ንግድ ያንቀሳቅሳል የሚባለው ሰው ከውጭ የሚመጣው ዕቃ ዋጋ ሲታይ ከሃምሳ ፓውንድ የማይበልጥ ሲሆን ሃያ ፓውንድ ካፒታል ያለው ደግሞ እንደ ከበርቴ ይቆጠራል፡፡

ከሐረር ወደ ውጭ ከሚላኩት ውስጥ ባሪያ ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ቡና፤ ትንባሆ ወርሲ፤ ቶብ እና ከጥጥ የተሠራ ልብስ፣ በቅሎዎች፣ ማሽላ፤ ስንዴ፣ ቃራንጂ፣ የተባለና ነጋዴዎች ለስንቅነት የሚጠቀሙበት ደረቅ ስንቅና “ጊይ” ቅቤና ማር ሙጫ እና የስብ ሞራ ናቸው፡፡ ወደ ሐገር ውስጥ የሚገቡትም የአሜሪካ አንሶላ ከጥጥ የተሠሩ ልብሶች ቀለም ያላቸውና የሌላቸው ክሮች ሻሽ፣ ጉፍታ፣ሐር፣ነሐስ፣ የመዳብ ሰሃን፣ማንቆርቆሪያ፣ ቴምር፣ ሩዝ፣ የስኳር ግግር፣ ባሩድ፣ ወረቀት እና ሌሎችም የከተማ ሰዎች በጣም የሚፈልጓቸው ሸቀጦች ሁሉ ነበሩ፡፡

ሐረር እንዲህ አርጅታ እንኳን ቢሆን ከጃንገር፣ ከጉራጌ፣ ከኦሮሞ፣ ከኦሎና ከሌሎችም ክፍሎች የሚወጡትን ባሮች እንዲሸጡና እንዲለወጡ የምታስችል ከተማ ናት። አል ማርኪዚ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ ግን ሐዲያ ስልብ ባሮችን ወደ ምስራቅ እንደምትልክ ይጠቅሳል።

ከኦሮሞ ባሮች ውስጥ የአርሲዎቹ በቀጥታ በኦጋዴን በኩል በቀጥታ ወደ በርበራ ይላካል። ከሁሉም ባሮች ደግሞ ሐበሻ አማሮች በጣም ከፍተኛ ዋጋ ሲኖራቸው የሸዋው ነጋዴ የባሪያ ንግድ እንዲቀር ከተከለከለ ወዲህ እምብዛም ገበያው ላይ አይገኙም። ሐበሾች ባሮችን በሚመለከት ምሳሌያዊ አነጋገር ሲኖር ይህም "የጦርነት ጊዜ ጓደኛ ብትፈልግ ኑቢያዊ፣ ሐብታም ለመሆን ብትሻ ሐበሻ፣ አህያ ብትፈለግ ሰዋሂሊ ግዛ" ይባላል። አንድ የሐበሻ ባሪያ በአንድ አነስተኛ ጭነት የሚገዛ ሲሆን ችግሩ ግን አብዛኛዎቹ መንገድ ላይ ይሞታሉ። ያም ሆነ ይህ ባሮች በሐረር ከተማ ዋጋ ሴቶች ከ100-400 አሽራፍ ወንድ ወጣቶች ደግሞ 9-150 አሽራፍ ያወጣሉ። ከዚህ በታች የሚተመኑ ደግሞ ለቤት አገልግሎት ሽያጭ ከተከናወነ በኋላ ከባሮች ሁሉ በጣም ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው ተብለው የሚገመቱት እንደገኛ ከመካከላቸው ይመረጡና ወደ ምዕራብ ዓረቦች ወይም በስኬት ኢማም እንዲላኩ ይደረጋል። በምትካቸውም ሩዝና ቴምር ይመጣል። በተጠቀሰው መልኩ ሲታይ በዚች አገር ላይ እንዱስትሪ ይመጣል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው።

በሐረር ክርስቲያኖች ዘንድ የዝሆን ጥርስ የንጉሳዊውያን ቤተሰቦች ሞኖፖሊ ሲሆን አሚሩ እንደሌሎቹ የአፍሪካ መንግስታት ሁሉ አንድ ዓይነት ንግድ ያካሂዳል። የዝሆን ጥርሱ የሚገኘው ጨርጨር በሚባለው ስፍራ በተለይም በኤረር ጫካ ውስጥ ሲሆን እነዚህ ዝሆኖች ቀኑ ሞቃት ሲሆን ከሐረር እና ከሌሎች ሸለቆዎች በመሰባሰብ ለመጠለል ወደ ጫካው ይገባሉ። ኦሮሞዎች ዝሆኖቹን ያድኑ እና በአንድ አነስተኛ ልብስ ይለውጡታል። አሚሩ በወኪሉ አማካኝይነት ወደ በርበራ ይልከውና ይሸጠዋል። ከዝሆን ጥርስ በጣም ትንሿ "ሩባ እጅ" /ሩብ የዝሆን ጥርስ (የተሾለው) " ኑስ እጅ" /ግማሽ የዝሆን ጥርስ/ ይባላሉ። ጥሩ "እጅ" የሚባለው የዝሆን ጥርስ የሚባለው በፈረሱላ ከ32 እስከ 40 ዶላር ወይም 27 የዓረብ ፓውንድ ያወጣል።

## 3.1.1 ቡና፤ ትምባሆና ወርሲ

የሐረር ቡናም ቢሆን በአውሮፓ ገበያ የታወቀ ነው፡፡ የሐረር ቡና የሚባለው በሐረር ከተማ አካባቢ በሚገኘው የአትክልት ስፍራ በብዛት በምዕራብ በኩል በሚገኙት የኦሮሞ አካባቢዎች ሲሆን እጅግ በጣም ጥሩ የሆነው ቡና ደግሞ ከሐረር የሰባት ቀን መንገድ ጉዞ ሊደረስበት ከሚቻለውና በይፋት መንግድ ከሚገኘው ጨርጨር ነው፡፡ አሚሩ ይህን ጥሩ ገንዘብ የሚያስገኝ ጥሬ ዕቃ በሌሎች እጅ ገብቶ የበርበራን ገበያ እንዳያጥለቀልቀው በመስጋት ራሱ በጥንቃቄ ያካሂደዋል፡፡ “ሐሸራ” ወይም የቡና ተክል ባለቤቶችም ሆነ ብለው እንዳያጠፉት ይሰጋ ነበር፡፡ ሐረር በነበርኩበት ጊዜ አንድ ሃያ ሰባት ፓውንድ የሚያወጣ ስልቻ ሩብ ዶላር ሲሸጥ ይህንን ቡና በግመል ጭኖ እስከ በርበራ ለማድረስ 5 ፓውንድ ኪራይ ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም በመጨረሻ የሚገኘው ትርፍ ጉልበቱን ጨምሮ የሚታሰብ አይደለም፡፡

የሐረር ትንባሆ ደማቅ ያልሆነ ቢጫ ሲሆን ጥሩ መዓዛ አለው፡፡ ይህም ትምባሆ ከፐርሺያና ከሌሎች የትንባሆ ዓይነቶች ጋር ሲቀላቀል ጠቀሜታ እንዳለው ይነገራል፡፡ አሎ ወይም የምዕራብ ኦሮሞዎች የሚባሉት ዋናዎቹ የቡና አምራቾች ከ(holcus) ጋር ሲተክሉት ከአምስት ወራት በኃላ ይደርሳሉ፡፡ ይህም ትምባሆ ለሁለት ሳምንት ያህል ይቀላል፡፡ ከዚያም እንጨቱ ይወገድና በጆንያ እየተሞላ ወደ በርበራ ወደብ ይላካል፡፡ የሐረር ወንዶች ትንባሆውን ከማጨስ ይለቅ ማላመጥ ይመርጣሉ፡፡ ሴቶቹ ግን ቅጠሉን ሱረት ትንባሆ ይጠቀማሉ፡፡ ትንባሆ የሚገዛው እንደሌሎቹ የንግድ እቃዎች ሁሉ በዓይን ግምት ሲሆን በአንድ ዶላር ሰባ ፓውንድ ክብደት ያለውን ማግኘት ይቻላል፡፡

ወርሲ የሚባለው ተክል አንጻራዊ በሆነ መልኩ በከፍተኛ ደረጃ በሐረር ከተማ ዙሪያ ይበቅላል፡፡ አብዛኛው ወርሲ የሚገኘው ግን ከከተማዋ በስተምዕራብ በሚኖሩ ኦሮሞዎች ነው፡፡ ይህ ተክል ዝናብ በማይቆምበት ወራት አካባቢ ይዘራና በሁለት ወር ውስጥ ደርሶ ይሰበሰባል፡፡ ወርሲና ባሪያ በበርበራ እና በመስካት መካካል ዋነኛው መስኮት ንግድ ነው፡፡ ወርሲ በዓረብ አገሮች የሚፈለገው ጺማቸውንና ሽሚዛቸውን ለማቅለም ሲሆን ሴቶችም የፊት ቆዳቸውን ቢጫ እንዲሆንላቸው ይፈልጉታል፡፡ ለውበት ከሚሰጠው አገለግሎት በላይ ከብርድ ይከላከላል ይባላል፡፡

### 3.1.2 ልብስ

የሐረር ቡናና ሻሽ ለሸዋ ልብስ እኩል መሆናቸው የሚነገርላቸው ሲሆን በውበታቸውና በአገልግሎታቸው አንድ ጥሩ የተባለ በአውሮፓ የሚገኝ የልብስ ማምረቻ ማሽን ከሚያመርተው ያላነሰ ነው። የንፋስ ዳርቻዎች ተብለው በሚጠሩት አገሮች የሐረር ልብስ ለትልልቅ ባለሥልጣኖች በስጦታ መልክ ለማቅረብ የሚመረጥ እንደሆነ ይነገራል። የሐረር ቶቤ እጥፍ ርዝመት ሲኖረው ወርዱም ሁለት ክንድ ከ18-20 ያህል ይሆናል። መልኩም ወደ ብርቱካን ያደላ ቀይ ሲሆን ዋጋውም በሐረር ከተማ እንኳን ቢሆን ስምንት ዶላር ያወጣል። ቶቤ የሚሠራው በሐረር ተራሮች በብዛት ከሚበቅለው ጥጥ ሲሆን ይህ ጥጥ እንደ ሐር ለስላሳ፣ በክረምት ወራት ሙቀት የሚሰጥ ነው። ድሩ ከእንጨት በተሠራ ማድሪያ በሴትም በወንድም በዚሁ ጥጥ ይሠራል።

ከሐረር ወደ በርበራ ወደብ ገበያ በየዓመቱ የባሪያዎች፣ የበቆሎዎችና የግመሎች ቅፍለት ይሄዳል። የመጀመሪያው ቅፍለት ቶቤ ፣ ወርሲ፣ ሙጫ እና ሌሎችንም ሸቀጦች ይዞ በጥር ወር ይነሳል። ይኸው ባሪያዎችን፣ በቅሎዎችን እና ሌሎቹ ሸቀጦችንም ይዞ የሚጓዘው ቅፍለት አንደኛው ወር ከመጠናቀቁ በፊት በርበራ ይደርሳል። አንድ ቅፍለት በአጠቃላይ 3000 ያህል ሕይወት የሚንቀሳቀስ ሲሆን "ኢቦ" ወይም መሪ በሚባል የአሚሩ መኮንን ይመራል። ማንኛውም የአሚሩ ከሊፋ በጂብሪል አቡበከር ጉሳዎች እየቆመ ከአራት እስከ አምስት መቶ ዶላር ያህል ገንዘብ መክፈል የሚገደድበት ሁኔታ ይኖራል። በሐረር ግምብ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ የሰማሁት ምሳሌያዊ አነጋገርም "በርበራ ላይ ሆኖ የሚያዝ ሰው የሐረረን እንደራ በእጁ ያስገባል" የሚል ነበር። ሆኖም ቀረ ቅፍለቱ ሰርሶ ሌላ የውጭ አገር ሸቀጥ ይዞ ይመጣል። ይህ ሸቀጥ በጥጥ፣ በሐር፣ በፎጣ፣ በሱረትና ትንባሆ ነው።

## 3.1.3 የቤት ቁሳቁስና የቤት እንስሳት

የሐረር የቤት ቁሳቁስ ጥቂት የቆዳ ምንጣፎች፣ አልፎ አልፎ የፐርሺያ ምንጣፍ፣ ባርጩማ፣ የሱማሌ ትራስ፣ ስጋጃ፣ ከእንጨት የተሠራ ማንኪያ፣ ከጫፉ የመጥረቢያ ዓይነት ቅርጽ ያለው የገንፎ ወይም የሾርባ ማማሰያና ቢላዋ ናቸው። በሐረር ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ካላቸው የቤት ውስጥ እቃዎች ውስጥ ቅል ከፍተኛ አገልግሎት ሲኖረው ለትንባሆ ማጨሻ /እንደ ጋያ/ እንደ ስኒ፣ እንደ ፒፓ፣ እንደ ውሃ ማምጫ ሆኖ ያገልግላል። ከዚህ በተጨማሪ በደንብ ያልተለመጠና ቅርፁ እምብዛም ማምጫ ሆኖ ያገለግላል። ከዚህ በተጨማሪ በደንብ ያልተለመጠና ቅርፁ እምብዛም የማይስብ የሸክላ እንስራ ለውሃ መጠጫ አገልግሎት ይውላል።

ሪቻርድ በርተን ሐረር በነበረበት ዘመን ሌላ በአንድ ዶላር መቶ ሃያ ያህል ዶሮዎች፣ ካለበለዚያም ስድስት ያህል ጥሩ አውራ ዶሮዎች መግዛት ይቻላል። ይህም ሆነ የሐረር ነዋሪዎች የሱማሌ ዶሮዎችን እንደ ጥምብ አንሰሳ ስለሚቆጥሩት አይፈልጉትም ነበር።
የፍየል ስጋ ጥሩ ሲሆን ግንባረ ጥቁር የሆኑት የበርበራ በጐችም ከዝናብ ወራት በኋላ እዚህም ሆነ የትም ቦታ ጣፋጭ ናቸው። ከሁሉም ባላይ በሁሉም ዘንድ ተፈላጊነት ያለው ነው። አትክልት እንደ ጫካ ተክል ስርዓት በሌለውና ባልተስተካከለ ሁኔታ በዘፈቀደ የሚበቅል ሲሆን ወይኑ በጊዜ ሳይቀጠፍ የሚቀርብበት ሁኔታም አለ። ዘንባባ በጣም ረጅም እስኪሆን ድረስ ያድጋል። እንዲያፈራም በጥቅም እንዲውልም ሁኔታው አይመቻችለትም። ሰዎቹ ሎሚና የመሳሰሉትን ተክሎች እንዴት እንደሚገርዙና እየተቀመቀሙ እንደሚያዙ እንዲሁም ማዳበሪያ እንደሚታቀፉ አያውቁም። ከቅል በስተቀር የሌላው ተክል ጥቅም እምብዛም አይታወቅም ማለት ይቻላል። ከተራሮች በሚመጣው ሸንኮራ አገዳ ስኳር የሚሠራ ሲሆን ሐበሾች "መሬቷ ተሸታለች" ከሚሉት አባባል ጋር ይጣጣማል። በዚህ ምስራቃዊ የአፍሪካ አገር በርበሬ ዋነኛው ቅመም ነው።

## 3.2 የሀረር ነዋሪዎች ኑሮአቸው በእጅ ሥራ

ሐረር በአስራ ዘጠነኛ ክፍለ ዘመን፣ የንግድና የግብርና ልማት ማዕከል እንዲሁም በኢማሬት /ግዛት/ መዲና ነበረች ይሁንና በዚህ አጋጣሚ ሐረሪዎች በወቅቱ ይካሄድ እንደነበረው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና ስልተምርት እራሳቸው “ጌይ”፣ “ጌይ ፋጋይ”፣ እና “ጋፋ” በሦስት ከፍለው ይሰሩ ነበር።

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የሐረር ከተማ ነዋሪ ወደ 20ሺህ የሚጠጋ ሲሆን ሻቃ መሐመድ ሙኽታር እንደዘገቡት ግን ይህን ቁጥር ወደ 35ሺህ ከፍ ያደርገዋል። ከሙኽታር በኋላ 12 ዓመት ቆይተው የመጡት ጀርመናዊው ዶክተር ፊሊፕ ፖሊሽኪ የመንግስት ባለሥልጣኖች 42ሺ ያህል ይሆናል ተብሎ እንደሚገመት አስፍረዋል። ይህም በሳር ሪቻርድ በርተን መጽሐፍ በተለይም በቅጽ ሁለት በገጽ 16 ዘጋቢዎች መረጃ መሠረት በሐረር ውስጥ በነበሩት አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ሐረሪዎች (አደሬዎች) ነበሩ። እነዚህም በዓረቦችም ሆነ በአውሮፓውያን “ሐሪ” አማሮች “አደሬ” በራሳቸው በሐረሪዎች ደግሞ “ጌይ ኡሱእ” ተብለው የሚጠሩ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች ሲሆኑ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ኤትኖሎጂካል ሶሳይቲ ቡሌቲን በቁጥር 7 በገፅ 35 እንደጠቆመው ደግሞ የተቀሩት በጋብቻም ሆነ እንዲሁ ለረዢም ጊዜ አብረው የኖሩ ኦሮሞዎችና ሱማሌዎች ናቸው። ሙኽታርም ቢሆን በመቶዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎችና ሱማሌዎች ወደ ሐረር ከተማ ገበያ መጥተው ይውሉና ማታ ወደየቤታቸው ይመለሳሉ ሲል ይገልፃል። እነዚህ ብሔረሰቦች የሐረሪዎች ቋንቋና ባህል ያዋህዷቸው ይኖሩ ነበሩ። በአጠቃላይ የሐረር ከተማን የከበባት የአሚሮች ግዛት ግን ሙኽታር እንደገመተው ሁለት ሚሊዮን ያህል ኦሮሞዎች ይኖሩበት ነበር።

የከተማው ነዋሪዎች ዋንነኛነት በንግድ ኢኮኖሚ የተሰማሩ ሲሆኑ ከዚህም ጋር የግብርናና ሌሎችም ይህን ያህል ቦታ የማይሰጣቸው ሥራዎችን ያከናውኑ ነበር። ከነዚህም ሥራዎች መካከል ሽመና፣ የወርቅና የብር አንጥረኛነት፣ ቀጥቃጭነት፤ የስጋጃ ሥራ፣ ግንበኝነት፣ የመፅሀፍት ጥረዛ፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል። ሴቶቹም የሽማ ጡዋፍ፣ በሽክላና በቅርጫት በአለላ ሥራዎች ተሰማርተው ነበር። ይሁንና የብረታ ብረት ቀጥቃጭነትና የሽክላ ሥራ የሚሠሩት “ሳኒ” በሚባሉ በሕብረተሰቡ የተለየ መደብ ስፍራ በሚሰጣቸው ሰዎች ነበሩ።

እነዚህ ሰዎች መሬት ቆፍረው የብረት ማዕድን በማውጣት በእርሻና ለጦር መሳሪያ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ ያመርቱ ነበር፡፡ ይሁንና እነዚህ ሰዎች በሕዝቡ ዘንድ ይናቁ ስለነበር ሥራቸውም አየሞተ መጣ፡፡

ሙኽታር በ1876 እንደዘገባው በሐረር ውስጥ ምንም ዓይነት ኢንዱስትሪ አልነበሩም፡፡ ሕዝቡ የሚያስፈልጉትን የኢንዱስትሪ ምርቶች ያገኝ የነበረው ከዓረብ ሀገራት በማስመጣት ነው፡፡ ሙኽታር በዚሁ ዘገባው ከዓረብ አገር ይመጡ ከነበሩት ውስጥ ከሐድረሞት /የመን ይመጣ የነበረው ምንጣፍ /ስጋጃ/ እንደሆነ ፣ የምንጣፎቹ አገልግሎትም ለመስገጃ ብቻ እንደነበር ጠቅሷል፡፡ ይህም መረጃ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከሙያቸው ተለይተው የማይመደቡ ጥቂት ብረታ ብረት ቀጥቃጮች ነበሩ፡፡ ሙኽታር ስለነበረው የሸክላ ሥራ ዓይነት እምብዛም ትኩረት ያልሰጠው ቢሆንም በተለይም በሽመና ሥራዎች ላይ ግን ከፍተኛ አድናቆት ነበረው፡፡ እንዲያውም በሱዳን ይሠሩ ከነበሩት በሽመና ሥራዎች የላቁ እንደነበረ ይጠቅሳል፡፡ ሪቻርድ በርተንም የሐረሪዎች ሥራ" የፐርሺያው በጥንካሬውና በመልኩ ይበልጣቸው ካልሆነ በስተቀር በሌሎች የምሥራቅ አገሮች ከሚሠራቸው የተሻሉ መሆናቸው አድናቆቴን ሳልጠቅስ ለማለፍ አልወድም ሲል አስፍሯል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግብፆች ሐረርን ከያዙና ብዙ ነገሮች ከተለዋወጡ በኋላ ወደ ሐረር የመጡት ፊሊፕ ፖለሺኪ ደግሞ በመፅሐፉ ሕዝቡ በኢንዱስትሪው መስክ እንቅስቃሴ ያደርግ እንደነበር አስፍሯል፡፡ በዚህ መሠረት ሐረሪዎች የሚያመርቷቸው የሽመናና የአለላ ሥራዎች በምሥራቅ አፍሪካ በእጅጉ የታወቁ ናቸው፡፡ የእንጨት ሥራም ቢሆን በዳበረ መልኩ ይካሄድ ስለነበር የአካባቢው ኦሮሞዎች ከእንጨት የተሠሩ ገበቴዎችን ይገዙ ነበር፡፡ ሸክላዎቹ ግን በተሽከርካሪ ረዳትነት ሳይሆን በእጅ በመጠፍጠፍ ይሠሩ ነበር፡፡ የቢላዋ፣ የሹካና የማንኪያ እንዲሁም የብር ማንጠር ሥራ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን ሥራው ተንቆ ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ ሥራዎች የብዙዎቹ የከተማ ሰዎች ወደ ንግድ ሥራ ሲሰማሩ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ዓመታት በዘላቂነት ከሌሎች እጅግ በተሻለ ሁኔታ ጠቀሜታ የነበረው ሥራ ግብርናው ነበር፡፡
እርሻም ታላቅ ክብር ያለው ሥራ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ገበሬም ብዙውን ጊዜ በተንኮልና በሐሰት ያልተበከለ /ያልተመረዘ/ ከሁሉም የተሻለ ታማኝ እንደሆነ ይታሰብ ነበር፡፡

በነጋዴዎች ዘንድ ለምስክርነት የሚመረጠው ገበሬ ነው፡፡ እንደቀልድ የሚነገረው እንኳን ቢሆን ነጋዴ የሚጠራው /የሚፈልገው/ ገበሬው "ሰውየው" ወደቤቱ እስኪመለስ ነበር፡፡ /ሰው ቢታጣ እንደሚባለው መሆኑ ነው፡፡/

ብዙ ዘመናትን የተራመደው የሀረር የግብርና አጠቃቀሙ የውጭ ተመልካቾች የዘገቡትና በጎረቤት ህዝቦች ማስተማሪያ እንደነበሩ ተዘግቧል፡፡ ግብርናው በመሐለኛው ከተማ ጌይ ፈጋይ በመስኖ እርሻዎችና ከከተማው የውጪ ክልል "ጋፋ" ይታረስ እንደነበረ የታወቀ ሲሆን የመስኖ እርሻው መስኖ እና በክራ ተብሎ ይከፈል ነበር፡፡

## 3.3.1 መሐከለኛው የከተማ ዙሪያ

መካከለኛው ክልል ወይም "ጌይ ፈጋይ" የሚባለው ከከተማው የግንብ የአጥር ክልል ጥቂት ማይሎች ያህል ራቅ የሚለው አካባቢ የሚሸፍን ነው፡፡ ይህም ስፍራ በከተማ ነዋሪዎች የሚታረስ ሲሆን በአካባቢው ነዋሪዎችም "ጌይ ሐራሺ" ይባላል፡፡ ትርጉም የከተሜው የአትክልት ስፍራ ማለት ነው ፡፡ ይሁንና ይኸው የአትክልት ስፍራ በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው፤ የመጀመሪያው ክፍል ማለትም የግንቡን አጥር የከበበውን የአትክልት ስፍራ አልፎ ሲሆን ከሱም ቀጥሎ የአንድ ሰዓት ያህል መንገድ በመጓዝ የሚገኘው የእርሻ ቦታ "ጌይ ፈጋይ" ተብሎ ይጠራል፡፡

በርተን ስለ አትክልት ስፍራ ሲገልፅ ‹‹በሐረር ከተማ አቅራቢያ ባለው የአትክልት ስፍራ /በመንገዱ ሁለት ሁለት ጐን/ ያለው አፈር መልኩ ቀይ ሲሆን በዚህ የለማ የአትክልት ስፍራ ፕላንቲይን የተባለ ሙዝ የመሰለ ተክል፣ ሎሚ፣ ማናት ነበሩበት፡፡ በአትክልቱ መካከል የላም ቀንዶች ከእንጨት ላይ ተሰክተው ይታያሉ፡፡ በተጠቀሱም አትክልቶች መካከል የቡና ዛፎች አሉ፡፡ ወርሲና ጫትም ተስፋፍቷል ሲል ገልጾታል፡፡

የአትክልቱ ሥፍራ በአብዛኛው የሚመረትበት ነው፡፡ እንደ በርበሬ ለዘመናት በአካባቢው ሲመረቱ የነበሩ ሲሆኑ ሌሎቹም የሐረር በሮች ለውጭ አገር ሰዎች ክፍት ከሆኑ በኋላ ነው፡፡ ግብጽ ሐረርን ከያዘች በኋላ ስለነበሩት ፍራፍሬ ሙኽታር በጻፈው መጽሐፍ በዝርዝር የገለፀ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ምናልባት በ19ኛው ክፍለ ዘመን የለሙ እንደሙዝ ሌምንስ /ምናልባት በሐረር ቋንቋ ትርንጎ፣ ዝርያ ሊሆን ይችላል፡፡ ቆምጣጤ /ሳፈርጂን/ እና አስራ አራት ዓይነት የወይን ዓይነቶች እንደነበሩ ይጠቁማል፡፡ ከእዚህም ሌላ በአካባቢው የሚበቅል የሸንኮራ አገዳ ዓይነቶችና የትንባሆ ተክልም ይለማ ነበር፡፡ ሙኽታር እንዲሁም እንደ ሸምብራ፣ምሥር፣ ባቄላ፣ነጭ ሽንኩርትና ቀይ ሽንኩርት፤ ሰሊጥ፤ ዱባ ከግብፅ ዝርያ የሚያንስ ቢሆንም ጥጥ ያሉ ተክሎች ግብፆች ሐረርን ይዘው በነበረበት ጊዜ ይበቅሉ እንደነበረ ዘግቧል፡፡ ሪቻርድ በርተን ስለ ሐረሪዎች ምግብ ሲገልፅ “ከዱባ በስተቀር ሌላ ቅጠላ ቅጠል ምግብ አይታወቅም ነበር” ይህም ምንም እንኳን የሚበላው ዱባ ቢሆንም ሌሎች ቅጠላ ቅጠል ምግቦች ይበቅሉ እንደነበረ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ሙኽታር በአንድ የአትክልት ስፍራ ውስጥ ድንች በቅሎ የተመለከተ ቢሆንም ባለ አትክልቶቹ ሲመገቡ አለመመልከቱን መግለጹ ነው፡፡

የሆነው ሆኖ ሙኽታር በውቅቱ በመካከለኛው የከተማ ክልል ስለነበሩት ተክሎች ይተንትን እንጂ መረጃዎቹ የተሟሉ ናቸው ብሎ መውሰድም ያስቸግራል፡፡ እኔ እንደ ደረስኩበት “ሩማን” /ፓምግራኔት/ “ የበለስ ፍሬ” /ፌግ/ ወይም በሐረሪኛ “ጌይ ቲኒ”፣ ኩጩሊ፣ሑልበት ዱቄት ሲሆን የሚመርና ለሾርባ የሚያገለግል የፈረንጅ ሱፍ ዱባ ሺፉ ብዙን ጊዜ ለመድሐኒትነት የሚያገለግል ፍሬ ፣ ሁለት ዓይነት ቃሪያ፣ ሒና /አብዛኛውን ጊዜ ሙሽሪትና ሙሽራው እጃቸውንና እግራቸውን የሚቀቡት ቀይ ቀለም ያለው ተክል/ ጉመንና ሌሎችም የጓሮ አትክልቶች ይበቅሉ ነበር፡፡

ይሁንና ሁሉም ጸሐፊዎችና አስረጂዎች በሐረር ውስጥ ቡና እና ጫት /በተለይም “ካታ ኢዱሊስ” የሚል ሳይንሳዊ መጠሪያ ያለውና የሚያመረቅን ተክል/ ለብዙ መቶ ዓመታት ይተከል እንደነበር ያምናሉ፡፡ ይህም ስምምነት በሰፊው ይመረት የነበረውን ማሸላና ገብስ ያጠቃልላል፡፡ በሙኽታር ማስረጃ ዝርዝር ውስጥ እንደ ስንዴና አጃ የመሳሰሉት የጥራጥሬ ዓይነቶች ግብጾች ሐረርን ከመያዛቸው በፊት ከዳጉሳና ጤፍ ይመረቱ ነበር ፡፡

## 3.3.2 ወደ ሐረር የገቡ አትክልቶችና ማን እንዳስገባቸው

መስተዋል ያለበት ሌላ ጉዳይ ቢኖር፣ የውጭ ሀገር በተለይም ግብጾች፣ ሕንዶች፣ ቱርኮችግሪኮች በብዛት ወደ ሐረር ሲገቡ በአስራ ዘጠነኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻና በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ብዙ ዓይነት ተክሎች መግባታቸው ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ፖሊሽኪ /ሐረር ገፅ 238/ ሲገልጹ (ከሙኽታር መረጃ ጋር ባይጣጣምም) ግብጾች አዳዲስ የወይን ተክሎችን ለውዝን፣ ኮክን፣ ሎሚንና በአባይ ወንዝ ዳርቻ /ደለል/ ላይ የሚበቅሉ እንደ በቆሎ፣አገዳ ስኳር፣ ድንች፣ ዱባ፣ ቀይ ስር፣ "ትሬፎይል" ያሉ ተክሎች ይዘው እንደመጡ ዘግበዋል፡፡ በመካከለኛው ምስራቅ አትክልቶች ወደ ሐረር መግባት አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ተብሎ የሚነገርለትም ኸዋጃ ኢብራሂም የተባለውና ራሱም ትልቅ የአትክልት እርሻ የነበረው ግብፃዊ ነው፡፡ ከግብጻዊው አትክልተኛ በተጨማሪም "ማኖሌ" የተባለ ግሪካዊ እሾሁ የሚዋጋ ፒር በሐረሪዎች ቲኒ የሚባል ተክል በ20ኛው ክፍለ ዘመን አስገብቶ አንዱን ችግኝ በአንድ ዶላር /ማሪያትሬዛ/ እንደሸጠ፤ በዚህ ተክል ተፈላጊነት ለአጥር አገልግሎት እንዲውል ታስቦ ቢሆንም እሱ ግን ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ በመስፋፋቱ ምክንያት ለአትክልቱ ፀር እንደሆነ ተመዝግቧል፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ሐረር በአትክልት ልማት ዝናን ያተረፈች ብትሆንም ደግሞ በዚህ ረገድ የነበራት የንግድ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ነበር ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ለአንድ እራሱን አሳምሮ ለቻለ ቤተሰብ አትክልትና ፍራፍሬ መሸጥ ያልተለመደ ወይም እንደነውር የሚቆጠር ስለነበር የመሸጥ ነገር አይነሳም፡፡ የሚደረገው ተክሉ ሲያፈራ ለዘመድ፣ ለወዳጅ፣ ለጐረቤት የተቀረውን ለቤተሰብ እንዲቃመሱት መስጠት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ይኸው ባህል በተለይም የቤተሰብ ኩራት ባልለቀቃቸው ዘንድ እንደቀጠለ ነው፡፡

## 3.3.3 ቡና

በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ዋነኛውን ሚና ይጫወቱ የነበሩት ቡና እና ወርሲ በተለይም ቡናን በተመለከተ ሰር ሪቻርድ በርተን በመጽሐፋ በተለይም በቅፅ ሁለት ገጽ 26 እንደጠቀሰው የሐረር ቡና በአውሮፓውያኑ ዘንድ ተፈላጊነቱ የታወቀ ነው፡፡ ፖሊሽኪ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ የቡና ተክል በሐረር የአትክልት ስፍራ በይበልጥም በምዕራብ በኩል በሚኖሩት ቦታውን በትክክል ለመጠቀም ጨርጨር በሚኖሩ ኦሮሞዎች በከፍተኛ ብዛት ይመረት ነበር፡፡ ፖሊሽኪ ጨምሮ በ1888 በቀረበው ዘገባ ሐረር ከ200-300 ቶን ቡና ይመረቱ ነበር፡፡ ዋጋውን በሚመለከት በሪቻርድ በርተን በተገለፀው መሠረት "ሐረርን 1856 ስጐበኛት እያንዳንዱ ክብደት 27 ፓውንድ ያለው ከረጢት ቡና ዋጋው ሩብ ዶላር ነበር፡፡ በ12 ከረጢት በማሸከም የኪራይ ግመል እስከበር ነራ ድረስ የመጣ ቡና 5 ዶላር ነበር፡፡ይህም ሽያጩ የዋጋውንና በጉዞ ወቅት ሊከሰት የሚችለውን አደጋ የማይሸፍን መሆኑን ያመላክታል፡፡

ይህም ሆኖ ደግሞ ሙኽታር "የሀገሪቱ ዋነኛ ሐብት ቡና ነው" ሲል ጽፏል፡፡ እንደ ሙኽታር አገላለጽ በወቅቱ ሐረርን ትገዛ የነበረችው ግብጽ ፍላጐትን የሚፈነጥቅ ሲሆን የሐረር ገዥ የነበረው ራዑፍ ባሻም ይህ እጅግ ተፈላጊ ተክል እንዲስፋፋ ማበረታታት ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ እንዲመረትም ያስገድ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በወቅቱ የነበረው የቡና ልማት ስልትና ዝርዝር ጥናት በተከተለ የአሠራር ዘዴ ይከናወን እንደነበረ ይኸው የወቅቱ ጸሐፊ ተንትኗል፡፡

## 3.3.4 ወርሲ፤ ትምባሆና ጫት

ወርሲን በተመለከተ የሳይንስ ስሙ "Eriosema Esythocarpa" በከተማው አካባቢ ዝቅተኛ ባልሆነ ግምት ይመረት ነበር፡፡ ይህ ተክል ከባሮች ጋርም ሆኑ በርበራና በመስካት መካከል ባሉት ገበያዎች ይነገድ ነበር፡፡ የወርሲ ጥቅም በዓረቢያ ወንዶች ዘንድ ከጥጥ የተሠራ ሸሚዛቸውን ለማቅለም ሲሆን ሴቶችና ሕጻናት ደግሞ ቆዳቸውን ብሩህ ቢጫ ቀለም እንዲኖረው ያደርግ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከብርድ ለመከላከል እንደሚረዳ ይታወቃል፡፡ ይሁንና ይኸው ተክል በጦርነት ጊዜ ዋጋው የሚቀንስ ሲሆን ዋጋው አንድ ፖውንድ ከሩብ ዶላር የበለጠ አያወጣም ነበር፡፡ ይህም መረጃ ሙኽታር ወርሲ ኦሮሞዎች ወደ ሐረር የመጣ ነው ሲል የገለጸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

የሐረርን ትንባሆ በተመለከተ ግን በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያየ አመለካከት አለ፡፡ በዚህም መሠረት በሪቻርድ በርተን የሐረር ትንባሆ መልካም መአዛ ስላለው ከሶሪያና ከሌሎችም አገሮች ትንባሆ ጋር ለመቀላቀል ጥቅም እንደነበረው ሲገልፅ፤ በሙኽታር ደግሞ ዓይነቱ ደካማ እንደነበርና መሆን በሚገባው መንገድ እንደሚዘጋጅ ጠቁሟል፡፡ በዚህ ምክንያት ትንባሆ ያመጣው ተጨማሪ ጥቅም እንደሰፈረ እንገነዘባለን፡፡ በፖሊሽኪም ግብፆች የሐረርን ትንባሆ ዓይነት ለመለወጥ /ለማሻሻል/ ጥረት ቢደረግም የተፈለገውን ያህል ውጤት እንዳልተገኘ ተገንዝቧል፡፡

ጫትም በከፍተኛ ደረጃ የሚመረት ሲሆን ይህም ተክል አንድም እዚያው በዚያው ይቃማል፤ ካለበለዚያም ወደ ኤደን ይላካል ሪቻርድ በርተንም ስለዚሁ የጫት ንግድ ሲገልጽ በ280 ግመሎች ተጭኖ ወደ ኤደን ይላክ እንደነበር አንድ ግመልም እስከ አርባ ብር ቅርንጫፎች ያሏቸው ቀንበጦች በውስጣቸው የያዙ በርካታ ከረጢቶችን ይሸከም ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ከረጢትም ያለ ጫትም እንዳይደርቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጐ ይጠቀለል እንደነበር አውስቷል፡፡ በጫት ቃሚዎች ዘንድ ቀንበጥ ይሰጣሉ፡፡ ዋጋውም ለአንድ ከረጢት አንድ ከሩብ ሩፒ ያወጣ ነበር፡፡ ለመንግስት የሚለው ጫትም በዓመት እስከ 150 ሩፒ ያስገኝ ነበር፡፡

ከዚህ በተረፈ የሸንኮራ አገዳ ተክል የሚለማው ለማላመጥ ሲሆን የሙዝ ተክል በከተማ ውስጥ የሚተከል ከመሆኑም በላይ ፍሬው አልፎ አልፎ የሚያሰክር መጠጥ በምስጢር ለማዘጋጀት ያገለግል ነበር፡፡

## 3.3.5 የመስኖ እርሻና የውኃ አስተዳደር

ሐረሪዎች የአትክልት ስፍራቸውን በበጋ ወራት በመስኖ ሲያለሙ የነበረ ሲሆን ለዚህ አገልግሎት ያውሉት የነበረውን ውሃ የሚያገኙት የሐረር ሕዝቦች በመተባበር ካሠሩት “ኩሪ” የውሃ ማጠራቀሚያ ነው፡፡ ይህም “ኩሪ” እራሱ ሰፊና ጥልቀት የሌለው በ24 ሰዓት ውስጥ ሊሞላ የሚችል በሙሉ ኃይሉ ይሠራ ጥቅም ላይ ይዋል ቢባል/ በ12 ሰዓት ውስጥ ከአንድ እርሻ የበለጠ የማያጠጣ ነበር ውሃው የሚመጣው ከምንጭ የሚታጠረው በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች ማለትም እንደ ቃጫ፣ እንጨት፣ ቅጠላ ቅጠል፣ ሣርና አፈር ነው፡፡ ከዚያም የኩሬው አፍ በጠፍጣፋ ድንጋይ ይዘጋል፡፡ የመስኖ እርሻ የሚያለሙ ሰዎች ወደ እርሻቸው የሚያስገባ ቦታ ያዘጋጃሉ፡፡

የመስኖ ውሃ አገልግሎቱ ይተዳደር የነበረው “ሚይ መላቅ” በተባለ የውሃው ዘበኛ ወይም አከፋፋይ ሲሆን ይህ ሰው ራሱም ገበሬ የሆነ ከራሳቸው ከገበሬዎቹም የወጣ ሆኖ በአካባቢው ገበሬዎች የሚመረጥ ነበር፡፡

የመስኖ ውሃው አከፋፈልም በመጀመሪያ ከግድቡ አጠገብ ለሚገኙ እርሻዎች እንዲዳረስ ይደረጋል፡፡ እያለማ እስከ መጨረሻው እርሻ ይደርሳል፡፡ ይሁንና አልፎ አልፎ ከመጨረሻው ዝቅተኛ ቦታ የሚገኘው እርሻ በውሃ እጥረት ምክንያት ለድርቅ አደጋ ይጋለጥ ነበር፡፡
እንደዚህ ያለው ሁኔታ ሲከሰትም የውሃው አስተዳዳሪ /አከፋፋይ/ ከሁሉም የበለጠ ውሃ ለሚያስፈልጋቸው እርሻዎች እንዲዳረስ ያደርግ ነበር፡፡ በዚህ አገልግሎቱም በሳምንት አንድ ቀን በዕለተ ዓርብ እርሻውን ውሃ እንዲያጠጣ ይመረቅለታል፡፡ ይህ የምርቃት ውሃ “ጁምአ ሚይ” ማለት የዓርብ ውሃ ይባላል፡፡ ሆኖም በምርቃት የሚገኘውን ውሃ አስፈላጊ ከሆነ ለራሱ ካላስፈለገው ደግሞ ለሌላ ሰው በክፍያ ሊሸጠው ይችላል፡፡

ይህም ሆኖ አብዛኛው የአትክልት ስፍራ በመስኖ የሚለማ ቢሆንም ጥቂት ግን ውሃው የተፈለገውን ያህል ሁሉንም ባለማዳረሱ የማይቻል ይሆናል፡፡ በዚህም በመስኖ የሚለማው የእርሻ ስፍራ “መስኖ” ሲባል የማይለማው ደግሞ “ቡኽራ” ይባላል፡፡ የ”መስኖ” እርሻ ልዩ ልዩ የቅንጦት ፍራፍሬ ተክሎች ጫትና ቡናን ሲያመርቱ “ቡኽራ” እርሻዎች ደግሞ ጥራጥሬ እና ድርቅ ሊቋቋም የሚችል ጫት ይለማባቸዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ጥራጥሬ በ “ቡኽራ” እርሻዎች ብቻ ሳይሆን “ ጌይ ፊጋይ” በተባለው ክልልም እንደሚለማ ልብ ማለት ይገባል፡፡

## 3.3.6 የውጭ ክልል

ከመካከለኛው ክልል ቀጥሎ የሚገኘው የውጭው ክልል “ጋፉ” የሚባለው ሲሆን ይህም ክልል በጣም ሰፊ የእርሻ ቦታ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ተራርቀው የሚኖሩት አብዛኞቹ ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ የሳር ክዳን ያላቸው ጐጆዎች የሚገኙባቸው ገጠሮችም አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡ ኦሮሞዎች የሚኖሩት እርሻ በማረስና ከብት በማርባት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከብችን የሚጠብቁት ህፃናት ሲሆኑ ትልልቆቹ በእርሻ ውስጥ ይሠራሉ፡፡

በዚህ አካባቢ ሌሎች ሰብሎች ቢኖሩም እንኳን ማሽላ ወይም በሐረሪዎች “ኢኺይ” የሚባለው ሰብል ዋነኛው ምርት ነው፡፡ እንደ ዶክተር አምሰብረና ዶክተር ፊሊፕ ፖሊሽኪ የእርሻ ሥራ በተለይም ግብጾች ሐረርን ይዘው በነበር ተበትና ራኡፍ ፓሻ ገዥ በነበረበት ጊዜ የእርሻ ሥራው ተስፋፍቶ ነበር፡፡ በሰር ሪቻርድ በርተን 1856 ሐረርን በጐበኙበት ጊዜ የእርሻ መስፋፋቱ ሥራ በሰሜን ምዕራብ ሐረር እስከሚገኘው ጨርጨር ድረስ ይሸፍን እንደነበር መጥቀሳቸው ይታወቃል፡፡

በውጭ ክልሉ ከፍተኛ መሬት ታርሶ ሳይዘራበት ይቀር እንደነበረ የሚገልፀው መረጃም ገበሬዎቹ በተለምዶ የሚያርሱት ለመኖር የሚያስችላቸው ማለት በመንደራቸው አካባቢ የሚገኘውን መሬት ብቻ ሲሆን ትንሽ ሲተርፋቸው ከከተሜው ጋር እቃ ይለዋወጡበት እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.4 የመሬትና የእርሻ ቦታ የባለቤትነት መብት

በመሠረቱ መሬት በተለይም ከሐረር ግንብ ቀጥሎ በሚገኘው "ጌይ ፋጋይ" ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ማለትም የአትክልቱ ስፍራ፣ የከተሜው የግል መገልገያ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የመሬት አጠቃቀሙ እንደገጠር እርሻ ሳይሆን በጥንቃቄ የተከለለና በመጠኑ የተወሰነ ነው።

በመንግስት ህጋዊነትም የማይንቀሳቀስ ንብረት ማለት መሬትና ቦታ የግል ይዞታ መሆኑ ተቀባይነት ነበረው። ባለቤቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ዶክመንቶችና ባለቤትነቱን እንዴት ሊያገኘው እንደቻለ የሚያስረዳ መረጃ አለው። ይህም ማስረጃ በቃዲው ዳኛ ይረጋገጣል። ይኸው "ሑጃ" የሚባል ማስረጃ በዓረብኛ ቋንቋ የሚፃፍ ብቻ ሳይሆን ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ ቅፅም ነበረው። በቀላል አገላለፅም የመንግስት የምስክር ወረቀት ሲሆን አለበለዚያ የማረጋገጫ የባለቤትነት ህጋዊ መብት ሊኖረው አይችልም።

በዶክመንቱ ውስጥ የተካተቱ ማብራሪያዎች (መግለጫዎችም)፡-

ሀ. የባለቤቱ ስምና እንዴት ሊያገኘው እንደቻለ፤
ለ. የግል ሀብቱ ዓይነት ማለትም ቤት ወይም መሬት እንደሆነ የንብረቱ
ባህርይ ማለትም ምን ዓይነት ቤት ወይም መሬት እንደሆነ፣
ሐ. ንብረቱ የሚገኝበት ስፍራ፤
መ. የንብረቱ መጠን በጋሪብ ሲለካ፣ /የጋሪብ ክፍልፋይ "ሩብ"፣ "ሩብ"፣ "ሐበሕ" እና "ዳኒቅ" ይባላል።
ሠ. የንብረቱ ወሰን በሁሉም አቅጣጫ ሲታይ፣ የሚያዋስኑትም የታወቁ አጐራባች እርሻዎች ወይም ቤቶች ወይም ወንዝ ወይም የሕዝብ ጐዳና፤
ረ. የተሸጠ ወይም የተገዛ ከሆነም ውሉ ከዚህ ቀደም ተተምኖ ወይም ተገምቶ እንደሆነ፤
ሰ. በውሉ መጨረሻ ላይም የምስክሮች ስም ይጠቀሳል፤
ሸ. የቃዲው ማህተምና የምስክሮች ፊርማም ይደረግበታል፤

ይህም የሀረሪው የመሬት ባለቤትነት መብት አመልካች ሁኛ በበርካታ ሐረርን የጎበኘና በጊዜው አንፃር የህዝቡን እድገት ደረጃ አመላካች እንደነበር የተዘገበ ነው፡፡

### 3.4.1 ከሐረር ከተማ ውጭ ባለው ወረዳ መሬት

የሐረር የመጨረሻ ወረዳ "ጋፉ" ሲባል በዚህም አከባቢ ያለው በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ለፖለቲካዊ አስተዳደሩ እና ለማዕከላዊ መንግስቱ ሥልጣን ደህንነት ለማጠናከር ታስቦ የተዘጋጀ መሬት ይመስላል፡፡

በዚህ መሠረት አሚሩ መሬት የሚሰጡትም ሆነ የማይንቀሳቀሱ ንብረት ባለቤትነት የሚያረጋግጡት ለዘውዱ ታማኝ ለሆነ ወይም አንዳች ጠቃሚ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ነው፡፡ እንደዚህ ያለው መብት የሚረጋገጥላቸው እንደጕሳ መሪዎች የወታደርና የሃይማኖት መሪዎች ለሆኑት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው ለዘመዱና ለመንግስት ታማኝ በመሆኑ ምክንያት አዲስ የሥልጣን ኃላፊነት የሚሰጠው ከሆነና ቀድሞ መሬት ካልነበረው በተለይም ተሿሚው ሰው እንግዳ ለአገሩ ባዳ ከሆነ ከሥልጣን ጋር መሬት የመስጠቱ አስፈላጊነት አያጠያይቅም፡፡ ይሁንና በተለምዶው ሕግ መሠረት የሚሾመው ሰው ድሮውንም ሰፊ መሬት ለነበረውና በትውልድም ሆነ ወይም በጕሳው የአካባቢው የበላይ ሆኖ ከቆየ ነው፡፡ ስለሆነም አሚሩ ሥልጣኑን ያውቅለታል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ተጨማሪ መሬት ይሰጠዋል፡፡ በሐረሪዎች ዘንድ ሥልጣን በሦስት ደረጃዎች የተከፋፈለ ሲሆን የመጀመሪያው "መላቅ" ቀጥሎ ያለው "ገራድ" ሦስተኛው ደግሞ " ደሚን" ነው፡፡ "መላቅ" የሚባለው የሰፈር ሹም እንደማለት ሲሆን እያንዳንዱ ሰፈርም የራሱ የሆነ ሹም ነበረው፡፡ በዚህ መሠረት አሰዲን-በሪ መላቅ፣ አሱም-በሪ መላቅ፣ ወዘተ እየተባሉ ይታወቁ ነበር፡፡ "ገራድ" በመንደር ወይም የከፊል መንደር ሹም ማለት ሲሆን "ደሚን" ደግሞ የመላው ጕሳ መሪ ነበር፡፡ የሥልጣናቸው ደረጃ በቅርበት ሲታይም በርካታ "ገራድ" አምስት ስድስት ደሚን በሥሩ ይመራ ነበር፡፡ ገራድ ወይም ደሚን ቢሆኑም ግን እያንዳንዱ በደረጃው የአሚሩ የአስተዳደር ተወካይ በመሆኑ ፍትህ እንዲሰፍን፣ግብር እንዲሰበሰብና አስራት እንዲገባ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ የበላይ ደግሞ የውጭ ወረዳ ገዥ የሆነው "ዶጊን" የሚባል ሹም አለ፡፡

"ዶጊን" ኃላፊነቱ የአሚሩን ደህንነት መጠበቅ ሲሆን "የአሚር አይን ነው" ብሎ በአጭሩ መጥራት ይቻላል፡፡ አንድ ሰው "ዶጊኝ" ለመሆን ለአሚሩ ታማኝ መሆንም ሆነ የአካባቢው ባላባት መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ከሁሉም አስቀድሞ ሐረሪ መሆን ይኖርበታል፡፡

በተጠቀሰው መልክ ስልጣናቸው የተተነተነው ባለሥልጣኖችም መለክ 300 ቃሪብ ለገራድ 600 ቃሪብ ግምት ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ክብርና ማዕረግ ባለው ሁኔታ በሚዘጋጅ ስነ-ሥርዓት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አሚሩ ቶቤ /ብትን ጨርቅ/ በተሿሚው ራስ ላይ ይጠመጥማል፡፡ ገራድ ሲሾም የሚፈፀመው ሥነ-ሥርዓት "ገራድነት መጠለል" ሲባል የገራድነት ልብስ ማልበስ ነው፡፡ "ደሚንነት መጣለል" ማለት የዳሚንነት ልብስ ማልበስ /በአማርኛ የማዕረግ ቀሚስ ማልበስ ወይም ካባ ማልበስ ጋር ይመሳሰላል፡፡

በምላሹም አዲስ ባለሥልጣኖቹ ለአሚሩ የተወሰኑ ጥጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ ይህ ስጦታ መሬትን በማደላደል ተግባር በአሚሩ መልካም ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆን በታማኝነት ለመግለጽ ያህል ነው፡፡

ይህም ሆኖ ደግሞ ሹመት አብዛኛውን ጊዜ ወደ በኩር ልጅ የሚሸጋገር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ግን ላልሆኑ ሰዎች ይተላለፍ ነበር፡፡ እንግዲህ ያው ዕድል አብዛኛውን ጊዜ መሠረት ሹሙ ገራድነት ሆነ ደሚንነት ከገባሮች በሚገኘው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሥልጣኑ በደንብ ይጠቀምበታል፡፡

## 3.4.2 የመሬት ይዞታ አይናና ሐርታ

በ19ኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛው የከተማ ነዋሪ ገበሬ የነበረ ሲሆን ቀደም ሲል እንደተ ገለፀውም ግብርና የተከበረ ሙያ መሆኑ ይታመንበታል። ይልቁንም የአትክልት ስፍራውን የሚያለሙት የሚያርሱ፣ የሚቆፍሩ፣ የሚኮተኩቱና የሚንከባከቡ እራሳቸው ናቸው። ይሁንና አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እህል የሚዘራበት መሬታቸውን በኪራይ ሊዝ ይሰጡ ነበር። ገበሬዎችም የኪራዩን ዋጋ ከዓመት ምርታቸው ይከፍላሉ።

ከሊዝ በተጨማሪ የዓመት ምርት በሚገኝባቸው እርሻዎች ሁለት ዓይነት "አይና" እና "ሐርታ" የሚባሉ የኪራይ መንገዶች ነበሩ። "አይና" የሚባለው ስርዓት ከሐርታ ቀደም ሲልም ሲሠራበት ነበር። በዚህ ስርዓት መሠረት ከባለ ርስቱ መሬት በተለይ የለማውን ክፍል ጭሰኛው አርሶ ይዘራና የተወሰነውን ምርት ለባለርስቱ ይሰጣል። አይና በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በተሻሻለ መልኩ ሲሠራበት ይገኛል። ለምሳሌ አንድ ግለሰብ አምስት ተኩል "ሺባት" ያለው ሰፊ መሬት አላቸው እንበል። ከዚህም መሬት ውስጥ ከ4 ሺባት የሚገኘው ምርት ለራሱ ሲወስድ ለገበሬው ከአንድ ተኩል ሺባት ደግሞ ለባለርስቱ ይሰጥ ነበር። ይሁንና እንዲህ ያለው አሠራር ለረዥም ጊዜ በአንድ ገበሬ የቀጠለ እንደሆነ የባለቤትነት ጥያቄ ወይም መሬቱ የኔ ነው ስሜት ስለሚያሳድር ጭሰኞችን በየጊዜውና እንደ አስፈላጊነቱ አብዛኛውን ጊዜ በየአራት ዓመቱ ከእርሻ እርሻ መቀያየር አማራጭ የሌለው ሆኖ ነበር።

ሁለተኛው የሊዝ ዓይነት ማለትም "ሐርታ" በኦሮምኛ "ኢርታ" በሐረሪዎች ደግሞ "ገረባን ገረብ" የሚባለው ደግሞ እርሻ የሚገኘውን ምርት በመከፋፈል ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የበላይነቱ የማከራየት ስልት ከአይና አንፃር ሲታይ የተሻለ የሚሆነው ገበሬው ሁሉንም መሬት በኃላፊነት ስለሚይዘው የሚያገኘውን ምርት ከፍ ለማድረግ ሲል እርሻውን በደንብ ሊንከባከበውና ሊጠብቀው ስለሚችል ነው። ከዚህም በተጨማሪ መሬቱ ከዚህ ወዲህ፤ አንተ ከዚህ ወዲህ እኔ ተብሎ የሚሰጠው ባለመሆኑ ከዳበረውም ሆነ ካልዳበረው እንዲሁም መሬቱ ይዳብርም አይዳብርም ጥቅሙና ጉዳቱ በሁለቱም ዘንድ ተመሳሳይነት አለው።

የእርሻው ሥራ በተመለከተም የሚከናወነው በግለሰብ ደረጃ ነው፡፡ ሆኖም በአንዳንደ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ለምሳሌ ጉብታን መደልደል፣ በአጨዳና በውቂያ ጊዜ ገበሬዎች "ጉዝ" ብለው በሚጠሩት ደቦ በሕብረት ይሠራሉ፡፡ በዚህ ደቦ ሥራ ባለምርቱ ወይም በደቦ እንዲሠራለት የጠየቀው ሰው የምግብ፤ የመጠጥና የጫት ግብዣ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡

## 3.4.3 የማሽላ ምርት

ማሽላ በአካባቢው ሕብረተሰብ በተለይም በሐረሪዎች "ኢኺይ" በኦሮሞዎች ደግሞ "ቢሽንጋ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ማሽላ ትንሽ ድቡልቡል ሰብል ሲሆን በመላው ሐረር አካባቢ ይበቅላል፡፡ ማሽላ ብዙ ዓይነቶች ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ "ፈንዲሽ" እና "ሙግራ" የተባሉት የላቁ አይነቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ ዝርያዎች ነጭ እንጀራ መጋገረ ይቻላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጡት "ጫርጫሮ" እና ፍረ-ላሚ" የተባሉት ናቸው፡፡ ከሁሉም ዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው "ወገሬ" እና " ዳንጋ" ሲሆኑ ከነዚህ ዓይነቶች የሚጋገረው እንጀራ በቀለሙ ሳቢ ስላልሆነ እምብዛም ተፈላጊነት የሌለው ቡኒ መልክ ያለው ማሽላ ነው፡፡ እነዚህ የማሽላ ዝርያዎች በረዥምና አጭር ጊዜ የሚደርሱ ብሎ በዝሪያቸው አበቃቀል ጊዜ በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ በረዥም ጊዜ የሚደርሱት ፈንዲሽ "ሙግራ"፣ "ጫርጫሮ"፣ " ወገሬ" እና "ዳንጋ" ሲሆኑ በአጭር ጊዜ የሚደርሰው ደግሞ በአጠቃላይ "ሐጪር ሰኚ" ተብሎ የሚጠራው "ፍረ-ላሚ" ነው፡፡

የማሽላ መዝሪያ ወርም በመጋቢት 15 እና ሰኔ 14 መካከል ይሆናል፡፡ በሐረሪዎች ዘንድ አራት ወራቶች ሲኖሩ እነሱም መንዚል ይባላል፡፡ እነዚህን ወራቶች

"በይግ" ---- ከመጋቢት 15 እስከ ሰኔ 14
"ኪርሚ" ወይም "ጋና" ከሰኔ 15 እስከ መስከረም 14
ዚራት ---- ከመስከረም -15 እስከ ታህሳስ 14
ጋይ ---- ከታህሳስ 15 እስከ መጋት 14 ናቸው እያንዳንዱ "መንዚል" ደግሞ አስራ አራት ቀናት ካሉት ከጋብሐሕ በስተቀር እያንዳንዱ 13 ቀናት አሉት፡፡ ይህም ዓመቱ 362 ቀናት በሚሆነው ስርዓት ፀሐይ የተቀመረ ሲሆኑ በአራቱ "መንዚላክ" የሚጠቃለሉት ጊዜያትም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ባይግ | 2. ኪርሚ | 3. ዚራት | 4. ጋይ |
| ሙሽሽራ | ሐንአሕ | ዓውዋ | ናዓኢም |
| ባትን አልሑት | ዚራዓ | ሲማክ | ባልዳሕ |
| ዓሹርታይን | ናትሕረ | አልጋፍራ | ሕሳደ አድሐ ድሐ ቢሕ |
| አቡልታይን | ታሪፊ | ዙባናነ | ሳድ ቡላ |
| ኡትሕራያ | ጋብሐሕ | ኢክሊል | ሳድ አሳ አዳሕ |
| አዳብራሕ | ዙብራሕ | ካልባሕ | ሳድ አክቢያሕ |
| ሐክአሕ | ሳሪፊ | ሻውላሕ | መቀደም |

ከነዚህ ውስጥ ከባይግ ወር ውስጥ ሙአሽሽ እና ባትናልሑት የተባሉት አብዛኛውን ጊዜ ደረቆች ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ማሽላ የሚዘራው ዝናብ በሌለው ወር ሲሆን ስርዓቱም "ደቅ ሰኙ" ይባላል፡፡ በዚህም ጊዜ "ፈንዲሻ"፣ "ሙግራ" እና "ዳንጋ" የተባሉት የማሽላ ዓይነቶች ይዘሩና "በአሱር ታይን" የሚመጣው ዝናብ ይጠብቃሉ፡፡ በአሱርታይን እና አቡል ታይን አን አበጸል ታይንጋ የሚመጣው ከባድ የዝናብ ወቅት ካለፈ በኂላም "ጫርጫሮ የሚበለው የማሽላ ዓይነት ይዘራል፡፡ በማሽላ የአዘራር ስርዓት "ዑት ሕራያ እና "አዳብራሕ" የመጨረሻዎቹ ወቅቶች ሲሆኑ ለመድረስ ከሦስት ወራት የበለጠ ጊዜ የማይወስደው "ፍሬላ" የሚባለው ዝርያ ይዘራል፡፡

## 3.5.1 የእርሻና የመስራት እንቅስቃሴ

በመሠረቱ የማረስና የመዝራት ሒደት ዛሬ በተቀሩት የኢትዮጵያ ግዛቶች ከሚካሄደው የተለየ አይደለም። ስለዚህም ለዘር ይሆናል ተብሎ የተመረጠው እህል በግራ ወይም በቀኝ እጅ እየታፈሰ ባልታረሰው መሬት ላይ ይፈሳል። ከዚያም ቀንበር በተሸከሙና ሞፈር በሚጐትቱ ጥንድ በሬዎች ይታረሳል። ገበሬውም እርፉን ይዞ በሬዎቹ መስመራቸውን ወይም ትልማቸውን ተከትለው እንዲሄዱ ይቆጣጠራቸዋል።

የማረሱና የመዝራቱ ሥራ ከተከናወነ በኋላ የተፈጥሮ ሂደቱ ይቀጥልና ዝናቡ ሲጥል እርጥበት ያገኘው ዘር ሲበቅል ቡቃያው በደንብ እንዲያድግ የሚያስቸግረው አረም ይታረማል። መሬቱ ውሃ በደንብ እንዲገባው በመቆፈሪያ በሐረሪ "አካፋ" ተብሎ በሚጠራ መሳሪያ እንዲለሰልስ ይደረጋል። ይህ ሁሉ የሚደረገው የተሻለ ምርት ለማግኘት ነው።

ሃጋይ ካብ የተዘራው እህል ማሽላው ከሆነ አገዳ ይሆናል። ይኸው በሐረር "አላ" የሚባል አገዳውም ጫፍ ላይ እንደኳስ የተድቦለቦለ የማሽላ እሸት ያወጣል። ከማሽላ አገዳ አንዳንዱ የሚጣፍጥ ስለሆነ እንደ ሸንኮራ አገዳ ይታኘካል። የማሽላው እሸት /በሐረሪም "አሺታ" ይባላል። በተለይም በወጣቶች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ተወዳጅነት አለው። በመወደዱም ሳይጠበስም ሆነ እየተጠበሰ ይበላል። ይሁንና ማሽላ የሚመረተው ደርቆ ተወቅቶና ተሰብስቦ እንጀራ እንዲጋገርበት እንጂ በእሸቱ ለመብላት አይደለም። ማንኛውም የማሽላ እሸት መድረቅ ሲጀምር ቅጠሉ ከአገዳው እንዲወገድ ይደረጋል። ይህም ቅጠል የማስወገድ ተግባር "ዋባሕ" ተብሎ ይጠራል። ቀጥሎም ያለቅጠል ምርቱን ብቻ ተሸክሞ የቀረው አገዳ አራትና አምስት እየሆነ ይታሠራል። ይህም ተግባር "አጋዳ" ይባላል። የዝናብ ወራት በክረምት መገባደጃ ሲያቆም የእሸት ወቅት ያልቅና ሰብሉ ለመሰብሰብ ዝግጁ ይሆናል።

## 3.5.2 የአጨዳና የውቂያ ሁኔታ

በሐረር የአጨዳ ወቅት የሚጀመረው በ"ሳውላሕ" ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ማሽላውን የያዘው የአገዳው የመጨረሻ ክፍል ማጭድ በመሰለና በአካባቢው "መንጫ" ተብሎ የሚጠራ መሳሪያ ይቆረጣል፡፡ ይህ "ጉማ" ተብሎ የሚጠራው አካል ከተቆረጠም በኋላ በከብቶች እበት በተለቀለቀ ውድማ /በሐረሪዎች "ዑድ"/ ላይ ይከመራል፡፡ ጉበዝ ገበሬም በዚህ ወቅት የተለያየ ዓይነት ያለው የማሽላ ዝርያ በመልክ በመልኩ ይለይና እንደየቀለማቸው አንዱን በሌላው ላይ ይከምረዋል፡፡ ይህም በመሆኑ በአንድ በኩል ክምሩ የተለያየ ቀለም እንዲኖረውና መልኩንም ማራኪ ሲያደርገው በሌላ በኩል ደግሞ ዝርያውን ለይቶ ወደ ጐተራ ለማስገባት ይጠቅማል፡፡ ከዚያም ክምሩ እንደ አስፈላጊነቱ እየፈረሰ ከወደ ጭንቅላቱ ወፈር ባለ ዱላ መውቂያ እየተደበደበ ማሽላው ከቆረቆዳው እንዲለይ ይደረጋል፡፡ በድሮ ጊዜ በአውድማው ውቂያ ከሚከናወኑት ክስተት አንዱ እንደ እህሉ ብዛትና ማነስ ሁኔታ እየታየ አንድ ወይም ሁለት በሬ የሚታረድ መሆኑ ነው፡፡

በምግቡና በመጠጡ እራሳቸውን ያረኩት ገበሬዎችም ከውቂያው ጋር አብሮ የሚሄድ ዘፈን በመቀባበል ይዘፍናሉ፡፡ የአንዱን አውድማ /ዑድ/ ገበሬው የሚለይበት ጥብጣብ መሳይ /መቀነት መሳይ/ ነገርም ግምባራቸው ላይ ሸብ ያደርጉ ነበር፡፡

እህሉ ከተወቃ በኋላ ማበራየት ይጀመራል፡፡ የማበራየቱ ተግባር የሚከናወነውም በመጀመሪያ ቆረቆንዳው ከሰብሉ በእጅ እየተፈለፈለ ከወጣ በኋላ ነው፡፡ አካፋ የመሰለ ከእንጨት በሚሠራ /መንሽ/ እየተዛቀ ወደላይ ከፍ ይልና ቀስ ብሎ ወደ ታች እንዲፈስ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ንፋሱ ገለባውን ይዞት ስለሚሄድ የማሽላው ፍሬ በአንድ ላይ ይሰበሰባል፡፡ ምርቱ ከግንዱ ከተለየ በኋላ በስልቻ እየተሞላና በአህያ እየተጫነ ወደ ቤት ይገባል፡፡ ከምግብ ይተርፋል ተብሎ የሚገመተው በጐተራ ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

### 3.5.3 ጐተራ

ከሐርላ ህዝቦች የመጣው የጉድጓድ አቆፋፈር እውቅና የአካባቢው ህዝቦች ከሐርላ እንደሚባሉ ዩሱፍ አህመድ (1961) ይገልፃል።

የማሽላ ማስቀመጫ ጉተራ የሚሠራው መሬት ተቆፍሮ ሲሆን አሠራሩም በእጅጉ ልዩ ነው። አፈሩ በሐረር "ቢሊሌ" ጢረ ዳጪ" የሚባለውና ለዚህ አገልግሎት ተመራጭ የሚያደርገው የጉድጓድ ጉተራው በኃይለኛ ዝናብ በቀላሉ እንዳይናድ ነው። በተጨማሪም ውስጥ ለውስጥ የሚያልፍ ውሃ ሰርጐ እንዳይገባ በመከላከሉ ነው። ሦስተኛው አፈሩ እየተፈረፈረ ከእህሉ ጋር አይቀላቀልም። ሌላው "ቡኻን ቡኻን" ተብሎ የሚጠራው የአፈር ዓይነት ቀደም ሲል የተጠቀሰው አፈር ዓይነት የመሬት ውስጥ ጉተራዎች የሚቆፈሩት "ቢሊሌ ጢሪ ዳጪ" አፈር ባለው መሬት ላይ ነው።

ጉተራዎች በሐረር "ኢኺይ-ገዱ"፣ በዓረብኛ ደግሞ "ሑፍራት አታዐመ" የተለመደው ዓይነት ጎተራ የብርሌ ጠርሙስ ቅርጽ አለው። ይህም ጉተራ የሚሠራው በመጀመሪያ ከሁለት እስከ ሦስት ሜትር ስፋት ያለው መሬት ጥልቀቱ አፍ ማለትም ከአንገቱ እስከ አንድ ሜትር ተኩል አንገት መሳይ የጉተራው አፍ "አፉጋር" ማሽላው ወደ ጉድጓዱ ሲጨመርና ከጉተራ ሲያወጣ እንደመቆሚያ የሚያገለግል ነው። በተጨማሪ ከጠፍጣፋ ድንጋይ ወይም ከእንጨት የተሠራ መክደኛው እንዲዘጋበት ያገለግላል።

እንዲህ ያሉት በጣም ትልልቅና ባለአምድ ጉተራዎች አሠራራቸው እንደ አነስተኛው ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ቅርፅ ያለው የአፈር ቁልል ጉድጓዱ አፍ አጠገብ ተከምሮ መተው ነው። በተረፈ ጉድጓዶች ወደ ውስጥ የማያስገባ ደረጃም ከታች እስከ ላይ ይሰራላቸዋል። ከዚያም ማሽላው ከተጨመረ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ ከወይራ ዛፍ የተቆረጠ አጣና ይረበረብና ቀዳዳው በመጀመሪያ በቀጫጭን እንጨቶች ከዚያም በጭቃ ይመረጋል። በመጨረሻም አፈር ይከመርበትና ይደመደማል። ይህም ሽፋን እህሉ በሚወጣበት ጊዜ ይነሳል። እንደዚህ ያሉት ትልልቅ የጉድጓድ ጉተራዎች ይሠሩ የነበሩት በመንግስት ደረጃ ነው። ዛሬ የሐረር አደባባይ የተሠራበት "ፈረስ መጋላ" ነበር።

ሁለተኛው ስፍራም “በመስፍኑ በር ማለትም ከመስፍኑ ግንብ አካበቢ በሚገኘው ስፍራ ነው፡፡ ከዚህ በተረፈ አንዳንድ ጐተራዎች አልፎ አልፎም ቢሆን ከግንቡ ውጭ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ በሐረዌ ውስጥ አው ባሐር ላይ፣ በሲዳሞ ውስጥ ጐና በተባለው ስፍራ ዛሬ ሐረር ወህኒ ቤት ባለበት አካባቢ የ”ሶና” ጐተራ ይገኝ ነበር፡፡ የሶና ጐተራ የሚባለው በግብጽ ዘመነ መንግስት የተቆፈረ ሲሆን በዚህ ጐተራ የግብር እህል ይሰበሰብበት ነበር፡፡ ግብጾች ለቀው አሚር አብዱላሂ ስልጣን በያዙበት ወቅትም በዚህ ጐተራ የነበረው እህል ለዘጠኝ ዓመታት በግብጾች ለተገዛው ሕዝብ የሞራል ካሳ ይሆን ዘንድ በነፃ ታድሏል፡፡ ከዚያም ለምፅዋት የሚሆን እህል ይከማችባቸው ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ አንድም ጠፍተዋል አለበለዚያም አገልግሎት አይሰጥም፡፡

የግለሰቦች የጉድጓድ ጐተራዎች ግን በጣም አነስተኛ ሲሆኑ ከ50 እስከ 120 አውሳክ ማለትም ከ25-60 አህያ ጭነት የሚያህል እህል ብቻ የሚይዙ ናቸው፡፡ /”አውሳክ” የዓረብኛ ቃል ሲሆን መጠኑም ከሐረሪዎች “ጣን” ጋር እንደሚመጣጠን አንድ አውሳክም የሁለት አህያ ጭነት እንደሚሆን አህያም እስከ 50 ኪሎ ግራም እንደሚሸከም ግመል 12 ፈረሱላ ወይም 261 ፎቶሊ ማት 106 ኪሎ ግራም ያህል እንደሚጭን ሙኽታር አስሯል፡፡

## ከዓረብኛ ጽሑፍ የተገኘው በአጭሩ

## አላባ መሰብሰቡና ግብሩ

ከዓረብኛ ጽሑፍ እንደምንረዳው ገበሬዎች እህሉን ወደ አሚሩ ጉድጓድ ጐተራዎች ይዘው የሚመጡት በጥር ወር ማለትም በመኸር ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ነበር፡፡ ማዕከላዊ ግምቱ ሲታይ በአሚር አብዱልከሪም የነበረው ገቢ ከፍተኛው ሲሆን ይህም ከአቡበከር ወይም አህመድ የተሻለ የመሬት አጠቃቀም ስላለው ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ጥራጥሬዎቹ በግለሰብ የጉድጓድ ጐተራዎች እያንዳንዱ ሰው ምን ያህል እንዳስገባ በትክክል ተመዝግቧል፡፡ እነዚህም ሰዎች ከታወቁት የሐረሪ ቤተሰቦች አባላት የታወቀ ነው፡፡

የዓረብኛ ጽሑፍ ማስረጃ በየጊዜው የ"ዛካት" /የምጽዋት/ ጐተራ / ሑፍረት ዘካት/ ለምጽዋት የሚሆን እህል አሚሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም "ሙዓሸር" ብሎ የሚጠራውን ከሚያኘው ምርት ከአስር እጅ አንድ እጅ ያዋጣ ነበር፡፡ ሪቻርድ በርተንም " አምራቾች አስር ከመቶ የሚሆን ግብር በዓይነት ይከፍሉ ነበር፡፡ ይህም የመንግስት ገቢ በማይነካ መልኩ ያሳድገዋል ሲሉ በመጽሐፉ ምዕራፍ ሁለት በተለየም በገፅ 24 ላይ አስፍሯል፡፡ /ይሁንና ሌሎች ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት ግብሩ በዝሆን ጥርስ በከብት፣ በቡና፣ ወዘተም ይከፈል ነበር፡፡ በሁሉም መልክ ይከፈል የነበረውን ግብር መጠን ምፅዋቱን በሚሰበሰበው "ዘካ-ማሪ" ይወሰናል፡፡ ይህንንም ውሳኔ ለማስተላለፍ "ዘካ-መሪ" በፈረስ ይሆንና ምርቱ ወደ ሚወቃባቸው አውድማዎች አንድ በአንድ እየተዘዋወረ ይመለከትና አንዱ ገበሬ ምን ያህል መክፈል እንዳለበት ጥቂት እህል ከምጽዋት ውጭ ያደርግና የተቀረውን ይገምታል፡፡ ከዚያም የተገመተው ያህል ወደ መንግስት የጉድጓድ ጐተራ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ጉድጓዱም ከመታሸጉ በፊት የተወሰነ ይቀርና ከፊሉ ለተቸገሩ ሰዎች ተመጥኖ ይሰጥ የተቀረውም ለወታደሮች ራሽን፣ ለቃዲ፣ ለመምህራን፣ እንደ ዓረፋ ላይ የሕዝብ በዓት ግብዣ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ ግብ ዶክተር ፊሊፕስ ፖሊሽኪ በወቅቱ እንዳሰሉት አሚሩ በዓመት እስከ 60,000 አርደብ ምርት ይገባ ነበር፡፡

# ምዕራፍ አራት ንግድ

# ክፍል አራት

## 4.ንግድ

### 4.1 በአጠቃላይ የሀረር ንግድ

ለሐረር ንግድ ማዕከልነት ሁለት መሠረታዊ ምክንያች ጂኦግራፊያዊ /መልክአ ምድራዊ/ አቀማመጧና ፖለቲካዊ ጠቃሚነቷ ናቸው፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ የብዙ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የንግድ መተላለፊያ ወደ ማዕከልና ባህር ዳርቻ ለመግባትና ለመውጣትም ዋነኛ የመገናኛ መስመር ስለነበረች ነው፡፡ ሙኽታርም በመጽሐፉ ሐረር የንግድ ማዕከል በመሆን ስለነበራት ጠቀሜታ እይታውን አስፍሯል፡፡

በሁለቱ የንግድ ዘርፎች ማለትም በአስመጪነት በላኪነት የንግድ ዘርፍ ሐረር የነበራት ሚና ሲስተዋል ከላረቢያ የሚመጡ የኢስያ አገሮች ከሐረር ሲሄድላቸው ወደ አፍሪካ የሚላኩ በሐረር በኩል ያሳልፉ ነበር ለምሳሌ ሐረስ የተባለው ጸሐፊ በሐረርና ሸዋ መካከል ከፍተኛ የንግድ ልውውጥ ሲደረግ እንደነበር ጠቅሶ፤ ይህም የሆነው ሐረር ለቀይ ባሕር ቅርብ ስለነበረች እንደሆነ አብራርቷል፡፡ ሐሪስ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልፅ “በአቡበከርና በክርስቲያኑ ንጉስ መካከል መልካም የወዳጅነት ግንኙነት እንዲፈጠር አድርጓል” ሲል የዓሊዩ አምባዎቹ የሐረር ነጋዴዎችም የዚህ ሁኔታ ተጠቃሚዎች እንደነበሩ ሲጠቁሙም “ሰማያዊና ነጭ ነዶ /ጣቃ/ ጨርቅ ከሕንድ የሚገቡ ቁሳቁሶች፣ የእንግሊዝ የሕትመት ውጤቶች፣ ሐርና ሻማ፣ ቀይ የጥጥ ማግ፣ የሐር ክር፣ ዶቃ/ማርዳ/፣ ጭስ/እጣን/፣ የነሐስ ሽቦ እና ቆርቆሮ የመሳሰሉት ዕቃዎች በባሮች ይለወጡ ነበር፡፡”

ፖሊሽኪም “ንግድ የሐረሪዎች ዋነኛ ሥራ ነበር” ሲል ጠቅሰዋል፡፡ ሪቻርድ በርተንም እንደዚሁ “ሐረር በጣም ጠቃሚ የንግድ ከተማ ስትሆን ሕዝቧም እንደዘይላ ሕዝብ ይኖራል፡፡ አሚሩም የኦሮሞ ነጋዴዎች እንዳይታለሉ ከማስጠንቀቅም በላይ እየመዘኑና እየለኩ በማይሸጡ ነጋዴዎች ላይ ደግሞ ቅጣት ወስኖ ነበር፡፡

ሐረር በአገር ቤት ውስጥም ከኢፋት፣ አውሳ፣ አርሲና ባሌ ከባህር ዳርቻዎችም በቀጥታም ሆነ በዘዋዋሪ መንገድ ከታጁራ፣ዶንጋሪት፣ ራስ ቆሬ፣ ባንዳር-ዚያድ፣ ራስ-ሐፎን፣ አውቢያ፣ ብራዋ፣ ሞቃዲሾ፣ኪሲማዩ፣ እንዲያውም እስከ ዛንዚባር ድረስ ትገናኝ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ከቀይ ባህር ዳርቻ አገሮች፣ ከፋርስ ባህረ ሰላጤና እንደ ሕንድ ቦምቤይና ካራቺ ካ አገሮች ጋርም ግንኙነት ነበራት።

## 4.2 ወደ ውጭ የሚላኩ የንግድ እቃዎች

ሐረር ከእርሻ ምርቶች በተጨማሪ ወደ ውጭ ሀገር ሲሄዱ የሚገበያዩት ወይም ወደ አገር ቤት ሲገቡ የዝሆን ጥርስ፣ ዝባድ እና ባሪያ ለመግዛት የሚጠቀሙበትን ገንዘብ ለማግኘት የሚቻልባት ምቹነት በደምሳሳው እንደ ባንክ ቤት የገንዘብ ልውውጥ የሚካሄድባት ማዕከል ነበረች። በዚህ መሠረት ከከፋና ከአካበቢው ስፍራዎች የሚመጡ ባሮች ወደ ሸዋ ይመጡና በጥቂት ሜትሮች የሕንድ ጨርቃጨርቆች ወይም አንዳንድ ጊዜም "ጉርዱም" በሚባልና በኦሮሞ ሴቶች የአንገት ዶቃ ይለውጡ ነበር። የዝባድም እንደዚሁ ከሸዋ ይመጣና ወደ ወደብ ያልፋል። ሙኽታርም ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጽ በሐረር አካበቢ የሚኖሩ ኦሮሞዎች ጥራጥሬ፣ ምስር፣ ዱራ፣ ቅቤ፣ ማር፣ የመሳሰሉትን ሸቀጦች ለነጋዴዎች ያቀርቡና ከውጭ በሚመጡ ዕቃዎች ይለውጧቸው ነበር። ሱማሌዎችም ጨው፣ እጣን፣ /ሙጫ/ እና የሰጐን ላባ በማምጣት ተመሳሳይ የገበያ ልውውጥ ያካሂዱ ነበር።

ወደ ውጭ ከሚላኩት ውስጥ ቡና፣ ትንባሆ፣ የከብት፣ የአንበሳና የነብር ቆዳና ሌጦ ፣ የሰጐን ላባ፣ ወርሲ፣በሐገር ውስጥ የሚመረት ልብስ/ቶቤ እና ሻሽ በተለይ ሸዋ የሚመረቱ/ የጀሮ ሎቲ፣ የእጅ አምባር፣ ሰም ፣ ማር፣ ቅቤ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ስንዴ ካራንጂ /ለጉዞ የሚያገለግል ዳቦ/ እና ለሳሙናና ለሻማ መሥሪያ የሚያገለግል እንደሚገኝበት ሙኽታር በርተን እና ሐሪስ ገልፀውታል።

## 4.3 ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ

### እቃዎቹ መለዋወጫ ገንዘብና በሚመለከተው

ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡት የንግዱ እቃዎች በአሜሪካ በአውሮፓ ወይም በሕንድ ጨርቃ ጭርቆች፣ መዳብ ቆርቆሮ፣ እርሳስ፣ ዶቃ፣ የተለየየ ቀለም ያላቸው የሐር ክሮች፣ ጨው፣ ቴምር፣ ሩዝና ስኳር ይገኙባቸዋል፡፡ የተቀሩት ቁሳቁሶች ግን በአነስተኛ ደረጃ ቢሆንም እንደወረቀት የጥይት ባሩድ ጥይት ሰዓት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሪቻርድ በርተንም የሐረር ሴቶች ከምዕራብ ሕንድ የመጡ ከጉሽ ወይም ከሌላ ጥቁር ቀንድ የተሠሩ ስድስት ወይም ሰባት ሽዋሊያዎችን በእጃቸው ላይ ያደርጉና ከውጭ የሚመጡ እቃዎች በመሀለቅም ይሸጡ እንደነበረ ጠቁሟል፡፡ ይህም  በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ጥቂት የሣንቲም ስብስቦችም ከ18ኛው ክፍለ ዘመንም ጭራሹኑ ዋጋ ቢስ ሲሆኑ ዋጋቸው የመጨረሻውን ደረጃ የያዘውም በአሚር ሙሐመድ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሙኽታር ንግድ የሚካሄደው ለልውውጥ ሲሆን ሐረር ገንዘብ የላትም ያለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ይሁንና በርተን “ በሐረር ውስጥ ያለው በጣም ትንሽ ከነሐስ የሚሠራና መሐለቅ ተብለ የሚጠራ ሲሆን ይህም ገንዘብ በእጅ የሚሠራ ከመሆኑም በላይ እንደ ኢጣሊያ ገንዘብ ምንም ዓይነት ምልክት ያልተደረገበት ልውውጥ ሲሆን ይንቀሳቀሳል፡፡ ሲመነዘርም 22 መሀለቅ አነድ አሽራፊ፣ አርባው መሀለቅ ከአንድ የሐረር ገንዘብ ተመን 22 መሐለቅ 1 አሽራፊ 3 አሽራፊ  1 ሪያል ፣ ቀርሒ ነበር፡፡ በድሮ ጊዜም አንድ ሪያል ከወርቅ ይሠራ የነበረ ሲሆን በበርተን የጉዞ ዘመን ግን ዋጋው ቀነሰና ወደ አንድ ማሪያ ትሬዛ ደርሶ ነበር፡፡

በዚህ በሚመነዘር መሐለቅና በልውውጥ በሚካሄደው የገበያ ሂደት ከውጭ አገር ዕቃ የሚያመጡ ሰዎች ለሀገር ውስጥ ነጋዴዎች ይሸጣሉ፡፡ የአገር ውስጥ ነጋዴዎቹም ለሕዘቡ እንደየአቅሙ ይሸጡለታል፡፡ የገጠር ቸርቻሪዎችም ከከተማ ነጋዴዎች ተፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ይገዙና በጣም ሩቅ ወደሆነ ስፍራ በመውሰድ እንደማር፣ የሰጉን ላባና ቡና በመሳሰሉ ሸቀጦች ይለውጧቸው ነበር፡፡ እነዚህም እቃዎች ወደ ከተማ ተሰባስበው ይገቡና ለውጭ ገበያ ይቀርባሉ፡፡

## 4.4 በከፍተኛ ደረጃ የሚካሔድ የውጭ ንግድ እንቅስቃሴ

የውጭ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ የሚካሔደው አንድም በግል ካለዘለዚያም እንደሁኔታው በሕብረት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት የገንዘብ አቅም ያላቸው ነጋዴዎች አንድ የተሟላ ቅፍላት ማለትም እስከ 30 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግመሎች ወይም አህዮች የሚሠማሩበት የረዥም ርቀት ንግድ ጉዞ ያዘጋጃሉ ወደ ባህር ዳርቻ ይወሰዳሉ፡፡ ፓሊሽኪ በዓት ውስጥ ከ70 የበለጠ የቅፍለት ጉዞ አይደረግም፡፡ ሪቻረድ በርተን /ቅጽ 2 ገጽ 28/ በዓመት ሦስት ቅፍለት ወደ በርበራ ይጓዝ ነበር፡፡ ሐሪስም እንደዚሁ የዘይላና የበርበራ ወደቦች በዓመት ሦስት ጊዜ በትላልቅ ቅፍለቆች ይገኙበት እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ በወቅቱም “በርበራ የሚጓዝ የሐረር ሀብት በእጁ ነው እየተባለ ይነገር እንደነበርም በርተን ዘግቧል፡፡ ይህም ሆኖ አንድ ቅፍለት ለማዘጋጀት አቅም ያልነበራቸው ነጋዴዎች ሕብረት ይፈጥሩና ዋጋውን አውጥተው እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ፡፡ ይህንንም የማይችሉት ደግሞ ዕቃቸውን በመስጠት በርበራና ዘይላ ሄዶ እንዲሸጥላቸውና በሚገኘው ሽያጭና ሐረር መጥቶ የሚሸጥላቸ ዕቃ እነዲገዛላቸ ያደርጉ ነበር፡፡ለዚህም ውለታ ወደፊት በአንዳንደ መንገዶች ለመመለስ የውዴተ ግዴታ ነበረባቸው፡፡

## 4.5 በንግዱ የትራንስፖርት አገልግሎት

ሪቻረድ በርተን እስላም ነጋዴ መስሎ ወደ ሐረር ሲመጣ በርሃውን አቋርጦ ሲያልፍ ያለጠበቀው ሁኔታ እንዳጋጠመው በግልፅ አስፍሯል፡፡ በሱ መግለጫ መሠረት የዚያንጊዜው የንግድ ጉዞ እንዲህ የዋዛ አልነበረም፡፡ ይልቁንም 19ኛ ክፍለ ዘመን የሐረር ባለሥልጣኖች በሐረርና በቅርብ አካባቢዎቿ የተወሰኑ ስለነበሩ ረዥሙን የንግድ ጉዞ ለማቋረጥ በኦሮሞዎችና በሱማሌ ጎሳ መሪዎች ትብብር አቋርጦ ማለፍ ይጠየቅ ነበር፡፡ እንዲህ ባለው ያልሰለጠነ መንገድ የሚካሄደው የንግድ ሁኔታ የጨፈገገ ነው፡፡ /ያለስጋት የሚከናወን አይደለም፤መንገዱን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቋረጥ ቢቻል ኖሮ የንግዱ እንቅስቃሴ የተሻለ በሆነ ነበር ሲል ሪቻረድ በርተን ይገልጻል፡፡ ንግዱ የሚካሄድባቸው ሁለት መንገዶች እንደነበሩ የሚገልፀው ሙኽታርም አንዱ የሱማሌ ኢሳ እና ኖሌ ኦሮሞ ግዛት የሆነው ጀልዲሳ ሲሆን ሁለተኛውም ጋዳቡርሲን አቋርጦ የሚታለፈው ደርሚ ነበር ይለዋል፡፡/

በዚህም ጊዜ የትራንስፖርቱን አገልግሎት በሞኖፖሊ ይዘውት የነበሩት ሶማሌዎች ሲሆኑ የህንን ወቅታዊ ሁኔታ ይጠቀሙበት ለነበሩ ሱማሌዎች የተጋለጡት ሐረሪ ነጋዴዎች ከሐረር እስከ ወደብ ድረስ ያለው የትራንስፖርት ኪራይ ዋጋ ከፍ ቢል ይህን ያህል አያስደነቅም የዚህም ትራንስፖርት ዋጋ መውረድ በእቃው ላይ ተጽእኖ ማድረጉ አልቀረም፡፡ ሙኽታር በሚሰጠው የጨው ዋጋ ምሳሌ መሠረትም "ወደብ ላይ አንዳችም ዋጋ የማያወጣው ጨው 3.5 ኪሎ ግራም በሚይዝ ስልቻ /አንካሮ/ እስከ 20 ቢያስተሮች / የግብጽ ገንዘብ/ ያወጣ ነበር፡፡ እነዚህም ከውጭ ወደ ውስጥ የሚመጡት ሸቀጦች የሚጓጓዙት ኦሮሞዎች ኃላፊነትና ወኪልነት ነበር፡፡

ባለቅፍለቶቹም ቢሆኑ የተለያዩ ጐሳዎች አደጋ እንዳይደርስባቸው የሚጠብቁ የተለያዩ "አባን" የሚባሉ የጐሳ መሪዎች ነበሯቸው፡፡ አባንም እንደግመል በቅሎና አህያ የመሳሰሉትን አጋሰሶችና የቅፍለት መሪዎች ያዘጋጁላቸዋል፡፡ ነጋዴው ዕቃውን ለማጓጓዝ ሲፈልግም የሚነጋገረው ከአባን ጋር ነው፡፡ ዕቃው አንድ ጊዜ ለአባን ከተሰጠ በኋላም ወደተፈለገበት ስፍራ ለማድረስ ኃላፊነት የሚሰጠው ነው፡፡ ዕቃዎች የሚደረሱባቸው ስፍራዎችም እንደ በርበራ፣ ዘይላ፣ ወይም ታጁራ ያሉ ወደቦች ወይም እንደ ኢፋት፣አውሳ ወይም ባሌ ያሉ ያገር ውስጥ የንግድ መናሃሪያዎች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ አንድ የባለዕቃው ወኪል ዕቃውን መረከብ ይኖርበታል፡፡

ምንም እንኳን የዕቃው ባለቤት ወይም ወኪሉ ከቅፈለቱ ጋር መጓ እንብዛም ያልተለመደ ቢሆንም እንኳን አልፎ ግን በእያንዳንድ ምክንያቶች እንደ አው ሲድ ሐም፣ እና አው አብዱላሂ ኢድሪስ ያሉ ነጋዴዎች ወይም ወኪሎች እስከ ዘይላ እንድያውም እስከ ሕንድ ድረስ ይጓዙ እንደነበር ይታወቃል፡፡

ከድሮ የግል ነጋዴዎች መካከልም እስካሁን ድረስ ስማቸው እንደአዲስ ሲነሳ መስማትና እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሐረሪዎቹ ኢቡ ጋሚታይ እና ሱም ዓበዲ ዋንጋ እንዲሁም ሱማሌ መሐመድ ኪንቶ እስከ ዘይላ ይጓዙ ነበር፡፡ አው አሊ አብዱላሂ በተከታታይ ጂዳ ሔደዋል፡፡ ኒረ ሙሐመድ ሙራድ ኤል-ኩረድ እስከ ቦምቤይ ተጉዘዋል፡፡ ሌሎችም እንደ አው ዓሊ ዋሶ አውዳሬም እና አሕመድ አብዱላሂ ካሲር ያሉትም ዳግማዊ ምኒልክ በ1887 ሐረርን ሲይዙ እንኳን በንግድ ሥራቸው ቀጥለዋል፡፡

## 4.5 በንግድ እንቅስቃሴውና አሚሮች

አንዳንድ አስረጅዎች ነገሩን ባይቀበሉትም ብዙ አሚሮች በንግድ እንቅስቃሴው ተሰልፈው እንደነበር ሲገልፁ ሌሎች ደግሞ ከአሚር መሐመድ ቢን ዓሊ ብቻ ተሰልፎ እንደነበረ ያምናሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የሕዝቡ ፍቅር ስላልነበረው ሲሆን እሱም ቢሆን ኢቱዎችን /ኦሮሞዎችን/ የበለጠ ያቀርብ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ብዙ ሰዎች እንደሚሉት ሁሉ ሙኽታርም ይኸው አሚር ሕዝቡ ሩዝ እንዳይበላ ሸንኮራ አገዳ እንዳያኝክ ጥሩ ልበስ በተራ ሰዎች እንዳይለበስ ይከለክል እንደነበረ በማስታወሻው አስፍሯል፡፡ ይህም ድርጊቱ በብዙ ሐረሪዎች ልብ ጥላቻን ፈጠረ፡፡ በመጨረሻም በሰው እጅ ተገደለ፡፡ ያም ሆነ ይህ አሚሮች ለቤተሰቦቻቸውና ለመንግስታቸው አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ያስመጡ እንደነበረ ግን አይካድም፡፡ ለማንኛውም አሚሮች የራሳቸውን ዕቃዎች ብቻም ይሁን ነጋዴዎች እስካሁን የታወቀ ነገር የለም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ግብፅ ሐረርን ከመያዟ በፊት የነበሩት የመጨረሻዎቹ አሚሮች ነግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው እንደነበሩ የሚገልፅ ጠንካራ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ሪቻርድ በርተን ስለአሚር አሕመድ /ሲገልፅ ከአሚሩ ዋነኛ ሥራዎች አንዱ ሀብትን በንግድ ማግበስበስና ማካበት ሲሆን ከፍተኛ የብር የቡናና የዝሆን ጥርስ ዋነኛው የንጉሳዊያን ቤተሰቦች ሞኖፖሊ ነው፡፡ አሚሮችም እንደሌሎቹ አፍሪካ ንጉሦች አንድ ወገን ያለው ንግድ ያካሄዱ ነበር፡፡ ኦሮሞዎችም እንስሳቱን ያድኑና በመሸጥ ልብስ ይለውጡታል፡፡

አሚሮችም ይህንን የዝሆን ጥርስ ተቀብለው በወኪላቸው አማካኝነት ወደ በርበራ ልከው ይሸጡታል ሲል ሙክታር ሌሎች የንጉሳውያን ሞኖፖሊዎችን በመጨመር የሰጉን ላባ፣ ሽቶ መስሪያ የሚያገለግል ዝባድ እና ሽራ እንደሆነ በማስታወሻው ላይ አስፍሯል፡፡

ነገሩ በተጠቃለለ መልኩ ሲያዩት አሚሮች በንገድ ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር ቢባል ያልተለመደ ሊሆን አይችልም ነገር ግን ምን ያህል ንግድ ያካሄዱ ነበር የሚለው ግን እንደየ አንዳንዱ ዝንባሌና ፍልጐት የሚወሰን ነው፡፡ ምናልባትም እንዳንዶቹ ሌሎቹ አንዳደረጉት ፈፅሞ አልነገዱም ይሆናል፡፡ አዚህም ላይ ቀደም ሲል አንደተጠቀሰው ሁሉ አሚሮች በምጽዋት ስም ከፍተኛ ግብር ያስገቡ ነበር፡፡ ወደ ሐረር ከሚገቡ እቃዎችም ጭምር እንደዚሁ፡፡ ሪቻርድ በርተንም ከነጋዴዎች አህዮች በየቀኑ የሚቀረጠው እስከ አስራ አምስት የሽራ ከረጢት ይደርስ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት አንዲት አህያ የምትጫነው ከአቅሟ በላይ በመሆኑ በነጂዋ እየተደገፈች ታልፍ ነበር ሲል ገልፀዋል፡፡ ፖሊሽኪም አሚሩ በየዓመቱ 25000 ጁኔ ያህል ገቢ ከቀረጥ ይሰበስቡ እንደነበር ጠቅሷል፡፡ ይሁንና አሚሮች የንገድ ሥራቸውን የሚያካሄዱት በወኪሎቻቸው አማካይነት እንጂ እራሳቸው በመግዛት አልነበረም፡፡

በአሚር መሐመድ ቢን አሊ ዘመን ወኪሎች ሆነው በሱ ምትክ የነግዱን ሥራ ሲያካሂዱ ከነበሩት መካከል አብዱላሂ ኢድሪስ፣ አበዱራህማን ገዛሊ እና አሊ ሳዲቅ የሚባሉ ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ ሰዎች ተቆጣጣሪነት አማካይነትም የአሚሮቹ ዕቃ ሲሄድ የዒሳ ወይም የጋዳቡርሲ ጐሳ ለሆነ “አባን” ሊመለስም ለጋርሶ አባን ይሰጣል፡፡ የሁለቱም ጐሳዎች መሪዎች የዒሳው ሐቂ ቁለ እና የጋዳቡርሲው አው ቡሕ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ዛሬም ቢሆን የነዚህ ጐሳዎች ዝርዮች የታወቁ ናቸው፡፡

ይህም ሆኖ የዓረብኛው ጽሑፍ አሚሩ በንግዱ ሥራ ላይ መሳተፉን አይገለፅም፡፡ ነገር ገን ሁለት ስፍራዎች በአሚሩ ከውጭ አገር የመጡ እቃዎች እንደነበሩ ተጠቁሟል፡፡ እነዚህም ዕቃዎች የመጡት በበርበራ በኩል ሲሆን የተላኩትም በሐጅ ጋሚ ነው፡፡ ሐጂ ጋሚም ምናልባት የአሚሩ ወኪል ሊሆን ይችላል በሁለቱም ጊዜዎች የመጡት ጨርቃጨርቆች ሲሆኑ አሚሩ የበርበራን ወደብ ይመርጥ እንደነበርም የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ዳሩ ግን እነዚህ ዕቃዎች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ፤ ጥርጣሬው ከፍተኛ ቢሆንም እንኳን ለንግድ የገቡ ናቸው ድምዳሜ በእርግጠኛነት መናገር ያስቸግራል፡፡

## 4.6 በንግዱ ከሕንድ ጋር ይደረግ የነበረ ግንኙነት

በንግድ ይመጡ ስለነበሩ ዕቃዎች በተለይም ጨርቃጨርቆችን በተመለከተ በርካታ ዓይነት ጨርቃጨርቆች “አጥላስ”፣ “ሒጪ”፣ “ጉጋራቲ” የሚበሉና በተደጋጋሚ የሚመጡት ከሕንድ የመጡ ናቸው፡፡ ዛሬም እንኳን ቢሆን ሴቶች የሚለብሱት “አጥላስ” እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ምናልባት ከሕንድ በሚመጡ ጨርቆች ላይ “አትላስ” እየተባለ በሚጠራው የንገድ ምልክት ምክንያት ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል፡፡ ከቦምቤይ ለሚመጣው እንደዚሁ፡፡ በአጠቃላይም የሐረር ሴቶችና የሕነድ ሴቶች አለባበስ የሚመሳሰለውም ከዚሁ የረዥም ጊዜ የንገድ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ይመስላል፡፡

## ስለ ሐረሩ አሚር አብድሸኩር ቢን ዩሱፍ

## (1783-1794)

በአንድ ወቅት በምሥራቅ አፍሪካ ፖለቲካ የበላይነት ሰፍኖባትና የሁሉም እምብርት የነበረችው ሐረር ከአህሐድ ግራኝ በኋላ በካርድ እንደተሰራ ቤት ብተንትኗ ቢወጣም እንኳን እስካሁን ሕልውናዋን ጠብቃ የመገኘቷ ጉዳይ የክልሉ ምስጢር እንደሆነ ይኖራል፡፡ አንድያም ሆኖ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር እስከ ተቀላቀለችበት እስከ 1887 ድረስ የነግድና የትምህርት ማዕከል ሆና መቆየቷ የሚታወቅ ነው፡፡

ታሪክን ወደ ኃላ መለስ ብለን ሐረርን ስንመለከታትም በአህመድ ግራኝ ጦርነት ማግስት የኦሮሞ ድንገተኛ ወረራ ተከሰተ፡፡ከዚያም በተጨማሪ በወቅቱ የደረሰው ረሃብ እጅግ ከፍተኛ መከራ እንዲወድቅባት አደረገ፡፡በዚህም መከራ ህዝቧ ከፍተኛ ስቃይ ደረሰባት፡፡ይልቁንም እንደ ስም ነጌብ፤ደከር እና ሐረማያ ያሉት ከተሞችም በኦሮሞዎችና ምህረት በሌለው ረሃብ እንዳልነበሩ ነበር፡፡ በወቅቱ የነበሩ የአይን ምስክሮች እንደገለፁትም የረሃብ ቸነፈሩ ሰው እርስ በርሱ የሚበላላበት ዘመን ሆነ፡፡ ይህም ሆኖ ኑር ቢን ሙጃሒዲን የተባለውና በአህመድ ግራኝ በኋላ ሥልጣኑን የያዘው መሪ ከተማዋን ከደጋማው አካባቢ ከሚመጡ ክርስቲያኖችና ድንበራቸውን ዘለው ወረራ ከሚፈፅሙ ኦሮሞዎች ጥቃትለመከላከል ይቻል ዘንድ ዙሪያ ምላሹን ምሽግ ማዘጋጀት ጀመረ፡፡ ከዚያም ዛሬ ጁገል ተብሎ የሚጠራውን ሀረርን እንደቀለበት የከበበውን ግንብ አስገነባ፡፡

ይህም ሐረርን ከጥቃት ለመከላከል ሲባል የተገነባ አጠር 3,348 ሜትር ዙሪያ ጥምጥም ርዝመት ሲኖረው በግንቡም ውስጥ ከተማው ያረፈበት 48 ሄክታር መሬት አለ፡፡ በዚህም ግንብ አምስት የመግቢያና የመውጫ በሮች የነበሩ ሲሆን በሮቹ የንግድ መቆጣጠሪያዎች የሕብረተሰቡ ሰላምና ደህንነቱን የሚጠብቅባቸው ኬላዎች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የከተማው ባህል ሊያድግ የንግድ ሥራ ሊስፋፋና የሃይማኖት ማዕከል ልትሆን ትችላለች፡፡

ስለ ሐረር ከተማ ማደግና መስፋፋት እንዲሁም ስለ ኢኮኖሚው ሲወሳ በሐረር ውስጥ ከ1887 በፊት የፖለቲካ ሥልጣን የበላይነት እንደነበራትና በ1577 ግን በሙሐመድ ጃሳ አማካኝነት የፖለቲካ ሥልጣን ከሐረር ወደ አውሳዎች ሲተላፍ ለአንድ መቶ ዓመት ያህል በጨለማ ዘመን ያለፈች መሆኗን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም በ1647 ላይ በዓ ቢን ዳውድ ዘመነ መንግስት ነፃ የሆነ የሐረር ከተማ መንግስት እንደተመሠረተም አይዘነጋም፡፡ ይህም አዲስ መንግስት ከተመሠረተ በኋላ ሐረር አንፃራዊ በሆነ መልኩ የጸና አመራር ለመያዝና አስተዳደራዊ ማሻሻል ለማድረግ ጥረት አድርጋለች፡፡

በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ በነበሩት የከተማዋን አስተዳደር ለማሻሻል ታላላቅ መሪዎች አንዱ የነበሩት የአሚር አብዱሸኩር የሀረር ነዋሪ የነበረው የኢስሀቅ ኢፋቴ በተለይም ስለ እርሻ ቦታና የተለያዩ የመኖሪያ ቤት ግዢ ሁኔታን የሚተነትኑት የሂሳብ መዝገቦች የመረጃ ምንጭ ሆነው ከዚህም በተጨማሪያ ተያያዥነት ያላቸው ስነ-ፅሑፎች ትውፊቶችና የዘመኑ አፈታሪኮች ውስጥ ለማካተተት ጥረት ተደርጓ፡፡

## 5 . አሚር አብዱሽኩር በአጭሩ

### አብዱሽኩር የወረሰው ሥርዓት አሚር አህመድ

ከታሪክ እንደምንማረው አንድን ስርዓት ገርስሶ በምትኩ አዲስ ስርዓት ሲገነባ ውስብስብ ችግሮች ይገጥሙታል፡፡ በአንፃሩም ሥርዓቱ ተደላድሎለት ሥልጣን የሚወርስ መሪ ደግሞ በዚያው ለመቀጠል አመቺ ሁኔታ ይሆረዋል፡፡ በዚህም መሠረት አብሰዱልሻኩር ኦሮሞዎችን በጀግንነት ተዋግቶና ለተወሰነ ጊዜ አስታግሷቸው ከነበረው ከአሚር አሕመድ ቢን አቡበከር 1756-83 በኋላ ስልጣን መያዙ እድለኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አሚር አህመድ ቢን አቡበከር ታላቅ የጦር መሪ እንደነበር በ1117 ዓመተ ሒጅራ 1763-49 ዓ.ም የተጻፈውና በሐረር ጃሚዕ መስጊድ ሚንባር የሚገኘው ታሪክ ማህደር ይመሰክራል፡፡ በዚህ ማህደር "ለኻሊባ ለከ ያ አሕመዱ" ማለት አህመድ ሆይ አንተን ጦር ገጥሞ የሚያሸንፍ የለም ተብሎ አስፍሯል፡፡ ይህም የአሚሩን ታላቅነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዓይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡ በዚህ መሠረት አሚር አህመድ ያካሄደው የመከላከል ጦርነትና ያገኘው ድል አሚር አብዱልሽኩር እፎይታን አግኝቶ አስተዳደሩን እንዲያሻሽል ረድቷል፡፡
በማሻሻሉ ከተማዋን ወደ ብልጥግና ሊመራትና የራሱን ሐብት ለማከማቸት እንዲበቃ እድርጎታል ማለት ነው፡፡

ከዓሊ ቢን ዳውድ ጀምሮ ሲቆጠር አስራ አንደኛው የሆነው አብዱልሽኩር ከ1785-94 እንደገዛ የሚነገር ሲሆን ነገር ግን ቴዴሺ የአሚሮችን ቅደም ተከተል ዝርዝር አውጥቶ በተነተነው መሠረት ከጁን 1783 እስከ ኖቬምበር 18 ቀን 1794 እንደገዛ ያመላክታል፡፡ አባቱ አሚር ዩሱፍ ቢን አቡበከርም ከ(1747-56) የገዛ ሲሆን አሚር ሙሐመድ፣ አሚር አብድ አልዱሽኩርና ገራድ ዑመር የተባሉ ልጆች ነበሩት ሲል ቸሩሊ ይገልፃል፡፡ አብዱልሙሐይሚኒን ደግሞ ባልታተመው ጽሁፍ አሚር ዩሱፍ ቢን አቡበከር፤

1. ዓብደላህ ቢን አሚር ዩሱፍ ዓርብ ሌሊት በሸዋል ወር 8ኛ ቀን 1143 ዓ.ሒ

2. ዓብደላህ ቢን አሚር ዩሱፍ ማክሰኞ በጁማዱ አልታኒ 20ኛ 8 ቀን 1146 ዓ.ሒ

3. ፋጡማ ቢት አሚር ዩሱፍ በሸዋል ወር 1148 ዓ.ሒ

4. ዓብደልማሊክ ቢን አሚር ዩሱፍ ዓርብ ሌሊት በድሐ አልሐጅ ወር 1149 ዓ.ሒ

5. አሚና ቢት አሚር ዩሱፍ በድሃ አልሐጅ ወር 9ኛ ቀን 1151 ዓ.ሒ

6. አብዱልሸኩር ቢን ዩሱፍ በ1153 ዓ.ሒ የተወለዱ ልጆች እን ደነበሯቸው ገልጿል፡፡

2. ትልቁ ቁም ነገር ሁለቱም መረጃዎች የአብዱሽኩርን ስም መዝግበው መገኘታቸው ነው፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ በአብዱልሸኩር እንደታየው ሁሉ የእያንዳንዱን ትክክለኛው የተወለዱበትን ቀን ባያመለክትም በአብዛኛው አቅርቧል፡፡ ስለዚህም ከአሚር አሕመድ በኋላ በአጭር ጊዜ የገዛው አሚር መሐመድ ቢን ዩሱፍ የአሚር አብድልሸኩር ቀዳሚ መሪ ብቻ ሳይሆን ወንድሙ እንደነበረ እንገነዘባለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሚር ዩሱፍ ከአንድ በላይ ሚስቶች ስለነበሩት የልደት ቀኑ መዛባት የተከሰተው ከዚህ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

አብዱልሸኩር ታሪክ የበለጠ ቀረብ ብለን ስንመረምረው ዓጃዝ የሚባሉት የቁርዓን 30 ምዕራፎች ሕግጋግ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መታሰቢያ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም መሠረት በዚሁ አሚር የግል ቁርአን ሕዳግ ውስጥ እናታቸው ዓለዊያ ሰዒድ ኢብን ዓሊ እንደሚባሉ ተጠቅሷል፡፡ በአንዱ ምዕራፍ ሕዳግ ላይ ምንም እንኳን ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ ባይኖርበትም የልጃቸው የሳራ አሚር አብዱልሸኩር በሌላውም የፋጡማ አብዱልሸኩር ስም ሰፍሯል፡፡ የፋጡማ ኢር አብዱሽኩር ስም ግን 1253 ዓመተ ሒጅራ /ዓ.ሒ/ ለባለቤቷ ዘመድ የንብረት ስጦታ እንደሰጠችው ይጠቁማል፡፡ ያም ሆነ ይህ መሀመድ ሁሴን አብዱልሸኩር አሻ እና አሚና የሚባሉ ሁለት ልጆች እንደነበሩት ሲገልጽ ቁርአኑ ላይ አማሩ ስንት ልጆች እንደነበሯቸው በትክክል ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የልጆቻቸውና የእናታቸው መረጃዎች በቁርአን ውስጥም ሆነ ከሌሎች ምንጮች ለማወቅ ጥረት የተደረገ ሲሆን እንዴት ሥልጣን እንደያዙ ስንመረምርም ስለሕጋዊ ዙፋን አወራረስ ጉዳይ እጥርጣሬ ላይ የሚጥሉ አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ ይኸውም ከሥልጣናቸው በኃይል የተገለሉት አሚር አህመድ 23 ተከታታይ አመታትን ገዝተው ሳለ የሳቸው ተከታይ የሆኑት አሚር መሐመድ ቢን ዩሱፍ የተባሉት የአባታቸውን ልጅ ግን ከዲሴምበር 16ቀን 1782 እስከ ሜይ 1 ቀን 1783 ማለትም ለአምስት ወራት ብቻ መግዛታቸው ነው፡፡ በዘመናቸው ሥልጣን ለመንጠቅ አንዳቸው ሌላውን በልዩ ልዩ መንገዶች ለማጥፋት ጥረት ሲያደርጉ ስለነበርም አሚር መሐመድ የተፈጥሮ ሞት ነው የሞቱት ብሎ መደምደሙን ከጥርጣሬ ላይ ይጥላል፡፡ ለምሳሌ ያህል አሚር አህመድ ቢን ወዚር በ1640 የሞቱት በመርዝ መርዞ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለዛሬው የቤተመንግስት የሥልጣን ሽኩቻና ሴራ የሚነግረን ሪቻርድ በርተን መሐመድ ቢን ዩሱፍ የእስር ላይ እንዳሉ ሞተዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የአሚር ዩሱፍ ቤተሰቦች ማለትም አህመድና አብዱሽኩር ትዕግስት በማጣት አሚር አሕመድን ከሥልጣን አስወግደዋቸው ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት አሚር አሕመድን ከሥልጣን ካስወገዱና አሚር መሐመድን ለአምስት ወራት በሥልጣን እንዲቆዩ ካደረጉ በኋላ በተራቸው ደግሞ አሚር አብዱሽኩር የአባታቸውን ልጅ ፈንግለው በመጣል ስልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጠዋል ማለት ይቻላል፡፡

ወደ ሥልጣን የመጡበትን ሁኔታና ስለቤተሰቦቻቸው ይህን ያህል ካልን በ1153 ዓ.ሒ. መወለዳቸውን በ1209 ዓ.ሒ. ማረፋቸውን ከተቀበልን 56 የጨረቃ ዓመታት ኖረዋል ማለት ነው፡፡ ከነዚህ ዓመታት ውስጥም ገዥ በመሆን 12 ዓመታት አሳልፈዋል፡፡

## 5.2 የአሚሩ አስተዋፅኦ

**አብዱሸኩር ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው**

ሀ. አሕመድ ሻሚ የተባለው ጸሐፊ እንደገለጸው አሚር አብዱልሸኩር ሐረር ከነበሯት ጥቂት ታላላቅ መሪዎች አንዱ ነበር። በተለይም "ጃድዋል አል-ሻሽ በተሰኘው ጽሁፍ ስለአሚሩ ረዘም ያለ ማስታወሻ አስፍሯል።

ለ. ዋግነርም ከአሚር አብዱሸኩር ትልቅ አስተዋጽኦ አንዱ "ሲጂል" /ማህደር/ እና ዲዋን /የሕዝብ ሐብትና ንብረት መዝገብ/ መያዙ ነው። እንዲህ ያሉት እስላማዊ ባህሪ ያላቸው የሕግ ሳይንስ አሠራሮች ከአሚር ኑር /1551-69 ዓ.ም/ በኋላ ሥልጣን ከያዘው ከዑትማን አልሐበሻ ጀምሮ ተረስተው ነበር።

ሐ. በአሚር አብድሽኩር ተግባራዊ የሆነውም በወቅቱ በቀይ ባህር አካባቢ ጐልቶ ይታይ በነበረው ፈጣን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል።

በዚህ መሠረት የሱ ተከታዮች ከዘመኑ ብዙ ያተረፉ ከመሆናቸው በላይ መረጃዎቹን ስለተውልን ባለውለታችን ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የአስራ ዘጠነኛዋ ሐረር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ምን ይመስል እንደነበረ ለሚያጠናቅር እንደ ማዕድን የሚቆጠሩ መረጃዎች ከመገኘታቸው በፊት

መ. የሐረር ታሪክ የጻፈው ፕሮፌሰር ሪቻረድ ኮክም ለታሪክ የሚረዱ የጽሑፍ መረጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ ማግኘት እንደማይቻል ጠቅሶ እንደነበር ይታወሳል። የፕሮፌሰር ሪቻርድ ኮክ ወዳጅ የሆነው ሠ. ቮልከን ስቲትዝ ስለመረጃዎቹ ሁኔታ አጠቃሎ ለመግለፅ ሲሞክር ስለኢትዮጵያ የሚያጠኑ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት በሚጽፏቸው ልዩ ልዩ ጉዳዮች የአንባቢዎችን ጥማት ለማርካት ይሞክራሉ።

አሁን በተገኙት መረጃዎች መሠረት ግን አብድሽኩር ዩሱፍ ወንድማማቶች አንዱ በሆኑትና ዛሬ በደቡብ ኢትዮጵያ ዝናቸው ገኖ በሚነገርላቸው ባሻ ሁሴን አማካኝነት "ቀድሪያ ጣሪቃ" እንዲስፋፋ አመች ሁኔታን እንዲፈጠሩ ይታወቃል።

ሸ. የባሌው ሼኽ ሁሴን አድባር ባለቤት ስፍራ መስጊድ እንዲሠራ አድርገዋል፡፡ የመስጊዱ በባሌ መሰራት የአሚሩን ባለፀጋነትና በወቅቱ በባሌው ሼኽ ሁሴንና በሐረር መካል ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችል በቂ ሰላም እንደነበር ያመለክታል፡፡ አሚር አብዱሽኩር የባሌ መስጊድ ብቻ በማሰራት አልተወሰነም "ሳር አምባንና አልዩ አምባ" የተባሉትን የሰሜን ሸዋ ግዛቱ ጋር ቀላቅሎ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ስለ አብዱልሽኩር ከሚያወሱት አፈ-ታሪኮችና ትውፊቶች በዛ ይገልፃሉና የጽሁፍ መረጃዎች ውስጥም አንዱ አንዲት እናት ልጇ ከአቅሟ በላይ እንድታቀርብላት ሲጠይቃት "እራስህን አሚር አብድልሽኩር አድርገህ መቁጠርህ ነው? /ሩህኻ አሚር አብድልሽኩርሪን መሰልተኽ/ ማለቷ ይገኝበታል፡፡ ይህም ፍላጐቱን የማያረካ ባለጸጋ አሚር አብዱልሽኩር ብቻ ተደርጐ ይወሰድ እንደነበር ያመላክታል፡፡ ከዚህ ጋር የሚመሳሰለውና የሚገናኘው የታወቀው የህፃናት መዝሙር የሚከተለውን ነው፡፡

| **በሀረሪው** | **በአማርኛ** |
|---|---|
| አን አሚሪንተኝ | (እኔ አሚር ነኝ) |
| አን አሚር አብዱልሽኩሪተኝ | ( እኔ አሚር አብዱልሽኩር ነኝ) |
| ዚኻሽኾ አሺዛኪንተኝ | ( የፈለግኩትን የማደርግነኝ) |

## 5.3 አሚር አብድልሸኩር የሒሳብ መዝገብ አያያዝ መገበያያዎች ገንዘብ

ከሁሉም አስቀድመን ስል ሂሳብ መዝገቡ አንዳንድ መግለጫዎችን ብንሰጥ ጥሩ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሂሳብ መዝገቡ 34 ገፆች ሲኖሩት በ34 ገጾች ላይም 64 ጉዳዮች ሰፍረውበታል፡፡ መዝገቡ የተጠራውም ጠብቆ ባልተሰፋ ክር ነው፡፡ የወረቀቱ ዓይነት የጥንት ሲሆን "ካራሳ" የሚባለውን ይመስላል፡፡ ይኸው መዝገብ ቀደም ብለው ከተፃፉት አንዱ ሲሆን ከዳር እስከዳር ባይሞላም እንኳን አሚሩ የገዛውን የእርሻ ቦታና የከተማ ቤት ዝርዝር ያካትታል፡፡ በመሠረቱ በሐረር ከተማ የነበረው የመሬት ይዞታ የደጋማው የሰሜኑ ኢትዮጵያ መሬት አያያዝ ጋር በፍጹም እንደሚለይ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሐረሩ የመሬት ይዞታ ስርዓት የእስልምናውን የግል ይዞታ ስርዓት የተከተለ ሲሆን ይህም "ሑጃ" በመባል ይታወቃል፡፡ የሰሜን ኢትዮጵያ ግን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ያለው ውስብስብ ስርዓት ነው፡፡

መዝገቡን ገለጥ አድርገን ስንመለከተው በሁሉም አርእስተ ጉዳዮች አምስት ነገሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ሰፍረው እናገኛለን፡፡ እነርሱም፣

1. የአላህ ቡራኬ /አንዳንዱም አሚሩን የሚያመሰግኑ/
2. የተገዛው ንብረት የእርሻ ቦታ፣ የድንጋይ ቤት ወይም ጎጆ፣
3. የክፍያው መጠን በገንዘብ ወይም በገንዘብና በዓይነት ምስክር፣
4. የተገዛበት ቀን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ስለ ግዢና ሽያጭ ሲወሳ የገዢና ሻጩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም መነሳቱ አይቀርም፡፡ ይልቁንም በወቅቱ ምን ይሸጥና ይለውጥ እንደነበረ ሲታወቅ የአሚሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ምንነትም የጐላ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህም መሠረት ሐረር ከጥንታዊ ባህላዊ ታሪኳ ጋር ጥሩ የመሬት አያያዝና የውሃ አጠቃቀም ስለነበራትም የራሷን ፍጆታ ችላ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በቅታ ነበር፡፡ በወቅቱ ለትርፍ ይሸጡ ከነበሩት ምርቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹም ቡና፣ "ወርሲ" እና "ጫት" እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ የቤት ግዥ በሚመለከት የቤት ኪራይ እንደገቢ ምንጭ እንዲያገለግል ከሚያሳየው መረጃ በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 5.4 ልኬትና ገንዘቡ

መለኪያውንም በሚመለከትም "ዜራ" ወይም "ኩት" /ማለት 45-56 ዕሜት 1 ክንድ/ የተባሉት እስከ ቅረብ ጊዜ ድረስ ይሠራባቸው ነበር፡፡ ስቲትዝ "ዜራ" ስለሚባለው መለኪያ ሲገልፅ ሃያ ጊዜ 60X60 ሳንቲ ሜትር ወይም ሃያ ጊዜ 2.7 ስኬር ሜትር የሚያካትተውን ሽብል ማለት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ሶሲ ዛምዛርቋል፣ ዋሱል እና ሳዋድ የሚባሉት መለኪያዎችም ከውጭ የመጡ ጨርቃጨርቅ የሚለካባቸው ጠቃሚ መስፈርቶች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ "ሻጂር"የተባለው ዓይነርግብ ግን በአብዛኛው የሐረር ሕብረተሰብ አይገለገልበትም ነበር፡፡

ምንም እንኳን ከመካከለኛው ዘመን በፊት በሐረር የነበረው የገንዘብ አጠቃቀም የሚያመለክተው መረጃ የተበታተነ ቢሆንም ከዓብድአሽኩር ዘመን ወዲህ ግን በተከታታይ በሥራ ላይ እንደነበረ እንገነዘባለን፡፡ስለዚህም "አሽራፊ" እና "መሐለቅ"የተባሉት በጥቅም ላይ ሲውሉ "ዲርሃምና ዲናር ግን እንብዛም በሥራ ላይ አይውሉም ነበር፡፡ ነገር ግን በከተማው ውስጥ እንደመገበያያ ያለግሉ እንደነበር አልፎ አልፎ ይወሳል፡፡

ከዚህ ሌላ ግን በሐረር ውስጥ በቤተሰብ ስም ነጠራት የተለመደ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ቢሆን እውደቱን አልጨረሰም፡፡ በመሆኑም ሚዛን፣ ጌራድ፣ ካለፈ የተባሉት የቤተሰብ ስሞች በዛሬው ጊዜም ይገኛሉ፡፡ እነዚህህ የቤተሰብ ስሞችም ሰዎች አያት ቅድመ አያቶቻቸው እነማን እንደሆኑ ቆጥረው ለመድረስ ይረዷቸዋል፡፡ ከቤተሰብ ስሙ በተጨማሪ የሐረር አምስት በሮች ማተ ማታ ከተቆለፉ በኋላ መክፈቻዎቹ የሚቀመጡበት "ቁፍሊ ጉይታ" የሚባል አለ፡፡ የ"ቁፍሊ ጉይታ" ኃላፊነትም የአምስቱን በሮእ መክፈቻ ከምሽት እስከ ጥዋት /ከፀሐይ መጥለቅ እስከ ጥዋት/ ውጋገን ድረስ መያዝ ነው፡፡

የሐረርን ኢኮኖሚ በምናወሳበት ጊዜ ዛሬም ቢሆን ያሉት መረጃዎች ያለተጠቃለሉ መሆናቸውን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ብዙ ግለሰቦች እጅ የሚገኙ መረጃዎችም የሚመረምራቸውና የሚያጠናቸው ሰው እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡እውነቱ ለመናገር እስካሁን ድረስ የተደረገው ሙከራ እንኳን እውነቱ እስከማግኘት የተገፋበት አይደለም፡፡ ይልቁንም የጽሑፎቹ ለመነበብ አለመቻልና በወቅቱ ይጠቀሙበት የነበረው ቋንቋ ነገሮች ሙሉ በሙሉ እነዳይታወቁ እንዳደረጋቸውም አይካድም፡፡

ሌላው ቀርቶ የአሚር አብዱሽኩር የሂሳብ አያያዝ መዝገብ እንደነበረው በመጀመሪያ ደረጃ መረጃነት ለማውሳት ካልሆነ በስተቀር ኢኮኖሚያዊ ትንተና እንኳን ለማድረግ አልተቻለም፡፡

ይህም የሽያጭ ርክክብ የተፈፀመው በምስክሮች ፊት ነው፡፡ ምስክሮቹም አልሰይድ ሙሐመድ ቢን ኻሊፍ ፣ዓርታብ ዑስማን፣ ሼኽ አብድልረሕማን ቢን ከቢር ዩሱፍ አልሰይድ ባቂ፣ አብዱበከር ኢብራሂም ላፎ፣ ሻንቆ ዓብድ አል-ረሕማን ሚዛንና ወርቅ ሲሆኑ ጌታችን አብደልሸኩርም በዚህ ጊዜ ተገኝተዋል፡፡ ከሁሉ የበለጠው ምስክርም አላህ ነው፡፡

ውሉ የተመዘገበው ቅዳሜ ሰፈር 4 1204 ዓ.ሒ

## 5.5 ዳኝነት

ከአሚር ዳኝነትና ፍትህ አስፋኝነት ከተገኘ ሰነድ የአረብኛ ሰነድ ትርጉም እንዲህ ይነበባል፡፡ “ይህ በአላህ ፍቃድ የተባረከ ማስታወሻ የጌታችን፣ ጠማሞችን ደምሳሽ የሆነው አሚር አብዱሽኩር ቢን አልሱልጣን አሚር ዩሱፍ ነው፡፡ አንድ ቀን ሼክ ሐሚድ ቡዲኔሕ ወደ ሲዲ አሚር አብደሽኩር ቤተ መንግስት መጣና ከሟች ወንድሙ ከዓሊ ሼኽ ሚስት፣ ከወንድሙ ልጅ ከአብዱልራህማን፣ ወንድሞቹ በወረሱት መሠረት ድርሻውን እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡ አሚሩም ከቢር ቢን ከቢር ሙሐመድ አንዱን ጉዳይ እንዲከታተል አል ሰይድ ባቂረን ደግሞ የአሊ ሼኽ ሚስት ጉዳይ እንዲከታተል ወከላቸው፡፡ ተወካዮቹም ከድንጋይ የተሠራው ቤትና እርሻው እንዲሁም የእናቱ ሦስተኛ ቦታ ውርስን በሚመለከት ለአሚሩ አሳወቁ እነርሱም ባቀረቡት መረጃ ተደሰቱ፡፡

አሚሩ ጉዳዩን ለቃዲ አብድልቀድር እንዲቀርብና እንዲከፋፈል እነርሱም የሁሉንም ንብረት ዋጋ አስልተው እንዲያመጡ አዘዘ፡፡ በዚህ መሠረት አብዱልረሕማን ከሚባለው ከመጀመሪያው ባሏ የሚደርሳትን ጥሎሽ ከዚያም ንብረቱን የሚከፍለው ዋጋ 40 አሽራፍ ቀንሰው አቀረቡ ቃዲውም በቁርዓኑ መሠረት የሚቀረውን ሂሳብ አከፋፈሏቸው፡፡

ከዚያ በኋላ ሚስትየዋ ከአሊ ሼኽ በጥሎሽ ያገኘችውንና 70 አሽራፍ ዋጋ ያለውን የንግድ ስፍራ “ያሳደግኩትን ባርያ መልስልኝ” በማለት አሚሩን ጠየቀቻቸው አሚሩም ጥያቄውን በመቀበል 70 አሽራፍ የሚያወጣ ባሪያ እያንዳንዱ ዜራ 4 አሽራፍ የሚያወጣ 17.56 ዜራ መሬት ፣ በአጠቃላይ 70 አሽራፍ፣ እንድትሰጠው ተስማማ። ውሉ በመሬት ላይ የሚገኘውን 5 አሽራፍ የሚያወጣ አንድ ከሣር የተሰራ ቤትንም ይጨምራል። በዚህ ውል መሠረት የ10 አሽራፊ ዋጋ ያላቸው 4 የብር ዲርሐም 16 አሽራፍ ዋጋ ያለው ሻዲር፣ 5 በካሽ፣ 7 አሽራፊ ዋጋ ያለው ገዚራ ዛምሐርቃል 9 አሽራፊ ፀሎት እንድታደርግላቸው በአጠቃላይ 82 አሽራፍዎች ተቀብላለች። ይህንን ውል በእማኞች ፊት የፈፀሙ ሲሆን እማኞቹም አብድልራሕማን ሚዛን ቢን ኡመር ዲን ሼክ፣ ከቢር ያህያ ቢን ከቢር ዓ አትባር፣ እና ኢድሪስ ቢን ናስር ነበሩ። ከእነርሱም በላይ ዋናው ምስክር አላህ ነው። ይህ ውል የተፈፀመው ዓርብ 1 ቀን 1207 ዓ.ሒ. ነው።

## 6. ገንዘብ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ሣንቲሞችን መጠቀም እንግዳ ነገር አይደለም የአክሱም ዘመን ሰዎች ከ3ኛው ምእተ ዓመት ጀምሮ በአብዛኛው ተቀባይነት ባገኘው ሐሳብ መሠረት እስከ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሣንቲሞች ይጠቀሙ ነበር፡ ፡ ሣንቲሞችን መስራትም እጅግ ውስብስብ የሆነውን የንግድና የከተማ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ይጠቁማሉ። አክሱም እንደዋነኛ የንግድ ማዕከልነቷ የተለያዩ ሳንቲሞችን የመጠቀምና ሣንቲሞችን የማምረት ጥበብ ለተከታይ ትውልዶች በማስተላለፍ የነበረችበትን የእድገት ደረጃ ለማሳየት እንደታሪካዊ መረጃነት ለመጥቀስ ተችሏል። በአሁኑ ጊዜ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኘው ሐሳብ አክሱማውያን እስከ 7ኛው ክፍለ ዘመን ገደማ በሣንቲም መጠቀማቸው ነው።

1. በ14ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢም በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በገን ዘብ መጠቀም መጀመሩን እንመለከታለን ለምሳሌ አለጃዛሪ እ. አ.አ በሰኔ 26 ቀን 1330 ባቀረበው ሪፖርት ሲናሮች በጥቅም ላይ ውለው እንደነበር አስታውሷል። እንደ አልመቅሪዝ ዘገባ እውፋቶእ ኢፋቶ እ.ኤ.አ በ1430ዎቹ ገንዘብን ይጠቀሙ ነበር። ከዚህም ሌላ በደማስቆ (ስርያ) የወይን ዘለላ እስሮች አራት ድርሃም የሳንቲም ዓይነት ሲያወጡ ሰላሳ ፓውነድ የሚመዝን ሥጋ በግማሽ ድርሃም ይሸጥ ነበር።

2. ዳሞትና ሳሄም አውፌት ኢፋት ሣንቲሞችን ለመስራት የሚ ያስፈልጋት ወረቀት የምታስመጣባቸው ቦታዎች ናቸው ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ ቃል ቃሻንዲ ኢፌት የምትጠቀምባ ቸው ድርሃሞችና ዲናሮች በግብጽ የተሠሩ እንደነበር ተጠቅ ሷል፡፡ ይሁን እንጂ ኢፋት ለሳንቲም መስሪያ የሚሆኑ ወር ቆችን ወደ ግብጽ ትልክ ወይም የግብጽን ሳንቲሞች ትጠቀም ግልጽ አይደለም፡፡

3. የድሮው አገር የኢኮኖሚ ይዞታ በጥቂቱም ቢሆን የዘገበው አል መቅትሪዚም በዚሁ ቦታ ውፍረቱ 3 መርፌ ያህል ሀኩና የተባለና ከብረታ ብረት ስብርባሪዎች የተሰራ ገንዘብ ለንግድ ልውውጥ ሚና እንደነበረው ገልጿል፡፡ በእርግጥ በዚያው አገር አንዲት ላምና በግ እንደየቅደም ተከተላቸው 5000 ሺ ና 3000 ሺ ሐኪና ያወጡ ነበር፡፡

4. ወንድም አንቶንዮ የተባለ ኢትዮጵያዊ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አንኮበር አጠገብ የግንደ በረት ስለተባለችው የንግድ ማዕከል በሰጠው ዘገባ ይህቺ የንግድ ማዕከል የሐንጋሪና የቬኒሺያን ዱካቶችና የሚሮችን የእስላችን የብር ሣንቲሞች ትጠቀም ነበር ይላል፡፡ እነዚህ ሙሮች እስላሞች የአገሬው ነዋሪ ይሁኑ አይሁኑ ጋገን እርግጠኛ የሆነ ማረጋገጫ የለንም የሳንቲሞቹ አመጣጥ ግን ምናልባትም በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ሙስሊም ሱልጣኖች ሳይሆን አይቀርም፡፡

5. በኢትዮጵያ ገንዘብ ታሪክ ውስጥ ቀደም ባለው ጊዜ በጣም የታወቁት አሞሌ ጨርቅ ቁርጥራጭ ብረትና አረር በ19ኛው ክፍለ ዘመን ግን የማር ትሬዛ “ጠገራ ብር” የዋነኛው የትል ልቅ ንግድ ስራ መለዋወጫ ገንዘብ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ ይህ ገንዘብ በአፄ ምኒሊክ የአገር ውስጥ ገንዘብን በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ መሥራት እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ ወሳኝ የሆነ አገልግሎት መስጠቱን ቀጥሎ ነበር፡፡

## 6.1 ገንዘብ በሐረር

ሐረር ለምስራቅ አፍሪካ ንግድ መውጫና መግቢያ እንዲሁም ለእስልምና ትምህርትም ወሳኝ ማዕከል ሆና ላለፉት አምስት ምዕተ ዓመታት ማገልገሏ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በሐረሪ ታሪክ የነበሩት ተጨባጭ እውነታዎችም ለንግድ ዕድገት ከዚሁ ጋር ለተያያዘው የሣንቲም ሥራ ዓይነተኛ ሚናን ተጫውቷል።

### 6.1.1 ሽያጭና ዋጋ በገንዘብ

1. ሐረርና አካባቢዋ ክፉኛ በድርቅ ተመተው በነበረበት ወቅት አንድ ሠዓ በአራት እፍኝ የሚመነዘር ማሽላ 12 አሽራፍ የሐረር ገንዘብ ያህል ሲሆን አንድ ሠዓ ጨው ደግሞ በ15 አሽራፍ በላይ እንደነበር ከታሪክ መዛግብት መማር ይቻላል። የሐረር ኢኮኖሚ ከድርቁ ጉዳት በኋላ አገግሞ ባንሰራራበት ወቅት ደግሞ የምግብ ዋጋ በመቀነሱ የዱራህ ማሽላ ዋጋ አራት ወይም አምስት መሃለቅ ሆነ መሃለቅ ማለት የአሽራፊ ምንዛሬ ነበር።

2. ሐረር በሌላ ወቅት በድረቅ ተመታች ይህም አሚር ኑር ኢብን ሙጃሂድ ሐረርን በገዛበት ከ1551-1567 በአንዱ ሰሞን ሲሆን በድራሀን ማሻላ ዋጋ ወደ ሁለት አሽራፍ ከፍ አድርጎት ነበር። ይህ ስለ አሽራፊና መሃለቅ የሚናገረው የመጀመሪያው መረጃ የተገኘው ኩኤንሪኮ ቼሩሊ ነው። ከእነዚህ ገንዘቦች የሚኖረን የመጀመሪያው ማስረጃ እንደምንረዳውም ምናልባትም አሽራፍን ወደ ሐረር ያስመጣው አሚር ኑር ሲሆን ገንዘቡም በወቅቱ በግብፅ ማምሉኮች ዘንድ እጅግ የሚሰራበት ነበር።

3. ምንም እንኳን በዚህ ወቅት በከተማው ውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረው የገንዘብ መጠን ባናውቅም መሐመድ ኢብን ሰይድ አልሸቲር ብቻ ከ35000 በላይ ገንዘብ እንደነበረው የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ። በእያንዳንዱ ሺህ 50ዎች ንጹህ የወርቅ መለኪያዎች ነበሩ። ማስረጃው ግን የገንዘበ ስም አይገልጸም። በዚህ አይነት ጥቂት መቶ ሺህ ሣንቲሞች በከተማው ውስጥ ሥራ ላይ እንደዋሉ መገመት ይቻላል።

4. አንዳንድ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ተጓዦች ጠቃሚ መረጃዎችን ሰጥተውናል። ከነዚህም መካከል እንግሊዛዊው ባርከር ስለ 19ኛው የሐረር ኢኮኖሚ ሁኔታ በተለይም ከ1842 እ.ኤ.አ ጀምሮ ስላለው ልውውጥ ጥቂት የመንደርደሪያ ሐሳብ የዘገበ ሲሆን ዕቃን በዕቃ መለወጡና ዋና የንገድ መለዋወጫ ዘዴ እንደነበርና በሐረር ማርትሬዛ ጠገራ ብር እንደገንዘብ ማገልግሉን ያስረዳል።

## 6.2 መሐለቅና ሌሎች ሸርፍራፊዎች በምንዛሬ

"መሃለቅ" በመባል የሚታወቀው ከመዳብ የተሰራች ሳንቲም ነበረ።ሀያ ሁለት መሀለቆች አሽራፍ ከሚባል የሣንቲም ዓይነት ጋር እኩል ናቸው። 40 አሽሪፍዎች ደግሞ ከአንድ የጀርመን ክራውን ጋር እኩል ዋጋ አላቸው። መሀለቅ የጁዳን ዲዋን ይመስላል። በአንደኛው የመሐለቅ ገፅ ላይ በአረብኛ "ላ ኢላህ ኢለላህ" የሚል ጽሁፍ ሲኖረው በሌላኛው ገጹ የገዢውን መስፍን ስም እናገኛለን። ከሚለው ባርከር ስድስት ዓመት በኋላም ክሩተንደን (1848) የሐረሪ ሳንቲሞች በሶማሌ ዳርቻዎች ጥቅም ላይ ውለው እንደነበር የሚገልፅ ተጨማሪ መረጃ ሲሰጥ በሐረሪ ሳንቲም አሽራፍ ለቦታው ብቸኛና ታዋቂ የሆነ ሳንቲም ነበር። መሃለቅ የተሠራውም ከብር ሲሆን የማርትሬዛ ዶላር 1/22ኛ (ከሃያ ሁለቱ አንዱ እጅ) ያህል ዋጋ ነበረው። እኔ (ባርከር ሰላገኘ) የቻልኩትና ናሙና በ910 የሒጅራ አቆጣጠር በአንደኛው ገጹ ላይ የአሚር ስም የተጻፈበት ሲሆን በሌላው ላይ (ላ ኢላሃ ኢለላህ) የሚል ጽሑፍ አለበት ይላል። በክሩትደን በተጨማሪ እንደተጠቀሰው በአሚር አብዱልሽኩር የወርቅ ገንዘብ በአገልግሎት ላይ ውሎ ነበር። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን በእርሱ ዘገባ የአሚሩን ስምና ገንዘቡ ስለተሰራበት የተጠቀሰ ነገር የለም። ይህ መረጃ በሐረር የነበረውን ሳንቲም የመስራት ታሪክ ዕውቀት ሊያጠናክርልን ይችላል።

ሪቻርድ በርተርን በ1855 እ.ኤ.አ በሐረር ሳንቲሞች ላይ የራሱን አስተያየት ሲሰጥ በዚህ ወቅት ብቸኛው የሐረር ሳንቲም ዓይነቱ ከአነስተኛ የነሐስ ሸርፍራፊዎች በእጅ የተሰራ ምንም ዓይነት ጥበብ ሽብርቅ ያልተጨመረበት እንደ ዘመናዊው የኢጣልያን ሳንቲም መሃከለኛ የሆነ መሀለቅ ነበር። ይህ መሀለቅ በአንድ ገጽ ዘሪበልር በሐረር የተመረተ በግልባጩም የሒጅራ አቆጣጠር 1248 ተጽፎበታል።

አሚሩ በከተማው ውስጥ ሌላ ዓይነት ሳንቲሞችን የሚያዘዋውሩትን ያለ ርህራሔ ይቀጣቸው ነበር ብሏል፡፡ በርተን በወቅቱ ስልነበረው የምንዛሬ ስሌት ሸልዬ ሲጽፍ ሃያ ሁለት ፐላንቴይን አንድ መሃለቅ ይሆናሉ፡፡ ሃያ ሁለት መሃለቅ አንድ አሽራፍ በዚህ ሰዓት የይስሙላ ሳንቲም ሦስት አሽራፊ አንድ ዶላር ነበር ብሎታል፡፡

በርተን በዚያን ወቅት ለነበረው የገንዘብ ልውውጥ የዓይን ምስክር የሆነውን ዘገባ ሰጥቶናል፡፡ የበርተን ሪፖርት የወቅቱን የገበያ ሸቀጦችና የባሮች ዋጋ ጭምር ያጠቃልላል፡፡ በዚህ መሰረት የሴት ባሮች ዋጋ ከ100 እስከ 400 አሽረፍ የወንድ ባሮች ዋጋ ከ90 እስከ 150 አሽረፍ መሆኑን በማስተዋል ጹፋቸዋል፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በሐረር ውስጥ 120 ቄብ ዶሮዎች ወይም ለእርድ ብቁ የሆኑ ስልሳ ስድስቶች ትልልቅ ዶሮዎች አንድ ዶላር ያወጡ ነበር፡፡

## 6.1.3 የሀረር ገንዘብ በሩቅ አገር ከነ አሻራቸው

1. በርተን ዘገባ ስለ ሳንቲም መሰስራትና በድንጋይ ላይ ስለተፃፈ ጽሑፍም /ኢንስክሪፕሽን/ ጠቃሚ የሆነ ሐሳብ ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን በ19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ባርከርና ክሩትንደን የሰጡን ዘገባ በከፊል ብቻ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ሁለቱም የፃፉት ሐረር በአሚር አቡበከር ሁለተኛ /1834-1852/ አገዛዝ ሥር የነበረችበትን ዘመን ነው፡፡ እንዲያውም ክሩትንደን የተጠቀሰው ሳንቲም የ 910 / ዘጠኝ መቶ አስር/ ሒጅራ አቆጣጠር /ዓመተ ሒጅራ/ ወይም /እኤአ/ በ1504 ነው፡፡ ይህ ዘመን ደግሞ ከአሚር አቡበከር የአገዛዝ ዘመን በጣም የቀደመ ነው፡፡ ምናልባትም ይህ ሳንቲም ገንዘቡ ይሰራ በነበረበት ዘመን ከሐረር ሶማሌ ጠረፍ እስከሚገኘው እስከ ራስ እሰር ቦታ ድረስ ይዘዋወር ስለነበርና ክሩተንደን ናሙናውን የገዛው ከዚያው አካባቢ ስለሆነ የእርሱም ሳንቲም የዚያው የድሮው ቅሪት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ፡፡

2. በቅርብ ጊዜ ደግሞ ከአገር ውጪ ፍሪማን ግራቨል ሞቃዲሾ ውስጥ በተገኘው ሳንቲሞች ላይ ጥናት ሲያደርግ ስለ ሁለቱ የሐረር ሳንቲሞች ጠቅሷል፡፡ የግሪንቨል ናት ከ1300 እስከ 1700 እኤአ ባለው ዘመን ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ይህም ጊዜ ቀደም ያለ በመሆኑ የሐረር ሳንቲሞች ከከተማ ውጭ ይንቀሳቀስ ነበር ብሎ መገመት ቢያስቸግርም ነገሩ ጭራሽ ሊሆን አይችልም ብሎ ማጣጣል አይገባም፡፡

3. ቀረብ ባለ ጊዜ ደግሞ 67 የሐረሪ ዝርዝር ሳንቲሞች በጨለንቆ አካበቢ ቀbናዋ በተባለው ቦታ መገኘታቸውን ያበሰረው የዡሶም ግኝት ከዚህ የበለጠ ሌላ ግኝት ይኖራል ብለን ተስፋ እንዲኖረን አድርጎናል።

## 6.3 በሳንቲሞች የተቀረፁት ማስረጃዎች

በአብዱልሽኩር ጊዜ ደግሞ የሳንቲም ሥራ ተንሰራፍቶ እናገኛለን። ብዙዎች የሐረሪ ሳንቲሞች ከ1197 የሒጅራ አቆጣጠር ወይም ከ1783 እኤአ ወዲህ የተሰሩ ናቸው። ከዚህ በተለየ ትኩረት የሚስቡ ሳንቲሞች ቢኖሩ በ124 እና 125 የሒጅራ አቆጣጠር 742/3 እኤአ ይሠራባቸው የነበሩ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የ16ኛው ክፍለ ዘመን ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ሳንቲሞች በ8ኛው ምዕተ ዓመት የተሰሩ ናቸው ማለቱ ያዳግታል። ምክንያቱም የ2ኛው መቶ ዓመት የሒጁራ አቆጣጠር ዓመታትን በቁጥር ሳይሆን በቃላት የመጻፍ ልምድ ነበረ ስለዚህ ሁለቱ ሳንቲሞቻችን የተሰሩበትን ቀን የሚገልጽ የአሃዝ ቁጥር አላቸው ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሳንቲሞች ካላቸው ቁጥር ውስጥ አንድ ሊጠፋባቸው ይችላል። የአጻጻፋቸው ስልት ካሊንግራፊ ካየንም ከ19ኛው ምዕተ ዓመት ሳንቲሞች ላይ ከተፃፉ ጹሑፎች ጋር ይመሳሰላሉ። ጥንቃቄ የተሞላበት ማስተዋል የሚያስፈልገው ሳንቲም ግን በ651 ሒጅራ ወይም 1218 እኤአ የተሰራው ነው። አራት ቤቶችን (ዲጂቶችን) መስጠቱ ቢከብድም በዚህ ሳንቲም አጻጻፍ ከኋለኞቹ ሳንቲሞች ጋር የአጻጻፍ ስልቱ መመሳሰል ይታይባቸዋል ማለት ይቻላል። ይሁንና ቀደም ላለው ጊዜ ወሳኝ የሆኑ ናሙናውን እስክናገኝ ይህን ሳንቲም ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊትና ቀደም ላለው ጊዜ ነጠላ ናሙና አድርገን ልንወስደው እንችላለን።

በግለሰብ ደረጃ የየትኛው መንግስት ሳንቲሞች እንደሆኑ ለመግለጽ ቢያስቸግርም ጊዜያቸው በ900 በ910 እና በ943 የሒጅራ አቆጣጠር ወይም 1495፤1504 እና 1536 እኤአ የሆኑ ሳንቲሞች አሉኝ ወይዘሮ ሄለን ብራውን በአሽሞሊያን ሙዝየም /ኦክስፎርድ/ የሙስሊም ሳንቲሞች ኤክስፐርት የሆኑት እነዚህ ሳንቲሞች ከሐረሪ ሳንቲሞች የሚመደቡ ሳይሆኑ ከዘቢድ /የመን/ እንደሆኑ ይናገራሉ። /ለእነዚህ ሳንቲሞች ላይ የበለጠ ጥናት እየተካሄደባቸው ነው፡/ የተሰሩበትም ዘመን በ1103 የሒጅራ አቆጣጠር ወይም 1685 እኤአ ለመሆኑ የሚገልፅ አንድ ስለ ሐረሪ ሳንቲሞች በቅርቡ በወጣው ጽሑፍ ላይ ተዘግቧል።

የተሰሩበት ዘመን 1197፤1203፤1204 በሒጅራ አቆጣጠር የሆኑና በአብዱልሽኩር ዘመን የተሠሩ ሳንቲሞች አሉን፡፡ ይህ ደግሞ በአንፃራዊ አነጋገር በሐረር ውስጥ ተከታታይ የሳንቲሞች ስራ የተጀመረበት ወቅት ይመስላል፡፡ ከሐረሪ አሚሮች አንዱ አሚር አቡበከር ሁለተኛ የገነዘብ እሴት /ቫልዩ/ ከሚገባው በታች ቀንሶት ነበር አንድ ታሪካዊ መረጃ ይህንን በተመለከተ ሲገልጽ፤

## 6.2.4 የገንዘብ ዋጋ መቀነስ ዲቫሉኤሽን

የገንዘቡ እሴት /ቫልዩን/ ቅነሳ በተሰራጨው በ11 ሸዋል 1257 አመተ ሒጅራ ሲሆን በረቢዓል አወል 1258 አመተል ሒጅራ ደግሞ ራሱ ገንዘቡም ተቀየረ፡፡ አሚሩ የሐረርን ከተማ ሽማግሌዎችን ከሰበሰባቸው በኋላ የደረሰበትን የገንዘብ ችግር ገለፀላቸው  አንድ የቀድሞ ገንዘብን በሃያ አዲስ ገንዘብ እንዲተኩ ወሰነ ይላል፡፡

እ.ኤ.አ በ1876 በሚስሮች /ግብፆች/ሥር ወታደራዊ ግልጋሎት ይሰጥ የነበረው መሐመድ ሙኽታር የተባለው ሰው በአሚር መሐመድ ኢብን ዓሊ ዘመን የነበረውን ሰፊ ያላለ ገንዘብ ስራ ሂደትና የገንዘብ ዋጋ ቅነሳ /ዲቫሉዌሽን/ አስመልክቶ ሰፋ ያለ ማስረጃ አስቀምጧል፡፡ ከመሐመድ ሙኽታር ዘገባ እንደምንረዳው ከሆነ የአሚሩ ወንድም ለሆነው የኦሮሞ ጉሳ ፍላጉታቸውን ለመጠበቅ ሲል “መሀለቅ ጋላ” የሚል ገንዘብ አሠርቶ ነበር፡፡ ይህም ዘዴ የገንዘብ የዋጋ ቅነሳ በመጠቀም እንዲቆይ አድርጓል፡፡ አሚሩ ማንኛውንም ድሮ /አሮጌውን ገንዘብ/ የነበራቸውን ሰዎች እሴታቸው /ቫልዩስ/ በተቀነሰው አዳዲስ ሳንቲሞ እንዲቀየሩ አዘዘ፡፡ የልውውጥ መጠኑ የወሰነው ለእያንዳንዱ 2,200 አሮጌ ሳንቲሞች 100 አዲስ ሳንቲሞች እንዲሆኑ ነበር እንደ ሙኽታር ግምት ጠቅላላው የልውውጥ ሂደቱ ማጭበርበር የተሞላበት ነበር ብሎ ክፉኛ ወቅሶታል፡፡ አሚሩ ውድ የሆኑትን የብር ሳንቲሞች ወደ ራሱ ካሸ ወደሆኑትና ዋጋቸው ወደ ቀነሰው ከአንዱ የብረት ዓይነትና በአብዛኛው ከቀረቆሮ ተቀይጠው ወደ ተሰሩት ሳንቲሞች እንዲለወጡ ማዘዙን መሐመድ ሙኽታር እንደሚከተለው ጽፎታል፡፡

የተለያየ ደረጃ ያላቸው የብረት ቁርጥራጮች ተዋህደው ወደ ቀጭን ቁርጥራጭነት ከተለወጡ በኋላ ከአንዱ ሚሊ ሜትር ውፍረት በላይ ሳይበልጥ ክብ ሲስክ በእርሳስ በተሰረሰ ጠፍጣፋ ብረት ላይ የተደረገ የአሚሩን ስም የያዘ ከዓረብ ብረት የተሰራ ማህተም ላዩ ላይ ተደርጐ በመዶሻ በመምታት የሳንቲሙ የአሰራር ሂደት ያልቃል ማለት ነው፡፡

አሚር መሐመድ ራሱ ላወጣውና ዝቅተኛ ዋጋ ላለው ገንዘብ ትንሽ ትኩረት በመስጠት ወንድ ልጅ ለሴት ልጅ የሚያቀርበውን ጥሎሽ በተመለከተ ሕግ አውጆ ነበር፡፡ አዋጁ የወጣው ለዙልቀይዳ 1279 ሒክራ ሰኞ ዕለት ነበር፡፡ በ1863 እኤአ አቆጣጠር ነበር ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ጥሎሽ የሚከፍለው 100 አሽራፍ ሲሆን ፈታ /የፈታች/ ለሆነች ሴት የዚያን ግማሽ /50 አሽራፍ/ እንዲሆን አድርጐ ነበር፡፡

## 6.3 ገንዘቡን መለዋወጥ

ግብጾችም ሐረርን በያዙበት ወቅት ለከተማይቱ የሚያገለገል የገንዘብ መፍትሔ ለመሻት ሞክረው ነበር፡፡ የአሚር መሐመድ ሳንቲም ዋጋቸው ማሻቀቡን (እንፍሌት ማድረጉን) ተስማሙ፡፡ በ1883 እ.ኤ.አ ሂልደር ክራንድ የተባለ ጀርመናዊ ተጓዥ ስለሐረሪ ሳንቲሞች ሲገልፅ የከተማው ገንዘብ የመግዛት አቅሙ 1/10 ኛውን /ከአስር እጅ አንዱን /መሸፈን አቅቶት እንደነበርና ዝውውር ወይም እንቅስቃሴን ሊሰጥ የቻለውም የከተማውና የአካባቢው ንግድ በጥሩ ደረጃ ላይ ስለነበር ነው ርዴይ እንደገለፀው 33 መሀለቅ ለአንድ ዶላር የነበረው ልውውጥ እኩል አልነበረም ብሎታል፡፡ ምክኒያቱም የከተማው ገንዘብ እሴት በአስራ አምስት እጅ ከልውውጥ ዋጋው ዝቅ ያለ ነው፡፡

መሐመድ ራዑፍ ባሻ ሐረርን ይዞ የነበረበት የግብጽ ጀነራል መጀመሪያ የሐረሪ ሳንቲሞች እንዳይዘዋወሩ አግዶ ነበር፡፡ ምክንያቱም የሐረሪን ሳንቲሞች በግብፅ ገንዘብ ሊተካቸው ስለአሰበ ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት የሳንቲሞቹን የኮፒ ይዘት ለማሳወቅ ጥቂቶቹን ለናሙና የሚሆኑት ወደ ካይሮ ለጥናት ልኮ ነበር፡፡ የግብፅ መንግስት ግን 1000 ሺህ የብር ፒየስተሮችና 300 ሺህ የመዳብ ሳንቲሞች እንደገ እገልግሎት እንዲሰጡ አዘዘ፡፡

ሐረር ጎን ለጎን አገልግሎት የሚሰጧት ሁለት ገንዘቦች ነበሩ። አንዱ የሐረሪ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የግብፆች ነበር ይሁን እንጂ መሀለቅ እራሱ ከ33 መሀለቅ ወደ አንድ ዶላር /ማርትሬዛ/ ዋጋው ቀንሶ ነበር። ከ300 እንዲሁም ወደ ማርትሬዛ ቀንሶ ነበር ከጊዜ በኋላ ደግሞ ጥናት ተደርጐበት ካበቃ ወዲህ የመሐለቅ ዋጋ ከ311 ወደ አንድ ማርትሬዛ / ጠገራ ብር/ ደረጃ ወርዶ ነበር።

ግብፆች አስር ዓመት ከገዙ በኋላ ሐረርን ሲለቁ አስተዳደሩን ለአሚር አብዱላሂ ኢብን መሐመድ /1885-1887/ አስረክበው ነበር። ለሁለት ዓመታት የገዛውም አሚር አብዱላሂ የሣንቲም ሥራውን እንዲቀጥል አዘዘ እኤአ ጥር /ጃንዋሪ/ 7 ቀን 1887 አሚሩ በአጼ ምኒልክ ጨለንቆ ላይ ስለተሸነፈና ሐረርም ወደ ማዕከላዊ መንግስት ስለተቀላቀለች የራሷ የሆነውን የሳንቲም ስራ አቆመች።

ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያ ቢሆን ሐረር የመጀመሪያ የሳንቲም ስራ ማዕከል ሆነች የምኒልክም የመጀመሪያዎቹ ሳንቲሞች በሐረር የተሰሩ ሲሆኑ ዘመኑም በ 1885 እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ነበር። ስለዚህ ሐረር የጥንቱን የአክሱማውያን የሳንቲም ስራንና የዘመኑን የሳንቲም ስራ አገናኝ ድልድይ ሆና ቆይታለች።

# ክፍል አራት ማህበራዊ ኑሮ

# ምዕራፍ ሰባት

## 7.የሐረር ከተማና ማህበራዊ ገጽታ

### 7.1 ከተማዋ በአጠቃሎና በወፍ በረር እይታ

የሐረር ከተማ በቀበሌ፣ በጉረቤት፣ በአድባራት የተዋቀረች ስትሆን ሕዝቧም በእድር፣ በጉረቤት፣ በቤተሰብ ማህራዊ ኑሮ የተዋቀረ ነው። የሐረር ከተማ የሕዝቡ ማህበራዊ መዋቅር ከሌሎች ማህበራዊ መዋቅሮች የሚለየው ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የነበረና ዛሬም ተጠናክሮ የቀጠለ በመሆኑ ነው። ይልቁንም በግንብ በተከበበችውና ጁገል ተብላ በምትጠራው የከተማው ክፍል ያለው መዋቅር ከሌላው የተለየ ነው።

የተለዩ የታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚገልጹት ደግሞ ሐረር በኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኝ፣ ዙሪያዋ በግንብ የታጠረች /የተከበበች/ ስትሆን በዓለማችን ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከመስፋፋታቸው በፊት የተቆረቆረች ከተማ ናት። የሐረር ከተማ ነዋሪዎች የራሳቸው የሆነ ቋንቋና ባህል አላቸው። ሐረር በታሪክ ዓምድ ላይ አላት እያሉ በአያሌው ጠቅሰዋታል። ከነዚህም ውስጥ ሪቻርድ አላን ኮክ /እ.ኤ.አ በ1971/ 1966 እንደገና በታተመው የበርተን መጽሐፍ ኤንሪኮ ቼሩሊ /እ.ኤ.አ በ1936/ ትሪሚንግሃም እ.ኤ.አ በ1965 እ.ኤ.አ እንደገና ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ስለሐረር ከተማ ታሪክ ጽፈዋል። ሌሎችም እንደዚሁ የፃፉት የታሪክ ምሁራን ብዙ ናቸው።

ምንም እንኳን ስለ ሐረር ወይም ስለሌሎች እስካሁን ድረስ በጥናት ያልተዳረሰባቸው የሐረር ዓይነት ከተሞች ከአሁኗ የሶማሊያ ሪፐብሊክ አንስቶ እስከ ኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ ቢገመትም የሰው ልጅ የጥንት ታሪክና የባህል ሁኔታ ከሚያጠኑ ምሁራን /በአርኪዮሎጂስቶች/ እምብዛም የተጠቀሰ ነገር አልተገኘም። የሐረር ከተማ ግን ከላይ በተጠቀሰው መለክ ከዚህ ቀደም ከተስፋፋና የከተማ ማዕከል ከነበራቸው የእስልምና ባህል የመጨረሻዋ ቅሪት ትመስላለች።

በቅርብ ጊዜ ስለሰው ልጅ የጥንት ታሪክና ባሕል ሁኔታ አጥኚ የሆኑት ሪቻርድ ዋይልዲንግ አንገብጋቢና ተፈላጊ የሆነውን ጥናት በዚሁ ዘመን ሌሎች ካጠኑት በላይ የተዋጣለት ጥናት አጥንተዋል ሊባል ይችላል፡፡

ከአበው ታሪክ /አፈ ታሪክ/ የምንረዳውና ከሌሎች ታሪካዊ ማስረጃዎች ጋር ተስማሚነት ያላቸው ምንጮች እንደሚገልጹት ሐረር ከአሚር ኑር የ1552-66 እ.ኤ.አ ጀምሮ የራሷን ታሪክና ባህል ይዛ መቆየቷን ያበስራሉ፡፡ በ1888 የታሪክ መጽሐፉን ለንባብ ያበቃው ፐሊሽኪ ደግሞ ቢያንስ ላለፉት አራት መቶ ዓመታት ያህል የሐረር ከተማ ለአካባቢው የእስልምና ወሳኝና የተሟላ የገበያ ማዕከል ሆና ቆይታለች ይላል፡፡

ሐረር ራሱን የቻለ ልዩ ባህል ያላትና በአንድ ከተማ ሊኖር ሕዝብ የባህል ውጤት ናት፡፡ ይህንን ዕውነት የሚያረጋግጥልንም የሐረሪ ሕዝብ የራሱን ማንነት የሚገልጽባት መሆኑ ነው፡፡ የሐረሪ ሕዝብ ሐረርን የሚገልጹት “ጌይ” በማለት ሲሆን ይህም የአማርኛ ቀጥተኛ ትርጉም ከተማ ማለት ነው፡፡ እራሳቸውን ደግሞ “ጌይ ኡሱዕ” በማለት ይገልፃሉ፡፡ ትርጉሙ የከተማው ሕዝብ ማለት ነው፡፡ በዚሁ ሁኔታ ባህላቸው “ጌይ” ማለት የከተማው ባህል ወይም ወግ ብለው ይጠሩታል፡፡ ራሱን የቻለና የኢትዮጵያ ሴሜቲክ ቋንቋዎች አካል የሆነውን ቋንቋቸው “ጌይ ሲናን” ይባላል፡፡ የከተማው ቋንቋ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሐረር የአንድን ሙስሊም ከተማ የአመሰራረት ፈርና በሙስሊም ሕዝብ አማካኝነት ለዚህ ዕድገት የበቃች በመሆኗ በማንኛውም መመዘኛ ብትታይ ሁሉንም የምታሟላ መሆኗ ግልፅ ነው፡፡

እያንዳንዱ የሐረር አካባቢዎች የተመሠረቱት ተጎራባች በሆኑ የተለየ ስያሜ ባላቸው ክፍሎች ወይም በነጠላው አጠራር “ቶያ” በተባለው ስሪት ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ክፍሎች እራሳቸውን የቻሉ አካላት ሳይሆኑ ስማቸውን ባገኙት ወይም ያኙበትን አካል ማዕከል በማድረግ ዙሪያውን ከበውት ይገኛሉ፡፡ በሐረር ውስጥ ብቻ የሚሆኑ ቶያዎች ተቆጥረዋል፡፡ የተሰየሙት ቦታዎች በሌሎችም የሙስሊም ከተሞች ሁሉ እንደ ጂኦግራፊያዊ /መልክዓ ምድር/ ስያሜዎች ሆነው ሲያገለግሉ፣ የቤት ቁጥር በሌለበትና የጎዳናዎችም ሆነ የጠባብ መንገዶች ስያሜ በሌለበት አከባቢ እጅግ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

ሐረር ቀደም ሲል ከነበሩት የሙስሊም ከተሞች ባህሪያት እየተለ መሄዱ ነው፡፡ በሐረር ውስጥ የሚገኙት ዞኖችም ሆኑ ተጎራባች “ቶያዎች” ከሌሎቹ በልምድ ከተዋቀሩት አካላት የተነጠሉና ሕጋዊ አወቃቀር የሌላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰፈር በማህበራዊ ይዞታው ራሱን የቻለ አካል የመሆኑ ጽንሰ ሐሳብ በተለያዩ የሙስሊም ጥናቶች ላይ የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡ አርተር ራንቦድ ይህንን እውነታ በታተመው መጽሐፉ ግለሰብ፣ ታዛዥነቱ መጀመሪያ ለቤተሰቡ ሲሆን ከዚያ ቀጥሎ ለሚኖርበት ቶያ ውስጥ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚያም ለሚከተሉት የሃይማኖት ተቋም ነው፡፡ የተለያዩ ዞን ነዋሪዎች በተለይ የሚገኙት በገበያ ቦታና መስጊድ አካባቢ ነው፡፡

በ1960 እ.ኤ.አ ጥናቱ ያሳተመው በጆበርግ ይህ ጽንሰ ሐሳብ ከኢንዱስትሪዎች መስፋፋት በፊት የተቆረቆሩ ወይም የተመሠረቱ ከተሞችን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑን ሲገልጽ፡፡ በነገድ መለያየት በብዛት የተንሰራፋው ከኢንዱስትሪዎች መስፋፋት በፊት በተመሰረቱ ከተሞች ውስጥ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ተከፋፍለው የሚኖሩት ነገዶችም ራሳቸውን ችለው ሊኖሩ የሚችሉ አካላት ናቸው፡፡ በማለት ያስረዳል፡፡

## ትምህርት በዓረብኛ ቋንቋና በሐረሪ

እርግጥ ነው እስልምና ወደ ኢትዮጵያ ደጋማ ስፍራዎች መቼ ዘለቆ እንደገባ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ቸሩሊ ከ1230-1289 በምሥራቅ ሸዋ አካባቢ የእስላም መንግስት ተመስርቶ እንደነበረ የሚገልፅ ጥንታዊ ጽሁፍ አሳትሟል፡፡ ቼሩሊ ውድ ኢብን ሒሻም አለማኽዙሚ የተባለውን የታሪክ ጸሐፊ ጠቅሶ እንዳሰፈረውም በ13ኛው ክፍለ ዘመን አነስተኛ የእስላም መንግስታት በምሥራቅና በማዕከላዊው ኢትዮጵያ ውስጥ ተቋቁመው ነበር፡፡ ይህ ዘመን የአካባቢው ሕዝቦች እርስ በርሳቸው በሚፋለሙበት ከዚያ ቅራኔ በመለስ በክርስቲያን የኢትዮጵያ ዘውዳዊ መንግስት ጋር የያማቋረጥ ይዋጉ የነበሩበት ክፍለ ዘመን ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሐረሪ የእስልምና ማዕከል ሆና ብቅ ያለች ሲሆን ለ3 ዘመናት በተደረገው ያልተቋረጠ ጦርነትም መሪዋ ኢማም አሕመድ ግራኝ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ደጋማ ግዛት ለመያዝ በቅቶ ነበር፡፡ ዳሩ ብን በፖርቱጋሎች ረዳትነት በክርስቲያኑ መንግስት ለመሸነፍ ችሏል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያኑ ወታደራዊ ኃይል የምታሰጋ ባትሆንም ሰላማዊ በሆነ መንገድ እስልምና እምነት

መስፋፋቱን እንዲቀጥል አስችላለች፡፡ ኢማሙን የተካው አሚር ኑር ከተሸነፈ ወዲህ የፖለቲካ ውዥንብሩ በሐረር ውስጥ ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል ቀጥሏል፡፡ ሐረር ተመልሳ የመናገሻ ከተማ ሆና ማገልገል የጀመረችው በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መካከል ላይ የአሊ ዳውድ ዘውዳዊ መንግስት ከተመሠረተ በኂላ ነው፡፡ እዚህ ላይ ለመጥቀስ የተፈለገው ዐብይ ጉዳይ ግን ስለ እስልምና አመጣጥም ሆነ ስለ እስላማዊ መንግስት አመሠራረት ሳይሆን ከዚህ ዘመን ጀምሮ ትምህርት መስፋፋት እንደተጀመረ ለመጠቆም ነው፡፡

እያንዳንዱ የታወቀ ሼኽም የእስልምና እምነትን በጠዋትና ማታ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ "ከቢር ጋር" ማለትም "የከቢሮች ቤት" በሁሉም ዕድሜ ደረጃ በተለይም ከታዳጊ ወጣትነት ዕድሜ ካለፉ ወንዶች ሁሉ ክፍት ሲሆኑ አብዛኞቹ እንደ "ሙሰተሚ" ማለትም እንደ አድማጭ ትምህርቱን በርቀት ለመከታተል ይችሉ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መስጊዶች እንደፀሎት ማድረሻና መማሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜም በግንብ በታጠረችው ሐረር ከተማ ውስጥ ሰማንያ ሁለት መስጊዶች አሉ፡፡

የመስጊዶቹ በዚህ ያህል መጠን መገኘት የእስልምና መሠረታዊ እውቀት በጽንሰ ሐሳብም ሆነ በተግባር እንዲሰራጭ አስችሎታል፡፡ እያንዳንዱ በመስጊዱ አጠገብ የሚኖር ወንድም ቢያንስ በጠዋቱና በማታው ፀሎት ወደ መስጊድ መሄድና ጸሎቱን ማድረስ ይጠበቅበታል፡፡

ሐረር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የእስልምና ሃይማኖት መማሪያ ማዕከል ሆና ቆይታለች፡፡ " ጣሊበል ዒልም" ማለትም "እውቀት ፈላጊዎች" ከመላው የአገሪቱ ማዕዘናት ይመጡ ነበር፡፡ በዚህም ሳቢያ "ወቅፍ"፣ "ዘካት" እና በየቀኑ "ሰደቃ" እየተደረገ ትምህርቱ ያለማቋረጥ እንዲቀጥል ይደረግ ነበር፡፡ ከአነሳሱ በሐረር የሐነፊ /የእስልምና ዓይነት/ የነበረ ቢሆንም አሚር ልጁን ለመዳር ሲል ወደ ሽፊዒ /ሌላው የእስልምና ዓይነት/ እንዲዛወር አደረገ፡፡

በዚህ ለየት ያለ ዘመን ትምህርት መጀመሩን የሚያረጋግጡ በጣም ጠቃሚ የሆኑ የጽሑፍ መረጃዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ጽሑፎች በአብዛኛው የሚገኙት በግለሰቦች እጅ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

የሐረሪዎች ወደ ድሬደዋ፣ አዲስ አበባና ወደ ሌሎች ስፍራዎች መሰደድም ለመጻሕፍቱ መበተን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የሚቀጥለው ማስታወሻም የተጠናቀረው ዕድሜያቸው ካለፉት ሦስት ምዕተ ዓመታት ጀምሮ ከተጻፉ 300 ጽሑፎች ከተነበቡ በኋላ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና ከነዚህ መጻህፍት መካል ጥቂቶቹ ከሦስተኛው መቶ ቀደም ብሎ የተጻፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በሐገር ውስጥ ይጻፉ ከውጭ ይምጡ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ለማንኛውም የተገኙት ጽሑፎች በአብዛኛው በዓረብኛ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን በሐረሪ ቋነቋ የተደረሱም ይገኛሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው እስላማዊ ባህል በርእስ ከተማዋ በሐረር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደ ነበር መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ ቸሩሊ ያገኘው "ኪታብ አልፈራኢድ" የተባለውና በሐረሪ ቋንቋ የተፃፈው መጽሐፍ የእስልምና ሃይማኖት ዋነኛ ትምህርት ሞራል ምን እንደሆነ በቀላል ዘዴ ያስረዳል፡፡ ይህም መጽሐፍ በአንድ በኩል በመጻፉ በወቅቱ መሠረታዊ የእስልምና እምነት ተብሎ ይሰጥ የነበረው ትምህርት ምን እንደሆነ ሲገልፅ በሌላ በኩል ደግሞ በራሳቸው ቋንቋ መጠቀማቸው የዓረብኛ ቋንቋ በሐረሪ ውስጥ እንደ እስላም ቋንቋ በስፋት ይሠራበት እንዳልነበረ ያሳያል፡፡

ቼሩሊ እንደሚገምተው ከሆነ የእስልምና ሐይማኖት በሚሰራጭበት በተወሰነ ወቅት የወንድማማችነት መንፈስ አብሮ ይሰበክ ነበር፡፡ ይህ ግምት ግን ትክክል ነው፡፡ ትክክል በመሆኑም ዛሬም ቢሆን የሙስሊም ወንድማማችነት መንፈስ በተለይም ቀድሪያ የተባለው በእምነት ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የፀሎት ስብሰባዎች ሳያቋርጡ ይካሄዳሉ፣ በመሰብሰብ ስፍራዎች የሚጠቀሙባቸው መጻሕፍትም የአማኞችን ሃይማኖት ግንዛቤ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

እንደመ ውሊድ፣ ሰለዋት፣ ጸሎት፣ መወድስ፣ መንዙማ ያሉት በግጥም የተደረሱ መጻሕፍት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል መንዙማ ሲባሉ በሐረር ግን ዚክሪ ተብለው እንደሚጠሩ ይታወቃል፡፡ የሐረሪዎቹ መፃህፍት በዓረብኛና በሐረሪ ቋንቋ እንደገና በጥንቃቄ ተዘጋጅቷል፡፡

ባለፉት ጥቂት ክፍለ ዘመናት የዓረብኛ ቋንቋ ከሐረሪ ቋንቋና ባህል አኳያ በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ቸሩሊ እንደሚለው የመጀመሪያዎቹ ዓይነት ጽሑፎች ምሁራን በዓረብኛ ቋንቋ የፃፏቸው የሃይማኖት፤ የሳይንስ፣ የሕክምና፤ የጆኦሜትሪ ወ.ዘ.ተ ሲሆኑ እነዚህ

መፅሀፍት ሁሉም ሊባል በሚችል ሁኔታ የተጻፉት በዓረቦች ይህም ካልሆነ ሐረር ውስጥ የተገለበጡ እንኳን ቢሆኑ በማንኛውም መለኪያ በሀገሩ ሰዎች ሊደርሱ የማይችሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛው ዓይነት የሃይማኖት ጽሁፎች ማለትም የዚክር ባህርይ ያላቸውና መሠረታዊ የእስልምና ሃይማትን አቅጣጫ የሚያስይዙ ናቸው፡፡ እነዚህንም ጽሑፎች አንድም በዓረብኛ ወይም በሐረሪ የተጻፉ ናቸው፡፡ ከነዚህም ጽሑፎች መካከል በርካታ ቅጅዎች ያሉት "ኪታብ አል ፈራዲ" የተባለው ጽሁፍ ጠቃሚ ስፍራ ይዞ ይገኛል፡፡

በመሠረቱ የዓረብኛና የሐረሪ ቋንቋዎች የእስልምና ትምህርት በማስፋፋት ረገድ የሚጫወቱት ሚና በዋዛ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሐረሪ ቋንቋ ከዓረብኛው ቋንቋ ጋር ጐን ለጐን ሲፃፍ ዓረብኛው ግን ለብቻው ምሁራኑ ብቻ ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡

ዓረብኛ ቋንቋ ከፍ ያለ ደረጃ ያለው የምሁራን ቋንቋ ሆኖ በጥቅም ላይ ይዋል እንጂ የግጥም ስነ ጽሑፍ በዚህ በሕብረተሰቡ የተለመደ ነበር፡፡በዚህ ምክንያት የእነ ኢብን ማሊክ "ዳላኢል አል ኸይራት" ያሉት በዓረብ ደራሲያን የተጻፉ ከፍተኛ የስነጽሁፍ ደረጃ ያላቸው ጽሁፎች በሐረሪ ውስጥ መገኘታቸው የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም፡፡
ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳን እስካሁን የተገኙት ማስረጃዎች በጣም ጥቂት ቢሆኑም የሐረሪ ምሁራን በዓረብ ደራሲያን የተጻፉትን መጻሕፍት ማንበብ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በዓረብኛ ጽፈዋል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እስልምና ሃይማኖት ምሁራን በሐረሪና በዓረብኛ ቋንቋ ከደረሷቸው የዚክሪ ጽሑፎች መካከል የአካባቢው ቅዱሳን ስምን ለማወደስ የተጻፉት ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹን በሀገር ውስጥ ደራሲያን የተጻፉ ናቸው ብሎ መለየት ያስቸግራል፡፡ ሆኖም ቋንቋውን የሚናገሩ ሊቃውንት ትክክል ይሆናሉ በሚል ግምት በሰዋሰዋዊ ስህተታቸው ምክንያት አንዳንዶቹ በሀገር ውስጥ ደራሲያን እንደተጻፉ መለየት ይቻል ይሆናል፡፡

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ተጨባጭ መረጃዎች በተጨማሪ ዓረብኛ ቋንቋ በቃዲ ፍርድ ቤት የሐረር አስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ያገለግል እንደነበር የሚያረጋግጥ ግልጽ ማስረጃ አለ፡፡ በዚህ መሠረት ቁጥራቸው ጥቂት ያልሆኑ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በዓረብኛ ቋንቋ ተጽፈው ይገኛሉ፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖ በዚህ እንዳለ በዓረብኛ ቋንቋ የጻፉት ሐረሪ ደራሲዎች ማንነት ያልታወቀ ከመሆኑም በላይ እስካሁን የተገኙት መጻሕፍት ቢሆኑ በሚገባ ተዳሰዋል ወይም ተተንትነዋል ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፡፡ በመጠኑ የታዩት መጻህፍት ይዘት ግን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

1. አንዳንድ ቀላል የሆኑ ጽሁፎችን በዓረብኛ ከመጻፍ ይልቅ በሐረሪ ቋንቋ መጻፍ ተመራጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም በሀገር ውስጥ ቋንቋ በተደረሱት ጽሁፎች ውስጥ ምን ያህል ዓረብኛ እንደተካተተ መመርመር የሚያስፈልግ ሲሆን በፍ ጥነት በጨረፍታ በሚደረግ ትንታኔ እንኳን ይኸው ዓረብኛ ቋንቋ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለተወሰነ ሐሳብ መግለጫ ጥቅም ላይ እንደዋለ መረዳት ይቻላል፡፡

እርግጥ እንደ "ቢስሚላህ" እንደ "ሸሃዳ" እና "ታሕሚድ" ያሉት ትምህርቶች የተጻፉት በዓረብኛ ነው፡፡ በነዚህ ትምህርቶች ውስጥ እንደ "ኩም ጊር" ማለት አንድ ሺ ጊዜ እና " አልፊ ኩም ጊር" ማለትም ሚሊዮን ጊዜ አንብባቸው የሚል ትዕዛዝ በሐረሪ ቋንቋ ተጽፎባቸዋል፡፡ "ተስቢህም ቢሆን የተፃፈው በዓረብኛ ነው፡፡ ነገር ግን ሰለዋቱ እንዴት እንደሚደረግና እንደሚፀለይ በሐረር ቋንቋ መመሪያው ተጽፏል፡፡ "ተስቢህ" የተጻፈ በዓረብኛ ነው፡፡ ይሁንና ማንም ሰው እንደሚጠብቀው ሁሉ እንዲህ ያለው የሐረሪ ቋንቋ በርካታ ከዓረብ በውሰት የተወሰዱ ቃላት እንደሚኖርበት የታወቀ ነው፡፡

ሌላው ጽሁፍ "ሙስጣፋ" ሲሆን ይህ መጽሐፍ ቀደም ሲል ከተገለፀው በመጠን አነስትኛ ሲሆን በእድሜም ዘግይቶ የተጻፈ ነው፡፡ ይሁንና የቋንቋው ስርጭት ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡

2. ሦስተኛው ከሰማኒያ መስመሮች ትንሽ በለጥ የሚል ሲሆን የፃ ፊውም ሰዓድ ሰዒድ ሚሂ ነው፡፡ ግጥሙ የሚጀምረው "ቢስ ሚላህ" ካለ በኋላ ሲሆን ከሱም በታች ከ "ሱረት አል ኢኽላስ" እና ታህሊል ሁለት መስመሮች በዓረብኛ ተጽፈዋል፡፡ ይህም

ሆኖ የሁለቱ ሱራ መጨረሻ ግጥሞች በግንባር ቀደምትነት የተተረጐሙ ሲሆን ከነሱ ቀጥሎ ያሉት መስመሮች የተጻፉት በሐረሪ ቋንቋ ነው፡፡ በሐረሪ ቋንቋ በተጻፈው ግጥም ውስጥ ግን አልፎ አልፎ የተለመዱት የዓረብኛ ሐረጐች መምጣታ ቸው አልቀረም፡፡ "ታሕሚድም" በግጥሙ መጨረሻ ላይ ተጨ ምሯል፡፡ ስለዚህ በዚህ ግጥም ምን ያህል የዓረብኛ ቋንቋ እንደ ገባ በምሳሌነት ለማሳየት ይቻል ዘንድ ሁለቱን የመጨረሻ መስ መሮች እንመልከታቸው፡፡

"ወኢን ሚነኩም ኢላ ዋሪዱሃ ዓእዛቡሃ ዘይጊረታም ኢላ" ካናንተ አንድም እንኳን ቢሆን የማይደርስበት የለም፣ ከናንተ እንኳን ቢሆን የሲኦል ቅሰጣት የማያገኝ አይኖርም፡፡

ከዓረብኛ በውሰት ዘወትር የሚወሰዱ ቃላት አብዛኛውን ጊዜ ወዳልተለመደ የቋንቋ መደባለቅ ይመራሉ፡፡ ለምሳሌ የሚቀጥለው መስመር የመጀመሪያ ግማሽ በዓረብኛ ሐረግ፣ ሁለተኛው ደግሞ የሐረሪ ቋንቋ አንድ ቃል ይዟል፡፡ መስመሩ እንዳለ የተጻፈው ግን በዓረብኛ አይደለም ፡፡ ለምሳሌ እንዲህ ይነበባል፡፡

"አንታ ኢዚ ወአንተ ሒዚ የቃነ መሐመድ ፈድሉካ"

ትርጉሙ "አንተ የኔ ታላቅ ክብር የኔ ማራኪ ሙሐመድ ሆይ ለሀብታችን ያንተ መትረፍረፍ ያንተ ሙላት በቂ ነው" የሚል ነው፡፡

በዚህ መሠረት በተጠቀሱትም ሆነ በሌሎች ተመሳሳይ ጽሑፎች በዓረብኛ አጠቃቀም የተወሰነ ቅርፅ እንዲኖረ ግልጽ ነው፡፡ ይህም እንደ ቢስሚላ፣ሸሃዳ፣ ተሰሊያ ወ.ዘ.ተ ያሉትን እንዲሁም ሌሎች ከሙስሊም ጋር አብረው የሚሄዱ መሠረታዊ የሆኑ ቃላትንና ሐረጐችን ሆነ አልሆነ ማወቅ አለበት፡፡ ይህም የተደረገው በአጋጣሚ አይደለም፡፡ በመሠረቱ እነዚህን ጽሁፎች በዓረብኛ ለመጠቀም የተፈለገበት መሠረታዊ ምክንያት ለመግባባትና ለማስተማር ስለተፈለገ ብቻ አይደለም ነገር ግን የሃይማኖቱን መሠረታዊ ግንዛቤ እንዲያውቁት፣ ደረጃ በደረጃም በአማኙ አእምሮ እንዲቀረጽ፣ በመጨረሻ የጠለቀ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡

1. ሌላው ለየት ያለ ምሳሌ አብዱልማሊክ የጻፈው ዚክር ነው፡፡ይኸው 600 ያህል መስመሮች ያሉት ሲሆን የተጻፈ ውም ነብዩ መሀመድን (የአላህ ሰላት በእሳቸው ይውረድ) ለማወደስ ነው፡፡ ያለምንም ጥርጥር ግጥሙ የተደረሰው በተመሳሳይ የዓረብ ድርሰቶች አነሳሽነት እንደሆነ ለመረ ዳት ይቻላል፡፡ ይህንን ግጥም ለመድረስ ስሜት ከሚያነሳ ሱት ጽሁፎች ውስጥ በሐረር ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ውለው የነበሩትና የታወቁት የቡሰትሪ "ቢርዳ"፣ የወርቅ "አልጠቃሲዳ አልዊትሪያ" ይገኙበታል፡፡ የአብዱልማሊክ ጽሑፍ "ቃሲዳ" ተብለው የሚታወቁትና ከቆዩት የሐረሪ ግጥሞች አንዱ ነው፡፡ የቤት አመታቱ በተመሳሳይ ፊደል ላይ የተመሠረተ ሲሆን መስመሩ ግን የተለያዩ ቃላት እን ደገለጽነው ቋንቋ በማቀላቀል ይለወጣል፡፡ ሲቀላቀልም የዓ ረብኛና የሐረሪው ቃል አጠቃቀም እንደ ሁኔታው ሊለ ዋወጥ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ጉልቶ ሌላው ቀጭጮ የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡ ብዙውን ጊዜ ዘዴው ዓረብኛ ወይም ሐረሪኛ ነው ተብሎ የሚለይ ሳይሆን እን ዲያው በደፈናው የሁለቱ ቋንቋዎች ዘዴ እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድ ነው፡፡

## 8.2 የስነ-ጽሁፍ እድገት በሐረር

### 8.2.1 የስነፅሑፍ ምንጭና መሰረታዊ አሳቤዎች

"ስነጽሑፍ የሚለው ቃል በጥሬ ትርጉም ስንወስደው መፃፍ በመዳፍ እንዲቻል በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት መጻህፍት እውቀትን አንድን ሐሳብ በዝርው በግጥም፤ በቅኔ መግለጽ ከንግግር ቋንቋ የተለየ ሰዋሰዋዊ ህጉን ጠብቆ መፃፍ የታተመ መጻህፍትን፣ ቀላጤዎችን፣ በራሪ ጽሑፎችን፣ መጽሔቶችን እየመረመረ የአጻጻፍ ዘይቤያቸውን የሚያጠና መስክ ነው። ስነ ጽሁፍ በተጨማሪ ስነቃልን፤ ትውፊት፤ ጥቅሶች፤ አባባሎችንና ምሳሌዎችን ከስነ-ጽሑፍ ይዘታቸው ጥበባቸው ጥልቀታቸው ፍልስፍናቸው የሚያጠናት መስክ ነው። ለምሳሌ አንድ ዜና መዋእል በአንድ ወቅት የተጻፈ ታሪክ እንኳን ቢሆን የቋንቋ አጠቃቀሙ የአንዱ ዘመን የአጻጻፍ ስልት ከሌላው ዘመን የአፃፃፍ ስልት በምን እንደሚለይ ይመረምራል።

ከዚህ አኳያ የሐረር ስነ-ጽሑፍ እድገትን እስልምና ከተስፋፋበት ጊዜ ተነስተን እንኳን ብንመረምረው የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን አልፎ እንደመጣ በህትመት ደረጃ የሚጠቀሱት ስራዎች በጣም ጥቂት ቢሆኑም በሌሎች የእስልምና እምነት ከተስፋፋባቸው አገሮች ጋር አያይዘን ልንመለከተው እንችላልን። በእርግጥም ባለፉት አንድ ሺ ዓመታት ሐረር በስነ-ጽሁፍ ረገድ የተራመደችበት ጉዳናዎች ስንመለከት በመጠኑም ቢሆን ዓረቡን አለም የሚያንጸባርቅ የስነጽሑፍ ባህርይ እንዳላት እንረዳለን ስለሆነም ወደ ሐረሪዎች ስነጽሑፍ ከመግባታችን በፊት የዓረቡን ዓለም ስነ-ጽሁፍ በመጠኑም ቢሆን እንቃኛለን።

በዓረቡ ዓለም ከእስልምና እምነት መስፋፋት በፊት ስለአረብኛ ስነ-ጽሁፍ እምብዛም የሚታወቅ ነገር አልነበረም ቢኖርም አንዳንድ ተረት ተረቶች፤ አፈታሪኮች የፍቅር ግጥሞችና የመሳሰሉት ነበሩ ከሰባተኛው እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ግን የስነ-ፅሁፍ መስኩ በርካታ የሃይማኖት መወድሶች፣ ታሪኮች የማስተማሪያ ጽሑፎች አስተያየቶች ፋብላዎች ተጽፈው ለንባብ በቅልቷ። እንደ አብዱላሂ ኢካን አል መቃፋ ያሉት ደራሲያን ኪታብ ኸሊላህ ታሪክ ጻፉ አብን ኢስሐቅ ደግሞ ሲረቱል ረሱል አላህ ማለትም የፈጣሪ መልእክተኛው ሕይወት በሚል ርእስ ጽፎ

ዝናን አገኙ፡፡ የኻሊፍ ሐሩን አረሺድ ፐርሺያዊ ወዳጁ የነበረው አቡናዋስ የተባለው ዝነኛ የስነጽሁፍ ሰውም ቃሲድ ቅርጽን የተከተለ በግጥም መልክ የተጻፉ ሥራዎች ነበሩት፡፡ ግጥሙ ከ60-100 መስመሮች ያህል ሊኖሩት ይችላሉ እንደ አልጃሒዝ ያሉ እውቅ ሰዎች ደግሞ “አደብ” የተሰኘ ስነ-ጽሁፍ ሕልውና እንዲያገኝ አድርገው ነበር፡፡ ከአደብ ስነ-ጽሑፎች መካከል ኪታብ አል-በያን የማረጋገጫ መፅሐፍና ኪታብ አል-ሐያውያን የእንሰሳት መጻሕፍት ይገኙበታል፡፡ የሱፊዝ ፍልስፍና ሲነሳ አል-ሑሴይን ኢብን መንሱር አልሐላጁ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል፡፡ የዚህ ሰው ፍልስፍና የተሞላበት ጽሑፍ በፈጣሪና በሰው መካከል ያለድልድይ ነው ከሚል የሚነሳ ሲሆን በእምነቱም ላይ የራሱ የሆነ ችግር ነበረበት፡፡ አል-ቃለባዲ የተባለው የአልሐጁ ተከታይም ዩሱፍን ፍልስፍና ለምዕራቡ ዓለም አስፋፍቷል፡፡

## 8.2.2 መርህ ምሶሶዎችና መመሪያዎች

አብል ሐሰን መሐመድ ኢብን አሕመድ አል ፋሪስ የተባለ ሰው ስለ ሱፊዝም ፍልስፍና ሲገልጹ የሱፊዝም ፍልስፍና በአስር ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው አንድነትን መለየት፤ ሁለተኛው የሚደመጥ ነገርን መረዳት፤ ሦስተኛው ጥሩ ተከታይነት አራተኛው ምርጫን መምረጥ አምስተኛው የሚመርጡትን ማወቅ ስድስተኛው ለስሜት ፈጣን መሆን ሰባተኛው የሐሳብ መከሰት ወይም መታየት ስምንተኛው ብዙ መጓዝ ዘጠነኛ ያገኙትን መጠቀም አስረኛው አናስቀምጥ ሲሉ መቃወም ብለዋል፡፡
ይህንን ጠለቅ ያለ ትርጉም ያለው ፍልስፍና

1/ አንድነት መለየት ማለት ምንም ዓይነት አስተሳሰብና እውቀት ፈጣሪን ማመን የሚቃረን መሆን የለበትም

2/ ረቂቅ የሆኑትን ሚስጥሮች በመማር ብቻ ሳይሆን ሳይማሩም ለማወቅ መቻል

3/ አውቆ መከተልና አስፈላጊ መሆን

4/ ትክክለኛ ምርጫ እንዲኖር ሌሎች የመረጡትን መምረጥ ወይም ሌሎችን ማስተማር ምርጫቸውን መረዳት

5/ የፈጣሪን ቃል ለመስማት መሰናክል ከሚሆኑ ስሜትን አደናቃፊ ነገሮች ፈጥኖ መውጣት

6/ በሐሳብ የሚታዩትን ነገሮች ሁሉ አውጥቶና አውርዶ የፈጣሪ

ያልሆነውን ሐሳብ መተው

7/ ትክክለኛውን እምነት ለመያዝ ተዘዋውሮ ማየት

8/ በፈጣሪ አምኖ መቀመጥ

9/ እውቀትን ማካፈል ብለን በጥቅሉ ልንተረጉመው እንችላለን፡፡

በአረቡ የስነ-ጽሁፍ ዓለም ከፍተኛ ቦታ አለው የሚባለው አል ሙታነቢ የተባለውና ከ915-965 የነበረ ሶሪያዊ ነው፡፡ አል ሙተነቢ ግብጽ ይገዛ የነበረው አብድልሚስክ ካፉር የተባለ ሐበሻ ንጉስ ወዳጁም ነበረ፡፡ በረቀቀ የስነ-ጽሁፍ ሥራው የሚታወቀው አል ሙተነቢ ከግብፅ ወደ ኢራቅ ሄዶ በርካታ ግጥሞችን ደርሷል፡፡

የስነ-ጽሁፍ ሰዎች ሌላ ኡመር ኻያም አል-መዓሪ አልሐረር፤ ኢብን ባቱታ አልኻሊድ ያሉ ነበሩ፡፡ ሐጂ ኸሊፋ የተባለው ቱርካዊ ደራሲም በ1630ዎቹ ኻሺፍ አል ዙኑን ጥንካሬን ለማስወገድ ሚዛን አልቅ የሐቅ ሚዛን የተባሉት መጻህፍት ለንባብ አብቅቷል፡፡ የሌሎችም ዓረቦች፤ ቱርኮች፤ ስፔይናውያን አፍሪካውያን የስን-ጽሁፍ ሥራዎች ተሰባስበው ታትመዋል፡፡

## 8.3 የሀረሪ ትውፊት ፎክሎር

ከዚህ አንፃር በመነሳት የሐረሪዎችን ስነ-ጽሁፍ መመርመር እንችላለን፡

1. ተረቶች
2. የሰርግ ግጥሞች
3. ፈጣሪን የሃይማኖት አባቶች የሚያወድሱበት ግጥሞች፤
4. የሕይወት ታሪኮች፤
5. የሒሳብ ገቢና ወጪ ዝርዝሮች፤
6. የአስተዳደር ፋይሎች
7. የሐይማኖት መጻህፍት
8. ሌሎች የሕጻናት ጨዋታዎች
9. ምሳሌያዊ አገላለጽዎች
10. ጥቅሶችን፤
11. በመፃህፍት ህግጋት የተጻፉትን
12. ደብዳቤዎችን ወዘተ…

ይሁንና ሁሉንም የስነ-ጽሁፍ ዘርፍ በዚህ አጭር ታሪክ ውስጥ ማካተት ስለማይቻል ምሳሌያዊ አባባሎችን እንዲሁም የልጆች ጨዋታዎችን በጥቂቱ እንመልከት፡፡

## 8.3.1 ተረትና ምሳሌዎች

የሐረሪዎች ተረትና ምሳሌዎች በአመዛኙ ከዓረብኛ ስነ-ጽሁፍ በተለይም ከእስልምናው ጋር የተያያዙ ሲሆን በሐረሪኛው መኽማኻ በዓረብኛው “ማቅማህ” መባላቸው እንደማስረጃ ነው፡፡ ይሁንና ማቅማህ ተረትና ምሳሌዎችን ሰምና ወርቆችን አጫጭር ታሪኮች በግጥምና በዝርዝር የሚተላለፉ ሐሳቦችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ከሚጠቀሱት የዓረብ ዓለም የስነ-ጽሁፍ ሰዎች ኢራቃዊው አልሐረሪ አል መደሐኒ ናቸው፡፡ በሐረሪዎች ዘንድ ውሪዮው ውሪ ማለት እንቆቅልሽ ጥቅሶች በዚህ ይጠቃለላሉ፡፡ በተረትና ምሳሌ ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

1. ደግ ሰው ሌላውን መጥፎ ሰው ራሱን አስቸገረ

   የገሲ ዚኻና ሩህዞው ታብ አሻ

2. ያገኘና የሞተ ዘመድ አያጣም

   ዛገኛዋ ዚሞታ አህሊ ዪቀብጡሜል

3. ጋብቻ በጨለማ እንደተወረወረ ድንጋይ አጋጣሚ ነው

   ሙራድ ነሲብ ኢንታ ጨልመቤ ዚገኞ ኡን ኢንታ

4. የወደደች አይን እራሷ ትናገራለች

   ዞደድቲ ኢን ሩሕዜሌ ታሲናት

5. ወደ ቤት የሚገባው በበሩ ብቻ ነው

   ጋር ጋምበሪ ገረቤ ይቦአሐል

## 8.3.2 የልጆች ጨዋታዎችና በዘፈንና ያለ ዘፈን የሚገልጹ ግጥሞች ጨዋታ

የሐረር ሕፃናት በሰፈራቸው በትምህርት ቤታቸው በመስክ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች የሚጫወቱበት ጨዋታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ በእንቅስቃሴዎች ከታጀቡ መካከል በዘፈንና ያለዘፈን የሚገለፁ ግጥሞ

| በሐረሪኛ | ትርጉም |
|---|---|
| አይዮ ዋህሬ ዲሽካ | እናቴ ጨረቃዬ ቁጭ በይልኝ |
| ሉንቃን ኢቀለሽካ ዲሽካ | ቆሎ እቆላልሁኝ ቁጭ በይልኝ |
| ሰሚን ኢመለሽካ ዲሽካ | ሰማይእሞላልሻለሁ ቁጭ በይልኝ |
| አዬ ፈጣ ሐረር | እናቴ በሐረር ፈታይ ናት |
| አው ላዚም አብዶሽ | አባቴ የመስጊድ አለቃ ነው |

ልጆች ከስምንት በላይ ሆነው እጅ ለእጅ ተያይዘው ይቆማሉ፡፡ በመካከላቸውም አንድ ልጅ ይቆማል፡፡ ይህም ልጅ በቤተሰብ በሕብረተሰብ እንክብካቤ የተያዘ ጠላት ቢፈልገው አሳልፈው የማይሰጡትና አንድነታቸው አጠናክረው የሚጠብቁ መሆኑን በተምሳሌትነት ይገልፃል፡፡ እጅ ለእጅ ከተያያዙት ልጆች የተከበበው ህፃን ሌላ ልጅ ሕፃኑን ከዚህም ሕብረተሰቡን መንጭቆ ለመውሰድ የሚፈልግ ሰውን የሚወክል ተምሳሌት በመሆን በሚከተለው ግጥም የተያያዘውን እጅ እየተዘዋወረ ለመበጠስና ልጁን ለመያዝ ይሞክራል ልጆቹም ግጥሙን ይቀበሉታል፡፡

## ግርዛት

የበሐረሪ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ይገረዛሉ፡፡ በተለይም ወንዶች ከተወለዱበት እለት ከሦስት እስከ ሰባተኛው ቀን ባለው ጊዜ ቤተ ዘመድ በተሰበሰበበት በሚከተለው ዘፈንና ግጥም እንዲሁም በጭፈራ ይገረዛሉ፡፡በዚህ የቀረበው ግጥም ዘፈኑ በተደጋጋ የሚቀጥል አጭር ስንኝ ነው፡፡

| **በሐረሪኛ** | **ትርጉም** |
| --- | --- |
| አብሱም ወናጉም | አንበሳ ገራዥ |
| ወናጕው አይቲዳርበኽ | አንበሳው እንዳይጕዳብህ |
| ኩም ከሃሳ ሐልበኽ | ከጕዳሽው ካሳ ትከፍላለህ |

በመጨረሻም ለዚህ ያደረሰን አምላክ ሰርጉንም ያብላን ብለው ምኞታቸውን ይገልፃሉ፡፡

ከነዚህም በተጨማሪ የቁርአን ቤት መወድሶች የሠርግ ዘፈን ግጥሞች አሉ ይሁንና ከጥንት ጀምሮ የነበሩት ግጥሞች ተረቶች ደብዳቤዎችና ሌሎችም የስነ-ጽሁፍ መረጃዎች የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ለመመረቂያ ማሟያም ካጠራቀማቸው በቀር ያልተሰቡ ስለሆነ በዚህ ረገድ ሰፊ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የሐረር ከተማ አወቃቀር

### 7.2 ከተማዋ የቆሻሻ ማስወገጃ፤ መስኪዶችና አድባራት

በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ለመግለጽ እንደተሞከረው ሁሉ ጀጎል ከተማ በአሚር ኑር /1570/ በግንብ ዙሪያዋን የታጠረችው የከተማዋን ሕዝብ በወቅቱ በአካበቢው ይኖሩ ከነበሩት ጦረኞች ለመከላከል እንደነበረ ልዩ ልዩ የታሪክ ማስረጃዎች ይገልጻሉ። በዚህ ምክንያት የአምስቱ በሮች ከፍተኛ ጥበቃ ይደረግላቸው የነበረ ሲሆን በሰላም ጊዜ ደግሞ አምስቱም በሮች ቀን ቀን ተከፍተው የአካባቢው ገበሬዎች የእህል ምርታቸውን በማስገባት እንደ ልብስ፣ ቅመማ ቅመሞችና ሌሎችም ሸቀጣሸቀጦችን እየሸመቱ ይወጡባቸው ነበር። በሮቹ ማታ ማታ ከመዘጋታቸው በላይ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ቀርተው ፀጥታ የሚያደፈርሱ እንዳይኖሩ ጥበቃ ይደረግ ነበር።

## የሐረር ከተማ አምስት በሮች ስም

| አቅጣጫ | በሐረርኛ | በኦሮምኛ | በዓረብኛ | በአማርኛ |
|---|---|---|---|---|
| ምስራቅ | አርጉባ በሪ | ከራኤረር ሳሄ | ባብ አረሕማ | ኤረር በር |
| ሰሜን | አሱም በሪ / ጨው በር/ | ከራ ፈላና ዘይስ አፈታል | ባብ አልፈቱህ ሰ/የድልበር/ | ፈላና በር |
| ምዕራብ | አሰማዕዲን በሪ | ከራ ሸዋ | ባብአነስር / የክርስቲያን በር ባብ አል ሐበሽ/ | ሸዋ በር |
| ደቡብ | በድሮበሪ/የሐኪሞች የጠንቋዮች በር | ከራ ቡዳዋ | ባብ አል ሐኪም /የጢቢቦች በር/ | ቡዳ በር |
| ደቡብ ምስራቅ | ሱቅጣጥ በሪ | ከራ ሶፊ | ባብ አልሰላም /የሰላም በር/ | ሰንጋ በር |

የጁገል ከተማ ከዳር ዳር በቤቶች የተሞላችና በርካታ ሕዝብ የሚኖርባት በመሆኗ ሊፈጠር የሚችለውን የጽዳት ጉድለት ለማስወገድ ልዩ ልዩ ስልቶች ተቀይሰው ነበር፡፡ ከነዚህም አንዱ ከጁገል ውጭ ያለውን የለማ እርሻ ቦታ በማይበክል ሁኔታ የተዘጋጀው የፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓት ነው፡፡ ይህ የፍሳሽ ማስወገጃ የእያንዳንዱን ሐረሪ ቤት ከጁገል ውጭ ከሚገኘው ቦይ ጋር ያገናኝ ነበር፡፡ በተጨማሪ የከተማዋ ፍሳሽ የሚወጣባቸው የግንቡ ቀዳዳዎች አንዳንዱ ሰውም እንኳን ሾልኮ ሊገባባቸው የሚችሉ ሰፋፊ ሲሆኑ “ወራባ ኑዱል” ወይም የጅብ ቀዳዳዎች ይባላሉ፡ ፡ ይህም የተባለበት የበከቱ እንስሳትን ጅቦች ገብተው የሚወስዱባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ ይሁንና ትልልቆቹ ቀዳዳዎች የተሠሩት ቆሻሻ ፍሳሽ እንዲወጣባቸው ነው? ወይስ ጅቦች እንዲገቡባቸው ነው? የሚለው ጥያቄ የታሪክ ፀሐፊዎችን ለሁለት ከፍሎ እንዲከራከሩበት አድርጓቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት “ትልልቆቹ ቀዳዳዎቹ መግቢያ እንዲሆኑ ሆን ተብለው የተሠሩ ናቸው፡፡

የሚሉ ጅቦች እንደከተማዋ ጠባቂና የክብር እንግዶች ተደርገው የሚወሰዱበት ሁኔታ ዛሬም እንዳለና ገንፎ ለነሱ ተብሎ እየተዘጋጀላቸው እንደሚመገቡ ያስረዳሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ "ጅቦች የፍሳሽ ቀዳዳዎቹን ተጠቅመው በመግባት ምግባቸውን ይለቅማሉ እንጂ እንዲስተናገዱበት ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም ባዮች ናቸው፡፡

በሐረር ከተማ ታሪክ እንደ ግብጾች፣ አማሮችን ኢጣልያውያን ያሉ የውጭ ኃይሎች ከፍተኛ የሆነ ለውጥ እንዲከሰት አድርገዋል፡፡ በዚህም መሠረት ግብፃውያን ዓረቦችንና አውሮፓውያን ጨምረው ሲገቡ የየአገራቸውን አሰራር የሚወክሉ ለውጦች አድርገዋል፡፡ አጼ ምኒልክ ወታደሮቻቸውን በጁገልና ከጁገል ውጭ ሲያሰፍሩ ብዙ የሐረር ቤቶች ፈርሰው በሌሎች ተተክተዋል፡፡ ኢጣሊያውያንም በጁገል አንደኛ መንገድ ላይ የሀገራቸውን ቤቶች የሚወክሉ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ገንብተውባቸዋል፡፡ ከጁገል ውጭ ባሉት ስፍራዎችም ግብፆች፣ ኢጣሊያውያንና ከዚያ በኋላ የመጡ ገዥዎች ጽሕፈት ቤቶቻቸውን ገንብተውባቸዋል፡፡ በአስተዳደር ሥራም ሆነ የመንገስትታቱ ሠራዊት አባላት ሆነው ወደ ሐረር ከመጡ በኋላ አብዛኞዎቹ ጀጐል ውስጥ መኖር ባይመርጡም በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሲገቡም የከተማይቱን ጥንታዊ መልክ በመቀየር አፍራሽ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህንን ለማስተካከል ብዙ ጊዜና ሀብት ይጠይቃል፡፡

በጁገል ውስጥ የተለያዩ የገበያ ስፍራዎች ሲኖሩ ከነዚህ ውስጥ "ጊዲር መጋላ" የሚባለው ጥንታዊ፣ ዋናውና ትልቁ ነው፡፡ "ጊዲር መጋላ" ትልቁ ገበያ በመሆኑ በሐረር ከተማ የሚኖሩ ሁሉ ዕቃ በመሸጥና በመግዛት ይተዳደሩበታል፡፡ በጊዲር መጋላ ዙሪያ ልዩ ልዩ ሸቀጣሸቀጦች የሚሸጡባቸው ሱቆች ስላሉ ገበያተኞች የሚፈልጉትን ይገዙባቸዋል፡፡ ሌላው ዋና ገበያ ፈረስ መጋላ ሲሆን ይህም ገበያ ጥንት የፈረሶች መሸጫ ስፍራ ነበር፡፡ "ፈረስ መጋላ" በአሁኑ ጊዜ ታክሲዎች ቆመው ተሳፋሪ የሚጠብቁበት ስፍራ ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጫት በየቀኑ ይሸጥበታል፡፡ ዛሬ ገበያው በጊዲር መጋላ በፈረስ መጋላ የተወሰነ ሲሆን ጥንት ግን ገበያው በአምስቱ በሮች አካባቢ ነበር፡፡

በገበያው በስተሰሜን አቅጣጫ “የኢጣሊያ” እየተባለች የሚታወቅ መስጊድ ሲኖር በዚህ መስጊድ አካባቢም የሙስሊም ሉካንዳ ቤቶች ይገኛሉ። እነዚህ ሉካንዳ ቤቶች በጁገል ውስጥ የሉም። ሆነ ተብለው ከጁገል ውጭ ያሉትን ሙስሊሞችን የሚያገለግሉ ሲሆን ከዚህ ሌላ በርካታ ትንንሽ ሉካንዳ ቤቶች በመላ ከተማ ውስጥ ይገኛሉ።

በሐረር ከተማ አወቃቀር ውስጥ መስጊዶች ከፍተኛ ስፍራ አልላቸው። በዚህ መሠረት በጁገል ውስጥ ብቻ 99 መስጊዶች እንዳሉ ሲነገር ኢሚል ፋቸር የተባሉ የታሪክ ፀሐፊ 88 እንዳሉ መዝግበዋል። ከ99 መስጊዶች ውስጥ 88 የቀሩበት ምክንያት የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በጥናቱ አስራ አንዱ መስጊዶች ፈርሰው ሊሆን እንደሚችል ጠቅሷል። ስለሆነም የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠፍተዋል የተባሉትን መስጊዶች መሰረት ቆፍሮ በማውጣትና በነበሩት ሁኔታ በመሥራት እስካሁን ድረስ ጉደሎ ሆኖ የቆየውን የሐረርን ታሪክ እንደሚያሟላው ይጠበቃል።

በሐረር ውስጥ ክብርና ምስጋና የሚገባቸው በርካታ ታሪካዊ ስፍራዎች ቢኖሩም የከተማዋ ጠባቂዎች ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ቅዱስ አድባራት አሉ። እስካሁን የተዘገቡ የሐረሪ አድባራት 365 ያህሉ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 44 ቅዱሳን እንዲከበሩ የተደረገው በአው አባድር ዘመን ነው። እነዚህ ከተማዋን የሚጠብቁ ቅዱስ አድባራት፣ “የአባድርን አድባር” በግንቡ ውስጥ ከግንቡ ውጭ ባሉ ቦታዎች ተሰራጭተው ከተማዋን በየቀኑ እየተፈራረቁና በአንድነት ሆነው እንደሚጠብቁ ይታመናል።

ሐረሪዎች በአድባራቱና በመስጊዶቹ ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ በዓላትን የሚያከብሩ ሲሆን ለምሳሌ የነብዩ መሐመድ የልደት ቀን /ነቢ መውሉድ/ በተወሰኑ አድባራትና “ከረቡ ጋራች” ማለትም የከበሮ ቤት ተብለው የሚጠሩት ስፍራዎች ይከበራል። ከበሮ እየተመታና እየተጨፈረ የሚከበረው “ሸዋል ኢድ” የሚከበር ሲሆን በተለይም በዚህ ዕለት በእድሜ የገፉ ሴቶች ፣ወጣቶች ደግሞ ጓደኞቻቸው የመዘየር /መጐብኘት/ ማህበራዊ ግዴታ አለባቸው። ወንዶችም በዚህ ጊዜ ፍራሻቸውን ዘርግተው ጫት ይቅማሉ።

የቅዱሳን አድባራት ኃላፊዎች የአውሊያዎች ደቀመዝሙርት የሆኑትና “ሙሪድ” ተብለው የሚጠሩ እንዲሁም ከቅዱሳኑ ጋር በመንፈስ ግንኙነት የሚያደርጉ እንጂ ኢማሞች ወይም የመስጊድ ሼኮች አለመሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ከሐረሪዎች አባቶችና እናቶች ጋር የሚገናኙ ሙሪዶች በሃይማኖቱ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ካላቸው የበለጠ ምክርና ሐሳብ ይጠይቃሉ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

## የሐረሪ ቤቶች አሠራር

ሐረር ከሌሎች የኢትዮጵያ ግዛት ከሚገኙት ከተሞች የውስጥ አወቃቀር የተለየ ግልጋሎቶች የምትለይበት በርካታ ሁኔታ ቢኖርም በተለይ የቤት ውስጥ አወቃቀሩ የጐላ ልዩነት ይታይበታል፡፡ አጠቃላይ ለግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ከጊዲር ጋር /ትልቅ ቤት/ እንጀምር፡፡ በትልቁ ቤት ውስጥ ሰዎች እንደ ቤተሰባዊና ማህበራዊ ኃላፊነታቸው ቅደም ተከተል የሚቀመጡባቸው አምስት መደቦች አሉ፡፡ በዚህ መሠረት ታላቅ እንግዳ ሲመጣ “አሚር ነደባ” ወይም የንጉስ መደብ ተብሎ የሚጠራው ስፍራ ይቀመጣል፡፡ ከታላቁ እንግዳ ያለ ሰው ደግሞ ድብቁ መደብ ወይም “ሱትሪ ነደባ” ፣ አራተኛው “ጢት ነደባ” ወይም ትንሿ መደብ አምስተኛ መደብ አሮጊት ሴቶች ይቀመጡበታል፡፡

ጊዲር ጋር /ትልቁ ቤት/ ተብሎ የሚጠራው የቤቱ ወንዶች ከጓደኞቻቸው ጋር የሚመገቡበት ቁርዓን የሚቀሩበትና የሚያድሩበት ነው፡፡ ሴቶች ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑበት ጢት ጋር ወይም ትንሽ ቤት አለ፡፡ “ኪርተት” የሚባል ከትልቁ ቤት ጋር የተያያዘ ጓዳ ሲኖራቸው ይህም ለመኝታና ለዕቃ ማስቀመጫ ይጠቀሙበታል፡፡ ኪርተት አጠገብ ራቅ ብሎ ዴራ የሚባል ሴቶች ምግብና ዕቃዎችን የሚያስቀምጡበት ስፍራ አለ፡፡ ሐረሪዎች እርስ በርሳቸው ሲጨቃጨቁ ሕጻናትን ከአካባቢያቸው የሚያርቁ ሲሆን ዴራ ገብተው በሐሳብ እስኪስማሙ ድረስ ይከራከራሉ፡፡

ሐረሪ ባልና ሚስት የፍቅር ግንኙነታቸውን በሚመለከት አብዛኛውን ጊዜ በግልፅ የማይነጋገሩ ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን ምልክት ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ በሶላት የሚጠቀሙበት የመታጠቢያ ጆግ ወትሮ የሚቀመጠው ወለል ላይ ሲሆን የቤቱ አባወራ ከባለቤቱ ጋር ለማደር በሚፈልግበት ጊዜ ግን ግርግዳው ላይ በተሠራች መስኮት /ጭጐት/ ላይ ያስቀምጠዋል፡፡ አባወራው ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ሚስትየው አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ታደርጋለች፡፡ ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ይህንን መልእክት በትክክል ስለሚገነዘቡ ወደዚያ ቤት መጥቶ ለማደር የሚፈልግ እንግዳ ቢኖር መኝታ እንደሌለ ይነግሩታል፡፡

ከጋብቻ በፊት የወሲብ ግንኙነት በዚህ ዘመን የተከለከለ ሲሆን ቃሉን መናገሩ ራሱም አሳፋሪ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ወጣት የወደዳትን ሴት ለማግባት ሽማግሌ ሲልክ በሁለቱ መካከል ከዚህ ቀደም አንዳች ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ጥርጣሬ ቢኖርም ቤተሰቦች ይህንን እውነት እንዳላወቁ መሆን የተለመደ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ደግሞ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያልተዳረች ልጃገረድ ብትኖር ይህንን ለማሳወቅ ሲባል በትልቁ ቤት ዕቃ መደርደሪያ ቦታ ላይ ስጋጃ ምንጣፍ ተጠቅልሎ ይቀመጣል፡፡ ምንጣፉ ልጃገረዲቱ ስትዳር ይሰጣታል፡፡

## ጋብቻ በሐረሪዎች

### 1.ቅድመ ጋብቻ

የድሮ ሐረሪዎች ወንድ ልጃቸውን ሆነ ሴት ልጃቸውን የሚድሩት በራሳቸው ፍላጐት መመዘኛ እንጂ በልጆቻቸው ፈቃድና ፍላጐት እንዳልነበረ የታወቀ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የወንዱ ሴት ዘመዶች ማንን እንደሚያገባ ስማቸውን፣ የማን ልጅ መሆናቸውን፣ ጠባያቸው እየዘረዘሩ የሚፈልጋት እንዲመርጥ ይነግሩታል፡፡ ይህም ካልሆነ የወላጆቹ ጓደኞች ከሴት ልጆቻቸው አንዷን እንዲያገባ ራሳቸው የጋብቻ ሐሳቡን ሊያነሱለት ይችላሉ፡፡ እሱ ራሱ ከዓይኑ የምትገባ ሴት ካየም እሷን ለማግባት እንዲፈቅዱለት ወላጆቹን ይጠይቃል፡፡ ወላጆቹም ስለልጅቱ ማንነት ያጣሩና ካመኑበት ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ ሴቷም በአንድ አጋጣሚ አይታ የወደደችውን ወጣት ለማግባት የምትፈልግ ቢሆን ወላጆቿ ስለልጁ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

በተለያዩ መንገዶች የጋብቻ ሐሳብ ከተጠነሰሰ በኋላ የወንዱ ቤተሰብ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌ ይልካል፡፡ በዚህ ጊዜ ሴቶቹ ለብቻ ወንዶቹ ለብቻ በሐሳቡ ይመክሩበታል፡፡ ለመልሱም ሌላ ጊዜ ይቀጠራል፡፡ የሴቷ ቤተሰብ በጋብቻው ሐሳብ የሚስማሙ ከሆነ የወንድ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ ስለሚሰጠው ጥሎሽ፣ በሠርጉ ዕለት የሚወጣውን ወጪ ስለሚሸፍን፣ ስለ ማህር፣ እና የሷ ካልሆነ ጥፋት ለሚመጣ ፍቺ ሊከፈላት ስለሚገባው ካሣ ውይይት ማድረግ ይቀጥላል፡፡ ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለጋብቻው ሆነ ስለ ክፍያው ይፈራረማሉ፡፡ ይህ የቃል ኪዳን ፊርማ የሚፀድቀው ከወንዱ ቤተሰብ ለሴቷ ቤተሰብ የሚበረከተው "ኩሻ ጫት" በተባለው ነው፡፡

## 2. የፍጥምጥም ጫት

ኩሻ ጫት ከተላከ በኋላ "ዘገን ሶዛ" በተባለው ስርዓት ማለትም ከጥዋት ጀምሮ በሚመታው ድቤ ስነ-ስርዓት "ኒካህ" ይታሠራል፡፡ የዘገን ሶዛ ስነ-ስርዓት የሚካሄደው ጥዋት በማለዳ በሴቲቱ ቤተሰብ ትልቅ ቤት /ጊዲር ጋር/ ሲሆን በዚህም ጊዜ አስር ሰዎች ያህል ከወንድ ከሴት ቤተሰብ አባላት ይገኛሉ፡፡ ስነስርዓቱ ከመካሄዱ በፊትም ሴቶች ከተፈጨ ሥጋ፣ እንቁላል፣ ከብስኩትና ከከረሜላ ጋር የሚቀርብ "ሙለዋሕ" የተባለውን ምግብ ለቁርስ ያዘጋጃሉ፡፡ የወንዱ ሽማግሌዎች ሁለት እስር ኩሻ ጫት (የፍጥምጥም ጫት)፣ ልብስ፣ ቀለበት፤ ሐላዋ ይዘው ሲመጡ ሴቶች ደስታቸውን በእልልታ ይገልፃሉ፡፡ ቤት እንደገቡም ሽማግሌዎቹን በሚመሯቸው አዛውንት ማዕከልነት "ፋቲሃ" ይቀራል፡፡ ከዚያ ወጣት ወንዶች በሴቶች የተዘጋጀውን ቁርስ ያቀርባሉ፡፡ ቁርስ ከተበላ በኋላ ጫቱና የመጣው ጥሎሽ ይሰጣል፡፡

የመጣው ስጦታ የሙሽራይቱ አባት ወይም ቃዲው ከተቀበለ በኋላ በዛ ያለውን ጫት ለወንዶች በማስቀረት የተቀረውን ጫት ከጥሎሹ ጋር ለሴቶቹ ይሰጣል፡፡ ሴቶቹም የመጣውን ጫማ፣ ቀሚስ፣ ሻሽ፣ እና ወርቅ የተሠሩ ጌጦችን እያዩ ያደንቃሉ፡፡ ኒካሕ ከተደረገ በኋላ ውሉም በሁለቱም ወገኖች ተፈፅሞ ሽማግሌዎቹ የሙሽራይቱን ቤተሰብ አመስግነው ይወጣሉ፡፡

ይሁንና የሠርጉ ዕለት ዘገን ሶዛ በተባለው የፍጥምጥም ዕለት ሊወሰን ላይወሰንም ይችላል፡፡ በማንኛውም ጊዜ ይወሰን፣ በሠርጉ ዋዜማ ማለትም ቅዳሜ ዕለት በወንዱና በሴቷ ቤት "አንቀር ማሕጠብ" ማለትም ጨንራ ማጠብ የተባለው ስነ-ስርዓት ይካሄዳል፡፡ በዚህ የአፎቻ አባላት እርስ በርሳቸው ከቤት ቤት እየተጠራሩ ይሰበሰቡና ወደ ሙሽራው ቤት በየፊናቸው ይሄዳሉ፡፡ እዚያ እንደደረሱ በደንቡ መሠረት ለመደገሻ የሚረዳ ገንዘብ ይሠጣሉ፡፡ ሠርጉ የተባረከ እንዲሆንም ፀሎት ያደርጋሉ፡፡

## 3. "እንቀር ማህጠብና እልእላ"

ጨገራ ማጠብ ወይም እንቀር ማሕጠብ የሚባለው ስነ-ስርኛት በሐረሪዎች ከፍተኛ ዝግጅት የሚጠይቅ ሲሆን የሚሰጠውም ግምት ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ወንዶች በሃይማኖቱ ትዕዛዝ መሠረት በሬውን ያርዱና መላው ደም እንዲፈስ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያ ቆዳውን ገፈው እያንዳንዱን ብልት በመልክ በመልክ አውጥተው ለሴቶች ይሰጣሉ፡፡ በአፎቻ የተደራጁት ሴቶች የቤተሰቡ አባላት፣ ቤተዘመዶችም ጐረቤቶችም የጭራ ክፍፍል አድርገው "ወቃሊም" ማለትም ደቆ የተከተፈውና ልዩ ልዩ ማጣፈጫ የተቀላቀለበት ሥጋ በውስጡ በመጠቅጠቅ ወቃሊም ይሰራል፡፡ ይህም ሙሽሪትና ሙሽራው ለአራት ቀናት በጫጉላ ቤት በሚቀመጡበት ጊዜ የሚመገቡት ይሆናል፡፡ በጨጓራው ፈርሱ ከተራገፈና በደንብ ከታጠበ በኋላ ከምድጃ አመድ ተደርጐበት አጥር ጊቢ ውስጥ ተዘርግቶ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ የጨጓራው አጠባና የሥጋው ከተፋ በሚካሄድበት ጊዜም ሴቶች ከበሮ እየመቱ መዝፈንና መጨፈር ይጀመራሉ፡፡ ግብዣውም ይቀጥላል፡፡ በድሮ ጊዜ ጨጓራ የሚታጠበው ወደ ማታ አካባቢ ወደ አው ዑመር ወንዝ ነበር፡፡ በ1902 ፈረስ መጋላ ላይ ቧንቧ ውሃ ሲገባ ግን ከዚያ ውሃ ወደ ቤት እየመጣ ማጠብ ተጀመረ፡፡ የቧንቧ ውሃ በየቤቱ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በየግቢው ውስጥ የአጠባው ተግባር ይከናወናል፡፡

በጨጓራ ማጠብ ዕለት ከሚካሄዱት ሌሎች ስነ-ስርዓቶች አንዱ ሒና ዑኻት የተባለው ምግብ ከሙሽራዋ ቤት ወደሰ ሙሽራው እና ከሙሽራው ቤት ወደ ሙሽሪቷ ቤት የመላክ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ ከሙሽራዋ ቤት ወደ ሙሽራው ቤት ሒና ዑኻት የሚላከው በሁለት ወንድ ወጣቶች ነው፡፡ ወጣቶቹም ለጨጓራ አጠባ የተሰባሰቡት ሴቶች ሲጨፍሩና ሲዘፍኑ ስለሚያገኟቸው ያመጡትን የድስት ወጥና ትልቅ መሶብ ሙሉ ምግብ ያለምንም ድጋፍ በጭንቅላታቸው ተሸክመው በዘፋኞቹ መካከል በማለፍ ለትልልቅ ሴቶች ያስረክባሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ “አላ አላ” የተባለው ስነ-ስርዓት ይካሄዳል፡፡ በዚህ ስነ-ስርዓት ሙሽራው ከወንድ ከሴት ሚዜዎቹ እንዲሁም ሴት ዘመዶቹ ጋር በመሆን ወደ ሙሽራዋ ቤት ይሄዳል፡፡ ሴት ዘመዶቹ ሒና ወደ ምትቀባበት ክፍል ውስጥ ከሌሎች ሴቶች ጋር በሚዘፍኑበትና በሚጨፍሩበት ጊዜ ወንዱ በግቢው ውስጥ በሚካሄደው ዘፈንና ጭፈራ ተካፋይ ይሆናል፡፡ ወደ ሙሽራዋ ክፍል መሄድ ግን አይፈቀድለትም፡፡

በሁለቱም ቤቶች የሚዘፈነው ዘፈን ከእስልምና እምነት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ሲሆን በአመዛኙ ሙሽሪትና ሙሽራው ሰላምና ፍቅር የተሞላበት ጋብቻ እንዲመሠርቱ፣ የተመሠረተውን ጋብቻ ፈጣሪ እንዲጠብቀው ቅዱስ አድባራቱ የአያት ቅድመ አያታቸው ቅዱስ መንፈስ ከእርኩስ መንፈስ እንዲጠብቃቸው የሚጠይቁ የፀሎት ዘፈኖች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በሙሽራይቱ ቤት ከተዘፈነ በኋላ ሙሽራው ወደ ቤቱ ሲመለስ በሙሽራዋ ቤት የነበሩ ሰዎች አጅበው ከቤት ያደርሱትና እዚያም ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሽራይቱ እቤቷ ትቆያለች፡፡ ይህ ዕለትም በሙሽራዋ ከቤተሰቧ ቤት የመቀመጥ የመጨረሻ እለት ይሆናል፡፡

የሠርጉ ዋዜማ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ሁኔታ ቅዳሜ ሲጠቃለል እሁድ ዕለት የአፎቻ አባላት የሆኑት ሴቶች ሙሽሪትና ሙሽራው ለመጀመሪያ ጊዜ አብረው የሚበሉትን ምግብ ማዘጋጀት ይጀምራሉ፡፡ ወደ ስድስት ሰዓት አካባቢ ሙሽራው ሽማግሌዎችን፣ ሚዜዎችንና አጃቢዎችን አስከትሎ ወደ ሙሽራዋ ቤት ይመጣል፡፡ ከዚያም ግብዣው ይቀጥላል፡፡ በድሮ ጊዜ ሙሽራዋ ከጫጉላዋ የምትወጣው ምግቡ ተበልቶ ካለቀ ቡኋላ ሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን ሙሽራው እንደመጣ ከጫጉላዋ ትወጣና ምሳ አብረው በመጋበዝ ወደ ባሏ ቤት በከፍተኛ ዕልልታና ጭፈራ ትሸኛለች፡፡ በድሮ ጊዜ ሙሽራውና ሙሽራይቱ በአህያ ላይ ተቀምጠውና ታጅበው ይሄዱ ነበር፡፡ አሁን ግን በመኪና ሆኗል፡፡

ሙሽሪትና ሙሽራው ወደ ወንዱ ቤት ሄደው ጫጉላ ቤት ከገቡ በኋላ ሱረቱል ያሲንና ተባረክ የተባሉት የቁርዓን ምዕራፎች ይቀራሉ፡፡ በደንቡ የመሞሽራቸውና የመመገባቸው ኃላፊነት የወንድና የሴት ሚዜዎች ነው፡፡ በዚህ መሠረት የወንዱ ሚዜዎች በቀኝ ተቀምጠው ሙሽራውን እንደሚያጉርሱት ሁሉ የሴቷ ስር ሚዜዎችም በሙሽሪት በስተቀኝ ሆና ታጉርሳታለች፡፡

ስለዚህም ሙሽራውም ሆነ ሙሽሪቱ እስከ ጫጉላው ዕለት ፍፃሜ በሚዜዎቻቸው አማካይነት ይጐርሳሉ እንጂ በእጃቸው አይመገቡም፡፡

ብዙውን ጊዜ የጫጉላ ቀናት አራት ሲሆኑ በነዚህም ቀናት ሙሽራይቱ ከሴት ሚዜዎች ጋር በተባለው ትልቁ ቤት ይቀመጣሉ፡፡ ሙሽራዋ ኪርተት ወደተባለችው ክፍል ከሚዜዎቿ ጋር እንደገባችም የሙሽራ ልብሷን ያወልቁላታል፡፡ ወዲያው የሙሽራው እህቶች / ዘመዶች/ ሴቶች ማር እንድትልስ ያቀርቡላታል፡፡ እሷም ለመጀመሪያ ጊዜ ትግደረደርና ትንሽ ተለምና ትልሳለች፡፡ ይህ የባሏ ቤተሰብ እንደማር የሚጣፍጥ እንዲሆንላት ከመመኘት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡

ሰኞ ጠዋት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ ሙሽሪት ድንግል ሆና መቆየቷን የሚረጋገጥበት ዕለት ሲሆን የሙሽራይቱ ቤተሰብ የደም ሻማ ወይም ቀይ አበባ መምጣቱን ይጠብቃሉ፡፡ የደም ሻማ ሐላዋ ከያዘ ድስት ጋር ተሸፍኖ እንደመጣም ቤተዘመድ እንዲመለከተው ይደረጋል፡፡ ከዚያ የሙሽራዋ ቤተሰብ በቀል ሙዝ ማለትም ሙሽሮቹ ጉጆ በሚወጡበት ጊዜ የሚጠቀሙበት ሙዝ፣ እጣን፣ ማጨሻ፣ መጥረጊያ፣ የልብስ ማስቀመጫ ስፌት፣ እጣን፣ ማስቲካ፣ ጀበና፣ ድስትና የመስገጃ ጆግ ይልኩላቸዋል፡፡

ማክሰኞ ጠዋት የሙሽራዋ "ኢናይ ገበታ" ማለትም የእናት ማዕድ የተባለውን ወቃሊምና ጡፍጡፍ ወደ ጫጉላ ቤቱ ይልካሉ፡፡ ከሰዓት በኋላ የሙሽሮቹ ቤተዘመዶችና ጓደኞች ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያመጣሉ፡፡

ረቡዕ የሙሽራዋ ታላቅ ወንድም ከረሜላ ያመጣል፡፡ ሙሽራዋም አንድ ጠርሙስ ውሃ፣ ኩልና የሚታኘክ እንጨት ትልካለች፡፡ ማታም ዘፈንና ጭፈራ ይኖራል፡፡

ሐሙስ የመጨረሻው የጫጉላ ቀን ሲሆን በዚህ እለት ሙሽራዋ ለጉጆ መውጫ የሚያስፈልገው ነገር ለጥሎሽ ከተሰጣት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ይገዛል፡፡ የሙሽራዋ ቤትም ምሳ ይበላል፡፡ የሙሽሪት አባት ለሙሽራው የቁርዓን የፎጣ ሽልማት ይሰጠዋል፡፡ ቁርአን ሃይማኖቱን እንዲያጠናክርበት ሲሆን ፎጣው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በጨለንቆ ጦርነት የተሰውትን ሙሽሮች እንዲታወሱበት ነው፡፡

የጫጉላ ሳምንት ከተጠናቀቀ በኋላ በሚቀጥለው “ሸኔይ ሻኔይ” የሚባለው ስነ-ስርዓት ሲሆን በዚህ ጊዜ ሙሽራይቱ ፀጉሯን እንደ ባለትዳሮች ትሰራለች፡፡ አለባበሷንም እንደዚሁ ይህም ስነ-ስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ የሙሽራይቱና የሙሽራው ወገኖች ይዘፍናሉ፡፡ ዘፈኑም ሁለቱም ወገኖች በሠርጉ ስላደረጉት እንቅስቃሴ የሚገልፁ ሲሆን በመጨረሻም ሙሽራይቱ በሁለት ወገኖች መካከል ትገባለች፡፡ ከዚያም ቤተሰቦቿም ወደራሳቸው የሙሽራው ወገኖችም ወደራሳቸው ለመውሰድ ይጐትቷታል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሙሽራዋ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሁለቱም ቤተሰቦች አባል መሆኗን ነው፡፡

ይህ ሁሉ ከተከናወነ በኋላ ሙሽራይቱ የባሏ ቤተሰቦች ወዳሉበት ክፍል ለእራት ትጋበዛለች፡፡ በዚህ ጊዜም ኩሻ ጫት ለቤተሰቦቿ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ስትደበቃቸው ከነበረው ወንድ አማቾቿ ጋር ትገናኛለች፡፡ ከዚያም ከባሏ ጋር በመሆን የባሏን ቤተሰቦች አባላትና በዚያ ዕለት በሚካሄደው ስነ-ስርዓት ለመገኘት የመጡት ሰዎች እጅ በመሳም ይመረቃሉ፡፡ በምርቃቱም ባልና ሚስቱ አዲስ ባለትዳሮች ለመሆናቸው እውቅና ይሰጣል፡፡

ከጫጉላ ቤት ፍፃሜ በኋላ አዲሶቹ ሙሽሮች ለአንድ ዓመት ያህል “ሐታም ጋር” በተባለው ቤት የቤተሰብና የወዳጅ ዘመድ እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይቀመጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከማንኛውም የቤተሰብ ግዴታ ነጻ ይሆናሉ፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ ሙሽራዋ እንደምትፀንስ የታወቀ ስልሆነ ሐራስ ጋር ማለትም የመውለጃ ቤት ይዘጋጅላታል፡፡

ስትወልድም በመውለጃው ቤት ውስጥ መጋረጃ ተደርጐላት ለ40 ቀናት ያህል ትታረሳለች፡፡ በዚህ ጊዜ እናቷና የልጁ እናት ልዩ ልዩ ምግብና መጠጥ በማምጣት እንድትጠገን ያደርጋሉ፡፡ ዘመዶች፣ ጓደኞችና ጐረቤቶች ይጠይቋታል፡፡ ባለቤትትውም ሚስቱን በየቀኑ ለአጭር ጊዜ እየመጣ ያያታል፡፡

ሐረሪ ሴት እንዳገባች መውለድ የሚጠበቅባት ሲሆን እስከ ስድስት ዓመት ድረስ ካልወለደች ግን ባሏ ጋር አብራ የመኖሯ ተስፋ በሁለቱ መካከል የሚኖረው ፍቅር ይወስነዋል፡፡ ባልየው ሚስቱን የሚወድ ከሆነ ግን በባህላቸው ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ያልተለመደ ቢሆንም እንኳን በእንደዚህ ያለው ግፊት ማለትም ልጅ ለመውለድ ሲል ሁለተኛ ሚስት ሊያገባ ይችላል፡፡

# አፎቻ

## 1. አፎቻ በአጠቃላይ

አፎቻ ማለት የህብረተሰቡ የጋራ ድርጅት /አውታር/ ሲሆን በመሠረቱ ትኩረት የሚሰጠው ለሠርግና ለቀብር ስነ-ስርዓት ጊዜ ነው፡፡የቤተሰብ ኃላፊ የሆነ ወንድ ሁሉ የወንዶች አፎቻ አባል መሆን አለበት፡፡እኤአ በ1975 ሐረር ውስጥ 24 የወንድ 14 የሴት አፎቻዎች ነበሩ፡፡ በሐረሪዎች ዘንድ አፎቻዎች ለማንኛውም ማህበራዊ ተቋማት እንደ ጀርባ አጥንትነት ይቆጠራሉ፡፡ በተለምዶ የሚታወቀውም ሆነ የማይታወቀው የሐረሪ አኗኗር ውስጥ አፎቻ ግምባር ቀደም የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡ የአፎቻ አባላትና የአባላቱን ሥርጭት ሁኔታ በሚገባ መመዝገቡ ሁለት የማጠቃለያ ሐሳቦችን የአባላቱን የሥርጭት ሁኔታ በሚገባ መመዝገቡ ሁለት የማጠቃያ ሐሳቦችን ለመስጠት ያስችለናል፡፡ እነዚህም ሁለት የማጠቃያ ሐሳቦች የሐረሪን ሕብረተሰብ የስብስብ ሁኔታ ከሌሎች ሙስሊም ከተመማዎች ጋር ለማወዳደር ይጠቅማል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሐረር የጋራ ፍላጐት ባላቸውና የአካባቢው አፎቻዎች የተከፋፈለች አይደለችም፡፡ ምክንያቱም አፎቻ በወሰን የተከለለ ማህበር ስላልሆነ ነው፡፡

ይህ አባባል ከዚህ ቀደም "የሐረሪ ማህበረሰብ አደረጃጀቱ ከሠፈሮች መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ ጋር የተገናኘ የአጋጣሚ ግንኙነት የለውም ከሚለው ሐሳብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ የበለጠ ለመረዳት የሚያስችለን ደግሞ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ በማንኛውም "ቶያ" ወይም ዞን የተለያዩ አፎቻዎች አባላት ይገኛሉ፡፡ በሁለተኛ አብዛኛውን ጊዜ የምናየው የአንድ አፎቻ አባላት የሚመጡት በጥቅሉ ከከተማው ነው ማለት ስለሚቻል ነው፡፡ ቢሆንም የአፎቻ ማህበርተኞች የተለያየ ፍላጐት ባይኖራቸውም አባላቶቻቸው የሚመጡት ከአንድ አካባቢ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ በግልጽና አጠር ባለ መልኩ ስናስቀምጠው ብዙዎቹ የአፎቻ አባላት ጎረቤታሞች ቢሆኑም ጎረቤታሞች ሁሉ ደግሞ የአፎቻ ማህበርተኞች ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

ዋናው ቁም ነገር የሐረሪ ሕብረተሰብ ተቋማትና መልካአ ምድራዊ ስርጭት ከማንኛውም ጉረቤት የራሱ የሆነ ቤተሰባዊ ትስስር /አህሊ/ የተወሰኑ ጓደኞች እና የተለያዩ አፎቻ ጓደኞች እንዳሉት የታወቀ ነው፡፡ ከከተማው ነዋሪ ጋር የራሱ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ከነዋሪው ህብረተሰብ ጋር በቤተሰብ፤ በጓደኝነት፤ በማህበራዊ ተቋማት /አፎቻ/ በማንኛውም የከተማ ጉንዮሽ የራሱ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ አገልግሎታቸውም አጭር ይሁን ረዥም የሆኑት ተቋማት የሐረሪን ህብረተሰብ ለማዋቀር ማህበረሰቡን ይመሰርቱታል፡፡

## 2. “ቶያ አፎቻ” እና የኅብረተሰብ ስብስብ

ይህም ሆኖ ማህበራዊ ቁጥጥር የማህበራዊ ፀባይ አገላለጽ በተለይም በየቀኑ በሚያጋጥሙ በአካበቢው ሊከሰት በሚችለው ችግር በሐረሪዎች ዘንድ የግለሰብን ሚና በተመለከተ ማዘጋጃ ቤትና በሥሩ ያሉት የአገልግሎት ተቋማት ባልነበሩበት ወቅት ሊፈታ የሚችለው ከላይ በጠቀስናቸው ተቋማት መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ ምንም እንኳን በድሮው ጊዜ በፍቺና በውርስ ላይ ያለውን ቅራኔ ለመፍታት በሸሪዓ ሕግና ደንብ የሚጠቀም የሸሪዓ ፍረድ ቤት ቢኖርም በከተማው ውስጥ በማዘጋጃ ቤት አማካኝነት ተንቀሳቅሶ ሕግና ደንብን የሚያከብር ፖሊሲ ግን አልነበረም፡፡ በከተማው ውስጥ የንጽህና አጠባበቅ እምብዛም አይታይም፡፡ በሐረር ውስጥ በተጨናነቁ መንደሮች ውስጥ የሚታዩትም ችግሮች በመጀመሪያ ደረጃ በጥንታዊው የማህበራዊ ድርጅቶች “በቶያ አፎቻ” የሚፈታ ነበር፡፡

## 3. ጋር አፎቻ

"ጌይ አፎቻ" ማለት በአጣዳፊ ጊዜ የሚደርስ እድር ማለት ነው። በቤተሰብ ውስጥ ሞት ሲያጋጥም የወንድና የሴት አፎቻዎች አስቀድመውና ፈጥነው በመድረስ ሁሉንም ነገር የሚያዘጋጁ አባላት ናቸው። በእያንዳንዱ ቤት በሞት አደጋ ወቅት መውጫ፣ ለሠርግ ጊዜ ያገለግላል የሞት ጊዜም "አሙታ ጌል" ሲባል የሠርግ ጊዜም ደግሞ "በለቹ ጌል" ይባላል። የቅርብ ጉረቤት ወይም "ጋራ ጋምበሪ" በቀጥታ የደስታም የሐዘንም ተካፋይ ነው። ለዚህ ምንም ግብዣ አያስፈልግም። ቤቱ ቤትህ ስለሆነ ለዝግጅትህ ቤትህን ስታጸዳና ስታስጌጥ በዚሁ ወቅት የርሱንም ቤት እንደዚሁ ማድረግ ይኖርበታል። ጎረቤቶች እያንዳንዳቸው በእኩልነት መተያየት አለባቸው። ይህ መንፈስ በሕዝቡ ዘንድ ሠርፆ ይገኛል። መደብ የለሽ ማህበረሰብ መምሰል አለባቸው። አንዱ የአንዱን ግዴታ በእኩልነት ስለሚወጣ ማለት ነው።

ሰዎች ከጎረቤቶቻቸው ጋር ቅራኔ ውስጥ ከሚገቡባቸው ምክንያቶች ዋነኛውና የየዕለት ተግባር ሆኖ የተገኘው በልጆቻቸው አንዳንድ ትክክል ያልሆኑ ፀባዮች አማካኝነት ነው። ልጅህ ከሠፈር ልጅ ጋር ከተጣላና አንተ ልጅህን ደግፈህ ከተናገርክ ጎረቤትህን ታገላለህ ማለት ነው። እንደሱ አንዱ ሰው ከቶያና ከአፎቻ ጋር በመጥፎ ግንኙነት ካለው ነገሮቹ ሁሉ እጅግ ይከብዳሉ። ለምሳሌ ትብብር በሚያስፈልግበት ቀንና ወቅት አያገኝም። ብልህ አባት ከሆነ ግን ልጆቹ ሲያጠፉ ጣልቃ ሳይገባ ችግሮቻቸውን እርስ በእርሳቸው እንዲፈቱ ያደርጋል።

በተመሳሳይ አነጋገር የዚህ ዓይነቱ ችግር ሲከሰት አባት ልጁን በሚገባ ይቀጣል። ይህም የሚሆነው አባቱ ከቶያና አፎቻ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዳይላሽበት ነው። በሐረር ውስጥ ላለው የማህበረሰብ ቁጥጥር ወሳኙ ሚና የሚጫወተው ይህ ዓይነቱ የሕዝብ አመለካከት ነው ለማለት ይቻላል። በተለምዶ እጅግ ተቀራራቢ የሆነ ጎረቤት ወይም በሐረሪ ጌይ አፎቻ የሚባለው የውስጡ ታዋቂ እንደማህበረሰቡ በጎ አድራጎት ኮሚቴ ሆኖ የሚሠራ ይመስላል።

ጥንትም ሆነ ዛሬ ጋር አፎቻ እንደጐረቤት ማህበራዊ ድርጅት ያገለግላል፡፡ የአፎቻ አባላት ወንዱና ሴቱ በሙሉ በጐረቤት ደረጃ ላለው ማህበራዊ ችግር በመወያየት የጋራ መፍትሔ ለምሳሌ የጎረቤትን ወሰን ገፍተው ቤት ቢያሰፉ ከዚህም በላይ ደግሞ አንዱ አንዱን በገዛ ጉልበቱ ቤቱን ሊሸጥበት ጉዳዩ እንደ መሠረታዊ ችግር ተነስቶ ይወያዩበታል፡፡

ሐረሪዎች በዓመት አንድ ጊዜ በተጠናከረ መልክ ይደራጁና የከተማቸውን ቆሻሻና በየመንደሩ እየተዘጉ የሚያስቸግሩት ቱቦዎችን በዘመቻ ወጥተው ያጸዳሉ፡፡ መንገድ መጠገንም እንደዚሁ፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ መንገዶች ለአገልግሎት በቅተዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ስራ በይበልጥ ጐልቶ የሚታየው በረመዳን ወቅት ነው፡፡

ቀድሞ “ጋር አፎቻ” ወንዶች በተከታታይ ወደ መስጊድ መምጣት አለመምጣታቸውን ይቆጣጠራል፡፡ የጎረቤት ሰው ወንዱ ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ መስጊድ ውስጥ መስገድ አለበት፡፡ ለ3 ቀናት በተከታታይ ከቀረ ከመስጊድ ሰው እና ጎረቤቶቹ ወደ ቤቱ ሄደው ምን ችግር እንዳጋጠመው ይጠይቁታል፡፡

በሐረሪ ማህበረሰብ ውስጥ በጋራ ለሚወዱት እርምጃና መተሳሰብ ቶያ ራሱን የቻለ አካል አለመሆኑን ያስረዳል፡፡ አንድ ቶያ በማንኛውም መልኩ ከሌላው አይበልጥም፡፡ በዚህ መልክ በአፎቻና በቶያ ተቋማት ውስጥ ዕለታዊ ድርጊቶች ይካሄዳሉ፡፡

## የመስጂድ ቶያ ጉርብትና

“መስጂድ ቶያ” “አካባቢው የመስጂድ ጉርብትና” የተባለው በከተማው መካከል ለሚገኘውና ከዋናው ገበያ ለማይርቀው ጎረቤት የተሰጠ ስም ነው። መስጂድ ቶያን ሕብረተሰቡ የተሟላ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱና ዋነኛው በሴቶች መሐከል ያለው ግንኙነት ነው። የመጠያየቅ ሁኔታው ምንም እንኳን ተከታይ ባይሆንም ቶያና አፎቻ በአንድነት ከማያስተሳስሯቸው መንገዶች አንዱ ነው። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ በመስጂድ ቶያ ውስጥ ጉልህ ሆኖ ይታያል። ከግቢ ውስጥና ውጪ ጓደኞቻቸውና እህቶቻቸው የሞቱባቸው ሴት አሮጊቶች /አዛውንቶች/ ወይም ጡረታ የወጡትን ጨምረን በአንድ ጊዜ ከአፎቻ ተሳትፎ ይገለላሉ ማለት አይደለም።

አንዲት ሴት የአፎቻ ትስስር ባይኖራትም በከተማይቱ ውስጥ ለሚደረጉት የዕለት ድርጊቶች እንግዳ አትሆንም። አንዲት ባለቤትዋ ያረፉ (የሞተባት ሴት) ሚች ባለቤትዋ ከሚሳተፍበት ቦታ አፎቻ ሌላ አስታዋሽ የሌላት እንዳትሆንና ብቸኝነት እንዳይሰማት ስትሞትም በሥነ-ስርዓት በወግ ትቀበር ዘንድ አስፈላጊው ሁሉ በአፎቻውት አባላ ይደረግላታል።

1. ጓደኝነት የመስጂድ ቶያ ነዋሪዎች ሕብረተሰቡ ሊያስተሳስር የሚችል ሁለተኛ አይነት ማህበራዊ ተቋም ነው። ይሁንና የወ ንዶቹ ግንኙነት የሚያደርገው በረባና ባልረባ ጉዳይ ሳይሆን ወሳኝ፤ ውስብስብና አንገብጋቢ በሆኑ ጉዳይ ላይ ነው።

2. የመስጂድ ቶያ ሕብረተሰብ ወጥ በሆነ ደረጃ ላይ መሆኑ በግልፅ የሚያየን አፎቻዎች፤ ጓደኝነት የቤተሰብን ተስስር በሚገባ ስናጤን ብቻ ነው። እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ግን ኙነቶች የሚታዩበትም በወንዶችና በሴቶች ቶያዎች መካከል ነው።

3. በመስጂድ ቶያ ያሉ ወንዶች በሁለት መንገድ ላይ በመመርኮዝ ከራሳቸው አፎቻ ውጪ ከሌላ አፎቻ ጋር ጓደኝነት ሊኖራቸው

ይችላል፡፡ ጥሩ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ በአፎቻዎች መካከል የመገናኛ ድልድይ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ ጓደኞች እርስ በርስ በጽኑ ቃልኪዳን የተሳሰሩ ስለሆኑም የተለያዩ አፎቻዎች አባል ቢሆኑም በራሳቸው አፎቻ ውስጥ የተከሱትን ነገሮች በሌላ አፎቻ ውስጥ ላሉት ጓደኞቻቸው ያሰማሉ፡፡ በአነስተኛ ደረጃ ቢሆንም የጓደኞቻቸውን ፍላጎት በራሳቸው አፎቻ ውስጥ ማን ፀባረቅ ይፈልጋሉ፡፡ ጓደኛሞች አንድ መንደር ውስጥ ሲኖሩና በተለያየ አፎቻዎች አባል ሲሆኑ የእያንዳንዳቸው ውይይት አመለካከት ለጓደኞች ስብስብ ጥሩ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

4. በተዘዋዋሪ ደግሞ መንደሩ በዚህ ተደራራቢ ግንኙነት የተነሳ ይበልጥ አንድነቱ ይጠበቃል፡፡ በተመሳሳይ አነጋገር ተደራራቢ የአህሊ ተስስር ሊያስገኝ የሚችለው አስተዋጽኦ ለትስስሩ ያለው ሚና የቶያና አፎቻ መዋቅሮችን በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡

እያንዳንዱ የሐረሪ ወንድ ከዝምድና ቀጥሎ ጓደኝነትና አፎቻ በሚባሉት የመቀራረቢያ መንገዶች ተሳስረው ይገኛሉ፡፡ በእናቶች መጠያየቅና ሽርሽር ጭምር በመደገፉ እንዲሁም ደግሞ በመስጂድ ደረጃ ያለው የወንዶች ግንኙነት በመታከሉ የመስጂድ ቶያ ህብረተሰብ ጥንካሬ በተሞላበት መንገድ አንዱ ከሌላው ጋር ይገናኛል፡፡ ሌሎች የሠሩትን አንዱ ያውቃል፡፡ አንዱ የሠራውን ሌላውም ያውቃል፡፡

## ቶያ በከተማ ነዋሪዎች ሕዝብ አንፃር ሲታይ

አንድ ሐረሪ ከመንደሩ ጋር ያለው ማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም ተከታታይ ያልሆኑ ድርጅታዊ ግንኙነቶች "ቶያ አፎቻ" ብሎ ይጠራል፡፡ የአንድ ቶያና መንደር አሠራር ለሌላው ሁሉ ይሠራል ብሎ የሐረሪን ህብረተሰብ እውነተኛ ገጽታ ማወቅ አይቻልም፡፡ ቶያ አፎቻ ሊዋቀሩ የሚችሉት

ሀ/ ከመቀራረብ የተነሳ ሊዳብሩ የሚችሉ ግንኙነቶች በተለይ ከሴቶች የመጠያየቅ ሁኔታና ወንዶች በጎረቤት በሚገኘው መስጊዶች በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ

ለ/ ሦስት ዋና ዋና ተቋማት ማለትም በቤተሰብ ትስስር /አህሊ/፤ በጓደኝነትና በአፎቻ ነው፡፡ በአጭሩ የመንደርተኛነት ግንኙነት አመለካከት ሲታነፅ ነው፡፡

## በሐረር ውስጥ የሙያ የሃይማኖት የጉርብትና ሁኔታ

የሙያ፣ የሃይማኖት ዘርፎችና ወይም በቅድመ ኢንዱስትሪ ከነበሩ ሙስሊም ከተሞች የአኗኗር ስልትን በተመለከተ ሲጆበርግ እንዳለው የጕሳዎች ስብጥር ከተወሰኑ ሙያዎች ጋርም የተያያዘ ሲሆን ይህም የብሔረሰቦች ሙያ የመለያየት ጉዳይ በቅድመ ኢንዱስትሪ ከተሞች በብዛት ይከሰታል፡፡ የመሬት አጠቃላይ ይዞታ መለያየት የተለመደ በመሆኑ ልዩ የሆነ ዞን፣ ወረዳ፣ ወይም ለተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ በሐረር የሚገኙ ሱቆች የተሰባሰቡት በገበያ ቦታዎችና ጎዳናዎች ነው፡፡ ይህም በተወሰኑ የሙያ ዘርፎች ውስጥ ያሉትን ነዋሪዎች ከዞን ወደዞን ወይም ከቶያ ወደ ቶያ የጋራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሐረር ውስጥ ነጋዴ ሱቅ ውስጥ ሊኖር ይችላል፡፡ የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች ሲኖራቸው ሱቆቻቸው የሚገኙበት ዞን ወይም ተጕራባች በሱቆቻቸው የሚኖሩ ከሆነ ደግሞ ሁለት አይነት ጉርብትና እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በተለያዩ ሃይማኖት ልማዳዊ መሥመሮች አባል መሆን ወይም በዓረብኛው “መዝሃብ” በአንዳንድ የሙስሊም ከተሞች በዞኖች ለመከፋፈል መመሪያ ሆኖ ይገኛል፡፡ በከተማው ውስጥ በስፋት የምናየው የሐረሪ ጠንካራ ሕግ /ሸሪዓ/ ሻፊዕይ ነው፡፡ ትሬሚንግሃም እንደዘገበው በግብፃውያን አገዛዝ የሓነፊ ሕግ መስመር ተጀምሮ ነበር፡፡
ይህም ምናልባት እውነት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን የሐነፊ ሕግ መስመር የሚያረጋግጥ መረጃ ከ1962 ወይም ከዚያ ወዲህ ባለው ዘመን ውስጥ አልተገኘም፡፡ ሆኖም በበድርበሪ የሚገኙ የወንዶች አፎቻና በአሱምበሪ የሚገኘው የሴቶች አፎቻ ሐነፊ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ስለዚህ የሐረር ከተማ የሐነፊን መስመር ይከተላል የሚለው የትሪሚንግሃም አባባል ትክክል አይደለም፡፡

የሃይማኖት መስመሮች በተለያየ የሱፊ ወንድማማችነትና ጨረቃ /የሃይማኖት አነስተኛ ዘርፎች/ በሙስሊም ከተማ ዞኖች ላለው ማህበራዊ ክፍፍል መሠረት ነው፡፡ በሐረር ከተማ ቅዱሳን አውሊያዎች /አዎች/ በስፋት ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ በከተማዋ ግንብ ውስጥ ከሚገኙት ቅዱሳን አውሊያዎች ብዙዎቹ ለተወሰኑ ቶያዎች ድንበር መለያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ነገር ግን

1/ አብዛኛውን ጊዜ የቅዱሳን አውሊያዎች ከቶያ መስጊዶች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የሁሉም ቶያ ወንዶች ወደዚያው መስጊድ ሲመጡ የቶያው ነዋሪ ባይሆንም ማንኛውም ሙስሊም ወንድ በመስጊዱ ሊሰግድ ይችላል፡፡
2/ አማኝ የሆነ ማንኛውም ሰው በሐረር የሚገኙትን መስጊዶችን መጐብኘት ይችላል፡፡
3/ አንዳንድ መስጊዶች ሞግዚት ሲኖራቸው ሌሎቹ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ አውአብዱልቃዲር አልጀይላን በሐረር ውስጥ በስፋት ከሚታመንባቸው ቅዱሳን አንዱ ናቸው፡፡

## አፎቻ እንደ ባህላዊና ልማዳዊ ተቋም

ዱሪ መሐመድ በ1965፣ ዋልድሮን ደግሞ በ1975 በተለይም በገጽ 12 እና 25 እንደጠቀሱት በሐረሪ ሕብረተሰብ ውስጥ የሴትና የወንድ ወጣቶች ቡድን እንዲሁም "ባሃ" የሚባል የሚዘዋወር በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የብድር የአዋቂዎች ማህበር አፎቻ አለ።

ዋልድሮንም የአፎቻ ተቋማትን ሲገልፅ " በሌሎች የሙስሊም ዋና ከተማዎች ሊኖር የማይችል ራስን በራስ የማስተዳደር አስተሳሰብ ሐረሪዎች እንደነበራቸው ያመላክታል ይለዋል። ይህም እውነታ በተለይም በአሁኑ ጊዜ ያለው የወንዶች አፎቻ በታላላቅ ሕዝባዊ ባህርያት ባሏቸው በዓላት በሚደረግው እንቅስቃሴ ስለሚስተዋል የዋልድሮንን አባባል ያጠናክረዋል። እርግጥ ነው የወንዶች አፎቻዎች እንደ ምዕራባውያን አገሮች ሁሉ ሊቀመንበር፣ ሥራ አመራር፤ ባለሥልጣኖች እንዲሁም ሕገ ደንብና ቃለ ጉባኤ ወዘተ አላቸው። ዋነኛው ዓላማቸው ግን የሐረሪን ወግና ልምድ እንዲሁም የሐረሪን ባህል ጠብቆ ለማቆየት ነው። ይህም ቢሆን ዋልድሮን ቀደም ሲል ሐረሪዎች ራስን በራስ የማስተዳደር ማህበራዊ ልምድ እንደነበራቸው የጠቀሰውን የሚያረጋግጥ ነው።

በእርግጥም ሐረሪ ሴቶች ዛሬ ያላቸው የእርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነትና የአፎቻቸውን እንቅስቃሴ ሲታይ ከጥንት ጀምሮ ወግና ስርዓት ባለው መንገድ ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድሩ እንደነበር መረዳት ይቻላል። በድሮ ጊዜም አንዲት ሐረሪ እናት የልጇ ዕድሜ ከ8-10 ካልደረሰ ማለትም ዕድሜዋ ከ25-30 ዓመት ካልደረሰ የአፎቻ አባል አትሆንም።

ሁለተኛው ዓይነት ማህበር ማለትም የአፎቻ አባላት በከተማ ነዋሪነት የተወሰነ ሲሆን ያገባ ወንድና ከለጋ ሕፃንነት ዕድሜ የወጣ ልጅ ያላት ሴት የአፎቻ አባል እንድትሆን ትዳረጋለች። በዚህ ማህበር በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ የሚንፀባረቀውም ማንኛውም ወንድና ሴት በሚመርጠው አፎቻ ውስጥ አባል የመሆን መብት ስላለው ነው።

# የአፎቻ ታሪክ

ለመሆኑ የአፎቻ ስርዓት መቼ ተጀመረ ብለን ስንጠይቅ ግን ብዙ አወዛጋቢ ጉዳዮች እናገኛለን። ስለሐረሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈው አውሮፓዊው ሪቻርድ በርተን ሲሆን ይህ አውሮፓዊ በ1854 ስላደረገው ጉብኝት ገልፆ በ1856 ባሳተመው መፅሐፍ፣ መሐመድ ሙኽታር በ1876፣ ፊሊፕ ፖሊትሽኪ ግብፆች በ1884 ሐረርን በያዙበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ በገለፀበትና በ1888 ባሳተመው መጽሐፍ ስለአፎቻ ያነሱት አንድም ነገር የለም። ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች ስለ ሀረሪዎች ቤቶች አሠራር እቅድ ስለሴቶች ልብስ፣ ስል ልብስ ስፌት ችሎታቸው፣ ስለወርቅ ማንጠርና ስለአንዳንድ የቤት ቁሳቁስ ሥራዎቻቸው ለ150 ዓመታት ያህል የቀጠለውን ቁሳዊ ባህላቸው ሁኔታዎች ባወሱባቸው ምዕራፎች ከመጠቆም አልተቆጠቡም። ምንም እንኳን ሐረሪዎች አፎቻ ሕልውና ያገኘው ሊታወስ ከማይችል ዘመን አንስቶ እንደሆነ የሚገልፁ ቢሆንም በዚህ ዘመን ተጀመረ የሚል መረጃ እስካሁን አልተገኘም። ይህ የሆነበት ምክንያት አንድም የአፎቻው አባላት ቁጥር 80 በሚሆንበት ጊዜ ለሁለት ሰለሚከፈል ወይም አባላት በማይኖሩበት ጊዜ ሕልውናውን ስለሚያጣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አዲስ አፎቻ ሊመሠረት የሚችል ሕግ ስላለው ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ሐረሪዎች እስከ አምስት ትውልድ እንጂ እንደ ኦሮሞ ወይም ሱማሌዎች ለረጅም የትውልድ ሐረጋቸውን ስለማይቆጥሩ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ አፎቻዎች ወጋቸውና ልምዳቸውን ጠብቀው ለረጅም ዓመታት የቆዩ ቢመስሉም አፎቻ ግብፅ ሐረርን ይገዛበት ከነበረበት ጊዜ /1875-1884/ ወዲህ እንጂ ከዚያ በፊት አልጀመሩም ወደሚል መላምት ማዘንበል ይመረጣል።

“ባሃ” የተባለው ሴቶች ብቻ የሚሰበሰቡበት ተዘዋዋሪ የብድር ማህበር ግን ሕልውና ያገኘው ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ይዛ ከነበረችበት ዘመን ወዲህ መሆኑን ለማውሳት እወዳለሁ። በ”በሀ” ማህበራዊ ግዴታ ኖሮ የሚመሠረት ሳይሆን አስፈላጊነቱን አምነው የሚገቡበት ነው። አባላቱም አብዛኛውን ጊዜ ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ልጆች ያላቸው ወጣት ሴቶች ናቸው። እነዚህም አባላት በአፎቻ ውስጥ እንደሚታየው ባሎቻቸውን ጥብቅ ልማዳዊ ሕግ ለመታሰር የሚፈልጉ አይደሉም። እርግጥ ነው የበሀ አባላት ቁጥር ጋር በሚወዳደርበት ጊዜ አነስተኛ ነው። እንዲያውም ከ30 እና ከ40 አይበልጥም።

እድሜያቸውም ቢሆን ከ20 እና ከ30 ዓመት አያልፍም፡፡ ቤተሰባዊ ጭንቀታቸውም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኖም እንደ አፎቻ ሁሉ በአዲስ መልክ ሊደራጁ ወይም ለሁለትና ለሦስት ሊከፈሉ ወይም አባሎች ከሌላቸው እስከነጭራሹ ሊጠፉ እንዲሁም የአፎቻን ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

## የወንዶች አፎቻ

ስለ አፎቻ አመጣጥና አጠቃላይ ባህርይ ይህን ከተገነዘብን ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስለ ሴቶችና ወንዶች አፎቻ ዝርዝር አስተዋፅኦ እንመልከት፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ቀደም ሲል ወንዶቹ "ቀብሪ አፎቻ" ሴቶቹ ደግሞ "ኢንዶች አፎቻ" የተባለ ማህበር ነበራቸው፡፡ የወንዶቹ አፎቻ ዓላማ አንድ አባል የሞት ሁነት ቢደርስበት ለቀብር ስነ-ስርዓት ማስፈፀሚያ የሚሆን ገንዘብ መርዳት ሲሆን የሴቶች ደግሞ በሠርግ ጊዜ መረዳዳት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በታወቁ በዓላት፣ የሐረሪዎች ዓውደ ሕይወትንና የከተማዋን ደህንነት በተመለከተ ተገቢው ፀሎት ማድረስ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ይህም ወግ ያለው የፀሎት ስነ-ስርዓት በሠርግ፣ በቀብር ስነ-ስርዓት /የቀብር ቦታ ሲቆፈር ጨምሮ/ የከተማውን ዙሪያ በአጠራት ግንብና ከግንቡ ውጭ ባሉት ስፍራዎች የሚገኙ አድባሮች ሲዘከሩ ሁሉ መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡ በመሠረቱ በድሮ ጊዜም ቢሆን እንዲህ ያለው ባህላዊ ልማድ መፈፀም የአንድ ሐረሪ ፀባይና የሞራል ግዴታ እንደሆነ ተደርጐ ይወሰድ ነበር፡፡

ወንዶች ጫት እየቃሙ የአፎቻ ስብሰባቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ የሚያወሩት ወሬ እያንዳንዱ ሐረሪ ሌላው ሐረሪ የሚያውቀው መሆኑን የሚያመለክት የማህበራዊ ደህንነት የመቆጣጠሪያ ዘዴም ነው፡፡ የወንዶች አፎቻ በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊ የማህበር ሥራ አመራር ስልት የሚከተል ሲሆን ዓላማውና ግቡ የሐረሪን ባህልና ቋንቋ ጠብቆ ለማቆየት ቢሆንም የተፃፉ ሕጐችና አንዳች ተግባር ለማከናወን የሚችል ዝግጁ የሆነ ኃይል አለው ማለት ይቻላል፡፡ የወንዶች አፎቻ ሕግ በተለይ በመዋጮ አከፋፈል ከዓይነት ወደ ገንዘብ፣ ከተወሰነ ክፍያ ይልቅ ከወቅቱ ጋር የሚሄድ፣ ከዘመናዊ መገናኛ ጋር እንዲቀናጅ በየጊዜው የሚሻሻል እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## የሴቶች አፎቻ

የሴቶች አፎቻዎች ግን በጽሁፍ የሰፈረ ሕግ የሌለው ከመሆኑም ሌላ ከጥንታዊው አመራር እምብዛም የተለዩ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በሐረሪ ማህበረሰብ ውስጥ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በቁሳቁስና በሐሳብ መረዳዳት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እንደጥንቱ ቀጥሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአፎቻዎች አባል የገንዘብ እርዳታ በሚያስፈልገው ጊዜ መዋጮ ማድረግ እንዳለባቸው ደንባቸው ያዛል፡፡

ምንም እንኳን በአሠራራቸው ልዩነቱ የሚታይ ቢሆንም የሴቶች አፎቻ ከወንዶቹ ጋር ተመጣጣኝ ተግባር ያከናውናሉ ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ መሠረት ወንዶች ቁርአን ሙሉ በሙሉ ማወቅና የፀሎት ጉዳዩን አጥብቀው መያዝ ሲገባቸው፤ ከሴቶች የሚጠበቀው ግን ከሌሎች በሐረር ከሚገኙ ሙስሊም ሴቶች ለየት ለማለት የሚረዳቸውን ጥቂት የቁርዓን ክፍል ማወቅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አንድም ለብቻ ካበለዚያም በአጠቃላይ በሚደረግ የፀሎት ሥነ-ሥርዓት ተካፋይ ለመሆን ይበቃሉ፡፡ ዋና ተግባራቸው ግን በታወቁ በዓላት በሠርግ፣ በግርዛት፣በለቅሶ፣ ወይም ልጆች ቁርአንን በሚጨርሱበት ጊዜ ምግብና መጠጥ አዘጋጅቶ ማቅረብ ነው፡፡

እንደዚህ ያሉ በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ በሚዘጋጀው ምግብና መጠጥም የምትችለው ልጆቿ ከ8 እስከ 10 ዓመት ዕድሜ በሚደርሱበት ጊዜ ማለትም በአጭር ጊዜ ስትለያቸው አንድም ለብቻቸው ካለበለዚያም ለዘመድ ወዳጅ ትታ ለመሄድ በምትችልበት ጊዜ ነበር፡፡ ስለዚህም በጊዜው አንዲት ሐረሪ በአፎቻ አባል ለመሆን የ25 እና የ30 ዓመት ወጣት መሆን ይኖርባታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ለአባልነት ዝግጁ ስትሆን ለመግባት ታመለክታለች፡፡ ሁሉም አባላት በአንድ ድምፅ ከተስማሙ አባል ትሆናለች፡፡ በመሠረቱ ሌሎች ጉዳዮች ለምሳሌ ሕጉን ለመለወጥ፣ ለመዋጮ፣ ለስብሰባ ፣አባል ከአፎቻ የሚባረረው አልፎ አልፎ ሲሆን ይኸውም ከስብሰባ አዘውትሮ በመዘግየት ይም እስከጭራሹ ባለመምጣትና የአፎቻ መሪዎቿን ስታጣጥል ነው፡፡ ይሁንና አንዲት ከአፎቻዋ የተባረረች ሴት የሌላ አፎቻ አባል መሆን ትችላለች፡፡ የመቅረትና የመዘግየት ባህሪዋ የማይለቃት ከሆነች በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ታጣለች፡፡

በዚህም ምክንያት ማህበራዊ ወስትናዋ፣ በሠርግና በመሳሰሉት የበዓላት ቀናት የሚያስፈልጋት ወጪ ቢኖር በቤተሰቧ እርዳታ ብቻ ትወሰናለች፡፡ ለማንኛውም የሐረሪ ሴቶች ስለአፎቻቸው ያላቸው አመለካከት በጣም ጠንካራ ነው፡፡

አልፎ አልፎ እንደሚከሰተውም አንዳንድ ባሎች ሚስቶቻቸውን የአፎቻ ወይም (ባሣ )አባል እንዲሆኑ ባለመፍቀዳቸው የመግብያውን ክፍያ የማይሰጡ ቢሆን እንኳ የሴቷ ዘመዶች ጉዳዩን ጉዳያቸው በማድረግ አስፈላጊውን ገንዘብ ያዋጡና ይከፍሉላታል፡፡ ሥራውንም ይሸፍኑላታል፡፡

እንዲሁም አንዲት አዲስ የአፎቻ አባል ለመሆን የምትፈልግ አመልካች በአጋጣሚ አባል ከመሆኗ በፊት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰርግ የምትደግስ ከሆነ አንድም ማመልከቻዋ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ካለበለዚያ በጣም ከፍተኛ የመግቢያ ዋጋ መክፈል ይኖርባታል፡፡ እንዲህ ያለው እርምጃ ወስደውም በሠርግ ጊዜ ከፍተኛ ገንዘብ ማዋጣትና ሥራ መስራት ስለሚኖርበት እንዲሁም ሴትየዋ አባል ለመሆን የፈለገችው ጊዜ አባል ሆና በሠርጉ ሰበብ ለመጠቀም ስለፈለገች ይሆናል ተብሎ ስለሚጠረጠር ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የአፎቻ አባላት እንደ ሰርግና ቀብር ባሉ እንዲሁም እርዳታ የሚገባቸው ሰዎች በሚኖሩበት ጊዜ በሕጋቸው በተጠቀሰው መሠረት ገንዘብ ማዋጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ እያንዳንዱ አባል የሚደርስበትን የሥራ ድርሻ ማከናወን አለባቸው፡፡ ከዚህ የአባልነት ኃላፊነት ነፃ ለመሆን የሚቻለው አንድም በቅርቡ የቤተሰባቸውን አባል የዳሩ እንደሆነ ወይም ለቅሶ ያለባቸው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ አንድ የአፎቻ ማህበር በአንድ ጊዜ ሁለት የአባላት ሠርጐች ቢኖሩበት በሥራው ጊዜ ለሁለት ይከፈላል፡፡

በሐረር ውስጥ የሴቶች አፎቻዎች ከ3 እስከ 5 መኰንኖች አሉት ፡፡ እነዚህ መኰንኖች “አፎቻ ራጋ” ማለትም የአፎቻ አዛውንቶች ሲባሉ አልፎ አልፎ በጤናማና በወጣት አባላት ለመተካት ካልተፈለገ በስተቀር የሚመረጡትም ለእድሜ ልክ ነው፡፡ ከአፎቻ ራጋ መኰንኖች ውስጥ ከሁሉም የበለጠ በእድሜ ባለፀጋ የሆነችው የስብሰባ ጠሪ ወይም “አፈ ጉባኤ” መዋጮ ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡ ገንዘብ ያዥም አለ፡፡

በማንኛውም አባል ቤት የአፎቻ ማህበር ስብሰባ በሚካሄድበት ጊዜ ከሁሉም በእድሜ የገፉት "አሚር ነደባ" የክብር መቀመጫ በዕድሜ ያነሱት ደግሞ ሌላው መቀመጫ ይቀመጣሉ፡፡

ቀደም ሲል በሐረር ውስጥ ባሐ የአፎቻን ተግባር እንደሚያከናውን ተጠቅሷል፡፡ ይህ አሠራር ሊከሰት የቻለው አንዲት ሴት አንድ ጊዜ አባል ከሆነች በኋላ መልሳ ስለማትወጣ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በቤተሰብ ውስጥ ሠርግ ሲኖር በሥራውም በዘፈኑም፣ በፀሎቱም በጭፈራውም ተካፋይ የሚሆኑ የአፎቻ አባላት ብቻ ሳይሆኑ የባሃ አባላትም ናቸው፡፡ ይህ ተሳትፎ ሀዘን በሚደርስበት ጊዜ ይኖራል የባሐና የአፎቻ አባላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እየተፈራረቁ ይወጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት የአፎቻ አባላት ምግብ ሲያዘጋጁ የባሃ አባላት ደግሞ ይዘፍናሉ፡፡ ይህ ጠዋት የሚፈፀም ሲሆን ከሰአት በኋላ ደግሞ የዘፈኑት ይሠራሉ፤ የሠሩት ደግሞ ይዘፍሉ፡፡

በመካከለኛ እድሜና በአዛውንትነት ዕድሜ የሚገኙ የአፎቻ አባላት የሆኑ ሁሉ በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ የአፎቻን ምንነት በተግባር መተርጐም ይጠበቅባቸዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ፣ ሴቶች የአፎቻቸው እንቅስቃሴ ልክ እንደ ወንዶቹ አፎቻ ሁሉ ለከተማዋ ሕይወት በጣም ጠቃሚ አስተዋፅኦ አለው፡፡ አስረጂዎች እንደሚናገሩት በሀዘን ሕብረተሰቡ እንደ ረሃብና ወረርሽኝ ያለ አደጋ ሲደርስ የሚያደርገው አስተዋጽኦ የማይናቅ እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡

የቀብር ስነ-ስርዓት በሚደረግበት ጊዜ የወንድ አፎቻ አባላት የመቃብር ቁፋሮውን፣ የመቅበሩን፣ የቀብሩን ፀሎት፣ መቃብሩ ባለበት ስፍራ ከግንቡ ውጭ ያከናውናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለሐዘንተኛው ቤተሰብ በምግብ መልክ ያዋጣሉ፡፡ ይሁንና ምግብና መጠጥ የማዘጋጀቱን ኃላፊነት የሚወስዱት ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ የመቅበሩ ሥራ በወንዶቹ የሚከናወን ቢሆንም ሴቶችም እቤት ሆነው በፀሎቱ ተካፋይ ይሆናሉ፡፡

የሴቶች አፎቻ በአስቸኳይ ፀሎት ጊዜም ረሃብ ወይም ወረርሽኝ ሲደርስ ከወንዶቹ ያላነሰ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ የተረጋጠ ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የመላ ከተማዋን አፎቻዎች ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ ሲፈጠር የወንዶቹ አፎቻ ከግንቡ ውጭ ወዳሉት አድባራት ሄደው ሲፀልዩ ሴቶቹ ደግሞ በግንቡ ውስጥ ባሉት አድባራት ይፀልያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች ምግብ አዘጋጅተው ሕዝብ ወደ ተሰበሰበበት በተለይም እንደ ገበያ ወዳለበት ቦታ በመውሰድ ያድላሉ፡፡ አፎቻዎች ከዚህ በተጨማሪ ልጆቻቸው አድገው ወደ ሌላ ስፍራ የሄዱባቸውና ባል የሞተባቸውን አሮጊቶች ይረዳሉ፡፡ አፎቻ አባላቱን በሥራ ማድከምና ጋብቻ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ግንኙነቱ ሞቅ ደመቅ ያለ እንዲሆን ለአሮጊቶች የመኖሪያ መጠለያ ለመስጠት፣ ከዚያም ባሻገር ለቤተሰቡ አስፈላጊውን ሁሉ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ የአፎቻ አባልነት በአንድ በኩል የሐረሪዎችን ወግ ጠባይና ባህል አጥብቆ መያዝን የሚጠይቅ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን የተቀረው የሙስሊም ዓለም ከሴቶች ከሚጠብቀው አንፃር ሲታይ ነፃ ሆነው ለመወሰን የሚችሉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ሠርግን በሚመለከት ዝርዝር መግለጫ እሰጣለሁ፡፡ በአባሪው ውስጥም ስለ እለቱ ስለስጦታው እና ስለማህበራዊ ቡድኖች እንቅስቃሴ ዝርዝር ሰንጠረዥ እንዲኖር አድርጌአለሁ፡፡

በዝምድና ደረጃ በዕድሜና በፆታ እንዲሁም በማህበር በአባልነት ደረጃ መለየት በየትም ስፍራ የተለመደ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የትልልቅ ሰዎች ማለትም የአባት ዘመዶችና የአፎቻ አባላት ጥሪ የሚከናወነው በአዋቂዎች አብዛኛውን ጊዜም በአባቶች የአፎቻ አባላት መልዕክተኞች ነው፡፡ ለአዋቂ ሴቶችም በመጀመሪያ በአዋቂ ሴት የጥሪ መልእክት ይተላለፋል፡፡ ካለበለዚያ ስነ-ስርዓቱን የበለጠ እናክብር ከተባለም ሁለት የአፎቻ አባት መልዕክተኞች በየቤቱ እየዞሩ የጥሪ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ያላገቡ ልጃገረዶች ማለትም አብዛኛውን ጊዜ የሙሽራዋ ጓደኞች ዘመዶች ወይም የሙሽራው እህቶች የሚጠሩት ባልተዳሩ ልጃረዶች ሲሆን ሙሽራዋ ራሷ የምትጋብዝ ቢሆን ግን በሦስት ጓደኞቿ ታጅባ ትሄዳለች፡፡ ከሦስቱ ጓደኞቿ መካከል ሁለቱ በአንድ ፎጣ ይሸፍናሉ፡፡ ያልተዳሩ ወጣት ወንዶችም የሚጋብዙት እንዲሁ ባልተዳሩ ወጣት ወንዶች ነው፡፡ ይህም ስነ-ስርዓት በሙሽራውና በጓደኞቹ ወይም በሙሽራው ወንድምና ጓደኞች ይሠራል፡፡

## ቤተሰብ ጓደኝነትና ማህበረሰባዊ አደረጃጀት /አፎቻ/ በከተማይቱ ያላቸው ቦታና ስርጭት

የሐረር ከተማ ማህበራዊ ተዋሕዶ በሦስት የመጀመሪያ ደረጃ ተቋማት ላይ በመሞርኮዝ የተከፋፈለ ነው፡፡ እነዚህም አህሊ /ቤተሰባዊ ትሥሥር /ማሪንያም ጋብቻና አፎቻ /ማህበረሰባዊ አደረጃጀት/ ናቸው፡፡

በሠንጠረዥ 1 ላይ ያለውን መሠረት ሃሳብ በግንዛቤ ውስጥ ካስገባን ዘንድ ስለ ሐረር ከተማ ያሉትን አህሊዎች የአሰረጫጨት ሁኔታ በሚከተለው መንገድ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

1ኛ/ እያንዳንዱ አህሊ በአንድ በተወሰነ የከተማዋ ዞን ወይን በተጎራባች መንገዶችና ክፍል ከመከማቸት ይልቅ በጠቅላላው ክልል ውስጥ በብዛትም ይሁን አነስተኛ በሆነ አኳኃን ተበታትነው ይገኛሉ፡፡

2ኛ/ በዚህ ስርጭት አኳኋን ዋልድሮን በጥናቱ እንደሚገልፀው በአንዳንድ ቦታዎች የደም ትሥሥር ያላቸው ሰዎች ተከማችተው በመላው ከተማ ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ ከእያንዳንዱ ቤት ጋር በዝምድና ተሳስሯል፡፡ በመጨረሻም ይህ ትስስር መላውን ሕዝብ ያዳረሰና በከተማው ነዋሪ ከፍተኛ ደረጃ መወዳጀት እንዲፈጠርና በማህበራዊ ኑሮውም አንድ እንዲሆን ያደርገዋል ከዚህም የተነሳ አንድ የሐረሪ ሰው በቅርቡ የማያውቀውን ሐረሪ ቢያገኘው ከዘመዱ ጋር እንደተገናኘ አድርጐ ይቆጥረዋል፡፡

## ጓደኝነት በሐረሪ

የሠፈራቸው የመልክዓ ምድር አቀማመጥ ስርጭቱ /ቅርበቱ/ ወይም የጓደኞቹን ዕለታዊ ግንኙነት የሚጐዳ መስሎ አይታይም። ምክንያቱም ራሳቸው በየቀኑ ስለሚፈላለጉና ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ስለሚሰበሰቡ ነው። ነገር ግን አንዱ ልጅ ከሌላ አካባቢ ጓደኞችን ከመሠረተ በማህበራዊ ሕይወቱና በቀበሌው ላለው ግንኙነት ማህበራዊ ድጋፍ ይሰጠዋል።

## የሐረር ሴቶች

## የሴቶች ደረጃን በተመለከተ

እንዳለ የሚያመለክት ሁኔታዎች ቢኖሩም በሌሎች አገር ከሚገኙ ሙስሊም እህቶች አንፃር ስትታይ ነፃ ናት ማለት ይቻላል። በሐረሪ ሴት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር የሚኖረው ከተዳረች በኋላ አንድ አመት እስኪሞላት ድረስ ብቻ ነው። ዛሬ ግን ቁጥጥሩ ይህን ያህል የጠበቀ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ፈቷን አትሽፈንም ባሏ ባይኖር እንኳን ወንዶች እንግዳ መቀበያ ክፍል ድረስ ለመቀበልና ለማስተናገድ ትችላለች። አብዛኛውን ጊዜ የራስ የሆነ የንግድ ሥራ ታካሂዳለች ወይም ታካሂድ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው አንድም የሐገር ባህል እቃዎችን በመሸጥ ካለበለዚያም ለሐረሪ ቤተሰቦች አገልግሎት የሚውለውን ልዩ ልዩ የአለላ ስፌት በመስፋት ነው። ስለዚህ አንዲት ሴት ምናልባት ከባሏ ጋር ብትፋታ ራሷንና ልጆቿን ለመርዳት ያስችላታል። ሙኽታር /1876/ የተባለው የታሪክ ፀሐፊ ወንዶች ሐረሪዎች በመስክ የእርሻ ተግባር ሲያከናውኑ ሴቶች ምርቱን ገበያ ውስጥ በመሸጥ ቤተሰቦቻቸውን ይንከባከቡ ነበር ብሏል። ይኸው ሙኽታር የተባለ ፀሐፊ እንዳጋለጠውም ሐረሪ ወንዶች ሚስቶቻቸው በጣም ቀናተኞች በመሆናቸው ከአንዲት ሴት በላይ አያገቡም። ከጋብቻ ውጭ ዝሙት መፈፀምም ሆነ መፋታት እምብዛም አይታይም። ሪቻርድ በርተንና ፖሊትስኪ /1888/ እንድገለፁት ሐረሪ ሴቶች ለልል ሞራልና ለሽርሙጥና አይንበረከኩም።

ከዚህ በላይ ደግሞ ለአንዷት ሐረሪ ሴት በማህበራዊ ሕይወቷ አፎቻዋ የበለጠ ነፃነት ይሰጣታል። ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሐረሪ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ጥንድ ጥንድ ሆነው ያማረና ከአበባ የተሠራ ስፌት ለስጦታ የሚሆን ምግብ በራሳቸው ላይ ተሸክመው በኩራት መንፈስ ሲጓዙ ማየት የተለመደ ነው።

እንኳንስ ከተማ ለከተማ በእድሜያቸው የገፉ ወይም ባል የሌላቸው ሴቶች ወደ መካ ለፀሎት የሚሄዱት ብቻቸውን ነው። ይህንን ተግባር ገንዘብ ካላቸው በተደጋጋሚ ሊፈፅሙ የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ ከፈለጉ ከቅዱስ ስፍራ አጠገብ ለመቀመጥ ቢፈልጉም ማንንም ማስፈቀድ ሳያሻቸው እዚያው መኖር ይችላሉ።

አንዷት ሐረሪ ሴት ባሏ ከሞተባት ከአራት ወራት በኋላ ተመልሳ ሌላ ወንድ ለማግባት ትችላለች። ቤተሰቦቿም ቢሆኑ እንድታገባ ሐሳብ ሊሰጧት ይችላሉ። ይሁንና ልጆች ካሏቸው አዲሱ ባል ልጆቹን በሚገባ ሊይዝልኝ አይችልም በሚል ግምት ከማግባት ይወሰናሉ። ይህም አንዷት ወጣት በቤተሰብ የመጣላትን ባል ሳታቅማማ በምታገባበት ሁኔታ ትልቅ ሴት ግን ቤተሰቦቿ ሐሳብ ቢያቀርቡላት እንኳን ለማግባት አለመፈለጓን የሚመለከት ነው።

ይልቁንም ሐረሪ ሴቶች ፎጣ የተባለ የራስ መሸፈኛ ሻሽ፣ ያገቡ ሴቶች ደግሞ ፀጉራቸውን የሚሸፍኑበት ጉፍታ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸው ከመሆኑ በስተቀር ዓይናቸውን ፈፅሞ አይሸፍኑም።

አንዷት ልጃገረድ በ---- ዓመት ዕድሜ ትዳር ትይዝ እንደነበረ ሁሉ ዛሬም እንደዚሁ ናት። ፍቺ ያኔ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እንብዛም የተለመደ አይደለም። አንድ ሐረሪ ያለው ሚስት በአማካይ ሲታይ አንድ ነው።

ይህም ሆኖ ፍችቺ በሚፈፅሙበት ጊዜ ለሙሽራዋ የተወሰነ ገንዘብ እንደሚሰጣት በጋብቻ ውሉ ላይ ይሰፍራል። ጋብቻው በሚፈርስበት ጊዜ ሴቷ ልጆቿን የማሳደግ ኃላፊነት ሊኖራት ሲችል ይህም ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው። በዚህ መሠረት በርካታ በአለላ ሥራና በቅርፃ ቅርፅ ሥራ ጥሩ ችሎታ ያላቸው ሴቶች በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተው የልጆቻቸው የትምህርት ቤት ክፍያ ሳይቀር የሚከፍሉት በገንዘብና

በእናትነት መንፈስ አስፈላጊውን እንክብካቤ አድርገው የሚያሳድጉ ሆነው ይገኛሉ። ጥንትም ቢሆን ሴቶች በጥሩ ሚስትነታቸው እንደሚታወቁና ባሎቻቸው ያመረቱትን ወደ ገበያ አውጥተው በመሸጥ የቤቱን ወጭ በከፊል ይሸፍኑ እንደነበር ገልፆታል።

ባህላዊ በሆኑ የሴቶች አፎቻዎች እንደ ሠርግና ሀዘን ያሉ ማህበራዊ ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲሁም እኩልነት በተሞላበት ሁኔታ ይወጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ በከተማው ውስጥና ከከተማው ውጭ ባሉት አድባራት የፀሎት ስነ-ስርዓት ሲካሄድ አብዛኛውን ጊዜ ምግብ የሚያቀርቡት፣ በፀሎትና በመዝሙር የሚሳተፉት የሴት አፎቻዎች ናቸው። እንደ አይዓቢዳ አይዓይሻ አይ ፋጡማ ማሕሙድ ያሉ የራሳቸው ሴት ቅዱሳን አሏቸው። ከነዚህም ውስጥ አይ አቢዳ ከሁሉም የበለጠ ታዋቂ ናቸው። የሴቶች አፎቻዎች የተጻፋት ባይሆን ሕግና ደንብ አላቸው። በተለምዶ ወይም ያልተፃፈ በዚህ ሕግና ደንብ መሠረት የተወሰኑ አድባራትን በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ መጐብኘት አለባቸው።

ምንም እንኳን በምዔቡ ማህበረሰብ ውስጥ ካለው ልምድ አንፃር ሲታይ የጾታ ልዩነትና የሥራ ክፍፍል ቢኖርም የሐረሪ የሴቶች ማህበራዊ ተቋም የታፈነ ነው ለማለት ያስቸግራል።

አፎቻን በጥቅሉ ስንመለከተው በሌሎች የሙስሊም ከተሞች አንድ ዞን እንደ ማህበረሰባዊ መለያ /መታወቂያ/ ተደርጎ ይቆጠራል። በጎረቤቶች ደረጃ ጥናት በደንብ የተካሄደባቸው የሙስሊም ከተሞች ውስጥ ዳል ኢክልማን ቡጃድ የተባለችውን የሞሮኮ ከተማ ዳርብን ወይም ዞን በደንብ የተደራጀችና ሕዝብ በከፍተኛ ዝምድና የተሳሰረ መሆኑን ይገልፃል። ኢክልማን 1974፡283 “እኔ የሐረርን ቶያን በቡዳድ ዓይነቱ ዳርብ ነው አልለውም። በተግባር እንደሞከርኩትም ሐረር ራሷን የቻለች ከተማ ነች። እንዲያውም የሐረር ቶያ በመሠረቱ ራሱን የቻለ ተቋምና የከተማዋ ተቋማት ምንነት ገላጭ ነው” ሲልም ያብራራል።

ሐረርን ከዚህ የሚለያት ነገር ቢኖር የባህላዊ ትርጓሜዋ ነው። እንዲያውም ሐረር በኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ያላት የሙስሊም ከተማ ናት። ከሐረሪ አፎቻ ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ የአማራው ዕድር እዚያው ሐረር ከተማ ውስጥ ይገኛል።

አንዳንድ ሁኔታዎች የአማራውን ተዛምዶ ከሐረሪም ጋር እንዳለ ይጠቁማሉ፡፡ የሐረሪ ቋንቋ ሴሜቲክ በመሆኑ ከስልጤ ቋንቋ ጋር ያለው ግንኙነት ማየቱ ይጠቅማል፡፡ ሔርበርት ሉዊስ እንዳለው ደግሞ ዝምደና ጓደኝነትና ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማህበረሰባዊ አደረጃጀት ለማወቅ ይጠቅማል፡፡

በሐረርና በሌሎች የሙስሊም ከተሞች ውስጥ ያለው ማህበራዊ አደረጃጀት የተለየ የሆነው ራሱን በቻለ የቦታ፤ የዘመንና ታሪክ አጋጣሚ ነውና የዚህን ውስብስብ ሁኔታዎች ሂደት በጥልቀት ለማወቅ መጣሩ ይበጃል፡፡ ላለፉት አራት ምዕተ ዓመታት ያህል ሐረር በአንድ ከተማ ብቸኛ ማዕከል፣ በከተማ ለሚኖረው ሐረሪ ጎጆ ነበረች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከረዥም ጊዜ በፊት ወደ እርሷ ለመምጣት ይፈልጉ የነበሩትን መከላከልና በሯን ዘግታ ኖራለች፡፡ የከተማው ሕዝብ ዙሪያውን የከበበው የኦሮሞ ሕዝብ ሐረሪውን በቁጥር ቢበልጡትም የከተማውን ሕብረተሰብ ኢኮኖሚያዊና የንግድ አውታሮችን በመያዝ ተጽዕኖ ያደርግባቸው ነበር፡፡ የሐረሪ ህብረተሰብ በአንድ የከተማው ማዕከል በመወሰኑ ማንነቱን ጠብቆ ኖሯል፡፡

የሐረሪ ብሔረሰብ ከቦታ ቦታ ባለ መንቀሳቀሱም በሌሎች ሙስሊም ከተሞች ውስጥ ያለውን የዘላኖችን ሁኔታ ሳይከተል ቀርቷል፡፡ ይህም በመሆኑ የሐረሪዎች ከተማ የራሷ የሆነ ፈር ተከትላ ከሌሎች ሙስሊም ከተሞች ተለይታለች፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የስፌት ሥራ በሐረር

የሐረሪ ሴቶችና ሐረር የምትታወቀው በእንግዳ መቀበያ ቤት በሚንጠለጠሉ ውብና ማራኪ የአለላ ስፌት ሥራዎችም ጭምር ነው፡፡ ምንም እንኳን አብዛኛው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር እንግዳ ወደ አንድ ሐረሪ ቤት ሲገባ በመጀመሪያ ዓይኑ የሚያርፈው በግድግዳ ላይ በተሰቀሉት በርካታ የአለላ ስፌት ሥራዎች ላይ ሲሆን የአለላ ስራዎቹ አይነት በግድግዳ ላይ በተሰሩ ብቻ የተወሰነ ነው ማለት አይደለም፡፡ ስፌቱ ለእንጀራ፣ ለቆሎና ማቅረቢያነት ሌላው አነስተኛው ከኩል ጀምሮ እስከ ልብስ ማስቀመጫ ከትንሽ ቁና ግማሽ ኩንታል እስከሚይዝ እንቅብ፤ የሚያጠቃልል ከፍተኛ የቤት ቁሳቁስ በመሆኑ ዓይነቱ ጥንካሬውና አሠራሩ እንዲሁም የሚጠይቀው የባለሙያ ችሎታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንዲት የጀበና ማቅረቢያ  የቀለበት ቅርጽ ያላት ስፌት በመጠንም በተሰራችበት ቁሳቁስም በሰራቻት ባለሙያ ከሌላዋ የጀበና ማቅረቢያ እንድትለይ ያስፈልጋል የብዙዎችን የውጭ ሀገር ጐብኝዎች ዓይን የሚማርከውም ይኸው የኪነጥበብ ኃይል መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

ሐረሪዎች በስፌት ስራ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የሚለይበትና የሚመሳሰልበት ሁኔታ ለመንደርደሪያ ያህል ለመሆኑ የስፌት ሥራ መቼ ተጀመረ የሚለውን እንመልከት፡፡

በመሰረቱ የስፌት ስራ በዚህ ጊዜ በዚህ ቦታ በእንደዚህ ያለ ስፍራ ተጀመረ ብሎ መግለጽ አይቻልም፡፡ አንዳንድ ጥንታዊ የአፈታሪክ ማስረጃዎች እንዲያስረዱት ግን ማርድክ የሚባለው የባቢሎን አምላክ እንደ ስፌት ስረሰ ቀላል ክብደት ያለው ነገር ውሃ ላይ ጣለ የተለያየ ቀለማት ያሉት አፈርም  ቀባው ከዚያም የጥሩ ስፌት መልክ ያለው ቁሳቁስ ከሆነ በኋላ ሰዎች ያንን አስመስለው መስራት ጀመሩ፡፡

የምእራብ አፍሪካ አፈታሪክ ደግሞ አፉ ክፍተት ያለው ክብ ስፌት ስራ ለአያት ቅድመ አያቻቸው ከአምላካቸው እንደተሰጠ ይናገራሉ በቅርስ መጠበቂያ ስፍራዎች ተቀምጠው የሚገኙ ስፌቶች ደግሞ እንደ እባብ እርግብና ሌሎችም ፍጡራን የተሳለባቸው ስለሆነ እንደ ጣኦት የሚጠቀሙባቸው ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ በዚህ ረገድ የአሜሪካ ቀይ ህንዶች ይታወቃሉ፡፡

እንደ ኢትዮጵያ፤ ሱዳን፤ ግብጽ ጥንታዊ አገሮች ደግሞ ከታሪካቸው፤ ከባህላቸው፤ ከአስተሳሰባቸው ካላት ቦታ የስልጣኔ ጉዳና ጋር አብረው የሚሄድ የስፌት ሥራዎች አሏቸው፡፡ የስፌት ስራ የህብረተሰብ እንጂ የግለሰብ ፈጠራ ባለመሆኑ እገሌ ይሰራው ነበር ማለት ቢያስቸግርም ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ በዚህ ረገድ ምርምር ያደረጉ ሊቃውንት ይህንን ለማለት ያስቻላቸው ጥንታዊ ወንዶች ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበረው በአደን ስለሆነና ለአደንም የአለላ ስራ ስለሚያስፈልግ የሴቶች ስራ ግን ፍራፍሬ ለቀማ ጋር የተያያዘ ስለሆነና  ፍራፍሬውን ለመያዝ እቃ መስራት ስለሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡

የስፌት አይነት እንደ ህብረተሰቡ ልምድና ባህል የተለያየ እንደሆነ ሁሉ የሚሰራበት ቴክኒክና ቁሳቁስም እንደሁኔታው ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ መስፌያውን በአለላ አከርማ ወይም በሰሌን አድርገው ውስጡን ሰንበሌጥ በሚባለው ሳር ይጠቀማሉ፡፡ ከባህር ጋር የነበራቸው ግንኙነት ምክንያት የዘንባባ ዝርያ ቅጠሎች ይመጣላቸው ስለነበር በዚህም ይጠቀሙ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የክርነት ባህሪ የሚያሳይ ተክሎች ለዚህ አገልግሎት ይውሉ ነበር፡፡ ከስፌት ስራዎች  አመጣጥ መረዳት    ይቻላል፡፡በአካባቢያቸው   ከቀርከሀና የዋርካ ዝርያዎችን የሚያገኙት በንግድ ምክንያት የሚገኙም እንደ አለላ እየሰነጠቁ ለስፌት ስራ የሚጠቀሙ ጥንትም ሆነ ዛሬ አሉ፡፡

ስፌቶች ውሃ ለመቋጠር ከሚችሉ እስከ ሽክሽክ የሚሰሩ ስለሆነ በውስጣቸው ያለው የተክል ዓይነትና መጠብም ሆነ የአሰራራቸው ዓይነት የተለየ ሲሆን ለምሳሌ ሙዳይ ላይም ውስጥም በቀጭኑ የተሰነጠቀ አለላ ሊሆን ቢችል ሰፌድ ወይም ለወማት ግን ውስጡ በሰንበሌጥ ሆኖ ላዩ በአለላ ካለበለዚያ በሰሌን ሊሰፋ ይችላል፡፡

## የስፌት ስራ የሚያጠቃልለው

1. በአለላ የሚሰራው ሙዳይ፤ ሰፌድ፤ ቁና፤ እንቅብ፤ መሶብ፤ አገልግል መሶብ ወርቅ ወዘተ…

2. በሰሌን የሚሰራው የወለል ምንጣፍ የግድግዳ ጌጥ፤ የምሳ ማቅረቢያ ሌማት፤ እንደ ዘንቢል ወይም እንደ ደብተራ፤ አኩፋዳ፤ የእቃ መያዣ ሌማት

3. በሸንበቆና በሸንበቆ ዝርያዎች የሚሰራው ቅርጫት የእህል መያዣ ጐተራ ወይም አነስተኛ ልብስ መያዣ ነገር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የስፌት ስራ ጥበብ ራሱን የቻለ ሰፊ በመሆኑ ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም በአነስተኛ ክብ ነገር ጀምሮ ስራው እስኪያልቅ ድረስ ክብ አድርጐ መስራት የወንጭፍ ስራ የቅርጫት ስራ የሰሌን ስራ፤ የስጋጃ ስራ ብሎ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ክብ አድርጐ የመስራትም ሆነ የወነጭፍ የሰሌንም ሆነ የወንፊት ሥራ እንድየዘመናት እንደሰው ብልሃት እንዲሁም እንደተሰራበት ነገር የሚለያይ በመሆኑ እዚህ ላይ መዘርዘር አያስፈለግል ቀርጹም ቢሆን ክብ አራት መዕዘን ሦስት ማዕዘን ወይም አራት ማዕዘን በላይ ሊሆን ይቻላል፡፡

በዚህ ረገድ የሐረርን ስፌት ስንገመግም ሁሉም የአሰራር ዓይነት ዘይቤዎች ያሉ ከመሆናቸውም በላይ የምስራቅ አፍሪካ የመካከለኛው ምስራቅና የሩቅ ምስራቅ ብቻ ሳይሆን አንዳንዶችም ከጥንት አውሮፓውያንና አሜሪካውያን ሥራዎች የሚመሳሰሉ እንዳሉ ስለ ስፌት ከተደረጉ ጥናቶች መረዳት ይቻላል፡፡

ሐረር በተለይም ከምስራቅ አፍሪካ፤ ከመካከለኛው ምስራቅ፤ ከሩቅ ምስራቅ ጋር ለረዥም ዓመታት የንግድ ልውውጥ ስታደርግ ስለቆየች ከእስልምና ጋር በተያያዘ ጉዳዮችም የጠበቀ ግንኙነት ስላላት የስፌት ስራዎች ላይ በዓረብኛ ፊደላት የሚገለፁ አንዳንድ የሃይማኖት ቃላት የሚያመለክቱት ይህን እውነታ ይመስላል፡፡ ይህም ሆኖ የሐረሪዎች የስፌት ስራ የራሱ የሆነ የመለያ ባህርይ ስላለው ዝርዝር ጥናት ይጠይቃል በጥቅሉ ሲታይ ግን፡-

ሀ. ስፌት የሐረር ሴቶች መታወቂያ ምልክት የወንዶች ኩራት የክብር መለኪያ

ለ. የሴቶች የባለሙያነት መለኪያና መመኪያ፤

ሐ.የአንድ ውብ የእጅ ሥራ ባለቤት፤

መ. በስፌት የተንቆጠቆጠ ቤት ጌጥና የአደራረደር ችሎታ ማንፀባረቂያ፤

ሠ. በልዩ ልዩ ምክንያት ስጦታ መስጠት ሲያስፈልግ ያለችግር ግዴታን መወጫ ማገልገሉ፤

ረ. ከሁሉም በላይ የቤት ቁሳቁስ ሆነው አንድ ቤተሰብ ያገለግላሉ። አጠቃላይ የስፌት ስራ ቀደም ያለ ቢመስልም ከጥንት እስከ ዛሬ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ይኸው የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ዛሬ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል።

በድሮ ጊዜ አንዲት የሐረር ልጃገረድ በስፌት ሙያ እንድትቀኝ ከልጅነት እድሜዋ ጀምራ እንድትሰለጥን ትደረጋለች የስፌት ስራ የእድሜ ልክ ሙያ መሆኑን ህብረተሰቡ የሚያምንበት ከመሆኑም በላይ ሕንፃ አዋቂ እንዲሁም ደህና ሀብታም ሳይባል የሚሳተፍበት ነው። በአካባቢው ልምድ መሰረት የመጀመሪያው የስፌት ሥራ ይቃጠልና በአመድ ልጅቷ እጇን እንድትቀባው ይደረግ ነበር። ይህም ሆኖ በአንድ በኩል የሥራ መጀመርን ሲያበስር በሌላ በኩል ደግሞ በሙያው ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ የመሰረት ድንጋይ እንደመጣል ይቆጠራል። በአሁኑ ጊዜም ቢሆን እድሜያቸው እስከ ዘጠኝ ዓመት የሚደርሱ ህፃናት ማለትም ጌሎች ለሚባሉት የሕፃናት ጓደኝነት ማህበራት ያልደረሱ “በሞይ ጋር” ማለትም በቤት ሙያ መለማመጃ ቤት ሆነው ከእድሜ እኩያቸው ጋር እንዲማሩ ይደረጋል። እነዚህ ሕፃናት ሙያውን የሚማሩት ጠዋት ዶሮ መጮህ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሲሆን የስፌት ሥራውን የምትለማመደው ግን የቤቱንም ሆነ የእርሻውን ሥራ አከናውና በምትመለስበት ጊዜ ማለትም ከአምስትና ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ነው። ልጃገረዲቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የምትሰራው ስፌት “ቢጢ ቢጢ” ተብሎ ሲጠራ ይህም ቀለም በሌለው ማለትም ከተፈጥሮ በተገኘው አለላ የሚሰራ ሲሆን ትንሽና ክረግ ነው። በደንብ መስፋት እንደ ጀመረች በቀይና በጥቁር አለላ መስፋት ትጀምራለች። ከዚያም አረንጓዴ በቢጫና በሌሎችም ቀለማት መስፋት ትቀጥላለች።

ከዚያም እስከተባለው የአለሳ ስፌት የመጨረሻ ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ከእለት ወደ እለት ሙያዋን ለማሻሻል ጥረት ታደርጋለች። ሆኖም እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚደረገው ትግል እስከ እድሜ ልክ ያለው ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል።

በእድሜ አንጋፋ የሆኑ እናቶች እንደሚያስረዱት አንዲት ልጃገረድ ከመዳሯ በፊት አንድ ጉፍታ ሙዳይ /የሻሽ ማስቀመጫ/ ሁለት /የእጣን ሙዳይ/ ሁለት ቢሻ ሙዳይ /የማስቲካ ሙዳይ/ አራት ኡፍ /የዝሆን አፍንጫ መሰል ስፌት/ አራት ፊጃን ጋር /የሲኒ ማስቀመጫ/ ስድስት ሰህና ሰጋሪ /ትንንሽ ሰፌዶች/ ማዘጋጀት አለባት። በአሁኑ ጊዜ ዋጋው ውድ በመሆኑ ቀረ እንጂ ትልቅና ውብ ቁናም ይሰፉ ነበር። ከዚህ ሌላ ሐማት ሞት (የአማት ስፌት)፤ ኡኻት ሞት (የእንጀራ ስፌት) መስራት አለባቸው።

ከሐረር ሴቶች ልምድ እንደታየው አብዛኛው ሴት በሁለት የስፌት ሥራ የተዋጣላት አዋቂ ከቶ ሊሆን አይችልም። ችሎታ ያላቸው ቢኖሩ እንኳን በጣም ጥቂቶች ናቸው። ሆኖም በአንድ ወይም በሁለት ዓይነት የስፌት ሥራ ታዋቂ መሆን ይቻላል።

በሐረሪዎች ዘንድ የስፌት ባለሙያ አለመሆን ብቻ ሳይሆን በቤቶች ግድግዳዎች ላይ በዓይነት በዓይነታቸው ማንጠልጠል ካልቻለች "ቦሰቲ" /ግዴለሽ ወይም ሰነፍ/ ተብለው ይሰደባሉ። በዚህም ምክንያት ለአንዱ ሰፌድ ዓይነት የተመደበውን ቦታ ሌላውን ማስቀመጥም ሆነ የተለያዩ ዓይነቶችን ደራርቦ ማስቀመጥ እንደ ነውር ይቆጠራል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው በሐረር ውስጥ የስፌት ሥራ ጥቅም ለአገልግሎት ለቤት ማስዋቢያና ለማንነት መለያ ተብሎ በሦስት ይከፈላል። ይሁንና ይህ የቆየ ልምድ በነበረበት ሊቀጥል ይችላል ብለን ስንጠይቅ ብዙ አጠያያቂ ጉዳዮች እንዳሉ እንረዳለን። ሴቶች በልጅነታቸው ወደ ትምህርት ቤት በመሄዳቸውና በቤት ያገኙት የነበረው የስፌት ስራ በትምህርት ቤት ስለማይሰጥ የስፌት ስራዎችን የሚተኩ ከብረትና በፕላስቲክ የተሰሩ መገልገያዎች በመቅረባቸው ዋጋውም ውድ ስለሆነና በሌሎችም ምክንያቶች እየተዳከመ ነው። ነገር ግን የስፌትሥራ ቅርስ የህብረተሰቡ ማንነት መለያና ከነባር ባህሉ ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑ ትኩረት የሚገባው ጉዳይ ነው።

# ክፍል አምስት

# ምዕራፍ አሥር

## ሐረር የእስልምና ማእከል

### 10.1 ታሪካዊ መልካ ምድራዊ ዳራ

የሐረር አምባ ለደገኛ ክርስቲያንና ኢትዮጵያን ለአፍሪካ ቀንድ ቆለኛ ሕዝቦች ስለዚህ አካበቢ ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሚታገሉበት ቋሚ ቀጠና ሆኖ ቆይቷል፡፡ይህም የቆየ የባላንጣነት ትግል በዘመናውያኑ የኢትዮጵያና ሱማሌ መንግስታት በመወረሱ ሁለቱም ታሪካዊ ማስረጃ በማቅረብ የሕጋዊ አለኝታነት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ጉዳዩ ከዚህ አንፃር ሲታይ የትኛው ሕዝብ አካበቢውን ቀድሞ እንደያዘ እንደኖረበት ባህላትና ፖለቲካዊ አመለካከቱም ወደ የትኛው አቅጣጫ እንዳዘነበለ መወሰን ያስቸግራል፡፡

በመሠረቱ የሐረር አምባ ከአዋሽ ደቡብ ምስራቅ ዝቅተኛ ቦታዎች ከሚነሱ የጨርጨር ተራሮች ጀምሮ እስከ ሐርጌሳ የሚዘልቅ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ አለው በዚህ ስፍራና በሚዋሰኑት በአርሲ የተራራ ሰንሰለቶች አካባቢዋ በርካታ የቅዱሳን ሰዎች መቃብሮች አድባራት በሚያስደንቅ ሁኔታ ይገኛሉ፡፡

## 10.2 እስልምና በሐረር አምባ

ሐረርም በ1521 የሙስሊም ማዕከል የነበሩት ፉኛምቢራንና ደከርን በተመለከተ የእስላማዊና ዓረባዊ ባህል እምበርት ስፍራ ሆናለች ከዚህ አኳያ ከሰሜን ሱማሌ ድንበር በተለይም ከዘይላ ጋር የነበራት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ገንኙነት እስከዚሀ ዘመን ድረስ ለህልውናዋ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ አካባቢ አንደዋነኛ ተደርጐ ይወሰድ የነበረው የእስልምና አይነትም የሱፊ ተከታዮች ያራምድ የነበረው ስርዓት ነው፡፡በዚህ አይነት ዓላማ የቅዱሳንና የነርሱን አድባራት ቅዱስ መቃብሮች በሚመለከት የተሟላ መረጃ ለመስጠት ባይሆንም በሱማሌ ኢትዮጵያውያን ድንበር የነበረው የቆየና የተሳሰረ ታሪክ መኖሩን ለማመላከት ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የነበረው የብሔረሰብ ስብጥርና ለውጥም ምን ይመስል እንደነበር ለሚነሳ ጥያቄ መልስ የሚሰጠው በመጠኑ ነው፡፡ ስለሆነ እስካአሁን ባለው ማስረጃ ለማለት የሚቻለው በሐረር አምባ የነበሩ ጥንታውያን ነዋሪዎች ሐረላ የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህም ነዋሪዎች በ14ኛውና በ16ኛው ክፍል ዘመን በሥልጣኔው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የግብርና አሠራር ከድንጋይ የተሠሩ ከተማዎችም ነበሯቸው የሐረሪዎች አባት ነው ተብሎ የሚታወቀው አባድር ሁመር አል ረዲ በ13ኛ ክፍለ ዘመን ሐረር ሲደርስ በሐርላ ጋቱራ እና በአርጎባ ሙስሊም ሕዝቦች ተቀባይነት አገኘ፡፡ በመሰረቱ እነዚህ ሕዝቦች በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ከሚገኘው የሸዋ ገደላማ ስፍራዎች የመጡ ናቸው፡፡ የአሁኑ ጊዜ ሐረሪዎችም በአብዛኛው በጦርነትና በ16ኛው ክፍለ ዘመን በደረሰው ረሃብ ካለቁት ሐርላዎችም በተዋረድ የተረፉ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ላለፉት 300 ዓመታትና ከዚያም በላይ ለሆነ ጊዜ ለሐረር አምባዎች ተንሰራፍቶ ይኖሩ የነበሩት እነዚሁ የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች በተጠቀሱት ምክንያቶች ቁጥራቸው አንሶ በሁለት የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተበልጠውና በሐረር ከተማ ውስጥ ተወስነው መኖር ጀመሩ፡፡

የተፃፉ የታሪክ ማስረጃዎችን ለመጥቀስ እስከሚቻለው ድረስ አብዛኛው የሐረር አምባ ነዋሪዎች ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ እርግጥ የኢትዮጵያውያን ግዛት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረበት ዘመን

ማለትም በ14ኛው ክፍለ ዘመን መካከልና ጦርነት በ1529 ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሐረር አምባ በመጠኑም ቢሆን በደገኞቹ ክርስትያኖች ተይዞ ነበር በዚህም መሰረት የአጼ ይስሐቅ 1414-1429 ሰራዊት እስከ ዘይላ የደረሰ ሲሆን ማዕከሉንም በሐረር አምባ ላይ አድርጐ ነበር፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ ቁጥር የነበረው ወታደርና ያኔ ጬዋ በመባል ይታወቁ የነበሩት የጦር መሳሪያ የታጠቁ ሰፋሪዎች ከሕዝቡ ጋር በመቀላለቀል በአካባቢው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ከሙስሊም ጋር እንዲቀላቀል አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳን የክርስትያን ቁጥር በአንዳንድ ታሪክ ፀሐፊዎች የተጋነነ ቢመስልም ኤረርና ጋራሙለታ እንደነበሩም የአርኪዮሎጂ ምርምር ውጤቶች ያስረዳሉ፡፡ እውነታው ግን ኢትዮጵያ በሐረር አምባዎች ላይ የበላይነት አግኝተው ነበር በሚባሉት ዘመን እንኳን በዳሞት በፋጣጋር የነበሩት ክርስቲያኖች ከሙስሊም አንፃር ሲታይ አልፎ አልፎ በኪስ ስፍራዎች (ፓኬት) የተቀመጡ እንጂ ብዙዎች አልነበሩም፡፡

ይህም ሲባል ያለምክንያት አይደለም፡፡ ቀደም ሲል በ1200 አካበቢ አርጐባ የሚባሉ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በስተምዕራብ ከሚገኘው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ገዳማት ስፍራዎች ወደ ሐረር አምባዎች እንደፈለሱ ተጠቅሷል፡፡ ከዚያም በፊት ግን በዚህ አካባቢ የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ዋነኛ ምንጭ ይሆናል ብሎ የሚታሰበው ከሰሜን ሱማሌ ዳርቻ በተለይም የዘይላ ከተማ ነው፡፡ እኛ እስከምናውቀው ድረስ በወቅቱ ከአረቢያ የባህር ወሽመጥ ያለማቃረጥ ይመጡ በነበሩት ሙስሊሞች ምክንያት ከመጀመሪያው አንድ ሺ ዓመተ ምህረት አንስቶ በዚሁ ስፍራ እስልምና ስር ሰዶ የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ከአዋሽ ወንዝ በስተምስራቅ የሚገኙ ሕዝቦች ወጐች ኢስማኢል ጂበርቲ የሚባል የሐይማኖት አባት በ10ኛው በ11ኛው ክፍለ ዘመን የእስልምናን ሐይማኖት እንዲስፋፋ ያመላክታሉ፡፡

በዚህ ዘመን እስልምና ከባህር ዳርቻ ዘልቆ ወደ ውስጥ በመግባት እስከ ሐረር አምባ ሥር እንደተስፋፋ መገመት ይቻላል፡፡ ይሁንና አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት አዲሱ ሃይማኖት ሊስፋፋ የቻለው ስደተኛ ነጋዴዎች አማኝ ባልሆኑት ሕዝቦች መካከል ገብተው እስልምናን በማስተማራቸው ነው የሚል ግምት እንዳለ እንደቻለም ትሪንግሃም አጠናቅሮታል፡፡ (1965፡149)

የዓረቦች በሕዝቡ መካከል መግባት በሕብረተሰብ ብሔረሰባዊ ማንነት ላይ ያመጣው ሉውጥ የለም ማለት የሚቻል ሲሆን በባህላዊ አመለካከታቸው የራሳቸውንና ደረጃቸውን በማወቅ በኩል ግን የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ይህም ሆኖ በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ብዙ ሙስሊሞች ራሳቸውን አንድም የነቢዩ መሐመድ የራሳቸው ካለበለዚያም በእስልምና ታሪክ ገፅ ዝና የነበራቸው ታላላቅ ሰዎች ዝርያዎች ነበሩ ብለው ስለሚናገሩት ጉዳይ ግን የተገኘ መረጃ የለም እንዲህ ያለውን የዘር ሐረግ ቆጠራ የምንቀበል ከሆነ እስከ ኢስማኢል ጀበርቲ ድረስ የሚቆጠሩትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሁሉ የአንድ ሰው የልጅ ልጆች ናቸው ብለን መቀበላችን ነው፡፡

አባድር ከ405 ሼኮች መስፋፋት ጋር በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሲደርስ ሐረሳ ጋቱሪና አርጐባ የሚባሉት የዋሪ ሕዝቦች እስላሞች ነበሩ አፈታሪክ ዋግነር (1978፤30) የሸዋ የሱልጣን መንግስትም በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን እንደተመሰረተ ከሚገልፀው ታሪክ ጋር ይገጥማል፡፡ ይህም ከአባድር ጋር የመጣው ቡድን የመጀመሪያው የእስልምና ሃይማኖት መምህር ሳይሆን ሃይማኖቱ በተጠናከረና ድርጅታዊ መልክ ባለው መንገድ እንዲቀጥል ያደረጉ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ይሁንና በሐረር አምባ መጀመሪያው ቅዱስ ከመሆናቸውም በላይ መታሰቢያ ይሆን ዘንድም ልዩ አድባር እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ የኢስማኢል ዲጂበርቲ ቅዱስ አድባርም በሰሜን ሱማልያ ኢረጋሽ በሚባል ወረደ ልዩ ስሙ ሐዳፈቲም በሚባል ስፈራ ይገኛል፡፡

በሐረር አምባ ላይ ለአመስት መቶ ዓመታት ያህል እስልምና የበላይነትን ይዞ ነበር፡፡ በኋላ ግን በሙስልምና ክርስትያኖች መካከል በተደረገው ያለሰለሰ ግጭት ምክንያት ሐረር ራሷ በ1559 ተይዛ ነበር፡፡ ይህም ማለት የእስልምናውን የበላይነት አደጋ ላይ ጥሎት ነበር ማለት አይደለም፡፡ በደቡብ ምስራቅ በተለይም በደዋሮ፤ በፈጣጋር በሃዲያና በባጂ አካበቢ የነበሩትም ስፍራዎች ግን ባልተቋረጠ ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ጥፋት ደርሶባቸዋል፡፡

እንዲህ ያለው ከሱማሌ ብሔረሰብነት ጋር የተያያዘ እስላማዊነት በሚስፋፋበት ጊዜ ከይዞታቸው ርቀት በኦሮሞ ሕዝብ መካከል እስልምና የማያስተምሩ ሐዋርያት እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ከዚህም መካከል ወረቃሉ የሚባሉት የመጀመሪያ አላ ኦሮሞ ከሚባሉት ገር የተቀላቀሉ ሙስሊሞች ይመስላሉ፡፡ እነዚህም እስከ 1880ዎቹ ድረስ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ አዲስ ጎሳ ፈጥረው ነበር፡፡ ቀጥለውም ባሬንቱ ኦሮሞ ከሚባሉት አንስቶ ጨርጨር እስከሚገኙት ኦሮሞች ጋር ኖረዋል ይህም ሲሆን ሱማሌነታቸውን አልረሱም በዚህ መሰረት ኦሮምኛ ብቻ በሚናገሩ ሰዎች አካባቢ በሚኖሩበት ጊዜ የሼክነትን ስፍራና የሙስሊም ሃይማኖት ተወካይነትን ስፍራ ያይገኙ ነበር፡፡

ሌላው እስልምናን የበለጠ ለማስፋፋት የተደረገ ጥረት በሐረሪ ኢመሪት ነው፡፡ ለምሳሌ የመጨረሻው የሐረር አሚር የነበረው አብዱላሂ (1885-1887) ከሱ በፊት የነበረው መሐመድም (1856-1887) ኑኑ ሚታና ያላ የሚባሉ ጎሳዎች መሪች የሐይማኖት መምህራን ልኮ ነበር በ1875 ሐረርን የያዙ ግብፆች ግን በወታደራዊ ኃይል ሊጠቀሙ ሞክረዋል፡፡

በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የቱርክ ጀርመን ፕሮፐጋንዳ በሙስሊሞች መካከል ይካሔድ እንደሆነ ማንኛውንም ፍንጭ ጀሮዎችንና አይኔን ከፍቼ እንድጠባበቅ መመሪያ ነበረኝ፡፡ በቅርቡ ሐረር በሚገኘው በቱርክ ቆንስል አማካይነት ሐጂ መሐመድ ኑር የሚባል ሼኽ ለማነሳሳት ተልኮ እንደነበር ተረድቻለሁ ማጋሎ የሚገኘው የኢጣልያውያን ተወካይም ወደገሎ ወርዶ ስለጉዳዬ ቅድመ ሁኔታ ወይም ሌላ ቅስቀሳ ጉዳይ እንዲያከናውን ግፊት አድርጎ ተሳክቶለት ነበር፡፡

## 10.3 የእስልምና ወደ ሐረር መግባት

በመሰረቱ ሐረር መቼ በታሪክ ነጥብ መስመር እንደተመሰረተች ግልጽ አይደለም፡፡ ምድርን በመቆፈር የታሪክ ምርምር የሚደረግበት አርኪዮሎጂም በደቡብ ኢትዮጵያ ጠንካራ እግሩን አልተከለም፡፡ ያለ ትክክለኛ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ደግሞ ስለከተማዋ አመሰራረትና ዘገምተኛ እድገት የሚኖረን መረጃ ከሰው አስረጂዎችና ሁኔታዎችን አመዛዝኖ ሊሆን ይችላል ብሎ ከመገመት ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖርም፡፡ አሕመድ ሻሚ ከተማዋ በቅድመ እስልምና እንደነበረች ግምቱን ያሰፈረ ሲሆን መች እስልምና እንደተቀበለችም ይጠቁማል፡፡

| | |
|---|---|
| ኢንቤም አረነኸ | እኛ አንተን አላየንህ |
| ወርቤን ሰመኔኸ | ስላንተ ግን ሰማንልህ |
| አመነቤኸ ሙሐመዶ | መሐመድ ሆይ ተቀበልንህ |

የሚለው ትውፊታዊ ግጥም በመጀመሪያ ሒጅራ ከዓረቢያ በ615 ዓ.ም ከነበረው የአክሱም መንግስት ጊዜ ወደ ሙስሊምነት እንደተለወጡ የሚያመለክት ማስረጃ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

ቀደም ሲል በታሪኩ እንደተጠቀሰው ሁሉ በሐረርና በድሬደዋ መካከል ሐርላ ተብሎ በሚጠራው መንደር ውስጥ በሚገኘው የመቃብር ድንጋይ ላይ በ400 ዓመተል ሂጅራ የተፃፈው ጽሑፍም በአካባቢ የሙስሊም ህብረተሰብ ቀድሞ እንደሰፈረ ያመለክታል፡፡ የሐረሪዎች አሚሮች የዘር ግንድ ታሪክም ምናልባት በ10ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ11ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ይገዛ ከነበረው ከአሚር ሐቦባ ይጀምራል፡፡ የእሱ ዘመነ መንግስት ከ233-333 ዓመተል ሒጅራ ይገዛ ከነበረው ማኽዙሚ ዘመን ጋር ይገናኛል፡፡ እስልምናም በዚህ ዘመን ወደዚህ አካባቢ ገብቶ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሰረቱ በመቃብሩ ድንጋይ ላይ የተፃፈው ጽሑፍና በአሚር የትውልድ ሐረግ በሚገልጸው ዘመን ሰፊ ልዩነት ስለሌለ በአካባቢው ቢያንስ ቢያንስ በአራተኛው ሂጅራ ክፍለ ዘመን እስልምና መሰራጨት ጀምሯል ማለት ይቻላል፡፡

ሐረር እንዴት እንደተቆረቆረች በሚያመለክተው የአካባቢው የታወቀ ባህል /ልምድ/ ደግሞ ሰባት ተቀናቃኝ የነበሩ መንደሮች አንድ በማድረግ የንግድና የትምህርት ማዕከል ሆናለች የሚል ነው። ከተማዋ ኮራ ብሎ በተቀመጠና በበርካታ የወንዝ ጅረቶች በተከበበ ኮረብታ ላይ ጉብ ብላ የተቆረቆረች ስትሆን ለአይን እይታ ኮራና ጎላ ብሎ የሚታየው ኮረብታም ከተፈጥሮና ከሰው ሰራሽ አደጋዎች ተከላክሎ አቆይቷታል። ዛሬም ቢሆን በአከባቢ ብዙ ሰዎችን በሚጨርሰው የወባ በሽታ ነፃ ስትሆን ከሩቅ ርቀት የጠላትን እንቅስቃሴ ለማሳየት የሚችለው ተራራዋም የወታደራዊ እዝ ማዕከል እንድትሆንም አድርጓታል።

በቂ ውሃዋና የአፈር አጠባበቅ ልምዷም ምርቷን ወደሌላ አካባቢ ልካ ለመሸጥ እንድትችል አብቅቷታል። የአክሱም ዘመነ መንግስት ከወደቀና ማዕከሉን ወደደቡብ አቅጣጫ ካዛወረ በኋላ ሐረር ዋና ዋናዎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች ከሕንድ ውቅያኖስና ከቀይ ባሕር ወደቦች ጋር የምታገናኝ የንግድ እንቅስቃሴ የተሞላባት መናሃሪያ ሆነ ቆይታለች። በተለይም ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የንግድ እንቅስቃሴው በ48 ሔክታር ላይ በተመሰረተችው ጁገል ማለትም በግንብ በታጠረችው ሐረር ከተማ የከተማ ባሕል እንዲዳብር አመቺ ሁኔታን ተፈጥሯል። በዚያ እንቅስቃሴ ምክንያትም ጁገል በእስልምናው ብዙ የመማሪያ ማእከሎችና በርካታ መስጊዶች ተገንብቷል።

## 10.4 የሐይማኖት አባቶችና መስኪጊዶቿ

በሐረር ውስጥ የሃይማኖት አባቶች ተብለው የሚታወቁት የመስጊድ ኢማሞች አዎች፣ሙሪዶች፣ሼኾችና ከቢሮች ናቸው፡፡ እነዚህ የሃይማኖት አባቶች የተሰጣቸውን ተግባር በየግላቸውና ከሌሎች ጋር የሚያከናውኑ እንጂ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች ሆነው የማይተዳደሩ ወይም የስልጣን ደረጃ የሌላቸው መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት "ኢማም" የሚባለው በአንድ መስጊድ ውስጥ በቀን አምስት ጊዜ ሲሰገድ የሚመራ ሲሆን በፆታው ወንድ፣በሚቻል መንገድ ሁሉ ሐረሪ ካለበለዚያም የኦሮሞ ደም ያለበት መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁንና በሁሉም መስጊዶች የተመደበ ኢማም ሊኖር ስለማይችል ቁርአን በሚያዘው መሰረት በአገልግሎትም ሆነ በልምድ የላቀ አስተዋጽኦ ያለው የተማረ ከሆነ የኢማምን ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በሐረር ካሉት መስጊዶች ትልልቆቹ ጁማ መስጊድና አው አብዳል መስጊድ ሲሆኑ የእነዚህም መስጊዶች ኢማሞች ከፍተኛ ከበሬታ ያላቸው ናቸው፡፡

ከኢማሞች ሌላ "ሙሪዶች" በታወቁ አድባራት ውስጥ ሲኖሩ እነዚህም ሙሪዶች ከነቢዩ መሐመድ የወረደ የዘር ግንድ ሐረግ እንዳላቸው የሚቆጥሩ ሐረሪዎች ናቸው፡፡ የሙሪድነት ማዕረግ የሚሰጣቸውም ከትውልድ ትውልድ በመውረስ ነው፡፡ ሙሪዶች ወደ አድባራቱ የሚመጣውን ጫት ተቀብለው በስፍራው ለሚገኙ ሰዎች በእኩልነት የሚከፋፍሉ፣እጣን የሚያጨሱ፣ ፀሎት በሚደረግበት ጊዜ ፀሎተኛውን የሚመሩና ፈቲሓ የሚያወርዱ ናቸው፡፡ ኢማሞች ሁሉ ወንድ መሆን ሲገባቸው ሙሪዶች ግን ሴቶችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ከመስጊዶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የሚከበሩ አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አው አባድር፣አው አብዱልቃዲር ጄይላን፣ አይ ዓቢዳ የተባሉት ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡

ሼኾችና ከቢሮች የሚባሉት ደግሞ በቁርአን እውቀታቸው በላቀ ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው፡፡ እነዚህም ምሁራን አዋቂዎችንም ሆነ ሕፃናትን ቁርአን፣ ሐዲስንና ስለሐረር ቅዱሳን ያስተምራሉ፡፡

ይሁንና ኢማም፣ሙሪድ፣ሼኽና ከቢር የተሰኙ ማዕረጎች ቢኖሩም አንዱ ሌላውን ይተካል ወይም አንዱ በሌላው አይጠራም ማለት አይደለም፡፡ ኢማሙም በእውቀቱ የጠለቀ ይሆንና ሼኽ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ሙሪዶች ደግሞ በእውቀታቸውና በተሰጥኦቸው በኃላፊነት ከሚወክሉዋቸው ቅዱሳንም ቢሆን የላቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## የሐረር ክብረ በዓላት

ሐረር ውስጥ የሚከበሩ በዓላት አንድም በቁርአን ላይ ካለበለዚያም በሐዲስ ላይ የተመረኮዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ሌሎች በዓላት ቢኖሩ ባህላዊ ወይም ‹‹ዓዳ›› ተብለው ይጠራሉ፡፡ ከዓዳ መካከል ዓሹራ፣ቁርአን ጌይ ዚያራ፣ሰፈር ዚያራ፣ነቢ መውሊድ፣ ኮኦታኝ መውሉድ፣ጁማቱል በርኸድሌ ሺኢሽታን መውሉድ፣ ሐራታኝ መውሉድ፣ ሐይዋን ሐይ፣ ኸቲመት፣ ሸዋል ኢድ፣ አረፋ የተባሉት ይገኙበታል፡፡

| የወሩ ኦፊሰ ላዊ ስም | የወሩ ሃይማኖ ታዊ በአል | የሐረር በአል | በአሉ የሚከበርበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| ሙሐረም | አሹራ /ኢድ አል አድሃ/ | አሹራ | - በአድባራት<br>- በቤት<br>- በጎዳና<br>- በሙዚየም |
| ሙሐረም | | ቁርአን ጌይ ዚያራ | በአድባራት |
| ሰፈር | | - ሰፈር ዚያራ<br>- ሰፈር ፋቲሐ<br>- ሰፈር ሞጫ | - በአድባራት<br>- በአድባራት<br>- በአድባራት |
| ረቢአል አወል | መውሉዱነቢ | ነቢ መውሉድ | - በአድባራት<br>- በከበሮ ቤት<br>- ነቢ.ጋር |
| ረቢአል ታኒ (ኮኦታኝ መውሉድ | | ኮኦታን መውሉድ | - በአድባራት<br>- በየቤቱ |
| ጆማዱአል አወል | | ጁማት አልበርኸድሌ / ሺኢሽታኝ መውሉድ/ | - በአድባራት<br>- በየቤቱ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጀማዱአል ታኒ /ሐራታኝ መውሉድ/ | | ሐራታኝ መውሉድ | - በአድባራት<br>- በየቤቱ |
| ረጃብ | ለ ይ ለ ተ ል ሚዕራጅ | | |
| ሸእባን | ለይለተል አልባ እራህ | ሐይዋን ሐይ/እረፍት ወር/ | - በየቤቱ |
| ረመዳን ወር ውስጥ ፍፃሜ | | - ጾም<br>- ኢደልፈጥር<br>- በድሪ አያም<br>- ኸቲመት | - በየቤቱ<br>- መስጊድ<br>- በአድባራት<br>በየቤቱ |
| ሸዋል | | - ሸዋልኢድ | - በአድባራት<br>- በየቤቱ |
| ዙልቂዳ | | | |
| ዙልሒጃ | ዓረፋ | ኢድአልሐደሃ<br>(ዓረፋ) | - መስጊድ /ስታዲየም/<br>- በየቤቱ |

ወርሃቱ ከጨረቃ መውጣት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ከዓመት ዓመት እለታቱ እንደሚለዋወጡ ማስተዋል ይገባል፡፡ በዓላቱ ቀደም ሲል በቀረበው ሰንጠረዥ አጠር ባለ መልካቸው የቀረቡ ቢሆንም መውሊድ፤ ያምንና ዓሹራን ብቻ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው፡፡

## 11.1 የነቢዩ መውሊድ

በሐረር  ውስጥ የነቢ መውሊድ ሶስት ጊዜ የሚከበር ሲሆን አንደኛ በወርሃ ራቢ አልአወል  ይከበራሉ፡፡ ከዚህ ወር በኋላ በሚመጡት ተከታታይ ወራትም ሁለተኛውና ሶስተኛው መውሊዶች ይከበራል፡፡ በዚህም መሰረት ኮአታኝ መውሊድና ሺኢሽታኝ መውሊድ ወይም (ጁማት አልበርኸድሌ) የሚሉ ወርሃትን እናገኛለን፡፡ ጁማት አልበርኸድሌ የተባለው መውሊድ ለፀሎት ከሚሰበሰበው ሐረሪና ሐረርን ከመሠረቷት 44 ቅዱሳን መካከል አንድ የሆኑት አውበርኸድሌይ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ሶስቱም የመውሊድ ቀናት በአድባራት ወይም በከበሮ ቤት "ነቢ ጋር" ከማታ ጀምሮ እስከንጋት በቁርአንና በሐዲስ ላይ የሰፈሩትን የመውሊድ ምዕራፍ የሚነበበው ለሶስት ተከታታይ ሰአታት ሲሆን ከዚያም በጭብጨባና በከበሮ የታጀበው ዚክር ይቀጥላል፡፡

ዚክር ሐሳቡ ከቁርአንና ከሐዲስ የወጣ ሆኖ የሐረር ሊቃውንት ከዜማ ጋር እንዲስማማ አድርገው በሐረሪ ቋንቋም ሆነ በአረበኛ ወይም በሌላው የሚግባቡበት ቋንቋ የገጠሙት ግጥም ነው፡፡ ከሶስቱ መውሊዶች በላቀ ሁኔታ የሚከበረው ሶስተኛው ሲሆን ቦታውም በአባድር አድባር ነው፡፡

## 11.2 ረመዳን ፆም ፍፃሜና ሹዋሊድ

የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ፆም በመላው ዓለም በሚቻል መንገድ ሁሉ በአንድ ቀን ተጀምሮ በሰላሳኛው ቀን ማለትም የረመዳን ጨረቃ ስትወጣ ተጀምሮ የቀጣዩ ወር ጨረቃ ስትወጣ በኢድ አልፈጥር ይፈታል፡፡ ይሁንና ከሰላሳ ቀናት ፆም በኋላ በመላው ዓለም ሚከበረው ኢድ አልፈጥር በሐረሪዎች ዘንድ ባህላዊና ልማዳዊ ሹዋል ኢድ ከፍተኛና አሰባሳቢ በአል ነው ወስደ፡፡ ይህም የሆነበት የራሱ ምክንያት ሲኖሩት አንደኛው ጾምን ያህል ከፈጣሪ ጋር የሚገናኝ ስርዓት አለቀ ብሎ መፈንጠዝ ስለሚመልስ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በዋናው የጾም ወር ሴቶች በወር አበባና በህመም፤ ወንዶች ደግሞ ሊያጾሙ በሚያስችል ልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚፆሙ እለታቱን አጉድለው ከሆነ እነዚህን ያጎደሏቸውን ቀናት በሸዋል ወር የመጀመሪያ ስድስት ቀናት አሟልተው ስለሚያጠናቅቁ የሁሉም የሴትና ወንዱን ደስታ ከዚያ በኃላ ይምጣ ከሚል ነው። ሆኖም እነዚህን ቀናት አንዱን ወር በሙሉ ሳያፋልሱ የጾሙ ሰዎችም ይጾሙባቸዋል።

ሹዋል ኢድ የሚከበረው ከበሮ በመምታትና ዚክር በማድረግ ሲሆን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ ዚክሩ ከቁርአንና ከሐዲስ የተወጣጣ ሆኖ በኣረብኛና በሐረሪኛ ተደርሶ በቃል የተያዘ የዜማ ግጥም ነው።

ሹዋል ኢድ ታላቅ የሃይማኖት በአል ከመሆኑም ሌላ ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች በኣሉ በሚከበሩባቸው አድባራት የክት ልብሳቸውን ለብሰው የሚገናኙበት እለትም በመሆኑ የመተጫጫ ቀን እንደሆነም ይታወቃል። በዚህም መሰረት ወጣቱ ወጣቷን በአጋጣሚው አይቶ ከወደዳት ወደ ቤተሰቦቿ ሽማግሌ ልኮ ሲፈቀድ ያገባታል። ሹዋል ኢድ ከዚህም በተጨማሪ ወደ አድባራቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ያልመጡ ወዳጅ ዘመዶች የሚዘይሩበት የሚጎበኙበት እለትም ነው።

## 11.3 ዓሹራ

በሀረሪዎች ከሚከበሩ ዓበይት የሃይማኖት በአላት አንዱ የሆነው አሹራ የሚከበረው በብዙ ምክንያቶችና በተለያዩ መንገዶችና ሥርዓቶች ነው፡፡ ከምክንያቶቹ መካከል የነቢ መሀመድ የልጅ ልጅ የሆነው ሰኢድ ሁሴን ያዚድ በተባለ አምባገነን ያልተመረጠ ከሊፋ የተገደለበትን እለት ለማስታወስ፤ ፈጣሪ አዳምንና ሄዋንን ህይወትንና ሞትን፤ ብእርና ሉኸን የፈጠረበት እንዲሁም አዲስ ዓመት መግቢያ መሆኑ ይገንዘቡታል፡፡ ብዙ ሀረሪዎች ኣመቱ በጥሩ ስኬት እንዲጠናቀቅ ወይም ያልተገለፀላቸው የህይወት ምስጢር እንዲገለጥላቸው ሲያከብሩት በእድሜ ከ50 ኣመታት በላይ ያሉት ደግሞ በጾም ያሳልፋታል፡፡

ሶስት መሰረታዊ ኩነቶች ህብረት ፈጥረው የሚከበሩ መሆናቸው ነው፡፡ ከሶስቱ አንዱ ጥንታዊ እምነት ትርከት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሙሳ ከጨቋኙ የፈርኦን ቀንበር ህዝቡን ያላቀቀበትና ቀይ ባህርን ያቋረጠበት፤ አብራሂም ጠላቶች ካቀጣጠሉበት የሰደድ እሳት ተርፈው ህያው የሆኑበት  እለት ነው ይባላል፡፡ የአሹራ ክብረ በኣል ኖህ ከጥፋት ውሃ ተርፎ መሬት ላይ በሰላም ያረፈበትን እለት ፈጣሪን ለማመስገን ከተለያየ እህል ዓይነቶች በሚዘጋጅ ገንፎ ይከበራል፡፡ የዓሹራ በኣል የሚከበርባቸው ምክንያቶች ትውልድ የሚጀመረው ከኖህ ዘመን ጀምሮ በመሆኑ ሀረሪዎች ይህን ቀን በገንፎ እራት ያስታውሱታል፡፡

ሁለተኛው የዓሹራ በኣል መከበር ምክንያት ጅብን ገንፎ ከመመገብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በመሰረቱ ጅብ ደርማ ሼኽ ማለትም የሀረር ቅዱስ በሆነው አውሊያ ወጣት ሼኽ ወይም በተለምዶ በደፈናው እንደሚባለው መልእክተኛ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጅብ ቢያንስ በኣመት ጣፋጭ ገንፎ መብላት አንዳለበት የሚገለጽ ትውፊታዊ ታሪክ አለ፡፡ በድሮ ዘመን በሀረር ተከስቶ በነበረው ረሃብ ለማዳው ጅብ የቤት እንስሳትንና ሰዎችንም ጭምር ሳይቀር መብላት በመጀመሩ ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ንፁህ ልቦና ያለው ሰው በረሃቡ ምክንያት በተፈጠረው ችግር ከጅብ ጋር የተገጠመው ውዝግብ ይረግብ ዘንድ ህልም አየ፡፡

በዚህ ህልም መሰረትም የሀረሪ ህዝብ ከተለያዩ እህል ዓይነቶች ያዘጋጀውንና ንጹህ ቅቤ እንደ ውሃ የተንቆረቆረበትን ገንፎ እስከ ዛሬ በየዓመቱ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡የገንፎ አበላሉ ስነስርዓትም የሚያስደንቅ ሲሆን እንደ ትውፊቱ ከሆነ የጅቦቹ መሪ ከሌሎቹ ጅቦች አስቀድሞ ይመጣና ከድንጋይ በተሰራው ገበቴ ላይ የተቀመጠውን ገንፎ ይቀምሳል፡፡ የጅቦቹ መሪ ገንፎው ወይም ቅቤው በቂ ካልሆነ አይበሉም በቂ ከሆነ ጅቦች መጥተው ይመገባሉ፡፡ አለበለዚያ ጅቦቹን ለመመገብ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች የጓደለውን ያሟላሉ፡፡

## 11.4 የበዓላቱ ፋይዳ

የሀረሪዎች የሃይማኖትም ሆኑ የባህል በዓላት ፋይዳ ፈጣሪ በመላእክት አማካይነት ስለዓለም ፍጻሜ ያስተላለፈውን ምንጊዜም በማስታወስ እራስን በጸሎትና በንስሐ አንፅቶ ለማቆየት ነው። እያንዳንዱ ሀረሪ በፈጣሪ የተሰጡትን ትእዛዛት አለመፈፀም ማለት በራሱ ላይ ከፍተኛ ጥፋት ማስከተል መሆኑን ይገነዘባል። የሀረሪ ህብረተሰብ ጤናማ ሆነ ደህንነት ፈጣሪን በማወደስና በመለመን የተመሰረተ እንደሆነም ያውቃል።እነኚህም በዓላት ጋር የቤት ንፅህና መጠበቅ የተለመደ ሲሆን ልዩ ልዩ ተባዮች፣ አይጥና እባብ የመሳሰሉ አደገኛ ፍጥረታትን ለማጥፋት እንደሚበጅ ይታመንበታል። በዚህም የሻእባን አጋማሽ ሃይዋን ሃይ ይከበራል።

በአላቱ ከዚህም በተጨማሪ በሀረር ውስጥ የሚገኙ የብሔር ብሔረሰቦች አባላት በእስልምና እምነት መሰረት የሚተሳሰቡባቸው፣ የሚጠያየቁባቸው የእርስ በርስ ይቅርታ የሚያወርዱባቸው የሚገባበዙባቸው በአጠቃላይ ነበዩ መሐመድን አማክለው የሚመሩባቸው የሚያከብራቸው በመሆናቸው ከፍተኛ ማህበራዊ ጠቀሜታ አላቸው። እንደ አሹራ ያሉት በዓላት ደግሞ ሀረሪዎች ከቅዱሳን መናፍስት በሀረርና በአካባቢዋ ከሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ብቻ ሳይሆን ጅብን ከሚያህል አስፈሪ አውሬ እንኳን በሰላም ለመኖር ጥረት የሚያደርጉባቸው እንደሆኑ ለረዥም ጊዜ ሲፈፀም ከነበረ የሀረሪዎች ልምድ መረዳት ይቻላል።

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## እስልምናን እንደ ግል እምነት የመቀበያ መንገዶች

### 12. ፆም በአጠቃሎ

ሀረሪዎች የእስልምና እምነትን የሚቀበሉት ከልጅነት እድሜያቸው አንስቶ እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም እምነቱ ስር እንዲሰድና እንዲጠናከርም ወደ ቁርአን ቤት የሚሄዱት ገና ከህፃንነት እድሜያቸው ጀምሮ ነው፡፡ እያደጉ ሲሄድም እያንዳንዱን ቁርአን ምእራፍ በልባቸው እንዲያጠኑት ይደረጋል፡፡ በቁርአን ቤት ቁርዓን ከጨረሱ (ካኸተሙ) በኃላ የቀለም መስበር በኣላቸውን በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ፡፡ አንድ ቁርአን የጨረሰ ልጅም በህብረተሰቡ ዘንድ እውቅናን ያገኛል፡፡ ከዚያም በከቢር ጋር የሚካሄደውን የላቀ ትምህርት እንዲማር ይደረጋል፡፡ ይህም በሀረሪ ቋንቋ እየተተረጎመ ይሰጣል፡፡ እስልምናን በራሳቸው ቋንቋ እንዲያውቁት በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

የእስልምና መቀበያ መንገድ መግቢያዎችና መግለጫዎች የተከለከሉ ነገሮችን ባለመስራትና የተፈቀደ ነገሮችን በማድረግ የሚገለፅ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሙስሊም ስጋ ቢበላ የሚበሉ እንስሳትን ብቻ በደንቡ መሰረት አርዶ መሆን አለበት፡፡

ሁለተኛ የእምነቱ ምሶሶ አንድ ሀረሪ ሙስሊም መፆሙ ሲሆን የሚፃመውም በረመዳን፤ ዓረፋ ወይም አሹራ ከመምጣቱ ከሶስት ከስድስት ወይም ከዘጠኝ ቀናት በፊት ቀደም ብሎ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ብቃት ያላቸው ሀረሪዎችም ነቢ መሀመድ በህይወት በነበሩበት ዘመን ሲያደርጉት እንደ ነበረው ሁሉ ዘወትር ሰኞና ሐሙስ ይፆማሉ፡፡

## 12.1 መማፀን

በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች እንደተጠቀሰው ሁሉ ለአንድ ሀረሪ ወደ ቅዱሳን አድባራት (አዋች) ሔዶ ጸሎት ማድረስ ወይም ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይዞ መጎብኘት ወይም መዘየር የህይወቱ አንድ ፈረጅ ነው። በተለይም ለህይወት በጣም አደገኛ ነው ተብሎ በሚታመንበት ወርሃ ሰፈር ዚያራው በተጠናከረ ሁኔታ ይካሄዳል። ሐረሪዎችም እርስ በርሳቸው ሲገናኙ "ሰፈር ሰላማ" ወይም ወርሃ ሰፈር በሰላም ይለቅልን እየተባባሉ ሰላምታን የሚለዋወጡ ከመሆናቸውም በላይ ሰላም የሚረጋገጠው በቅዱሳን አማካይነት እንደሆነም ያምናሉ።

አንድ ሀረሪ በቁርአንና በሐዲስ እንደተጠቀሰው ሁሉ በመጠኑም ሆኖ ሽቶ መጠቀም ይገባል። በዚህም መሰረት ፀሎቱ በሚደረግባቸው ስፍራዎች ሁሉ ጥሩ መዓዛ ያለው እጣንና ሰንደል ይጨሳል። ከተገኘም ሽቶ ይረጫል። እጣን ወይም ሰንደል ሁሉንም በአንድ ጊዜ ማጨስ ከጥሩ ማዓዛው ሌላ ፀሎት በፍጥነት እንዲጓዝና የፀሎት መልስም ቶሎ እንዲመጣ ያደርጋል የሚል አመለካከት አለ። ከዚህም በተጨማሪ የገነትን በር የሚጠብቁ መላእክትም ደስ እያላቸው ቶሎ ቶሎ እንዲፈቱ ያደርጋል ተብሎም ይታመናል። ጥሩ ሽታ ያለው እጣን በጥዋት ሲጨስ ሰይጣንና እርኩስ መናፍስትን ያርቃል አምስቱን የሀረር በሮች የሚጠብቁ አድባራትም ነቅተው ህብረተሰቡን እንዲጠብቁ ያደርጋልና እያንዳንዱ ሐረሪ የገነትን በር የሚጠብቁ መላእክት በሩን ቶሎ ቶሎ እንዲከፍቱ ፀሎታቸው ቶሎ ደርሶ ቶሎ መልስ እንዲያገኝ ከሞቱ አባቶቻቸው ጋር ያለሙሪዱ ለመገናኘት ያጨሳሉ።

ከዚህም ሌላ በመኽሪብና በዒሻ መካከል የሞቱ ቤተሰቦችን ፈጣሪ ምህረት ያደርግላቸው ዘንድ ሴቶች እጣን አጭሰው ጸሎት የሚያደርጉበት ጊዜ አለ። ይህም ሚስትጃብ ወይም ሰአቱ አልሒጃብ ወይም የመከላከያ ሰአት ተብሎ ይጠራል። በሀሪዎች ዘንድም ሙታንን መመገብ እየተባለም ይጠራል። አንድ የሙት መንፈስ በተጠቀሰው ሰአት ጭስ እየጨሰ ሚስቲጃብ ካልተደረገበት ይራባል። ከተራበም አውሊያዎችን ፈጣሪ ልመናቸውን አይሰሚቸውም ይባላል እንዲት ሴትም ሚስቲጃብ ካደረገች በመጨረሻው የፍርድ ቀን ወደ ገነት የመግባት እድሏ እንዲያስፋላት ይረዳታል።

በሀረሪዎች ዘንድ ቅዱስነት በህዝቡ እንጂ በማንም የሚሰጥ አይደለም ይህም የሚሰጠው በሶስት መንገዶች ሲሆው ስውር ወሊ፤ ሁለተኛው ሳይታሰብ ድንገት ብቅ የሚል ቅዱስነትና ሰውየው ከሞት በኃላ አስክሬኑ ሲሰወር ነው፡፡ ስውር የሚባሉት ማንም የማያያቸውና ራሳቸውን ቢሆን የማይከሰቱ ሆነው ነገር ግን ህዝቡን በከራማቸውና በመንፈሳቸው የሚባርኩና ከፈጣሪ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ የማይከሰቱት ቅዱሳን የማይቆጠሩ ሲሆኑ እንደ ጊስቲ ካሚላ (ልእልት ካሚላ) አውሊያ ዳሃቦ አባይ ሮዳ ያሉት ናቸው፡፡ ቅዱሳን የሚከስቱት በህልም ወይም በውን ሲሆን በዚህም ጊዜ ልዩ ልዩ መልእክታቸውን በአንዳንድ ሰዎች አማካይነት ያስተላልፋሉ፡፡ ከሞቱ በኃላ አስክሬናቸው የሚሰወሩት ደግሞ በሙስሊም አቀባበር ስነ ስርአት መሰረት ከተገነዙ በኃላ ነው፡፡ እነዚህ የበቁ የሃይማኖት አባቶች የሚሰውሩት በአንድና በሁለት ምእተዓመት ሲሆን በቅርቡም ማለትም በ1980 ላይ የአርጎበሪው ሼኽ አህመድ ከአው አብዳል መስጊድ ተሰውረዋል፡፡ ይህም ሲሆን አልተደነቀም ሼኽ አህመድ ከተሰወሩ በኃላ ብዙም ሰዎች በህልም እየታየ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡በዚህም መሰረት ዛሬ እኚህ ሰው ከሐረር ቅዱሳን ለመሆን በቅተዋል፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

## የሀረር አድባራት

### 13.1 አድባራቱ እንደ ልማድና ባህል

በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በግንብ በተከበበችው ሀረር እስልምና ሃይማኖት በጥንታዊውም ሆነ በዘመናዊው መልክ እንዲሰራጭ ዋነኛው ሚና ተጫውታለች፡፡ ከዚህ አንጻር አድባራት ማለትም የተከበሩና የቅዱሳን የሃይማኖት መሪዎች አፅም ያረፈባቸው መቃብሮች መንፈሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ማዕከሎች ናቸው፡፡ በሙስሊም አፍሪካውያን ዘንድም ቅዱሳን አድባራትን ማክበርና በጎብኙት (መዘየር) የተለመደ ክስተት ነው፡፡ በመሰረቱ አድባራት ሁለት የማታረቁ ወይም የሚቃረኑ የባእድ አምልኮቶች ፀሎት የሚፈፀምባቸው ስፍራዎች ነበሩ፡፡ አሁን ደግሞ በእስልምና ሃይማኖት መመሪያ መሰረት ይፀለይባቸዋል፡፡ አድባራት ከዚህም ሌላ በርካታ አገልግሎቶች አሏቸው፡፡ ከነዚህም ወስጥ

1. አልፎ አልፎ የሚደረጉት ዝየራዎች በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች አባላት መሆናቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ሳይለዩ ሁሉም ሙስሊሞች የሚገኙባቸው ተገናኝተውም ፀሎት የሚደረሱባቸው መሆናቸው፤
2. ሌላው የትምህርት ማእከል መሆናቸውና፤
3. ማህበረሰቡ በየእለቱ ጸሎቱን የሚያደርስባቸው ቦታዎች መሆናቸው
4. አብዛኛዎቹም እስልምና ቢያንስ በኢትዮጵያ ኢንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ናቸው፡፡ ትረንግሃም ኢስላም ኢን ኢትዮጵያ አድባራት የፖለቲካ አመለካከቱን ያሳያሉ፡፡ በሐረር ውስጥ አድባራት በብዛት የሚገኙ ሲሆን “ጀበል አል አውሊያ” ማለትም የአድባራት አምባ ተብላ በተለምዶ ትጠራለች፡፡ ይህም ሆኖ በትክክል መናገር አስቸጋሪውና በተለምዶም “አሐድ አላሁ ቢላዩም ዘዩቀኻችሌ” ማለትም ከአላህ በስተቀር የማያውቁህ መሬት ውስጥ የምትገኘው ቅዱስ ሆይ የሚለው በፊት የነበሩ የሚመለክባቸው አሉ ተብሎ በጥልቅ ስሜት እንደሚታሰብ ነው፡፡

በሐረር ውስጥ አድባራት በብዛት የሚገኙ ሲሆን ከተማዋም “መዲነቱን አውሊያ” ወይም “ጀበል አል አውሊያ” ማለትም የቅዱሳን መናገሻ ወይም የቅዱሳን አምባ ተብላ በተለምዶ ትጠራለች፡፡ ይህም ሆኖ በሀረር ያሉትን አድባራት ብዛት በትክክል መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለምዶም ሱንዙርቲቤ   አሐድ አላሁ ቢላይ ዘዩቀኹ ማለትም በአላህ ብቻ ለምትታወቁ፤ በሀረር ከርሰ ምድር ያላችሁ ተብሎ በጥልቅ ስሜት እንደሚታሰብ የሚያመለክት ጉልህ ማረጋገጫ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የከተማዋ አባት ተብለው ከሚጠሩት አባድር በቤተሰብ ደረጃ የሚጠሩ መቃብሮች ያሉባት ሀረር የተለያየ ጠቀሜታ ያላቸው አድባራትን ታስተናግዳለች፡፡ እነዚህም አድባራት በመላ ከተማዋ ከከተማዋ ባሻገር ጭምር ተሰራጭተዋል፡፡ አንዳንዶቹ ከሱፊዎች አባቶች ጋር የሚዛመዱ ሲሆን ሌሎችም በከፍተኛ ስራዎች ዝናን ተጎናጸፉ ምሑራንና ጥቂቶቹ ደግሞ ባከናወኑት ጀግንነት የተሞላ ጀብዱ በመፈፀማቸው የሚከበሩ ናቸው፡፡ አድባራት የወንዶች ብቻ ሳይሆን መላው ህይወታቸውን ማለትም የመንፈሳዊ ብርሃን ጮራ ሆኖ የምታገለግል ስትሆን ብዙ ቀድሪያዎችም ከሀረር ጋር ሰበበ ዝምድና እንዳላቸው ይገለጻሉ፡፡

ይህም ሆነ ስለ ሀረር አድባራት የተደረገው ጥናት ገና በጨቅላ እድሜ ላይ እንደሚገኝ ድርሳናቱ ያመለክታሉ፡፡ የተደረገ ጥናቶችም ስለነሱ ሙሉ ምስል የሚሰጡ አይደሉም፡፡ እስካሁን ድረስ በርተን ፖሊሽኪ ሌሎችም ባለፈው ክፍለ ዘመን አጥንተዋል፡፡ ቼሩሊ የተባለው ተመራማሪም በ1930ዎቹ ላይ ስለአድባራቱ አንዳንድ ጠቀሜታ ያላቸውን ማስረጃዎች አሰባስቧል፡፡ “ኢትዮጵያን ስፒክ ሐረር” በሚል ርእስ በ1965 እ.አ.አ ባሳተመው መጽሀፍ ለምን አድባራቱ እንደቆሙ አስታወቋል፡፡ ዋግነርም በ1970ዎቹ ላይ አድባራቱ ስም ለመመዝገብ ሞክሯል፡፡ ኤፎቸር በ1980ዎቹ አድባራቱን ስም በተሟላ ሁኔታ ማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ዋግነር የዚክርን ትርጉም አሳትሟል፡፡ ዋልድሮን አድባራቱ ስላላቸው ማህበራዊ ጠቀሜታ ጠቁሟል፡፡ ብራውኻምፐር በተለይም ከከተማዋ ውጭ ያሉ አድባራትን በማክበር እንደምን እስልምና እንደተሰራጨ ለማየት ሞክሯል፡፡ ምንም አንኳን መሰረተቢስ ከሆነው ድምዳሜው መጠንቀቅ አስፈላጊ ቢሆንም ትርሚንግሃም “ኢስላም ኢን ኢትዮጵያ “ በሚል ርእስ ያሳተመው መጽሐፍ ጠቃሚ ነው፡፡ እነኚህ ተመራማሪዎች ሁሉም ሀረርን አጥንተዋል፡፡ የአድባራቱ ጥናት ግን አልተሳካላቸውም፡፡

## 13.2 አዎች፣አድባራት ቅዱሳት እነማን ናቸው?

በነጠላው አንድ ሰው "አው" ሲሆን ትርጉሙ አባት ማለት ነው። አዋች ቅዱሳት አባቶች ናቸው። በአላህ የተወደዱ እነማን ናቸው? ብሎ ከእስልመና በፊት የነበሩ ቅድመ እስልምና የምናመልክባቸው ቅድመ አያች ናቸው ወይስ ባከናወኑት ሥራ ከሞቱ በኋላም ጭምር የሚታሰቡ ጠቃሚ ግለሰቦች ናቸው ብሎ መደነቁ የማይቀር ነው። በእርግጥም ለዚህ በውስጡ ውስብስብ ረቂቅ ጉዳዮችን ጥያቄ ቀላል ማብራሪያ መስጠት አስቸጋሪ ነው።

1. ይሁንና በአሁኑ ጊዜ ባለው የአዎች ዝርዝር ለጊዜውም ቢሆን መጠቃቀ ይቻላል። ስለሆነም እንደ አብዱልቃድር ጀይላን፣ በሺር አልሐፊ፣ ሼክ አሕመድ በርኸድሌ፣ እና ሌሎች ብዙዎቹ የሚዘከሩ ናቸው። አሕመድ አል ነጋሽ፣ ጀበርቲ ኢስማዒል ዩሱፍ በርኻድል፣ ሼኽ ሑሴን እና ሌሎችም እነርሱን የመሳሰሉ ከሐረር ውጭ የሚገኙ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን የሚዘከሩ የሚከበሩ ናቸው።

2. በሐረርር ውስጥ በሚገኙ መስጊዶች ውስጥም የአሚሮች መቃብሮች እናገኛለን። ለምሳሌ በጃ መስጊድ ውስጥ የኢማም አሕመድ መቃብርና በመስጊዱም አቅራቢያም የአሚር ኑር "ቁቢ" አለ። በሥራቸው ከተከበሩት ሼኮች መካካልም ከሁለም የበለጠ የሚከበረው የሼኽ ሐሺም አድባር ነው። በስነ-ምግባራቸው ከሚከበሩ ሴቶች መካከል በይበልጥ የሚታወቀው የአይ አቢዳና ይገኙበታል። ከነዚህም አድባሮች መካከል ጥቂቶቹ አዲሱ የእስልምና እምነት የሰረፀባቸው በቅድመ እስልምና የነበሩ የማምለኪያ ስፍራዎች ናቸው።

## 13.3 አድባራቱ ሲጠኑ በተመራማሪዎች ሲዳሰሱ

እኔ በሐረር አካባቢ ያሉትን አድባራት ምንነት ለመለየት ፍላጐት ያደረብኝ በሐረር መስጊዶች ዙሪያ ያደረግሁት ጥናት ካጠናቀቅሁ በኋላ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ከአብዱልሙሑይሚን አብዱናሰር ስብስብ ሥራዎች በመነሳት አባ ኢሚል ፍቸር ስለአድባሩ እንዲያጠኑ አሳምኛቸው ነበር። እሳቸውም የሰጠኋቸውን ሐሳብ በደስታ በመቀበል አድባራትን በመመዝገብ ምንነታቸውን ለመለየት ሞክረው ነበር። ነገር ግን ማንም ቢሆን ቁጥራቸውን አያውቅም፣ አንድም ሰው ቢሆን አልቆጠራቸውም ። ይህም አሰልቺና ጊዜ የሚወስድ ነው። በማለት እሳቸውም መቁጠራቸውን አቋረጡ። ለአድባራቱ ብዛት መሠረታዊ ምክንያት ለዘመናት የተለያየ ባህርይ የነበራቸው ታላላቅ ሰዎች ስለተካተቱ ብዛቱ ሊሆን ይችላል።

የሐረር "አውሊያዎች" ጉዳይ ሲነሳ "የኹዱም" ማለትም የመሰወር ጉዳይም መወሳት ያለበት ነው። ይኸው "ወሊ" የሚለውን ስም ሕብረተሰቡ እንዲያስታውስ እንጂ የመጨረሻው ግብ በአላህ ወዳጅ በመሆን በወዳጅነቱም ይህችን ዓለም ፈጣሪ እንዳይረሳት ማድረግ ነው። በዚህም ምክንያት ጥቂቶቹ የተቀደሱ ግለሰቦች ስማቸው ባይጠራ ይመርጣ። "ሱንዙርቲቤ ዚትሔጀብኹሌ የቦርዲ" ማለት "እያንዳንዱ ስፍራና በቅርበትም የተሰወራችሁ አውሊያዎች ሆይ ምስጋና ይድረሳችሁ" የሚለው ፀሎትም የነዚሁ አውሊያዎችን ብዛት መቆጠር እንደሚያዳግት ያመላክታል። በዚህም ምክንያት ሰዎች የተወሰኑትን አውሊያዎች ስም እንጂ የሁሉንም አያውቁም። አብዛኛውን ጊዜ ሱፊዎች "ኹዱን" በሚለው እንጂ በፖለቲካው ወይም በአስተዳደሩ ከፍተኛውን የሥልጣን ስፍራ ይዘው የማይገኙትም ለዚሁ ነው።

2. አባ ፋቸር እንዲህ ያለውን አድካሚና ተቆጥሮ የማይዘልቅ የቅዱሳን ስፍራ መመዝገቡን ትተው አድባራቱ ከሃይማኖት አኳያ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ በሚመለከት ወቅታዊ የሆኑ ጽሁፎችን ማጠናቀር ጀመሩ። የመጨረሻው ጽሑፋቸውም "በሐረር ውስጥ የሙስሊም ቅዱሳን አከባበር ከሐይማኖት አንጻር" /The Cult of Muslim Saint in Harar Religious Dimension/ ጽሁፋቸው እስላማዊ ገጽታው፣ መንፈሳዊ ግንኙነቱና ተግባራዊ እንቅስቃሴው ምን እንደሚመስል ሲገልጹ "ከሀይማኖት አኳያ በሌላው ስፍራ እንደሚገኘው ሁሉ /ሁለንተናዊ/ ነው።

ሐይማኖታዊ ስሜቱ በሰው ልጆች ስውር ሕሊና ውስጥ የተቀበረ ነው፡፡ ጥንታዊው የሰው ልጅ እውቀት በውስጡ ቀድሞ የተፈጠረውን ሐሳብ ወይም ከጥንቱ ከጥዋቱ ሲፈጠሩ አበሮ የተወረሰውን እምነት ለማወቅ በርቱ ፍላጐት አምሮት አለ” ካሉ በኂላ ቀጥለውም “እነዚህም አስተሳሰቦች ለዛፍና ለድንጋይ እጣን በማበርከት ይገለፃሉ” ይላሉ፡፡ በሳቸው ትንተና መሰረት እነዚህ ቅዱሳን ስፍራዎች ከሰው ልጅ የግንዛቤ አቅም በላይ በመሆን የመለኮታዊ ባህርይ መግለጫ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከራማቸው ለተገለፁላቸው ቅዱሳንም ሕልውናቸው እንደሚሰማቸውና ስሜት እንዲያሳድሩባቸው ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳት ሐረር ስለሚገኙት ውስብስብ አድባራት ባህሪና ወደዚያ በመሄድ ስለሚፈፀመው ዝየራ በአዲስ የጥናት ጉዳና ለማጥናት ይሞክራሉ፡፡ በዚህም መሠረት እውነተኛና እውነተኛ ያልሆኑ 2 ቁቢዎች መቃብሮች፣ የቋጥኞችና የዛፎች አድባራት በማለት በሦስት ይመድቧቸዋል፡፡

3. አሕመድ ሮበሌ ደግሞ እነማን አድባር ሊኖራቸው እንደሚችል በሦስት ይመድቧቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ምድቦች

ሀ. በሕይወት ዘመናቸው ሼኽ ተብለው አንድም ራሳቸው ተዓምር የሚሠሩ፣ ካለበለዚያም ሌሎች እንዲሠሩ የሚያደርጉ ሲሆኑ ሲሞቱ ግን “ወልይ” ይባላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሐረሪዎች መቃብር ይሠሩለትና አድባር /አው/ ፡፡ በመባልም ሲታሰብ ይኖራል፡፡ / አይረሳም/፡፡ ከዚያም በዓመት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ይዘየራል፡፡

ለ. አድባራት አገሩን ከጠላት ሲከላከል ደሙን ለፈሰሰና ሕይወቱን ላጣ የሚሠራ ነው፡፡ እንዲህ ያለው በጦር ሜዳ ላይ ሲዋጋ ከሞተ አድባሩ በስሙ ይሰየማል፡፡ ሐረሪዎችም ይጐበኙታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደዚህ ያሉት ጉበዝ ሰዎች ሲሞቱ አስክሬናቸው በጋልማ መቃብር ወይም ለየት ባለ ስፍራ ይቀበራል፡፡ ሐ. በመጨረሻው አድባር ለገዥዎች የሚሠራ ነው፡፡ አገር ገዥው … በሕይወት ዘመኑ ጥሩ ወይም አገሩን የሚያፈቅር ሰው ከነበረ ….. በሮብሌ ምደባ መሠረት ሲሞት የከተማዋ ሕዝብ በስሙ አድባር ይሠሩለትና ሳይረሳ ሲታሰብ ይኖራል፡፡ እናም በየጊዜው አድባሩን ይዘይሩለታል፡፡

የሱፊ አባቶች አድባራት በሐረር ቀርቶ በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ አልኖሩም፡፡ እንዲያውም በንጹህ መንፈስ በሕልም የታዩና በባህሉ /በልምዱ/ መሠረት ተቀባይነትን ያገኙ ናቸው፡፡ በእስልምና እምነት ሕልም በከፍተኛ ደረጃ ፍች የሚሰጠው መሆኑም መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሐዲስ ውስጥም ስለሕልም ጠቀሜታ የሚወሳ ሲሆን “ሕልማችሁ ራዕይያችሁ ነው፡፡ ተብሎለታል፡፡ በቁርአን ውስጥ በተለይም በሱራህ ውስጥ ነብዩ ዩሱፍ ሕልም ሲተረጉም መስማት የተለመደ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው ጥሩ ህልም ለማለትም ቢፈልግ ወይም ከዚህ አኳያ ጥሩ አቅጣጫ ለመያዝ ቢሻ ዒሻራ ማለትም ምን ማለት እንዳለበት መወሰን አለበት፡፡ ይህንንም ለማድረግ የሚችለው ለዚህ ሲባል የታዘዘውን ልዩ ስግደት ማለትም “ሰላቱን እስቴኻራ” ማድረስ አለበት፡፡ በህልም ከቅዱሳት ጋር መገናኘትን በተመለከተ ብዙ ታሪኮች እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በሐረር የሚገኙ አብዛኛዎቹ “መቃም” ተብለው የሚጠሩ አውሊያዎች አድባራት የተሠሩት በሕልም ታይተው ሲሆን አንድ በተለይ ተሰውረው ለሚኖሩት ደግሞ “መትሄጀብ” የሚባል አድባር አላቸው፡፡ “መትሄጀብ” የሚባለው ስም የሚያመልክተው አንድ ንፁህ የአላህ ባሪያ የሆነ ሰው አውሊያው ያረፈበትን ስፍራ በህልሙ ያየውና እዚያው ስፍራ አድባሩ ይሠራለታል፡፡

ወሊን፣ጓደኛን ወይም ቅዱሳን በሚመለከት በቁርዓን የሰፈረው አመለካከት በሐረር ሙስሊሞች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው፡፡ በዚህ መሠረት በሱራህ 10 ቁጥር 62 ላይ “ተመለከቱ በአላህ ወዳጆች ፍርሃት የለም፣ ማዘንም እንዲሁ” የሚለውም ስለቅዱሳን ጉዳይ በተወሳ ቁጥር ይጠቀሳል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም በሱራህ 18 ከቁጥር 60-82 ድረስም በአካላዊና በመንፈሳዊ እውቀት መካከል ያለው ልዩነት ሰፍሯል፡፡ የሱፊ ታሪክ ተከታዮች የሆኑት ሐረሪዎች “ዊርድን” ማለትም “ምርቃቱን” ለመቀበል አስቀድሞ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን ማለፍ ይኖርበታል ብለው ያምናሉ፡፡ ሙሪዱ ወይም እውነትን ፈላጊው ሐዋርያም የታሪክ ለመሆን ራሱን ዝቅ ማድረግና በልቦናው ውስጥ የተቀረፀውን ትዕቢቱን አስቀድሞ ማስወገድ አለበት፡፡ ሁሉም “የቱቅ ሲሲሲላሶች” ከነቢዩ መሀመድ ጋር የተዛመዱ መሆናቸውን መስማት የተለመደ ነው፡፡

## 13.4 የአዋች ፅንሰ ሀሳቦች

ሐረር ቀድሪያ ታሪቅ በመላው ኢትዮጵያ በማሰራጨት የታወቀች ናት፡፡ ይኸው በ16ኛው ክፍለ ዘመን የየመኒ ተወላጅና የጥንቱ ሱፊዎች አባት የአብዱልቃዲር ጀይላነ /10787-1166/ ተከታይ የሆኑት ሸሪፍ አቡበከር ከሕንድ ውቂያኖስ በኩል ወደ ሐረር በመግባት ቀድሪያ ታሪቋን መሠረቱ፡፡ በዚህም ሰው ስም ገናና የሆነ ሲሆን በመላው ኢትዮጵያ ከእጣን ጋር በተያያዘ ሁኔታ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በዛሬው ጊዜ ዓይደሩስ ማለት እጣን ማለት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እጣኑ ሲጨስ "ዓይደሩስ የባህር ንጉስ" ይባላል፡፡ በዚህ መሠረት ከሐረር 15 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ የሚገኘው የአብዱልቃዲር ጄይላን እናታቸው "ኡማኮዳ" የቀድሪያ "ማቃምስ" በከፍተኛ ደረጃ የሚከበሩ ናቸው፡፡ በሐረር ውስጥ የጂላኒ ተወካይ የሆነው የአው ቁራቤ ሊማይ አድባር አስማዲን በሪ ይገኛል፡፡

ይሁንና በሐረር ያለው የዚያራ ተግባር በቀድሪያ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ቀደም ሲል ስልዊርድ በተጠቀሰው ላይ እንደተወሳው ሁሉ በሐረር ውስጥ ዊረድ ለመሆን ገደብ የለም፡፡ አንድ ሰው ዊረድ ለመሆን የተለያየ የቱሪቅ መንገዶችን ለመከተል ይችላል፡፡ በሶፊያ እንደሚታየውም የወንድማማች ቡድንን በብዛት መመልከት የተለመደ አይደለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ጥቂት የወንድማማቾች ቡድኖችን ለመያዝ የሚችሉ ብዙ አድባራት በየቦታው ስላሉ ሊሆን ይችላል፡፡ በአስረጂ መሠረት የታሳውፍ መሠረታዊ መርህዎች የተቀደሰው ሕግ ሸሪዓ፣ ታሪቅ ማለትም (መንገድ) ፣ሐቂቃ ማለትም (ሐቅ) ናቸው፡፡ እነዚህም ሦስት መርሆች የአላህን ትዕዛዝ ፍቅር በተሞላበት መንገድ ለመፈፀም የሚመሯቸው ቀጥተኛ ጉዳና ናቸው፡፡

አንዳንድ ግለሰቦች በሕይወት ዘመናቸው "ከራማ" ሊኖራቸው ወይም ተአምር ሊፈፅሙ ስለሚችሉ እንደ አውሊያ ይቆጠራሉ፡፡ እነርሱም ከሌሎች በተለዩ የእውቀት ኃይል የማዳን ችሎታ ሊኖራቸው ወይም በተራ ሰዎች ሊደረግ የማይችል ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሕብረተሰቡ ችሎታቸውን በቀላሉ ሊለየው ይችላል፡፡ በቀላሉ ለመለየት መቻሉም እንደአውሊያ እንዲቀበላቸው ያደርጋል፡፡

ስለ አድባራት፣ ስለአውሊያዎችና ስለመሳሰሉት ይህን ያህል ካነሳን ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ “ስበረካ” እናውሳ። በመሠረቱ እስላም ግዴታ የሆኑት ፀሎቶች አብረው እንዲፀልዩ መንፈሳዊ ድጋፍን በመስጠት የሚያበረታታ ነው። ይህንን የሚያደርግበት ምክንያት በመጨረሻው የፍርድ ቀን አብሮ መፀለይ በግል ከመፀለይ ይልቅ የበለጠ ተቀባይነት ስላለው የምህረትን መጠን ለመጨመር ያስችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ከዚህ በላይ ደግሞ “ከራማ” ያለው ወሊ በረካ ማለት ምህረት ይኖረዋል። ስለሆነም ወልዩ በሕይወት ባለበት ጊዜ ግለሰቦች ወደሱ እየሄዱ የተሻለ ሕይወት ይኖራቸው ዘንድ እንዲባርካቸው ሲዘይሩ፣ ከሞት በኋላ ወደ መቃብሩ ሄደው አክብሮታቸውን ይገልፃሉ። ይህም ዝየራ ጉብኝት በእስልምና የተከለከለ አይደለም። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ አጥባቂ እስላም አድባራቱ እንዲያማልዱ የመጠየቅን ልምድ በፍፁም የማይቀበለው ጉዳይ ይሆናል። በእርግጥ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ባህል በሃይማት ላይ ተጽዕኖ ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህም ሆኖ ደግሞ የተማሩ ሼኮችም ሰዎች የአምልኮ ተግባርን ሲፈፅሙ አይቶ ትክክል አይደላችሁም ብሎ ውሳኔ ከማሳለፍ በፊት የማይዘይረው ሰው ፍላጐትን ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። ዝያራው በማንኛውም መንገድ አድባሩን ከማምለክ ጋር የተያያዘ ከሆነ የእግዚአብሔር ሥልጣን በጠነከረ ሁኔታ መዳፈር ይሆናል። እኔ ራሴ በተለይም ክርስቲያኖች ሼኽ አባድር ያሉበትን መሬት ሲስሙ ተመልክቻለሁ። በዚህ ጊዜ አባድርን አክብረው መሬቱን የመሳም ጉዳይ ከእስላም ሃይማኖት ደንብ አኳያ እንደምን እንደሚመለከቱት ጠይቄ ነበር። የእርሱ መልስም ይህን የሚያደርጉት ለአድባሩ ሳይሆን ለሃያሉ ፈጣሪ እንደሆነ ነግረውኛል።

ይህም ሁሉ ሆኖ አጠቃላይ ሐረሪዎች በከተማዋ የሚገኙ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት የዘርና የመሳሰሉትን የባዕድ አምልኮ ተግባራት እንዳያከናውኑ የሚከለክላቸውና የአላህን አንድነት መሠረታዊ እውቀት የሚሰጣቸውን “ተውሂድ” ስለሚማሩ ከ”ሽርክ” እንዲጠበቁ መታወቅ ይኖርበታል።

## 13.5 "አው አባዲር አውዚኛ" (አባድር አባታችን)

ስለአድባር አመጣጥ ታሪክ ሲወሳ ሁሉም በ12ኛው ክፍለ ዘመን ከአርባ ተከታዮቻቸው ጋር ከሂጃዝ ከመጡት አው አባድር ማለትም ከዑመር አልሪዳ ጋር ይወሳሉ። እነዚህም ሰዎች ወደሐረር እንደመጡ መሪያቸው ማን እንደሆነ ለይተው ማወቅ ነበር። ምንም እንኳን መሪያቸውን ማን እንደሚሆን ለመምረጥ በአብዛኛው አድባር በጓደኞቻቸው ፊት ብዙ ፈተናዎችን አልፈው ለመሪነት እንደበቁ ይስማማሉ። በዚህም መሠረት ብዙ ከራማዎችን ተአምራትን በመሥራት የተቀደሱና የከተማዋ አባት ለመባል በቁ። አሁንም ቢሆን የከተማዋ አባት እሳቸው ሲሆኑ ሐረር በሚለው ስሟ ምትክም አባድር እየተባለች የምትጠራበት ጊዜ አለ።
ከሂጃዝ የመጡት የሃይማኖት አባቶች መሪያቸውን ከመረጡ በኋላ ግዛቶቻቸውንና ኃላፊያቸውን ተከፋፈሉ። ከተማዋን በአምስት እኩል ስፋት ባላቸው ክፍሎች ከለሏት። እነዚህም አዳዲስ ማዕከሎች ቁርአን ትምህርት መማሪያ ማዕከሎችና ከባህል ጋር በተገናዘበ መልኩ እስልምና የሚሠራጭባቸው ስፍራዎች ሆነው ማገልገል ጀመሩ።

እንደ ሚባለው አባድር ከመጡ በኋላ በአገሩ የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰብ አባላት ሰብስበው ስለአዲሱ አስተዳደራቸው እንዲያውቁ ካደረጉ በኋላ በየስፍራው ሾሞዋቸው ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ከሚያወሱት መሃል "ፋትህ መዲናተል ሐረር" በሚል የፃፈው ያህያ ነሰሩላህ ሲሆን እሱም "አባድር እያንዳንዱ ብሔረሰብ መሪ መመደባቸው በሐረርና በአካባቢዋ አጎራባቾች መካከል ጠንካራ ግንኙነት ፈጥረዋል" ይላል። አባድር ከዚህም በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ገጠር ከተማይቱ ወደ ሐረር ገበያ ምን ማምጣት እንዳለባቸው ወስነውላቸው ነበር ይባላል። እስከዛሬ ድረስም በአካባቢው ያሉ ብሔረሰቦች ለአባዲር የገቡትን ቃል አክብረው እንደሚገኙና ሐረር በየእለቱ የሚያስፈልጋት እንደሚያቀርቡላት የሐረር ነዋሪዎች ያምናሉ። "አባድር ሩቡት ቦኢ"፣ "ባዱም ዜይገርሴ ዊጁም ዘይቢክሌ" አባድር ከተማዋን ትተው እንደማይተዋትና ልጆች እንደማያለቅሱ ቃል ገብተዋል" የሚሉ ሁለት ተረቶች ይህንን እውነታ የሚያንፀባርቁ ናቸው። ከዚህም ሌላ " አባድር ጦም አያሳድር" እየተባለ በየጊዜው ሲነገር ይሰማል።

# ታጅ ሞውረድ፤ ኢማመት መጣለል

የአድባር አድባር የተለየዩ ተግባራት የሚያከናውኑበት ቦታ ነው ከነዚህም ውስጥ “ ታጅ ሞውረድ” ማለትም የንግሥ በዓል የሚያከብሩበት እና ከፍተኛ ባለሥልጣናት ኢማመት መጣለል” የተባለው ኢማመት የሚጠመጠሙበት መሆኑ ይገኙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያየ የእስልምና እውቀት ዘርፍ የተካኑ ዓሊሞች /ሊቃውንት/ በአድባሩ ይሰበሰቡና ልዩ አገልግሎታቸውን ለሕብረተሰቡ ይሰጣሉ፡፡ የሌሎቹ አድባራት ሙሪዶችም በአባድር ሼክ የሚመረጡ ሲሆን የአባዲር ሼኽ ሥልጣን ደግሞ በሐረር ከተማ መንግስት ዋነ ቃዲ ይፀድቃል፡፡ ባለፈው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የአካባቢው ኦሮሞዎች የመጨረሻውን መሃላቸውን የአባድርን ስም በመጥራት ይፈጽሙ ነበር፡፡

በሐረር ያሉት አድባራት የከተማ ካርታ ወይም የመሬት አቀማመጥ መለያ ሆነው ከማገልገላቸው በላይ ሕብረተሰቡ እራሱን የሚለይባቸውና የኔ ናቸው የሚላቸው ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ የኩራት ምልክቶች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት በመላው ከተማ በከፍተኛ ደረጃ በሚከበሩት አድባራት ስም የአው አባድር ልጅ፣ የሼኽ ሁሴን ልጅ፣ የአይ አቢዳ ልጅ ሲባል መስማት የተለመደ ነው፡፡ አድባራቱ ሁሉ ደግሞ የአባዲር አድባር የላቀውን ደረጃ ይይዛል፡፡ ሐሺም በአሁኑ ጊዜም በጥቅም ላይ መዋል ላይ ያሉትን አንድ “ፋትሁ አልረህማን” እና “ሙስጠፋ” ያሉትን ጽሑፎችን የደረሱ እንዲሁም የብህትውና ሕይወት በማሳለፍ የታወቁ ናቸው፡፡ አይዓቢዳም ቢሆኑ በሐረሪዎች ውስጥ የስርዓት ፀሎት ማዕከል በመሆን ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሴቶች ልጅ እንዲወልዱ፣ እንዲያገቡ፣ ሐዘናቸውን እንዲገልፁ እና በአጋጣሚ በሚደርስባቸው ልዩ ልዩ ሴት ነክ ጉዳዮች ሁሉ ችግራቸው እንዲያቃልልላቸው ወደ አይአቢዳ አድባር በፀሎት ይሄዳሉ፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አራት

## ዚያራ ለጉብኝት መሄድ ሥርዓቱ ማህበራዊ ፋይዳው

### ዚያራ ለጉብኝት መሄድ

አሉላ ፓንክረስት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ወደ ቅዱስ ስፍራዎች ሄዶ ፀሎት የማድረስ ተግባር በአምስት ይከፍሉታል፡፡

1ኛው.ከተለመደው የእለት ተእለት ጉዞ ማለትም ከቤት ወጣ ብሎ ከመመለስ የተለየ መሆን አለበት፡፡

2ኛው.ዓላማውም ዝም ብሎ ዞሮ ተዟዙሮ ለመምጣት ሳይሆን የተወሰነ /የታወቀ/ ግብ አለው፡፡ ጉዞውም በአንድ በታወቀ ልዩ ቀን እና መንፈሳዊ ፋይዳ ተለይቶ ለሚታወቅ ተግባር ነው፡፡

3ኛው.እንዲሁም ጀማው /ሙስሊሙ ዘያሪ በብዛት/ ባለበት እንጂ ለብቻ የሚሆን አይደለም፡፡ ሪቹዋል ክብረ በዓላዊ ክብረ ድግስ፤

4ተኛ .ስለት መግባትና መስጠት በምትኩ ከአድባራቱ ኃላፊዎች ተወካዮች ምርቃት መቀበል እንዲሁም ሰጦታ መለዋወጥ መኖር አለበት፡፡ መመጽወት የተገባ ነገር ዘራፊዎች አደጋ እንዳያደርሱባቸው የተከለከለ ነው፡፡ በመሆኑ ወደ ዚያራ የሚሄዱ ሁሉ የሰላምና ፀጥታ ምልክቶች ሆነው ይታያሉ፡፡

በሐረር አድባራት ውስጥ የሚከናወነው ዝያራ ምን እንደሚመስል ስንመለከተው፤ ከሁሉ አስቀድሞ በሐረር ከተማ በአምስቱ በሮች በሚወከሉት አምስት ሰፈሮች በዚክሪ ስርዓት ከሚከናወነው “ነቢ ጋር” ሌላ ሦስት የዚየራ ልምዶች ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ በአድባራቱ ውስጥ በየዓመቱ የሚከበሩ በዓላት ሲሆኑ ዓላማቸውም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንዲሁም የግል ችግሮች ይወገዱ ዘንድ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ለግል ጉዳይ ከሚደረጉት ዝያራዎች በስተቀር የተቀሩት ሁለቱ ግን ማህበራዊ ፋይዳ አላቸው፡፡

እነዚህ ዓመታዊ ዝያራዎች አሉላ ያላቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሲሆን የመጀመሪያው በዓል በአስረኛው የሂጅራ ወር የሚውለው የሂጅራ በዓል ነው፡፡ ሁለተኛው ወር ሰፈር እንደ ወርሃ ግንቦት አደገኛ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የግንቦት አድባር እንደሚባለው ዓይነት " ሰፈር ፋታህ" ተብሎ ወሩን ሙሉ ልዩ ፀሎት አከባበር ይደረግበታል፡፡ በዚህ ጊዜም ንፍሮ ይቀቀላል፡፡ በ27ኛው ቀን በብዙዎቹ አድባራት ሲፀለይ ይታደራል፡፡ በሐዲስ ውስጥ ሁለተኛው የሒጅራ ወር እንደመጥፎ ገድ ተደርጐ እንደሚወሰድ ተጠቅሷል፡፡

አድባራትን ከመዘየር ጋር የተገናዘበው ሌላው ምክንያት ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ድርቅ፣ ወረርሽኝ ወይም የተለያየ የሕብረተሰብ አባላት ባለመግባባት እርስ በእርስ ሲጋጩ ሊሆን ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የከተማዋ ማህበረሰብ አባላት፣ ብዙ ጊዜ ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ፣ አነስተኛ የሆነ መዋጮ ያዋጡና ካሉት ትልቅ አድባራት በአንዱ "ሰደቃ" ያዘጋጃሉ፡፡ በድርቅ ጊዜ ገበሬዎች የእርቅና የምርት ምልክት የሆነውን አረንጓዴ ዝንጣፌዎችን በመያዝ ወደ ከተማው አድባራት ይመጡና ይዘይራሉ፡፡ ይህም ዓይነቱ እንቅስቃሴ "ያ ሐፊዝ" ይባላል፡፡ ይህም የተባለበት ምክንያት ከአንዱ አድባር ወደ ሌላው አድባር በሚዘዋወሩበት ጊዜ " ያ ሐፊዝ" ማለትም " አዳኙ" ከአደጋ አዳኙ ሰዋሪው ሆይ የሚለውን ሐረግ ስለሚደጋገሙ ነው፡፡

ሌላው የዝየራ ዓይነት በግል ጉዳይ ሲባል የሚደረግ ነገር ነው፡፡ ይህም ዝያራ ግለሰቡ በሚያመቸው ወይም በሚያስፈልገው ጊዜ ወደ ሚፈልገው አድባር ይሄድና ችግሩን ከሙሪዱ ጋር በመሆን ያቀርባል፡፡ ምንም እንኳን ለብዙ ጉዳዮች በአብዛኛው ወደ አድባር የሚሄዱ ቢሆን ነገሩን ቀረብ ብለን ስንመለከውም አንዳንድ አድባራት ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ችግር ጋር የተያያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህም መሠረት ሥጋ የሚፈልጉ ወደ አውደበና፣ ለጫት ወደ አው ወሪቃ፣ ለጋብቻ ደግሞ ወደ አው መያ እንዲሁም እንደየ ችግራቸው ወደ ሌሎች ብዙ አድባራት ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳን እርግማን በቤተሰቡ ቢደርድር ጉዳት ስለሚያስከትል የሚደፋፈር ባይሆንም እንዳንዶቹ እቃ ሲሰረቅባቸው ሌቦቹን ይረግሙላቸው ዘንድ ወደ አድባሮች ሄደው የደረሰባቸውን በደል ሲገልጹ ይታያሉ፡፡ እንዲህ ያለው ጸሎት "ወሊ ሐኪም" በመባል ይታወቃል፡፡

ሴቶች “ሲራ” የሚባል ልዩ ቂጣ “ቡን” (ቅቤ ያለበት ቡና) በተለያዩ ጊዜያት ያዘጋጁና “ሲራ ዋ ቡን” ወይም ቡን ፋታህ የተባለ ልዩ የፀሎት ስነ-ስርዓት የሚያደርሱ ሲሆን የዚህም ፀሎት ምንነት ለአላህ እንጂ ለሌላ ለማንም ሰው አይናገሩም፡፡

ሐረር ቡናና ጫት ለሰው አገልግሎት እንዲውል የተደረገባት / የተለመደባት/ ናት ተብላ የምትወሰድ ናት፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለት ተክሎች ከማንኛውም የሐረሪዎች እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ ጫት የሌለበት የበዓል ስነ-ስርዓት የለም፡፡ ቡናም እንደ ጫት እንኳን ባይሆን በልዩ ልዩ ጊዜያት እየተፈላ ይጠጣል፡፡ በዚህ መሠረት በዓመት በዓሉ ጊዜ “ራብሳ” የሚለው የጫቱ ኃላፊ አድባሮቹን ለመዘየር ከሚመጡት የበዓሉ ተሳታፊዎች ጫት “ጀባ” እንዲሉ ይጠይቃል፡፡ ከዚያም ሙሪዱ ስነ-ስርዓቱን በፀሎት ሲከፍት ጫቱን ለሁሉም ያድላል፡፡
ቡናውም እንዲህ፣ በ”በራብሳው” አማካይነት “ጀባ” ተብሎ ሲቀርብ የሙሪዱ ምርቃት ይቀጥላል፡፡

የአድባራቱ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዓረብኛ የሚቀሩት ጽሑፎች “ሻሪፉል ዓለሚን” እና “ፈትሕ ራሕማን” ሲሆኑ ዓረብኛ ለማይሰሙት ሲባል ደግሞ የዚክር ጊዜ ይኖራል፡፡ እያንዳንዱ ዚክር የሚቀርበው በባህሉና በልምዱ በሚታወቁ የቤተሰብ አባላት መሪነት ሲሆን ዚክር የሚቀርበው በባህሉማ በልምዱ በሚታወቁ ቤተሰብ አባላት መሪነት ሲሆን ዚክር በድቤ እየታጀበ በሚወርድበት ጊዜም በተሳታፊው ስነልቦና የፈውስ ለውጥ ስሜት ያሳድራል፡፡ ይህም ሆኖ ወንዶችና ሴቶች ዝሙት እንዳይፈጽሙ ሲባል የሚቀመጡት ለየብቻ ነው፡፡ መጠነኛ ወደ ሆነ ተመስጦ በሚያስገባው ነቢ ሑቢ ሐለፊ ማለትም “የነቢዩ ፍቅር ስሜቷን ሰለባት” የተባለው የውዳሴ ዚክር በሚቀርብበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች የዚክሪ ዓይነቶች በጸሎት አድራሾቹ ላይ የተለየ የመቅበጥበጥ ስሜት አያሳድሩም፡፡

ሁሉም ዓይነት ብሔረሰቦች እንዲረዷቸው በሚል በተለያየ ቋንቋ የሚደርሱ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህም መሠረት በሐረር ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች የሚደረሱት ዚክሪዎች የዓረብኛ፣ የሐረሪ፣ የኦሮምኛ፤ የአማርኛ እና የሱማልኛ ቋንቋ ቅልቅል ያለባቸው /ማካሮኒክ/ ሆነው እናገኛቸዋልን፡፡ ዚክሮች በአጠቃላይ ሲገመገሙ የምዕመናኑን ልብ ለመሳብ የሚጠቅሙ ጥሩ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

ከተጠቀሱት በዝየራ የሚከናወኑ የፀሎት ዓይነቶች ሌላ “ዒጃባ” ማለት የፀሎት ጥያቄ መመለስ የሚባል አለ፡፡ ይኸው የፀሎት ዓይነት በሐረሪ ሴቶች ልምድ እጅግ በጣም አስፈላጊው ነው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በእያንዳንዱ ሐረሪ ቤት በዒጃባ ጊዜ እጣን ይጨስና በሕይወት ላሉትም ሆነ ለሞቱት ፀሎት ማድረግ የተለመደ ነበር፡፡ የፀሎቱ ምስጥርም በሞት ያለፉትንና በሕይወት ያሉ ሰዎችን በመንፈስ ለማገናኘት ነው፡፡ በመንፈስ ለመገናኘት ይችሉ ዘንድም የሞቱ ዘመዶቻቸውን ከአውሊያዎች መካከል የበለጠ የሚወዱትን እንዲሁም የነቢዩንና የአላህን ስም በመደጋገም ያነሳሉ፡፡ ሲሄዱም ወደ ተመስጦ ይገቡና ከቅዱሳን መናፍስት ጋር ተገናኝተው ልመናቸውን ያቀርባሉ፡፡ ፀሎታቸውን ጨርሰው ከተመስጦ ሲወጡ መንፈሳዊ እርካታ ማግኘት እንደሚችሉ አስረጂዎች ይናገራሉ፡፡

# ክፍል ስድስት

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

## አድባራት ከሐረርና ከአካባቢዋ ሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት

### 15.1 የአድባራቱ ገፅታ

አድባር የሚለው ቃልም ሰዎች የሠሩት የፀሎት ስፍራ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ከተፈጥሮ ነገሮች ጋር የተሠራ ሆኖ ለቅዱሳኑ /ወሊ/ መታሰቢያ ሊያገለገል ይችላል። ስለዚህ አድባር "ኩባህ" /ሸጠጥ ብሎ ሙሉ በሙሉ በድንጋይ የተሠራ ግንብ/ ወይም በእንጨት የተሠራ እኛ ቤት ሊሆን ሲችል በሁለቱም መንገዶች የተሠራው አድባር አብዛኛውን ጊዜ የድንጋይ ካብ ወይም በእንጨት አጥር ይደረግለታል። በቤቱም እውነተኛ የቅዱሳን መቃብር ወይም በስሙ የተሠራ መቃብር መሰል ስፍራ በውስጡ ያለበት ሊሆን ይችላል። ወደ እነዚህ ቅዱሳን ስፍራዎች ፀሎት ለማድረስ መሄድም አልፎ አልፎ ሐጅ የሚለው ቃል በጥቅም ላይ ይውላል። አብዛኛውን ጊዜም ዚያራ ተብሎ በትክክል የሚጠራ ሲሆን ብዙዎቹ ወደቅዱሳኑ የመቃብር ስፍራ ፀሎት ለማድረስ የሚሄዱትም እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ነው። ለአድባራቱ ስጦታ የሚበረከተው ስለቱ ከደረሰ በኋላ ነው። ያ ስለት መስዋዕት ማቅረብ ቢሆን የሚመረጠው ወንድ እንስሳ ሲሆን ይህም እንስሳ በአድባሩ በር መድረክ ላይ ይታረዳል።

ታዲያ ምንም እንኳን እስልምና በአባቶች ማመንና መቃብራቸው ላይ ወስዶ መስዋዕት ማቅረብን አጥብቆ የሚቃወም ቢሆንም በሐረር አምባ በሚገኙ ሕዝቦችና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ በነበሩ ሱማሌዎች ጭምር እንዲህ ያለው ልምድ እንደቀጠለ ነበር። ስለዚህም የቅዱሳን አምልኮ የቆየውን የሕዝብ ባህል ከእስልምና እምነት ጋር በተዛመደ መልኩ ማካሄድ ሲሆን በአካባቢው ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ እንደነበረ ያስገነዝባል።

## 15.2 አድባራቱ የሚገኙበትና ህዝቡ

1. በዚህም መሠረት ኮምቦልቻ አጠገብ እንደሚገኘው አው ንጉስ ጉጉዋ እና አናኖ የሚገኘው አው ዓሊ ፋፍ ያሉት አድባራት በምሥራቅ ሐረር አምባ የሚኖሩ ኦሮሞዎችን ጠቃሚ ማዕከላት ሆነው ነበር፡፡ አው ዓሊ ፊፍ የተባለውና ከሐረር በስተሰሜን ምስራቅ 25 ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በጃርሶ ኦሮሞና በኢሳ ሱማሌ ድንበር ላይ በሚገኝ አኖን በተባለው ስፍራ አድባሩ የተሠራለት ቅዱስ፣ ከአባድር ወንድ ልጆች አንዱ ነው፡፡ የአካባቢው ኦሮሞዎችም "ዓሊ ፊፍ በላ ፊፍ መጥፎ አጋጣሚዎችን ሁሉ አርቅልን" እያሉ ይጠይቁታል፡፡ የታወቁ ባህላዊ ታሪኮች እንደሚያወሱት ከሆነም ከእለታት አንድ ቀን ሴት ልጁ ለፀሎት የሚጠቀምበት ውሃ እንድታመጣለት ይልካታል፡፡ እሷ ግን ከወንድ ጓደኛዋ ጋር ወንዝ ውስጥ እየተጫወተች ጊዜዋን በማጥፋት አባቷን አስጠበቀች፡፡ አባቷም በዚህ ክፉኛ ተናደደና ልጁንና ጓደኛዋን በመርገም ዛሬም ይታያል ተብሎ ወደ ሚነገረው ድንጋይ ለወጣቸው፡፡ ከዚያን ጦሩን አነሳና መሬቱን ወጋው፡፡ ወዲያው በጦር በተወጋው መሬት ላይ ምንጭ ተንደልድሎ ፈለቀ፡፡ ይህም ምንጭ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ "ቡርካዓሊ ፊፍ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ስለዚህም ኦሮሞዎችና ሱማሌዎች አብዛኛውን ጊዜ በነብዩ ልደት "መውሊድ" እና የመኸር እህል ከሰበሰቡ በኋላ ወደዚህ አድባር በመምጣት ፀሎታቸውን ያደርሳሉ፡፡

2. በምስራቅ ባሬንቱ ኦሮሞዎች ዘንድም እንደ ሼኽ መሐመድ ኸለፍ፣ ሼኽ አደምና አው ዑስማን ያሉት ቅዱሳን የአምልኮ ስፍራዎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደተጠቀሰው ሁሉ የሱማሌና የሐረር ዓምባ ሙስሊሞች ታሪክ ግንኙነት እንዲኖረው በማድረግ ረገድ ኢስማዒል ጀበርቲ በዋነኛነት የሚወሳ ነው፡፡ ለዚህም ሰው ሐዳፍቲሞ ከተሠራለት አድባር ሌላ ለምሳሌ በሐረር ከተማ በኤረር በር አጠገብ ተሠርቶለታል፡፡ በሶማሌዎች በተለይ የሚከበረው ቅዱስ ሸሪፍ ሙሕዩልዲን ዩሱፍ አል አክዋን በርኸድል ዓሊ ነው፡፡ ይህ ሰው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ከዓረቢያ የመጣና የኢፋት አዳል መንግስት ያቋቋሙ ሰዎች አባት ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ፡፡ የዚህ ሰው አድባር ሰሜን ምስራቅ ሐረርጌ ልዩ ስሙ ዶጐር በሚባለው ስፍራ ላይ ይገኛል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚከበሩለት አድባራትም በሐረርና ከሐረር በስተደቡብ ምዕራብ 15 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ በምትገኘውና ጋራድ አብድአልቀዲር ኑር ተብላ በምትጠራው ስፍራ ይገኛል፡፡

የአው ኹጡብ /አው ኹጡብ አልዲን ዑመር/ ቅዱስ ስፈራ ከሱማሌዎች ጋር በተለየ ሁኔታ ይያያዛል፡፡ ይህ ሰው የአባድር ዘመድ እንደመሆኑ መጠን ዓረቢያ ውስጥ በተለይም ሒጃዝ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጥቶ ሐረር መቀመጥ ይጀምራል፡፡ ከዚያ የአካባቢው ሴት ያገባና እስከሞቃዲሾ ድረስ የሃይማኖት ትምህርት ለማስፋፋት ይጓዛል፡፡ በመጨረሻም አድባሩ ከተሠራለት ከሐረር ደቡብ ምስራቅ በሚገኘው ቢሲዲሞ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ይሞታል፡፡ በዚህም መሠረት የሱን የዘር ሐረግ የሚቆጥሩ ዝርያዎቹና ሌሎች በየዓመቱ በወርሃ ረጀብ አስራኛው ቀን በገባ በሚውለው ዓርብ እለት ወደ ስፍራው በመሄድ ፀሎት የሚያደርሱ ሲሆን መስዋዕትም ያቀርባሉ፡፡ ወርሃ ራጀብ በሙስሊሞች ቀን አቆጣጠር ሁለተኛው ወር ነው፡፡ ሁለተኛው አድባርም ሞቃዲሾ ውስጥ እንደሚገኝ ይነገራል፡፡

3. አብዱልቃዲር አልጄላኒ የተባለው የሱፊ ቅዱስ ግን እኛ ባተኮርንበት ስፍራ ብቻ ሳይሆን በመላው ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ በአጠቃላይ ከፍተኛ ከበሬታ አለው፡፡ ይኸው ዝናው ገኖ የሚታወቀውን "ታሪቃ" /ወንድማማችነት/ ቃድሪያ የሚል አመለካከት የተመሠረተ ሰው ከ1077-1166 ባግዳድ ውስጥ የኖረ ሲሆን ወደ ሰሜን ሕልውናና ድርጊት አጥብቀው ያምናሉ፡፡ ታዋቂ አፈታሪኮች እንደሚያመለክቱት አብዱልቃድር ጄይላን አርባ ያህል ሕይወት የነበራቸው የሚባሉት በርካታ አድባራት ሁሉ የሱ ለመሆናቸው ይታመናል፡፡ በሐረርም የቀድሪያ ፀሎት ማድረሻ ቅዱስ ስፍራው በከተማዋ ደቡብ ምዕራብ፣ ከግንቡ ውጭ ባለው ቦታ ይገኛል፡፡ ሌላው የዓብዱልቃዲር አድባር የሚገኘው ባሌ ውስጥ ሼኽ ሑሴን በተባለው ስፍራ ሲሆን የተመሠረተውም አው ሑሐመድ በተባለና ከበርበራ በመጣ ኼሽ ነው፡፡ በምስራቅ ሐረርና በፉኛንቢራ የሚገኘው የቀድሪያ አድባርም በኖሌና በጃርሶ ኦሮሞዎች ውስጥ እስልምናን በማስፋፋት ረገድ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡

በአብዱልቃድር አድባራት ከፍተኛ የፀሎት በዓላት የሚካሄዱት በዓረፋ /ዱል ሒጃ/ ማለትም በሙስሊም የሐጅ ፀሎት ቀን፣ በሙሐረም አዲሱ ዓመት እና በነብዩ የልደት ቀን ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወር በገባ በየሦስተኛው ዓርብ ዕለት ይታሰባል፡፡ በዋናዎቹ የዲኘሎት በዓላት አማኞች አድባሩ ባለበት ቅጥር ግቢ ይሰባሰቡና ዜማ እያዜሙ ከበሮ እየመቱ በጣውላ /ከበል/ እያጨበጨቡና እየጨፈሩ ያከብራሉ፡፡

ሌላው የአብዱልቃዲር የፀሎት ስፍራ የሚገኘው ቦኬ /ጨርጨር/ ውስጥ ነው/ ይሁንና ከሐረር አምባ በስተምስራቅ በኩል የሚገኙት አድባራት ታሪክ እንደአንፃራዊና ውስን በመልካም ሁኔታ የተጠናቀረ ሲሆን በምዕራብ የጥራቱ ሥራ ክፍተት እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ ክፍል ከቃል ከተገኙት ማስረጃዎች በመነሳት በ1973 የተጠናቀረ እንኳን ቢሆንም ከጐደሉት አንዳንዱ ዓላማ ለማጠናከር ታስቦ ተጠናቅሯል፡፡ ይህም ጥንቅር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ዘመኑ በ1870 ሲሆን በዚህ ጊዜ ሐሚድ ቡልቻ ቡልዲዬ የተባለ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት በኢቱ ኦሮሞ ውስጥ የባኤ ጎሳ አባል የሆነ እረኛ ቦኬ ውስጥ በሚገኝ አንድ ዛፍ ሥር ይተኛል፡፡ በዚህ ጊዜም በህልሙ አንድ ትልቅ ዛፍ ያይና ይቆፍራል፡፡ ቆፍሮም የአብዱልቃድር ጄይላን የቀብር ቦታ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ከዚያ ሐረር ውስጥ የቁርዓን ትምህርቱን ይቀጥልና በ1900 ላይ ይሞታል፡፡ ይህ ሰው በህልሙ ያየው ዛፍ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አጥር ይደረግለትና የአብዱልቃዲር መታሰቢያ አድባር ይሆናል፡፡ ከሃምሳ ዓመታት በፊት የገለምሶ ኢማም የነበሩት ሼኽ ዑመር ዓሉም አነስተኛ መስጊድ ሠርተውለታል፡፡

እኚሁ ሼኽ ዑመር የተባሉት የኢቱ ባኤ ጐሳና የወረቃሉ ሰው ሲሆኑ ቀጥሎ ከሚገኙት ከሼኽ መሐመድ ሐረር ጋር በመሆን ወደ ወሎ ሄደው የሃይማኖት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡

4. ከወሎ ከተመለሱ በኋላ በልበሌይቲ በተባለው የትውልድ ስፍራቸው የሙስሊም ትምህርት ማዕከል አቋቁመው ነበር፡፡ ከዚያም የገለምሶ ኢማም ወደመሆን ደረጃ በመሸጋገር የኢቱዎች መሬት ላይ የቀድሪያ ወንድማማችነት መሪ በመሆን ለብዙ ዓመታት አገልግለዋል፡፡ እኚህ ሰው በኸልዋቸው ውስጥ ሆነው በተመስጦ መፀለይ ይመርጡ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን ምናልባት በፀሎት ላይ እያለ እዚያ እንዲቀብሯቸው አዘው ነበር፡፡ በ1952 ውስጥ ሲሞቱም ሰዎች ትዕዛዛቸውን በማክበር አስክሬናቸው በኽልዋቸው ውስጥ እንዲያርፍ አድርገዋል፡፡ ከሳቸውም በኋላ ልጃቸው በሼኽ መሐመድ ሲራጅ የቀድሪያ መሪ በመሆን አግልግለዋል፡፡ በሼኽ ዑመር ዓሊ አድባር የሚከበሩት ዋና በዓላት ከአብዱልቃድር ጄይላኒ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ እነርሱም በዓረፋ፣ በሙሐረምና በመውሊድ አነቢ ናቸው፡፡

እነዚህን በዓላት በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ በገለምሶ ብቻ እስከ አስር ሺ የሚሆኑ ሰዎች እየመጡ ያከብሯቸው እንደነበር ፀሐፊው ራሱ ባደረገው የሰው ለሰው ጥናት ለመረዳት ችሏል፡፡

5. ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሼኽ መሐመድ ሐረር የዑመር ዓሊ ጓደኛና በአንድ ዘመን የኖሩ ሰው ናቸው፡፡ እሳቸውም የተወለዱት በስተምስራቅ ደነባ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ነው፡፡ የኢቱ ኦሮሞና የባሌ ጎሳ አባል ሲሆኑ ከአጐራባች ሱማሌዎች ጋር የጋብቻ ግንኙነት ፈጥረዋል፡፡ከዚያ ሼኽ ዑመር ዓሊ ጋር በመሆን የሃይማኖት ትምህርታቸውን ወሎ ውስጥ አጠናቀዋል፡፡ ወደ ጨርጨር ከተመለሱም በኋላ ከአዳ ቡልቱም ብዙ ከማትርቀው ሳቅታ በተባለች ረግራጋማ መንደር የቁርዓን ት/ቤት አቋቁመው ነበር፡፡ የሳቸው ዝንባሌም በምዕራብ ሐረር ዓምባ ለሙስሊም ወንድማማችነት በጣም ጠቀሜታ በነበረው በቀድሪያ ስርዓት ነበር፡፡ /እዚህ ላይ ሰይድ ሐሴይን የተባሉ ከምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም ጉሬ ኢሉባቡር በ1930ዎቹ የመጡ ሰው በጋራሙለታ አካባቢ የዱኒያ ስርዓትን በማስተማር መጠነኛ ተቀባይነት አግኝተው እንደነበር ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

6. መሐመድ ሐረር በ1930ዎቹ ሞተው ጭሮ በተባለው ስፍራ ሲቀበሩም ጓደኛቸው ዑመር ዓሊ የቀድሪያውን ሥርዓት ለመቀጠል ተክተዋቸዋል፡፡ ከጭሮ ውስጥ ለዚህ ሰው አድባር የተሠራላቸው ከመሆኑም ሌላ አዘውትረው ይሰግዱበት ከነበረው ቁኒ የተባለ ዛፍ ጥላ ሥር ሃይማኖትን የሚመለከት ስብሰባ የሚካሄድበት "ሐድራ" ተቋቁሞ ነበር፡፡ ይህ ሐድራ የተባለ ሐይማኖት ነክ ጉባኤ ከፊል አማኞች "ገልማ" የሚሉት ጉባኤ እንዲተካ በራሳቸው በሼኽ መሐመድ ሐረር ትምህርትና መመሪያ ይሰጥ ነበር፡፡ በመሠረቱ ገልመ የሚለው ቃል የኦሮሞ ገጠሬዎች በአንድ ስፍራ ሆነው ከትውልድ ትውልድ እንዳሉ የሚቆዩ አምልኮት የሚካሄዱባቸው ቤቶችን የሚገልጽ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ግን ሙስሊሞችና ሙስሊም ያልሆኑትን እየሰበሰቡ ሃይማኖታዊ ተግባሮች ያከናውናሉ፡፡

## ቅድመ እስልምና በፊት የነበሩ የእምነት ቦታዎች

ከቢር ሐሰን ወረቃሉ ሲሆኑ የዘር ሐረጋቸውን የሐረር ሕዝብ አባት ናቸው ከሚባሉት ከአባዲር አንስቶ የሚቆጥሩ ናቸው፡፡ የከቢር ሐሰን መወለድ ከአምስት ትውልድ በፊት ከጨርጨር ወደ ሐረር የመጡት ሼኽ መሐመድ ረሺድ ተናግረው እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህም በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ሲሆን ከቢር ሐሰን በ1970ዎቹ ላይ በልበላቲ ጨራቲ የሚገኘው አድባራቸው ኢማም ሆነው ነበር፡፡ ሐሰን ኢቱ ኦሮሞዎችን የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ማድረግ ሲጀመር የነበሩ የመጀመሪያው ግንባር ቀደም መምህር ሲሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች በነርሱ ላይ የጠላትነት ተግባር ሲፈፅሙ ተከታዮቻቸውን እጅግ አደገኛ ለሆነ ሁኔታ ዳርገው ነበር ይባላል፡፡

በዚህ ምክንያት ከቢሮ ሐሰንና ተከታዮቻቸው በአነስተኛ ስፍራ ተወስነው የቆዩ ሲሆን እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስም እምነት ባልነበራቸው ሰዎች ያልተቋረጠ ጥቃት ይሰነዘርባቸው ነበር፡፡ በኋላ ግን በሌሎች ቅዱሳን ከፈጣሪ የሚሰጠው ከራማ ስለተሰጣቸው በሰውም ሆነ ሰው ከሚያስበው ውጭ የሚፈጥሩት ተዓምር ተቀባይነትን አገኙ፡፡ አድባራቸው ኢቱዎች የእስልምናን እምነት የሚቀበሉበት ዋነኛ ማዕከል ሆነ፡፡ በተለይም የበልበሌይቲ ሰዎች የዓርብ ፀሎታቸውን ካደረሱ በኋላ ወደዚህ ስፍራ በመምጣት ይዘይራሉ፡፡

ዶባ /ጨርጨር አጠገብ መና ቀሎ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የሚገኘውና ዛሬ ወና የሆነው የሸሪፍ አሕመድ መስጊድ ለረዥም ጊዜ ሙስሊሞች ቅዱስ ፀሎታቸውን ሲያደርሱበት የነበረ እንዲሁም ከጥንታዊ መስጊዶች አንዱ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቀረው የመስጊዱ ግንብ የውስጥ ግርግዳ ብቻ ነው፡፡ የአካባቢው ሕዝብ የሸሪፍ አሕመድ መንፈስ እዚያው ስለሚገኝ ከሰዎች ጋር በመንፈስ ይገናኛል ብለው ያምናል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ሰው የኃይማኖት አባት ምስክራቸው ከሚገባው በላይ ያባክኑ ነበር፡፡ ሸሪፍ አሕመድ የሚመጣውን አደጋ አስቀድመው በማወቅ የተፈጥሮን ፀጋ እንዳያባክኑ፣ አጃ የተባለውንና ከዚያ በኋላ የጠፋውን የእህል አይነት እንዲያከብሩት ከከብቶች ይልቅ ሊመጣ የሚችለውን ድርቅ ሊቋቋሙ የሚችሉት በጉችና ፍየሎች በመሆናቸው እነርሱን ማርባት አል እንዳይሉ አስጠንቅቀዋቸው ነበር፡፡

ሐርላዎች ግን ባሳዩት የጥጋበኝነት ባህሪይ ምክንያት ፈጣሪ ለረዥም ጊዜ የቆየ ድርቅ ለቀቀባቸውና አብዛኛዎቹ በርሃብ አለቁ፡፡ ሸሪፍ አሕመድና ቤተሰቦቻቸው የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ በመከታተል ለረዥም ጊዜ ሕዝቡን እየተረዱ ርሀቡን ተቋቋሙት፡፡ በዚህ ምክንያት በዲባ ነዋሪዎች ዘንድ በረሃብ ዘመን ሕዝቡን ዘብ እንደሚጠብቅ ቅዱስ ተደርገው ይወስዳሉ፡፡

የሸሪፍ አሕመድ እና የኢማም አብዱራህማን መቃብር በመስጊዱ ዋነኛ በር ግቢያ በሰሜን ምዕራብ በኩል አለፍ ብሎ በሦስት ማዕዘን በተሠራ የድንጋይ ግንብ ተሠርቶ ይገኛል፡፡ በምስራቅ ባለው ግንብ ደግሞ በፀሎት በአድራዎች እሳት እያነደዱ ሌሊቱን የሚያሳልፉበት "ሐድራ" አለ፡፡ ኦሮሞዎች ከልዩ ዓመት በዓላት ሌላ በወርሃ "ቢራ" /መስከረም እስከ ጥቅመት/ ወደ ሸሪፍ አሕመድ አድባር በመሄድ ፀሎታቸውን ከእግዚአብሔር ፊት እንዲደግፍላቸው /እንድያማልዳቸው/ ይማፀኑታል፡፡

"መነ ቃሉ" የሚለው የቦታ ስም "ወረቃሉ" የሚለውን የኦሮምኛ ቃል የሚተካ ሲሆን የሀም በባሬንቱ ኦሮሞ መካከል የሚገኙ የሱማሌና የሐረር ሙስሊም የሃይማኖት አስተማሪዎች የሚጠሩት ነው፡፡

ሁኔታዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታዩ፣ ከእስልምና እምነት ጋር ለቅዱሳኑ የሚሰጠው ክብርና በመቃብራቸው /አድባራቸው/ ላይ የሚካሄደው የአምልኮ ፀሎት የሐረር አምባ ሕዝብ የባህሉ አካል ሆኖ ቆይቷል፡፡ በታሪካቸውና በማህበራዊ ሕይወታቸው የሚያስከትለው ውጤት ወይም የሚኖረው ተጽእኖም ብዙ መልክ አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአድባራት አመሠራረት ቅደም ተከተል ሲጠና የሙስሊም እምነት የመስፋፋ አካሄድት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ያሳያል፡፡ አድባራቱ የሃይማኖት አስተማሪዎቹ ምን እንደሠሩም የሚመሠክሩ ማስረጃዎች ሆነው ይታያሉ፡፡ ከዚህም በላይ እስልምና ሩቅ ባልሆነ ጊዜ በተሠራጨባቸውና በጠንካራ ሁኔታ ባልገባባቸው ስፍራዎችም አዳዲስ አድባራት መቋቋማቸውም ባህላዊ ትስስሩን ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳን ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁሉ አምልኮተ ቅዱሳን በጠበቀ መልኩ ሲታይ ከሙስሊም ከኦርቶዶክሶች አስተሳሰብ ጋር የማይጣጣም ቢሆንም እስልምናን ለማስፋፋት ግን ተጨባጭ ወይም ወቅቱ የሚፈቅደው መሳሪያ በመሆን አገልግሏል፡፡

ስለሆነም አንዳንድ ጊዜ አጨቃጫቂ መሆኑ ባይቀርም በአብዛኛው ሕብረተሰብ አእምሮ ተቀባይነት ያለው የቅዱሳትን ታላቅነት ቅደም ተከተል ደረጃ አለ ደረጃውንም ከሞላ ጐደል በሦስት ክፍል መለየት ይቻላል፡፡

1. በቀበሌውና በአካባቢው ነዋሪዎች የሚከበሩ እንደ ጫፍሬው ሸሪፍ ኑር ዓሊ ያሉት ቅዱሳን፣

2. በክልል ደረጃ ጠቃሚ እንደ ዑመር ዓሊ /በልበሌይ ጨርጨር/፣ ኮምበልቻ አካባቢው አው ኑጉስ ወይም ዶጐሩ ዩሱፍ በኽድሌ ያሉ ቅዱሳን፣

3. ይህ ጥናት በሚያካትታቸው ስፍራዎች በጠቅላላ የሚከ በሩ ቅዱሳን ለምሳሌ አብዱልቃዲር ጀይላን ዋነኛ መስጊ ዳቸው ሐረር ሆኖ በሁሉም ዘንድ ይከበራሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ “አውሊያዎች” የቤተሰብ፣ የጐሳ ወይም የብሔረሰቡ ደህንነት እንዳይጐዳ ዘብ ሆነው እንደሚጠብቁ ይታመናል፡፡ ከራማቸውና በረካቸው ከሰዎች የሚለየው የማይለካ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን አማኞችን ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ጭምር ነው፡፡ አንዳንዱ ቅዱሳን ዝናብ /ኢስቲስካ/ እንዲመጣ የሚደረግ ፀሎት በመደገፍ ለየት ባለ ሁኔታ ኃይል ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ሴቶችና ከብቶች እንዲወልዱና አዝመራው እንዲበዛ ያግዛሉ፡፡ ከዚህ የተለዩትም በንግድ ሥራና ጉዞ ላይ በሀብትና ንብረት አደጋ እንዳይደርስ የሚጠብቁ ናቸው፡፡

ከዚህ ሌላ ከ10ኛ-16ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው ጊዜ እስልምናን ሲያስፋፉ የነበሩ ቅዱሳን ከነሱ በኋላ ከመጡት ቅዱሳን የበለጠ ኃይል እንደነበራቸው ተደርጐም ቢታሰብም መሠረታዊ የሆነ ልዩነት ስለሌላቸው የዓብዱልቃድር የአባድር፣ የኢስማዒል ጀበርቲና የሌሎቹንም ዝነኞችና ዝናና ከራማ በማጐናፀፍ ከአምላክ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሚቻል የሃይማት አባቶች ያስረዳሉ፡፡

ነገሩን ከስነልቦና አኳያ ስንመለከተው ቅዱሳኑን በማክበር ጉዳይ ከእስልምና በፊት ከነበረው አምልኮ ጋር ይሄዳል /ይገጥማል/፡፡ በመሆኑም አውሊያዎች በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለውን ሰፊ ርቀት

እንደድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ ከዚህም በላይ ደግሞ አማኞች ከአላህ ጋር እንዲገናኙ የሚያስችላቸው ተጨባጭ መንገድ ይመስላቸዋል። ከዚህም ባሻገር ጥልቅ ሥራ በነበረው የአባቶች አጉል አምልኮ ለመተካት እንዲቻል ቅዱሳንን ማክበር በእስልምና ተቀባይነት አለው። ለምሳሌ ጥንታዊ እምነት ያልነበራቸው ጥንታዊ አባቶች እንደ ቦልቱም ባሉ የአምልኮት ስፍራዎች ከብት እያረዱ መስዋዕት ያቀርቡ የነበረ ሲሆን ዛሬ ለእስልምና ቅዱሳን ተገቢ እንሆነ ተደርጐ ይቀርባል። ጥንታዊ የባዕድ አምልኮ ማምለኪያዎች ዛሬ የሙስሊሞች መስገጃ ሆነዋል። አመልኮት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በሁለት ከፍለን ልንመለከተው እንችላለን። በአንድ መልኩ የቅዱሳኑ ተወካዮች ፀሎት ለማድረግና ስለት ለማድረስ ከሚመጡት አማኞች የቀበላ። በስለት የሚመጣውን ንብረትም ለድሆች ያሰራጩታል። በሌላ በኩል ደግሞ በሙስሊም ወንድማማችነት ማህበራዊ አንድነትም እንደመሠረታዊ ግዴታ የሚወሰድ በመሆኑና ድሆች ወደቅድሳን ቦታዎች መጥተው ፀሎት ለማድረስ እንዲችሉ የተገኘውን የመከፋፈል ጉዳይ የሚያጠያይቅ አያደርገውም። የስርጭቱ አሠራር ጥሩ በሆነ መጠንም የሽኩም ዝና ከፍ ይላል።

በአጠቃላይ ቅዱሳኑን የማክበር ልምድ ከቁሳዊና ከማህበራዊ ትርጉሙ አኳያ የድሆችንና በኑሯቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ልምድ ነው የሚል ግንዛቤ ያመጣል። ከዚህም ሌላ ወደ መካ ሄደው ፀሎት ለማድረስ አቅም የሌላቸው ሰዎች ፍላጐት መሆኑ ተግባር ራሷ ታሳያለች። ስለዚህም ዚያራው "የድሆች ሐጅ" እየተባለ ይጠራል። አውሊያዎችን የማምለክም ጉዳይ ከብሔረሰብ ብሔረሰብ ይለያል። በጥንት ጊዜ የሱማሌ የኦሮሞ፣ የሐረሪና የአፋር ሰዎች በአንድ አድባር በሰላም ተሰብስበው ፀሎታቸውን ያደርሱ ነበር። በነዚህ አካባቢዎችም የጦር መሣሪያ ይዞ መግባት የተከለከለ ነበር። ከዚህም በላይ ሃይማኖታዊ መቻቻልም እንዳለ ማስተዋል ይቻላል።ለምሳሌ አነድ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታታይ ጨርጨር ወደሚገኝ አድባር በረካ ለመቀበል ሲመጣ ሙስሊሞችም ወደቁልቢ ገብርኤል በመሄድ ፀሎት ሲያደርሱ ተመልክቻለሁ። በቅዱስ ስፍራዎች ውስጥም ማንኛውንም አመጽ ቢያስነሳ እንደሰይጣናዊ ተልዕኮ ተደርጐ የሚወሰድ ከመሆኑም በላይ ያስረግማል።

ቅዱሳኑን ማምለክ በሰፊው የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ አውሊያዎች ደግሞ በብሔረሰባዊ ወይም በብሔራዊ ደረጃ ታላቅነታቸው የሚወሳላቸው አሉ፡፡ እንደ ኡስማኢል ጀበርቲ፣ አሕመድ ቢኒ ኢብራሂምና ኑር ቢኒ ሙጃሂድ ያሉት በመላው የሐረር አምባ እንደ ብሔራዊ ጀግኖች ይከበራሉ፡፡ አባድር ዑመር አል ሪዳ ደግሞ የሐረሪዎች ጠባቂ ቅዱስ ናቸው፡፡ የኖሌው አው ኑጉሥ፤ የጃርሶው አው ዓሊ ፊፍ፣ የኢቱው አው ሰዒድ፣ የሱማሌው ዩሱፍ ባርኻድል ቅዱሳን ናቸው፡፡ /ሰይድ ሙሐመድ አብዱልሐሰንም ከቅዱስ ይልቅ ብሔራዊ ጀግና /ናቸው፡፡

ከሌሎች ተግባሮቶችው ጋር በነዚህ ቅዱሳንና ጀግኖች ስም የብሔር ብሔረሰብ ማንነት ስሜት በከፍተኛ ደረጃ እንዳደገ ካለፉት ሦስት አስርተ ዓመታት መመልከት ይቻላል፡፡ እስላም እንደ አንድ የአካባቢው የቆየ ባህላዊ እሴት በኢትዮጵያውያን ባለስልጣኖች የሚፈፀመውን ግፍ ለመቃወም ወኔ ሰጥቷቸዋል፡፡

# ማጠቃለያ

ቅደመ ታሪክ ማስረጃዎች ቁፋሮዎች የመቃብር ላይ ፅሁፎች ሌሎች ፅሑፎችም ስለሀረር አስረጂነት እንዳለ ሆኖ ተዘግበው ከሚገኙት የአረብኛ፤ ጣሊያንኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ ፅፎች የታሪክ ጉዞውን በሚገባ ያስረዱታል።

ሀረርን ለመግለፅ ሦስት ምሶሶዎች የመጀመሪያውን ንግዱ ሁለተኛው የእስልምና ሃይማኖትና ከተማዋ ራሷን በገላጭነት የቅድመ ታሪክን መካከለኛውን ዘመንና እስካለንበት ድረስ ያለውን ያስረዳሉ።

በሀረር ታሪክ ንግድ እስልምና በሚገባ ለማሰራጬት ማስቻሉ ብቻ ሳይሆን ቀይ ባህር አፍሪቃ ቀንድ የአረቡን ዓለምን ያስተሳስራል። እስልምና በንግድ በሚገባ ተደገረፏል። ነጋዴው ሁሉ የሃይማኖቱ አስተማሪ ነው የሚባለው ከዚህ ነው። በዚሁ የእስልምና ሃይማኖት መሰረትን ትምህርት ባህል ሥነ-ፅሑፍ በመበልፀጉ የግንባታው ፅህረትና ስነጥረዛው የህዝቡን ማንነት በሁለንተናዊ  እሳቤውን ቀርጸል።የእለት ተእለት ኑሮ ሆኖ እስልምናን ይኖረዋል። ኩነቶች በከተማዋ ውስጥ ከውጪ የሚመጣውን የንግድ እቃ ከመሐል ኢትዮጲያ ወደ ውጪ የሚላከው በማስተላለፍ አገሪቱን ከውጪው ዓለም መገናኘት አስችሏል። በዚህም ለኢትዮጲያ ባደረገችው አስተዋፅኦ የኢትዮጲያ ታሪክ ማስገኘቱ ለሀረር ታሪክ የኢትዮጲያ ታሪክ ምሉእ አይደለም። በዚህ አጭር ታሪክ ለመዘርዘር አልቻለም። የሚደንቀው ከኩሽቲክ ከህዝቦች መሐል  በዙሪያዋ የክርስትና ሃይማኖት ህዝብ መሐል እጅግ አነስተኛ ሆኖም ከሺ አመት ታሪክ እውን መሆኑ በስፋትና በጥልቀት የሚያጠኑት ነው፡ ይህ አጭር ታሪክም መንደርደያ ይሆናል ከሚል እሳቤ ነው።

# ዋቢ ጽሑፎች


1. አብድልሙሑይሚን አብዱልናስር የሐረር ታሪክ ያልታተመ

2. አህመድ ዘካሪያ 1991 የሐረር ሳንቲሞች የመነሻ ጥናት በኢትዮ ጵያ ጥናት ምርምር ኢንስቲትዩት መጽሔት ቁጥር 24

3. አህመድ ዘካርያስ የጁገል ዳግማዊ ልደት የሐረር ምልክት የሆነው ግንብ ያልታተመ

4. የሐረሪዎች ኪነጥበብ የአለላ ስራ በአሚና ኢስማኢል ሸሪፍ ዓይን አር ሶልቨር ማን " የኢትዮጵያዊያን ባህላዊ የፈጠራ ሥራዎች" በሚል ርእስ በአርታኢነት ባዘጋጀው ውስጥ የተ ካተተና በቅርቡ የሚታተም

5. አር ፔ አዛስ እና አርቻምበርድ በ 1931

6. ጆን ቡሽ ሆዘር 1955 " የተቃጠለ ፊት ያላቸው ሰዎች አገር"

7. ሪቻርድ ኮክ 1971 " የሐረር መያዝ" የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት መጽሔት ቁጥር 9

8. ኤንሪኮ ቸሩሊ 1936 የኢትዮጵያ ጥናት (የሐረሪን ታሪክና ቋንቋ በሚመለከት)

9. ኤንሪኮ አሩሊ 1971 "ኢስላም ኢየሪ ኦጂ"

10. ላዲስላስ ፍራጉ 1935 " አቢሲኒያ ኦን ዘ ኢብ" (ሐበሻ በዋዜማ ላይ)

11. ፓል ሔንዝ 1977 " ኢትዮጵያን ጆርኒ"

12. ጃራ ኃይለ ማርያም 1991 ታሪካዊዋን የሐረር ከተማ እን ደነበረች ለማቆየት የሚደረግ ጥረት በሪቻርድ ፓንክረስት ውስጥም የተጠቀሰና በመጀመሪያው ብሔራዊ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ የቀረበ

13. ወልፍ ሌስላው 1965 "ኢትዮጵያ ስፔክስ" የሐረሪዎች ባህል አመጣጥ ጥናት

14. መሐመድ ሙኽታር “ ስለሐረር አንዳንድ ማስታወሻዎች “ ጆን ስፔንሰር 1952 “ “እስላም ኢትዮጲያ” በሚል ርእስ ካሳ ተመው

15. ፒ ፓሊስክ 1888 ሐረር በሚል ርእስ ባሳተመው

16. ፒ ፓሊስክ 1888

17. አርኖልድ ቶይንቢ 1965 ከናይል እስከ ኒዠር “ በሚል ርእስ ካሳተመው

18. ኢቭን ዎፍ 1934 “ መሄድ መልካም በነበረበት ጊዜ” በሚል ርእስ ካሳተመው

19. ዩሱፍ አሕመድ 1960 ስለሐረር አሚሮች /1825-1875/ (አንዳንድ የቤት ኢኮኖሚን በተመለከተ ያደረጉት ጥናት ኤት ኖሎጂካል ቡስቴን ቁጥር 10)

20. ሪቻርድ ፓንክረስት ዘ ኢትዮጲያን ቦርድሳንድስ 1997

21. ጴጥሮስ ፔትርደስ የልዑል ራስ መኮንን ታሪክ 1961 ኢ.አ

22. ራይሞንድኤሲልቨርማን አርታኢ ኢትዮጵያ ትራዲሽናል ክረኤቲቭቲ 1999

23. ተክለፃዲቅ መኩሪያ የግራኝ አሕመድ ወረራ 1966 ኢ.አ

24. ላጲስ ጌዴሌቦ የኢትዮጵያ የገባር ሥርአት ጀምር ካፒታሊ ዝም 1983

25. ላጺሶ ጌዴሌቦ ረጅም የሕዝብና የመንግስት ታሪክ 1982

26. ላጺሶ ጌዴሌቦ የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶች መሣሪያዎች 1999